# ድብቁ እውነት ሲገለጥ

## ክፍል አንድ (ተሻሽሎ የቀረበ)

## ሦስተኛ ዕትም

የአገራችን ዳኢዎች ሳዲቅ ሙሐመድና መሰሎቹ፣ እንዲሁም አሕመድ ዲዳትና ተከታዮቹ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ

በሳሂህ ኢማን

**የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

2007 ዓም

**ስጦታ፡-**

**ለ፡**....................................

**ከ፡**.....................................

# ማውጫ

ምስጋና ……………………………………………………………………4
መቅድም ……………………………………………………………………5
መንደርደሪያ……………………………………………………………………10
1. ሙግት አንድ ፡- መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መሆኑ……………………12
1.1. የተበረዘው ማን ነው? መጽሓፍ ቅዱስ ወይስ ቁርአን? ……………14
1.2 መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተበረዘ ተባለ ……………………………………57
1.3 ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ በነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳትና በሙፈሲሮች የተሰጠ ምስክርነት ……………………………………67
2. ሙግት ሁለት፡- መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አዕምሮ ሊቀበለው የማይችላቸው አሳቦች በውስጡ መያዙ ……………………………………93
2.1 ልጇን ቀቅላ የበላች እናት……………………………………………101
2.2 ልጅ ከአባት በእድሜ መብለጡ ……………………………………111
2.3 የአላህ ነቢይ የሰውን ፋንድያ እንደ ምግብ…………………………112
2.4 በወር አበባ ላይ ያለች ሴት…………………………………………113
2.5 ሳይወልድ ለሞተ ወንድም ስም የማስጠሪያ ሕግ……………………124
2.6 አህያ በሰው ቋንቋ ስለ መናገሯ………………………………………129
2.7 የዛፎች የንግስና ውይይት……………………………………………132
2.8 የጾታ ፍቅር በአላህ ቃል ውስጥ………………………………………135
2.9 የሰው የግል መልእክት በአላህ ቃል ውስጥ……………………………145

3. ሙግት ሦስት፡- መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በአሳብም ሆነ በመልእክት ያላቸው አለመስማማት……………………………………153
3.1. አላህ ከሥራ ደክሞት አረፈ መባሉ……………………………………156
3.2. ያዕቆብ በልጁ በዮሴፍ ላይ ያሳየው ምቀኝነት……………………168
3.3. ሙሴ የአላህን ጀርባ አይቷል መባሉ…………………………………176

4. ሙግት አራት፡- መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ሥህተቶችን መያዙ……..189
4.1 የኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊነት የትንቢት ቃል…………………………189
4.2 ይሁዳ ኢየሱስ ክርስቶስን የሸጠበት የትንቢት ቃል……………………194

5. አባሪ……………………………………………………………………196

6. ማጣቀሻዎች ……………………………………………………………198

# ምስጋና

በመጀመሪያ የሥራው ባለቤት ለሆነው፣ ታላቁን ተልዕኮ፣ የወንጌሉን ሥራ ከእርሱ ጋር እንድሠራ፣ ታማኝ አድርጎ ለቆጠረኝ፣ ባለፍኩባቸው መንገዶች አብሮኝ ለነበረው፣ ለውዱ ጌታዬና አምላኬ ለልኡል እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በእርሱ ደስታዬ ወደር የለውም፡፡

ይህንን ሥራ አምላኬ በእኔ መሥራት አስቦ፣ ፅንሱን በውስጤ ማንቀሳቀስ ሲጀምር፣ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ፣ በተለያየ መልኩ፣ ከእኔ ጋር ለመሥራት ቀኝ እጃቸውን የሰጡ ወገኖች በቁጥር በርካታ ነበሩ፡፡ በተለይም አንደኛ፣ ሁለተኛ እያልኩ፣ ስማቸውን መጥቀስ ተገቢ የሚሆንብኝ ወገኖች አሉ፤ ሆኖም በአንዳንድ ምክንያቶች ያንን ማድረጉን አልፈለግሁትም፡፡ ይህንን ሲያነቡ ግን ምን መልእክት ማስተላለፍ እንደፈለግኩ እንደሚገባቸው በእርግጠኛነት መናገር እችላለሁ፡፡ ለእነዚህ የልኡል አምላክ ባሪያዎች ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ አብረን በመሥራታችንም ደስታዬ ታላቅ ነው፡፡ ወደር በሌለው የአምላካችን እርሻ ውስጥ ትንሽዋን ጠጠር አብረን መጣል ችለናል፡፡

በመጨረሻም ይህንን ስናደርግ እንደ አንድ ቤተሰብ እየተገጫጨንም፣ እየተያያዝንም ሊረሱ በማይችሉ ትዝታዎች እየታጀብን፣ የተሰባሰብንባት በባእድ ምድር የጌታ ምስክር የሆነችው፣ ያች ውቧ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ጥላ ውስጥ ላሉ፣ የውዱ ጌታ ድንቅ ልጆች፣ ያለኝን አክብሮትና ምስጋና ልገልጽ እወዳለሁ፡፡ ዛሬም ፍቅራችሁ በልቤ ውስጥ አለ፤ ይኖራልም፡፡

# መቅድም

ማንኛውም ሰው ደስ ያሰኘውን ሃይማኖት መከተል፡-

- በአገራችን ሕገ መንግሥታዊ መብቱ[1]
- ሰብአዊ መብቱ
- ከአምላኩም የተሰጠው የመምረጥ ግላዊ መብቱ እንደሆነ አምናለሁ፡፡

ይህንን በሦስት የተገመደ የሰው ልጆችን ሕጋዊ መብት ማክበር ግዴታዬም ብቻ ሳይሆን ፈቅጄና አምኘበት የማደርገው የግል አቋሜም ጭምር ነው፡፡ ሰው ይህኛው የሃይማኖት መንገድ ወደ አምላክ ያደርሰኛል ብሎ አምኖ መከተል ከፈለገ፣ ትክክለኛነቱ ላይ ጥያቄ ቢኖርብኝም የወደደውን መከተል መብቱ ስለሆነ፣ የተከተለው መንገድ ክብር ሊሰጠው ግድ ነው፡፡ እናንተም ሙስሊም ወገኖቼም ስለመረጣችሁት መንገድ፣ ምንም ዓይነት ተቃውሞም፣ ጥላቻም የለብኝም፤ ምርጫችሁን አከብራለሁ፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም የሰዎች ምርጫ፣ በዓለም ያለው ሁሉም ሃይማኖት በአምላካዊው እውነተኛ መነጽር ሲታይ ትክክለኛ ነው ማለት አለመሆኑን ሁላችንንም የሚያግባባን ነጥብ ይመስለኛል፡፡ አሊያማ አንተም እኔም ትክክል ነን፣ ተባብለን የራሳችንን መንገድ ብቻ በጠበጠብን ነበር፤ ግን አልሆነም፡፡ **በሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 48** ላይ "አላህ ተናግሮ እያለ" እንኳን መቀበል የተቻለ አልሆነም፡፡

> **ሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 48**
>
> ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል፡፡ ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን <u>**አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር**</u> ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ) በጎ ስራዎችንም (ለመስራት) ተሽቀዳደሙ፡ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው በርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል፡፡

ይህ የሆነው እውነት አንጻራዊ (Relative) ሳይሆን፣ አንድና አንድ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ መነጋገር ያለብንም ስለዚህ አንድና ብቸኛ እውነት ነው፡፡ ይህን እውነት ካገኘነው ብቻ ነው፣ የሃይማኖታችንን ግብ የምንጨብጠው፡፡ ታዲያ ይህ አንድና ብቸኛ እውነት የት ነው ያለው? እውነትን መፈለግና ስለ ትክክለኛው እውነት

[1] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገ መንግስት፣ ህዳር 27/ 1987፣ አንቀጽ 27

መነጋገር በእኛ አልተጀመረም፡፡ ከእኛ ቀድመው በዙዎች አድርገውታል፤ በነቢዩ ሙሐመድ ዘመንም የነበሩ የነቢዩ የቅርብ ዘመዶች ይህንን አድርገውት ነበር[2]፡፡

የእውነት "አለርጅክ" ካለበትና "የእኔ ብቻ!" ከሚል ችኮ እና ሰነፍ ሰው፣ በስተቀር እውነትን መነጋገር የሚከለክል ሕገ መንግሥትም፣ መለኮታዊ ትእዛዝም፣ ሰብአዊ ስርአትም የለም፡፡ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት የተነሳሁት የአገሬ ሕገ መንግሥት ከሰጠኝ መብት በተጨማሪ፣ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአንም ይህንኑ መብት ስላጎናጸፉኝ ነው፡፡ በሁለቱ መጻሕፍት ያሉኝን የመብት አንቀጾች ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጀመር በቅደም ተከተል ላስነብባችሁ፡-

**የኤፌሶ መልእክት 4 ፡ 25**

ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በእርሳችሁ ብልቶች ናችሁና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፡፡

**1 የጴጥሮስ መልእክት 3 ፡ 15**

በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን፡፡

ወደ ቁርአን ስሻገር ደግሞ፡-

**ሱረቱል አል-ነኽል (የንብ ምዕራፍ) 16 ፡ 125**

ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ፡፡ በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው፡፡ ጌታህ እርሱ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው አዋቂ ነው፡፡ እርሱም ቅን የሆኑትን ሰዎች አዋቂ ነው፡፡

ادْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ ۖ وَجَادِلْهُم بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعْلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِ ۖ وَهُوَ أَعْلَمُ بِالْمُهْتَدِينَ

**ሱረቱል አል-ኒሳዕ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 82**

ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ መለያየት ባገኙ ነበር፡፡

---

[2] *Ibn Ishaq,The life of Muhammad,translated by A.Guillaume, Ameena Saiyid oxford university press, Karachi 1955, page 98-99.*

أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ الْقُرْآنَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ اللَّهِ لَوَجَدُوا فِيهِ اخْتِلَافًا كَثِيرًا

ስለዚህ እውነትን መነጋገር ማንም ሊሽራርፌው የማይችል መብታችን ነው፡፡ ይህንን ስናደርግ ደግሞ በሁለቱ መጻሕፍት አንቀጾች ላይ እንደሚታየው የአፈጻጸም መርህ አለው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "በትሕትና" በማለት ሲገልጸው፣ ቁርአን ደግሞ "በለዘብታ ቃልና በመልካም ዘዴ" በማለት አስቀምጦታል፡፡ ከዚህ የወጣ ሁሉ አመጽ ነው፡፡ ለአላህ አለመገዛት ይሆናል፡፡ ይህም የሰዎችን በሦስት የተገመደ መብትም መጋፋት ይሆናል፤ የከፋ ውጤት አለው፡፡

ሰዎች በእንዲህ አይነት ውይይት ሊኖራቸው ስለሚገባ አቋም ባህሩ ዑመር የተባሉ ሰው ኡስታዝ አህመዲን ጀመል "ክርስቶስ ማን ነው? 303 ወሳኝ ጥያቄዎች" በሚል ርዕስ ከጻፉት መጽሐፍ መቅድም ላይ እንዲህ ብለው ነበር፡፡ መተግበር ከቻልን ለሁላችንም መልካም ምክር አለው፡-

> "በአሁኑ ሰዓት በአንዳንድ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል የምናየው ሰላማዊ የሆነ የሃይማኖታዊ ውይይት (ክርክር) ለኛ ጥሩ ተምሳሌት ሊሆነን ይችላል፣ ብለን እንገምታለን፡፡ እንዲህ አይነቱን ሰላማዊ የሆነ ውይይት እንደ ድፍረትና የሌላውን ሃይማኖት እንደመንካት አድርገው የሚቆጥሩ አንዳንድ ወገኖችም አይጠፉም፡፡ እነዚህ ወገኖች የያዙት አቋም አንድም የሃይማኖታቸውን መመሪያ በጥልቀት ካለማወቅ፣ አሊያም የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ አንችልምና ሰው ፊት እንዋረዳለን ከሚል ከንቱ ስጋት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ለነዚህ ወገኖቻችን የምንላቸው ነገር ቢኖር፣ የሃይማኖታችሁ መመሪያ (መጽሐፍ) በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል በአግባቡ እንድታዩት፣ እንድትፈትሹትና እራሳችሁን ጥሩ ተወያይ አድርጋችሁ ለማቅረብ እንድትሞክሩ ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ የራሳቸውን ድክመት ለመሸፋፈን ሲሉ፣ ለተራው ሰው ሃይማኖቱ እንደተነካና እምነቱ እንደተዘለፈ አድርገው በማቅረብ ሆን ብለው ህዝቡን ለዱላና አላስፈላጊ ግጭት እንዲጋበዝ የማድረግ ሥራ ሢሠሩ ይታያሉ፡፡ ይህ አይነቱ ድርጊት በፈጣሪም በፍጡርም ዘንድ ያስወቅሳልና ሁላችንም እናስብበት፡፡"

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የዚህ ጽሁፍ አላማ እስልምናን ማጠልሸት ወይንም ማጣጣል ሳይሆን፡-

1. ሰዎች ሁሉ የጠራውን እውነት በማወቅ ከአምላካቸው ጋር እንዲታረቁ፣ የመዳንን እውነት ለማሳየት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ 2 ቆሮ 5 ፡ 18-21 ላይ እንዲህ ይላል፡-

   "እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፣ የማስታረቅን አገልግሎት ሰጠን፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር

ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር፡፡ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅን ቃል ሰጠን፡፡ ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፣ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፣ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን፡፡ እኛ በእርሱ ሆነን፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኃጢያት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢያት አደረገው፡፡"

ስለዚህ ሙስሊም ወገኖቻችንን ከሚወዳቸውና ለደህንነታቸው ሲል አንድ ልጁን በኃጢአተኛ ሰው ምሳሌ በመላክ የኃጢአታቸውን ዋጋ ከከፈለው አምላክ ጋር እውነትን በማወቅ እንዲታረቁ፡-

2. በአገራችንና በውጭ ባሉ ዳኢዎች፣ በሳዲቅ ሙሐመድ አሕመድና በመሰሎቹ፣ እንዲሁም ዛሬ በሕይወት በሌሉት በአሕመድ ዲዳትና በደቀ መዝሙራቸው በዶ/ር ዛኪር ናይክና በሌሎቹም እየተዘጋጁ ለተሰራጩ መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርአንን ላነጻጸሩበት ሥራዎቻቸውና መጽሐፍ ቅዱስ የአላህ ቃል አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ ላነሷቸው መሞገቻዎች ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ታስቦ ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ አንባቢዎቼን ሁለት ነገሮችን ማሳሰብ እወዳለሁ ፡፡

- መጀመሪያ ሙስሊም የሆናችሁ ወገኖቼ በዚህ መጽሐፍ የምናወራው ሁላችን "እንወድሃለን" ስለምንለውና ተስፋ ስለምናደርገው የሁላችንም አምላክ እና የእርሱ ስለሆነው ቃል ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ በሕይወታችሁ ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ስለዚህ በስሜታዊነትና በሃይማኖተኝነት መንፈስ ተሞልታችሁ ሳይሆን፣ እውነትን ለማወቅ በሚፈልግ ልብ ውስጥ ሆናችሁ እንድታነቡት እጠይቃለሁ፡፡ ይህ የአንድ የእርስዎን ሕይወት ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም፡፡ በእርስዎ ሥር ያሉትን የቤተሰቦችዎንም ሕይወት የሚመለከትና ትክክለኛ ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ የምናወራውም ስለ ቀናትና ስለ ሳምንታት አይደለም፡፡ ስለ ዘለአለም ስለሆነ ቸል ሊሉት አይገባም፡፡ አምላክ እረድቶን እየኖርን ያለነው ሁሉም መረጃዎች በቅርበትና በተደራጀ ሁኔታ በሚገኙበት ዘመን ላይ ነው፡፡ ይህም መጽሐፍ ዝም ብሎ ባልተጨበጠ መረጃ ላይ ተንተርሶ የሚያወራ ድርሳን አይደለም፡፡ በአብዛኛው እርስዎ የሚያውቋቸውንና የማያውቋቸውን የእስልምና የእምነት መጽሐፍትን ምንጭ አድርጎ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው፡፡ ስለዚህ ለቀረቡት መረጃዎች ዋቢ የተደረጉትን መጽሐፍት ማግኘት ከቻላችሁ እያመሳከራችሁ እንድታነቡ እመክራለሁ፡፡ ምናልባት አሳቤን ለመግለጽ የተጠቀምኩባቸው ቃላት ስሜታችሁን ሊያስቆጡ የሚችሉ ሆነው ብታገኟቸው፣ እናንተን የማስቆጣት አላማ የሌለኝ መሆኑን ተገንዝባችሁ

በቅንነት አንብቡት፡፡ ጥያቄም ሆነ አሳብ ማቅረብ ብትፈልጉ በአድራሻዬ ልታደርሱኝ ትችላላችሁ፡፡ አሁንም ደግሜ ማሳሰብ የምፈልገው የዘላለም ሕይወት ቀልድ አለመሆኑን እንዳትረሱ ነው፡፡ በአውቃለሁ መንፈስ ተይዛችሁ ችላ ስትሉ፣ ጥፋት እንዳይመጣ ጥንቃቄ አይለያችሁ እላለሁ፡፡ ብዙዎች አላህ ለእነርሱ ያለውን አላማ ሳይገነዘቡ እንዲሁ በጭፍን እኔ አውቃለሁ በሚል ተጉዘው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የገሃነም እራት አድርገዋል፡፡ እናንተ ግን እንደ እነዚያ እንዳትሆኑ አደራ እላለሁ፡፡

- ሁለተኛው በአጠቃላይ ይህንን መጽሐፍ ለማንበብ እድሉን ላገኛችሁ ሁሉ ነው፡፡ መጽሐፉን ለማዘጋጀት ሳስብ የሥነ ጽሑፍ ችሎታው ኖሮኝ ሳይሆን፣ እውነት አፈር ለብሳ፣ ሐሰት ገዝፎና "አብቦ" እንዳይወጣ፣ ሰዎችም ፍቅር ከሆነውና ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም ከሆነው አምላክ ተለይተው እንዳይጠፉ፣ ድብቁን እውነት ወደ አደባባይ ለማውጣት ካለኝ ቅን ልቡና አንጻር እንደሆነ በአፅንኦት ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ስለዚህ ስታነቡ ማስተላለፍ የፈለግሁትን መልዕክቴን ልትገነዘቡልኝ ሞክሩ እላለሁ፡፡ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

**ሳሂህ ኢማን**

# መንደርደሪያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት በተቺዎቹ ዓይንና ለሙግቶቻቸው መልስ

ሰይጣን በየዘመናቱ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበትን እውነተኛውን የሕይወት ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ለሰዎች አጣጥሎና አቅልሎ ለማሳየት አንዳንድ ለሃይማኖታችን ቀናኢ ነን የሚሉ ሰዎችን የራሱ አሳብ አገልጋይ አድርጎ ቀድሞ አስነስቶ ነበር፡፡ በዚህ ዘመንም አምሳያዎቹን አላጣም፡፡ አግኝቷል፡፡ የሰው ልጆች ወደ እግዚአብሔር ፍቅር እንዳይመለሱ፣ ከእርሱም ጋር ታርቀው እንዳይድኑና ባዘጋጀላቸው ውብ ስፍራ በገነት ለዘላለም በደስታ እንዳይኖሩ ለማድረግ፣ በእነዚሁ ሰዎች በብርቱ ሰርቷል፡፡ አሁንም ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ እየጣረ እንዳለ በግልጽ ይታያል፡፡

አሁን ያለነው የእግዚአብሔር ፍርድ ሊገለጥ ባለበት በመጨረሻው ሠዓት ላይ ነው፡፡ ሰይጣንም ወደ ገሃነም እሳት ለመጣል ጥቂት ጊዜ እንደቀረለት ገብቶታል[3]፡፡ ስለዚህ ካለፉት ዘመናት ይልቅ በዚህኛው ዘመን ከእግዚአብሔር ቅን መንገድ ሰዎችን መመለሱን በሙሉ ኃይሉ አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ቁርአንስ ቢሆን እርሱ /ሰይጣን/ ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነው ይል የለ?[4] በየዘመናቱ ሰዎችን ቅን ከሆነችው ከአምላካችን መንገድ እንዲመልስ ለማገዝ ሠራተኛ ሆነው የተገኙለት ሰዎችም ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፡፡ ቢሆንም የዘመናት ሥራውና አላማው ምን እንደሆነ ያለፈው ዘመን የቤተ ክርስቲያንና የሰይጣን የውጊያ ውሎ ታሪክና የአምላካችን የእግዚአብሔር ቃል በምክሩ አስጠንቅቆናል፡፡ ስለዚህ ሰይጣን በሚያስነሳቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ስጋት አይገባንም፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና አሳቡን በጭራሽ አንስተውም፡-

> 1 የዮሐንስ መልእክት 4 ፡ 1-3
>
> ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፡፡

---

[3] የዮሐንስ ራዕይ 12 ፡ 12

[4] ሱረቱል ፋጢር 35 ፡ 6

ሰይጣን ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጆች ያለውን ጠላትነት ከሚያንጸባርቅባቸው መንገዶች አንዱ እውነትን መሰወር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፤ ይህ እውነት የሰው ልጆች እውነተኛውን የጽድቅ መንገድ በማወቅ፣ አምላካቸውን እየወደዱትና እየተገዙለት በመኖር፣ እርሱ ወደ አዘጋጀላቸው የዘለአለም ደስታ እንዲገቡ መንገዱን ያሳያል፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር ፍቅሩን፣ እውነቱን ለሰው ልጆች የገለጸው በእውነተኛው ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ሰይጣንም ለክፋቱ አዋጭ ስለመሰለው በዚህ ዘመን ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ ያለው በእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝነት እንከን መፍጠሩ ላይ ነው፡፡ ለዚህም የአገራችን ዳኢዎች ሳዲቅና መሰሎቹ፣ እንዲሁም አህመድ ዲዳትና ደቀ መዝሙራቸው ዶ/ር ዛኪር ናይክ መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርአንን እናነጻጽራለን በማለት ሥራውን እየሠሩለት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለመሞገት የሚያነሷቸው ጥያቄዎች በርካታ ቢሆኑም ከእነዚያ መካከል የሚከተሉትን አራቱን በዚህ በክፍል አንድ መጽሐፍ ምላሽ እንዲሰጥባቸው መርጫቸዋለሁ፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መሆኑ
2. መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አእምሮ ሊቀበለው የማይችል አሳቦችን መያዙ
3. መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በአሳብም ሆነ በመልእክት ያላቸው አለመስማማት
4. መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ሥህተቶችን አቅፎ መያዙ

ቀሪዎቹን ጌታ ቢፈቅድና ብንኖር በተከታታይ በሚወጡት የመጽሐፉ ክፍሎች ምላሽ ይሰጥባቸዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አምላካችን ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅርና የደህንነት እቅዱን የገለጠበት እንከን የሌለው የራሱ ቃል መሆኑን የእስልምናን የእምነት መጽሐፍትንም ጭምር በማጣቀስ የሥራው ባለቤት ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን አሳያለሁ፤ ላነሷቸውም የመሞገቻ ጥያቄዎቻቸው አጥጋቢ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡

# 1. ሙግት አንድ

## መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መሆኑ

ከቀድመው የእስልምና ዘመን ጀምሮ እስካለንበት ቀን ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተበርዟል ውንጀላ የሚያሰሙ የእስልምና ዳኢዎች ቁጥር በርከት ያለ ነው፡፡ ለቀደመውም ዘመን ይሁን የአሁኑን ዘመን ሊወክሉ የሚችሉት የዓለም የእስልምና ምሁራን ፕሬዘዳንት ኢማም ዩሱፍ አል ቃራዳዊ "ኢስላምን መረዳት" በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲህ ሲሉ ያሰፈሩትን እናገኛለን፡-

> በኢስላምና በሌሎች መለኮታዊ እምነቶች መካከል ያለው ልዩነት ኢስላም ለሰው ልጅ የተላከ የመጨረሻው መልእክት ከመሆኑ አኳያ አላህ መሠረታዊ መርሆዎችን መጠበቁ ነው፡፡ እናም መበረዝና መከለስ አላገኘውም፡፡ በሌላ በኩል የሌሎች ሃይማኖቶች ምንጮች የተጠበቁ አይደሉም፡፡ ተበርዘዋል፣ ተከልሰዋል ወይም ጠፍተዋል፡፡[5]

ኡስታዝ ሳዲቅ ሙሐመድም እንዲህ ብሏል፡-

> ኦሪትም ሆነ ኢንጅል እንዲሁም ሌሎቹ ጥንታዊ ቅዱሳንና መለኮታዊ መጽሐፍት ከቅዱስ ቁርአን መውረድ በፊት ተበርዘዋል፡፡ ለእነዚህ መጽሐፍት መበረዝ ዋናውና ትልቁ ምክንያት የመጽሐፍቱ መጠበቅ ከአላህ ቃልኪዳን አለመግባቱ ነው፡፡ አላህ መጽሐፍቱን ሲያወርድ ጠብቁ ያለው ለነቢያቶቹና ለተከታዮቹ ነበር፡፡[6]

ይህ የሁሉ ድምጽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቁርአን ግን አላህ ራሱ ሊጠብቀው በሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9 ቃል ኪዳን ገብቷል ይላሉ፡-

> **ሱረቱል አል-ሒጅር (የሒጅር ምዕራፍ) 15 ፡ 9**
>
> እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡

ስለዚህ በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ደርሰዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ ተበረዘ ሲሉ፣ የአበራረዙን ሁኔታ፣ የቁርአን አንቀጾችን አባሪ በማድረግ አምስት ነጥቦችን ያቀርባሉ[7]፡-

---

[5] *ኢስላምን ለመረዳት ገጽ 11*

[6] *ሳዲቅ መሃመድ አህመድ(አቡ ሃይደር)፣ ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ)፣ 2003 ገጽ 18*

[7] *Ibide page 19-22.*

- እውነትን ከውሸት ጋር በመቀላቀል፡- ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2፡ 40-42፣ ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የዒምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 71፣ በዋቢነት ተጠቅሰዋል፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን በኦሪት ዘፀአት 32 ፡ 1-4 የወርቅ ጥጃውን አሮን ሠራው ተብሎ የተጠቀሰው ነው፡፡ በቁርአን በሱረቱል ጣሃ (የጣሃ ምዕራፍ) 20 ፡ 87-90 እንደተጠቀሰው ጣኦቱን የሠራው ሳምራዊው ሆኖ ሳለ በአሮን ቀይረውት መገኘቱ ነው ይላሉ፡፡
- እውነቱን መደበቅ፡- ዋቢ የቁርአን አያዎች ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 71፣ ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2 ፡ 42፣ 146
- እውነቱን መሸሸግ፡- ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 15
- ምላስን ማጣመም፡- ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰብ ምዕራፍ) 3 ፡ 78፣ ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 46
- ቃላትን ከስፍራው መቀየር፡- ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 3 ፡ 75፣ ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 46፣ ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 41

በእውነቱ እነዚህን የቁርአን አንቀጾች መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ ለማሳየት መጠቃቀስ ጽንፈኝነቱንና አላዋቂነቱን እዩልኝ በሎ ራስን አደባባይ ላይ እንደ ማስጣት ይቆጠራል፡፡ እነዚህ አባሪ ተደርገው የተጠቃቀሱ የቁርአን አንቀጾች የኋላ ታሪክ በእውነት ያሉትን ያሳይላቸዋል? ሌላ ቢፈላልጉ ይሻል ነበር፤ ተሳሳቱ፡፡ በእያንዳንዱ ነጥብ የተጠቃቀሱ የቁርአን አንቀጾች ቁርአን እና ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልእክትና መልእክተኛ አለመሆናቸውን ከሚያሳዩት ወገን መሆናቸውን ላረዳቸው ያስፈልገኛል፡፡ ይህንን በሰፊው በኋላ አሳያለሁ፤ ለአሁኑ ግን ሁለት ነጥቦችን ላንሳ፡-

1) የቁርአን አንቀጾቹ የወረዱበት አስባብ /ምክንያት/ ከመጽሐፍ ቅዱስ መበረዝ ሐሳብ ጋር በምንም አይገናኝም፡፡ ነበር እንኳን ቢባል ምክንያቱ አጥጋቢ ሊሆን አለመቻሉ ነው፤
2) የተዘረዘሩ የቁርአን አንቀጾች መበረዙን ለማሳየት የወረዱ ናቸው ከተባለ፣ ቁርአን እርስ በእርሱ መጋጩት ይጀምራል፡፡ የአላህ ቃል ከሆነ ደግሞ፣ ምንም አይነት ግጭት ሊታይበት አይገባም፡፡ ስለዚህ ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚመለከቱት የአገራችንና የውጮቹ የእስልምና ዳኢዎች ድምዳሜያቸው ተቀባይነት አይኖረውም፤ እመለስበታለሁ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ስላለው የመበረዝ አለመበረዝ እሰጥ አገባ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ ወዳልገለጧቸው፣ የእስልምና መጽሐፍት ውስጥ ወደ ተደበቀው እውነት እንለፍ፡-

## 1.1. የተበረዘው ማን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ቁርአን?

በመጀመሪያ እነዚህ የእስልምና ዳኢዎች በሁለቱ መጻሕፍት መካከል መበረዝን እንደ ምክንያት ማንሳታቸው ደስ ያሰኘኝ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ፡፡ እንግዲህ አላህ ጠባቂው ነው በተባለለት በቁርአንና ሰዎች እንዲጠብቁት ታዘዙ በተባለለት በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል መበረዝ እንደ ምክንያት ከተነሳ፣ እውነት የተበረዘው ማን ነው? የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግሉን የሚችሉ አካላት፣ በተለይም በእስልምና ምሁራኑ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የሃይማኖቱ የመረጃ ምንጮች፣ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ብለው ለማመናቸው የሚጠቅሱት ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9 ነው፡፡ ይህ አንቀጽ ለመረጃ ከተጠቀሰ የምጠይቀው ጥያቄ ይኖረኛል፡-

- አሁን ላይ በክርስቲያኖችና በአይሁዳውያኑ እጅ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ነው ብሎ ለመናገር የሚቻለው እንዲሁ በደፈናው ሳይሆን፣ ያልተበረዘውን መጽሐፍ ቅዱስ በእጅ ይዞ ካመሳከሩ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ ያመሳከሩበት ያልተበረዘው መጽሐፍ ቅዱስ በእጃቸው ይኖር ይሆን?
- እውን ይህ መሞገቻ በአላህ ባህርይ መነጽር ሲታይ አጥጋቢ ነው ማለት ይቻላል? አንዱን የራሱን ቃል በሰው ሲያስጠብቅ፣ ሌላውን ራሱ ሊጠብቀው ቃል እንዲገባ ያስቻለው ምክንያቱ ምንድን ነው? አላህ ከባህርይው ውጭ አይሠራም፤ ታዲያ የየትኛው ማንነቱ መገለጫ ነው? መጽሐፍ ቅዱስም ሰዎች የአላህን ቃል እንዲጠብቁት ሲያዝ ይታያል፡፡ ይህ ማለት ግን ቁርአን እንደሚለው ሰው ከአላህ ተሽሎ ቃሉን /መጽሐፉን/ ከጠላት እንዲጠብቀው ታዘዘ ማለት አይደለም፡፡ በተሰጠው የእድሜ ዘመን ሁሉ ቃሉ የሚያዘውን እየታዘዘ እንዲኖር ማስጠንቀቁን ለማሳየት የገባ ቃል ነው፡፡ (መጽሐፈ ኢያሱ 1 ፡ 7-9፣ 1ኛ መጽሐፈ ነገስት 2 ፡ 3-4፤ ኦሪት ዘዳግም 28 ፡ 13)
- ይህ መደምደሚያ በትክክል ቁርአንንና የነቢዩን ሐዲሳት ባገናዘበ መልኩ ተጠንቶ የተደረሰበት መደምደሚያ ነው ማለት ይቻላል? ለዚህስ ምን ያህል እርግጠኞች ናቸው?
- በአላህ ስለመጠበቃቸው ካነሳን ገሃድ ከወጣው እውነተኛ ታሪካቸው የሚታየው የመጽሐፍ ቅዱስ በአላህ መጠበቅ ወይስ የቁርአን?

ተሚጋቾቹ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ አበው እንደሚሉት "ሞኝ ያሸንፋል" አይነት እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ በእስልምና ምሁራኑ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የመረጃ ምንጮች በጉልህ ድምጻቸውን አውጥተው የሚናገሩት "የመጽሐፉ ሰዎች የቀደሙት መጻሕፍት /መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው/ መጀመሪያ ላይ አላህ ባወረደበት ሁኔታ ያለምንም እንከን አሁን ድረስ ይገኛሉ" የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ የአይሁዳውያኑንና የክርስቲያኑን ማሕበረሰብ የመረጃ ምንጮች የሚሰጡትን ምላሽ ለጊዜው አቆይቸዋለሁ፡፡ ሌላው ሱረቱል አል-ሒጅር

(የሒጅር ምዕራፍ) 15 ፡ 9 ምንም ስለ ቁርአን በአላህ መጠበቅ ያወራል ቢባልለትም ቁርአን የአላህ ቃል እንዳልሆነና ነቢዩ ሙሐመድም የእርሱ መልእክተኛ እንዳልሆኑ ከሚያረጋግጡልን በርካታ የቁርአን አንቀጾች መካከል አንዱ መሆኑን ምን ያክል ያውቁ ይሆን?

እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እራሳቸውን የሚቆጥሩ የእስልምና ዳኢዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን መከራከር ሲፈልጉ፣ የማደናገሪያ ሐሳባቸውን እንዲደግፍላቸው አስበው አንቀጹን ይይጥቀሱት እንጂ እንደሚሉት የቀደሙት መጽሐፍት "ተበረዙ" ብሎ ለመናገርና በአላህ ስለመጠበቃቸውና አለመጠበቃቸው ለማውራት ተፈልጎ የወረደ አንቀጽ አይደለም፡፡ ይህም አድራጎታቸው በየትኛውም የቁርአን ተፍሲር ሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ምእራፉ በራሱ በታሪካዊ ስህተቶች የተሞላ ቢሆንም የተጠቀሰው ክፍል ለምን እንደ ወረደ ለማወቅ የሚፈልግ ከአንቀጽ 6 ጀምሮ ቀጥሎ እስካሉት አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 11 ድረስ በማንበብ የክፍሉን ሙሉ አሳብ ማግኘት ይችላል፡፡ ያም ሆኖ በስልጣናቸው አንቀጽ 9ን እንዳሉት ሊያስወሩት ከፈለጉ ግን ታዲያ አላህ በቃሉ መሰረት ቁርአንን ጠብቆታል ማለት ይቻላል? ከምን ከምን ነበርስ የሚጠብቀው? ብዬ ለመጠየቅ እገደዳለሁ፡፡

ኢብን አባስ ለዚህ አንቀጽ በሠራው ማብራሪያ አላህ ቁርአንን ከሰይጣን እንደሚጠብቀው፤ ማለትም ሰይጣናት እንዳይጨምሩበት፣ እንዳይቀንሱበት እና ከሕግጋቱ እንዳይለውጡበት ከእነርሱ እንደሚጠብቀው ያብራራል፡፡[8] ሁለቱ ጃላላዎች በሰሩት ማብራሪያም አሁንም አላህ ቁርአን እንዳይለወጥ፣ እንዳይበረዝ፣ እንዳይጨመርበትና እንዳይቀነስበት እንደሚጠብቀው ያትታል፡፡[9] ሆኖም ከከሊፋ ኡስማን የእሳት ትንታጎች ሊጠብቀው ግን አልቻለም፡፡

ለማንኛውም ምንም እንዲያ ቢባልለትም ቁርአን በአላህ ጥበቃ የተደረገለት መጽሐፍ አይደለም፡፡ እስልምና አንድ ካለበት ዘመን ጀምሮ የነበሩ፣ አሁንም በሕይወት ያሉ፣ የሃይማኖቱ ሊቃውንት ሁሉም ሙስሊም ማሕበረሰብ ልቡን ሠጥቶ ባመነባቸውና በተቀበላቸው መጽሐፍቶቻቸው ምንም ሳይደባብቁ፣ "አዎን ቁርአን በእርግጥ የተበረዘና ለትውልድ ያለምንም እንከን መተላለፍ ያልቻለ መጽሐፍ ነው" ሲሉ በአንድ ድምጽ የእማኝነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ እስላማዊ የመረጃ ምንጮች፣ አሁን ያለው ቁርአን፣ ሙሉነት የጎደለው፣ የተጨመረበት፣ የተቀነሰበት፣ የተሰረዘና የተደለዘ፣ በርካታ ክፍሎቹ የጠፉ እና በእሳት የጋዩ መሆናቸውን በግልጽ ይናገራሉ፡፡ የመረጃ ምንጮቹ ስለ ቁርአን

---

[8] Abdullāh Ibn 'Abbās, Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, *translated by Mokrane Guezzou, Royal Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought, Amman 2008, page 273.*

[9] Jalal al-din al-mahalli and Jalal al-din al-Suyuti, Tafsir Al-Jalalayn, translated by Feras Hamza, Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought Amman, Jordan 2007, page 270.

ከአላህ ጥበቃ ውጭ መኖር፣ መበረዝ፣ መሰረዝና መደለዝ፣ እንዲሁም ስለሌሎች ተጨማሪ ሁኔታዎች የሚናገሩትን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

### 1.1.1. የቁርአን ቅጅዎች በከሊፋ ኡስማን ትእዛዝ በእሳት መጋየታቸው

የቁርአን የመጀመሪያው ከአላህ ጥበቃ ውጭ የሆነበትና ለትውልድ ያለምንም እንከን ሊተላለፍ ያልቻለበት ምክንያት በከሊፋ ኡስማን የደረሰበት የእሳት ቃጠሎ ነው፡፡ የቁርአንን አነባበብ መንገዶች ብዛት በተመለከተ ነቢዩ ሙሐመድ ምእመናቸውን ወክለው በገብርኤል አማካኝነት ከአላህ ጋር ከፍተኛ ድርድር አድርገው ነበር፡፡ በዛም ድርድር ቁርአን በሰባት የአረብኛ ዝዬዎች እንደ ወረደ እና በሰባት የአነባበብ መንገዶች እንዲነበበብ እንደተፈቀደ የታመኑት ሐዲሶች ይናገራሉ፡፡

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ** 2፣ **ቁጥር** 1906

> ነቢዩ በቤኑ ጊፋር ኩሬ ነበሩ፤ ገብርኤልም ወደ እርሳቸው መጥቶ "ተከታዮችህን **በአንድ የአነባበብ** መንገድ ወይንም ስልት እንድታስተምራቸው አላህ አዞሃል" አላቸው፡፡ እርሳቸውም "ይቅርታና ምህረት አላህን እለምናለሁ፤ ተከታዮቼ ያንን ማድረግ አይችሉም" አሉት፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እርሳቸው መጣና "ቁርአንን ለተከታዮችህ **በሁለት የአነባበብ** መንገድ እንድታስተምራቼው አላህ አዞሃል" አላቸው፡፡ እርሳቸውም "አላህን ምህረቱንና ይቅርታውን እጠይቃለሁ፣ ተከታዮቼ ያንን ማድረግ አይችሉም" አሉት፡፡ ከዛም ለሦስተኛ ጊዜ መጣና እንዲህ አላቸው፡- "ቁርአንን ለተከታዮችህ **በሦስት የአነባበብ መንገድ** እንድታስተምራቸው አዞሃል" አላቸው፡፡ እርሳቸውም "አላህን ምህረቱን እና ይቅርታውን እጠይቃለሁ ተከታዮቼ ይህንን አይችሉም" አሉት፡፡ ገብርኤልም ለአራተኛ ጊዜ መጥቶ "አላህ ቁርአኑን ለተከታዮችህ **በሰባት የአነባበብ መንገድ እንድታስተምራቸው አዞሃል**፤ **በየትኛውም የአነባበብ መንገድ ቢያነቡት ትክክል ናቸው"** አላቸው፡፡[10]

ነገር ግን ነቢዩ ሙሐመድ ከሞቱ ከሃያ ዓመታት በኋላ በ652 ዓም ላይ ይህንን የአላህን እና የነቢዩን ትእዛዝ ከእቁብ ያልቆጠረ ሥራ ተፈጸመ፡፡[11] አዘርባጃንን እና አርመንያን ሊወር የወጣው የእስልምና ሰራዊት ቁርአንን በተመለከተ ተቃርኖ እንደተፈጠረ እና እንደተለያዩ ከሊፋ ኡስማን ዜና ይደርሰዋል፡፡ በዚህ ወቅት አላህና ነቢዩ "በየትኛውም መንገድ ቢያነቡ ትክክል ናቸው" ማለታው

---

[10] *Imâm Abul Hussain Muslim bin al-Hajjaj, English Translation of Sahih Muslim, translated by Nasiruddin al-Khattab, Dar-us-Salam, Riyadh 2007 page 339*

[11] *https://www.al-islam.org/restatement...and-muslims.../uthman-third-khalifa-muslims*

ትክክል አይደለም በማለት አራት ሰዎችን በመመደብ በቁሬይሾች የአነባበብ መንገድ ብቻ በማጻፍ በዚሁ መንገድ ብቻ እንዲነበብ ትእዛዝ አወጣ፡፡ በዚህም ሳያበቃ በሰዎች ሁሉ እጅ የሚገኙትን የቁርአን ቅጆች ለማመሳከሪያነት እንኳን እንዳይተርፉ በአጠቃላይ ሰብስቦ እሳት ለቀቀባቸው፡፡[12]

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4987**

> የሶርያና የኢራቅ ሙስሊሞች አዘርባጃንን እና አርመንያን ለመውረር ጦርነትን ባወጁበት ወቅት ሁዜይፋ ቢን አል-ያማን ወደ ኡስማን መጣ፡፡ <u>ሁዜይፋ በሶርያና በኢራቅ ሙስሊሞች በቁርአን አነባበባቸው ባላቸው ልዩነት ፍርሃት ነበረበት፡፡</u> ስለዚህ ኡስማንን እንዲህ አለው፡- "የምእመናኑ መሪ ሆይ! ከእነርሱ በፊት የነበሩት አይሁዶችና ክርስቲያኖች እንደተለያዩት ይህ ትውልድ በቁርአኑ ከመለያየታቸው በፊት ልትታደጋቸው ይገባል"፡፡ ኡስማንም እንዲህ የሚል መልእክተኛ ወደ ሃፍሳ ላከ፡- "የቁርአኑን ጽሁፍ ላኪልን፤ ትክክለኛ የቁርአን ቅጅ ካደራጀን በኋላ መልሰን እንልክልሻለን"፡፡ ሃፍሳም ለኡስማን ላከችለት፡፡ ኡስማንም ዛይድ ቢን ሳቢትን፣ አብዱላህ ቢን አዝ-ዙቤይርን፣ ሳኢድ ቢን አል-አስን እና አብዱር-ራብማን ቢን ሃሪሳ ቢን ሂሻምን ዋናውን ቅጅ በትክክል እንዲገለብጡ አዘዛቸው፡፡ ኡስማን ለሦስቱ ቁሬይሻዊ ሰዎች እንዲህ አላቸው፡- "ምናልባት ከዛይድ ጋር ቁርአን ውስጥ በአንዳች ባትስማሙ ቁርአን በቁሬይሽ ዝዬ ስለወረደ ዝም ብላችሁ በቁሬይሽ አነጋገር ጻፉት፡፡" እነርሱም እንደተባሉት አደረጉ፤ ብዙ ቅጅዎችንም ጻፉ፡፡ ኡስማንም ዋናውን ቅጅ ለሃፍሳ መለሰላት፡፡ ኡስማንም ለእያንዳንዱ የሙስሊሞች ከተሞች አንድ አንድ ቅጅ ላከላቸው፤ ሌሎቹ ቁርአናዊ ቅጅዎች፣ በተበታተነ መልኩ የነበረ የቁርአን ጽሁፍ ይሁን ሙሉ ቅጅ <u>እንዲቃጠሉ አዘዘ ተቃጠሉም</u>፡፡

እንግዲህ እነዚህ ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩ ዳኢዎች ሱረቱል አል-ሒጂር (የሒጅር ምዕራፍ) 15 ፡ 9 የቁርአንን በአላህ የመጠበቅ ዋስትናን ያሳያል ካሉ፡-

- በመሠረቱ አላህ የራሱን መጽሐፍ ለመጠበቅ ኪዳን መግባት አስፈላጊው ነበር ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ቢሆንም ለቁርአን ጠባቂው ራሱ ከሆነ፣ ለነቢዩ የሰጣቸው መጽሐፍ ከሊፋ ኡስማን በእሳት ሲጋይ የት ነበር?
- ሊጠብቀው ኪዳን የሰጠለት መጽሐፍ እንዲያ ሲቃጠል እያየ በዝምታ መመልከቱ፣ የከሊፋው ድርጊት ትክክል ነበር ማለት ነው? ትክክል ከነበርና አላህም የመጽሐፉ ብቸኛ ጠባቂ ከሆነ፣ ለቃጠሎ የዳረገው

---

[12] *Al-Bukhari, Muhammed Ibn Ismaiel, Sahih Al-Bukhari, translated by Muhammad Muhsin Khan, Dar us Salam, Riyadh 1997, vol 6 page 425,*

*ምክንያት በመጀመሪያ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ይህስ የአላህን የጥበቃ ኪዳን ያረጋግጥልናል?*

- *ይህ እየሆነ ያለው ነቢዩ ከሞቱ ከሃያ ዓመታት በኋላ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የመጀመሪያውን ቁርአንን ከተበታተነበት የማሰባሰቡን ሥራ የሠሩት ሁለቱ ከሊፋዎችም አልፈዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ቁርአን ለቃጠሎ የሚያበቃው ችግር ውስጡ ከታየበት፣ ጠባቂው አላህ ከሆነ ይህንን ያክል ዓመታት ከመጠበቅ ይልቅ፣ መጀመሪያ ላይ ችግሩ እንደተከሰተ ወዲያውኑ ማስተካከል ለምን አላስፈለገውም? ይህስ የአላህን የጥበቃ ኪዳን ያለምንም እንከን እየተፈጸመ እንደ ነበር ያሳያል ብላችሁ ታምናላችሁ?*
- *ነቢዩ ከሞቱ ከአንድ ዓመት በኋላ ቁርአን ሙሉ ለሙሉ የመጥፋት አደጋ ተጋርጦበት ነበር፡፡ ቁርአንን ከዚህ አደጋ ለመታደግ መደረግ ስለሚገባው ነገር ከሊፋ ኡመር ከከሊፋ አቡበከር ጋር ተመካክሯል፡፡ በዚያም ቁርአኑን ከተበታተነበት በማሰባሰብ በመጽሐፍ መልክ ይጠረዝ፤ ይህንን ሐላፊነት ዛይድ ቢን ሳቢት ይውሰድ የሚል ውሳኔ ላይ ደርሰው፣ ዛይድ ቢን ሳቢትም የሥራ ታሪኩ ይነግረናል፡፡*[13] *ቀድሞ ይህ ተሰርቶ እያለ አሁንም ከዓመታት በኋላ ቁርአን ለእሳት የሚያበቃው ችግር ከተገኘበት፣ እንዲህም እየሆነ አላህ የቁርአን ጠባቂው ነው ከተባለ፣ በገባው ቃል መሠረት ጥበቃ አድርጎለታል ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል? አላህ ጠባቂው ከሆነና በኋላ ለእሳት የሚያበቃው ችግር ከነበረበት ያኔ ላይ ማስተካከል አይችልም ነበር?*
- *ይህ የከሊፋ ኡስማን አድራጎት፣ የመነሻ ምክንያት ነቢዩ ሙሐመድ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ተከስቶ፣ አላህ ገብርኤልን ወደ ነቢዩ በመላክ መፍትሄ ተበጅቶለት እንደነበር ሐዲሳቱ ነግረውናል፡፡ እንግዲህ የቁርአኑ ጠባቂ አላህ ከሆነ፣ ይህንን የጥበቃውን ተግባር በሚጻረር መልኩ ከሊፋው ለነቢዩ የተሰጣቸውን ቁርአን በእሳት ሲያጋይ በዝምታ መመልከቱ ምን ተብሎ ሊተረጎም ይችላል?*
- ከሊፋ ኡስማንን በቁርአን መነጽር እስኪ እንገምግመው፡-

**ሱረቱል አል-አሕዛብ 33 ፡ 36**

*አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና **<u>የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡</u>***[14]

---

[13] *Al-Bukhari, Muhammed Ibn Ismaiel, Sahih Al-Bukhari, translated by Muhammad Muhsin Khan, Dar us Salam, Riyadh 1997, vol 6 # 4679, page 156*

[14] ኢቅራ ቁርአን ሶፍት ዌር፣ ነጃሺ መልቲሚዲያ ፕሮዳክሽን የተዘጋጀ

وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلَا مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ ۗ
وَمَن يَعْصِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا مُّبِينًا

እንግዲህ ከሊፋው አላህ እና ነቢዩ ሙሐመድ የደነገጉትን በሰባት መንገድ እንዲነበብ ያዘዙትን ትእዛዝ በመጣስ አላህንና ነቢዩ ሙሐመድን ልክ አይደላችሁም መሆን ያለበት እንዲህ ነው ብሎ አርሚቸዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ አላህ ምንም አላለውም፤ ታዲያ አላሁ ማን ነው? ማረም የቻለው ከሊፋ ኡስማን? ጥበቃውስ ምንድን ነው? ኡስማን ካልሆነ እጠብቀዋለሁ የሚለውን ቃል አላህ አልተናገረም ማለት ነው፤ ስለዚህ የተዘበራረቀ ታሪክ ያለው ቁርአን የአላህ ቃል አይደለም ማለት ነው፡፡ ቢሆንማ ኖሮ ማንም እየተነሳ ሊያስተካክለው እጁን አያነሳበትም ነበር፡፡

- አላህ ቁርአንን ሊጠብቀው ቃል ከገባ ይጠብቀዋል፤ በየትኛውም ዘመን ስህተት ሊገኝበት ከቶውን አይችልም፡፡ እየታዬ ያለው ግን ከዚህ የተለየ ነገር ነው፡፡ እንግዲህ ቁርአን የሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9ን አፈጻጸም የሚቃረኑ ነገሮች እየተፈጸሙበት የነበር ከሆነ፣ ከአላህ ማንነት ጋር ግጭት ስለሚያሳይ ቃሉ "የአላህ ቃል ነው" ብሎ በድፍረት መናገር አይቻልም፡፡

## 1.1.2. ቁርአን ከጅምሩ ጀምሮ ሰፊ ልዩነት ባላቸው፣ አራትና ከዛ በላይ በሆኑ ቅጂዎች ዛሬ ላይ መገኘቱ

ከሁሉም ሙስሊም እንደበት ቁርአን እስካሁን ድረስ አንድ ቅጂ ብቻ እንዳለውና በእርሱም ምንም የነጥብ ስህተት እንኳን እንደሌለበት ይነገራል፡፡ ነገር ግን እንዲህ እንደሚወራለት አለመሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን የራሳቸውን ቁርአን ያዘጋጁ ሰዎች ቁጥር በትንሹ 23 ይደርሳል ይላሉ፤[15] ጀፈሪም (Arthur Jeffery) የጥንት ጽሑፋቱን ቁጥር 29 ያደርሱታል፤ በመካከላቸውም ስላለ ልዩነት ብዙ ብለዋል፡፡[16] ከከሊፋ ኡስማን ሞት በኋላም፣ ቁርአን ሃያ የሚደርሱ ቅጂዎች እንዳሉት የታሪክ መዛግብት ያስገነዝባሉ፡፡[17] ከእነዚያ ሃያ ከሚደርሱት ቅጂዎች መካከል በበርካታ ልዩነቶች ተሞልተው እዚህ ዘመን ላይ ከሚገኙት አራቱን ልጥቀስላችሁ፡፡ ከአራቱ ቅጅዎች ሦስቱ እጄ ላይ እንደሚገኙም ሳልጠቅስላችሁ አላልፍም፡፡

1. **የዋርሽ ቁርአን ቅጂ፤-**

---

[15] *Ahmad von Denffer, Ulum al Qur'an, 1981 pdf page 82*

[16] *Arthur Jeffery, Materials For The History Of The Text Of The Qur'an,The Old codices, Cairo, 1936*

[17]

ይህ የቁርአን ቅጅ "ከአላህ ፈቃድ ካገኙት" ከሰባቱ የአረብኛ ዝዬዎች መካከል በአንዱ በመዲናዊ ዝዬ የተዘጋጀ የቁርአን ቅጅ ነው፡፡ በዚህ ዝዬ በአስተማሪነት ኢማም ናፊ አል-መደንይ /70-169 ሂ/ ይታወቃሉ፡፡ እኚህ ሰው ከሊፋ ኡስማን በመካ የአረብኛ ዝዬ ብቻ እንዲነበብ፣ ያዘጋጀውን ቁርአን በዛው በመዲና ካስቀመጠና የራሱ ቁርአን እንዲኖረው የሚፈልግ ሰው ከዛ እንዲገለብጥ ትእዛዝ ካስተላለፈ ከአስራ አራት ዓመት በኋላ የተወለዱ ሰው ናቸው፡፡ በዚህ ዘመን ላይ ተወልደው፣ ለትምህርት ደርሰው ተምረው አስተማሪ ሆነው ያስተማሩት ከከሊፋው በተቃራኒ በመዲና ዝዬ ነው፤ እንዴት ሊሆን ቻለ? የከሊፋው ሥራ የአላህ ፈቃድ አልነበረም ማለት ነው? ወይስ ሰዎች እንደወደዱ ፈቃዳቸውን ያደርጉበት ነበር? እነዚህን እና ሌሎች ብዙ ጥያቄዎችን እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡ ለማንኛውም ይህ ሁኔታ ከከሊፋ ኡስማን አስተሳሰብና ድርጊት ጋር በቀጥታ የሚቃረንና ምናልባት "ወደ አላህ" እና ወደ ነቢዩ ሙሐመድ አሳብ የሚመለስ ይሆናል፡፡ በዚህ የከሊፋ ኡስማን ድካም ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል፡፡ ይህንን የቁርአን ቅጅ በመጽሐፍ መልክ ያዘጋጀው የኢማም ናፊ አል-መደንይ ተማሪ የነበር የአንድ ቁሬይሻዊ ባርያ የነበር **ኡስማን ኢብን ሳኢድ አል-ቁጥቢ** /110-197 ሂ/ የተባለ ሰው ነው፡፡ የተወለደውም ከከሊፋ ኡስማን ሞት ከ54 ዓመታት በኋላ ነው፡፡ ይህ ሰው ያዘጋጀው የቁርአን ቅጅ በአሁን ጊዜ በሊቢያ፣ በአልጀሪያ፣ በሞሮኮ፣ በቱኒዚያ፣ በምዕራብ አፍሪካና በሱዳን በሚኖሩ ሙስሊሞች እየተገለገሉበት ይገኛል፡፡ ይህ ቅጅ በእጀ ካሉት አንዱ ነው፡፡

1. 
2. 

1. mushâf in the riwaya of Warsh. This is printed in Morocco.
2. This is a mushâf from Algeria with the riwaya of Warsh.

## 2. የቃሉን ቁርአን ቅጂ፡-

ይህ የቁርአን ቅጅ ከዋርሽ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ከአንድ አስተማሪ የመነጨ ነው፡፡ ከኢማም ናፊ አል-መደኒይ /70-169 ሂ/ በመዲና ዝዬ የተላለፈ ቁርአን ነው፡፡ ይህንን የቁርአን ቅጅ ያዘጋጀው **በአቡ ሙሳ ኢሳ ሚና አል-ዛርቂ** /120-220 ሂ/ የተባለ ሰው ነው፡፡ ይህም ሰው ከከሊፋ ኡስማን ዘመንና ድርጊት እሩቅ የሆነ ጊዜ ላይ የተወለደ ሰው ነው፡፡ ያዘጋጀው መጽሐፍ በአሁኑ ጊዜ በሊቢያ፣


ቱኒዚያ፣ በኩዋታር በከፊል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፤ ይህም ቅጅ በእጀ ይገኛል፡፡




The riwaya Qâlûn from Nâfî. This mushâf is published in Tunisia by ad-Dâr at-Tunissia lilnashr.[18]

### 3. የአል-ዱሪ ቁርአን ቅጂ፡-

ይህኛውም ከሰባቱ ዝዬዎች አንዱ በሆነው በደማስቆ የአረብኛ ዝዬ የተዘጋጀ የቁርአን ቅጅ ነው፡፡ ይህ ቁርአን የተላለፈው በአቡ አምር ኢብን አል-አላ /68-154 ሂ/ ነበር፡፡ እኒህም ሰው የተወለዱት ከሊፋ ኡስማን ያዘጋጀውን ቁርአን ወደ ደማስቆ ከተላከና ሰዎች ሁሉ ከዛ ቁርአን ቅጅ እንዲገለብጡ ካዘዘ ከ16 ዓመታት በኋላ ነበር፡፡ ምንም ከሊፋ ኡስማን እንዲያ ብሎ ትእዛዝ ቢያወጣም እኒህ ሰው አንተን ከምሰማ "አላህን" እና ነቢዩን ብሰማ ይሻላል ያሉ ይመስላል፤ ከከሊፋው በተቃራኒ አስተምረዋል፡፡ ያንንም ተማሪያቸው ኢራቃዊው በአቡ አምር ሃፍስ **ኢብን ኡማር ኢብን አብዱልአዚዝ አል-ባግዳዲ /ሞት** 246 **ሂ/** በመጽሐፍ መልክ ሰድሮታል፡፡ በአሁኑ ወቅት በከፊል በሱዳንና በምእራብ አፍሪካ አገሮች በሚኖሩ ሙስሊሞች ተቀባይነት አግኝቶ እየተገለገሉበት ይገኛል፡፡




The Qur'an in the riwaya of ad-Dûrî from Abî Amrû This mushâf is from Sudan

### 4. የሃፍስ ቁርአን ቅጂ፡-

[18] *http://www.islamic-awareness.org/Quran/Text/Qiraat/hafs.html*

ይህኛው የቁርአን ቅጅ በኢራቅ በኩፋህ የአረብኛ ዝዬ የተዘጋጀ ቁርአን ነው፡፡ ኢማም አሲም አል-ኩፊ /127 ሂ የሞተ/ በሚባሉ ኢራቃዊ ሰው የተላለፈ የቁርአን ቅጅ ነው፡፡ ይህኛውም የከሊፋ ኡስማንን ተግባር ይቃረናል፤ በመጽሐፍ መልክ ያተዘጋጀው ደግሞ የእኒህ ሰው ተማሪ የሆነው ' የተባለ ሰው ነው፡፡ ይህ ቅጅ በሳውዲ አረብያ የሚታተመውና አብዛኛው ሙስሊም የሚጠቀምበት የቁርአን ቅጂ ነው፡፡ በእኔ ምናልባት እርስዎም ቁርአን ካለወ ት በርስዎም እጅ የሚገኘው ቁርአን ማለት ነው፡፡

This  is a well known and common mushâf of the Qur'an printed in the Saudi Arabia. They have adopted the Hafs Qirâ'a.

በቁርአን ቅጂዎችና በነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ዙሪያ ሰፊ ምርምር ያደረጉ የእስልምና ምሁራን በዚህ ዘመን አገልግሎት እየሰጡ በሚገኙት የቁርአኑ ቅጂዎች ላይ ጥልቀት ያለው ምርምር አድርገዋል፡፡ እናም በእነዚሁ የቁርአን ቅጅዎች መካከል በርካታ መሠረታዊ ልዩነቶች እንዳሉባቸው ይናገራሉ፡፡ በኢስላሚክ ጥናቶች የድህረ ምረቃ (MA ISLAMIC STUDIES) ምሩቅ ሳፊ አል-ሻሐዳ የተባሉ ምሁር THE SEVEN AHRUF በተሰኘው ጽሁፋቸው በቁርአን ቅጂዎቹ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ሰባት ያደርሱታል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰባትም ያስበልጡታል፡-

1. የአነባበብ ልዩነት
2. የአናባቢ ሥርአተ ነጥቦች የፊደላትና የቃላት ልዩነት
3. የቃላት ለውጥና የአንቀጾች ቁጥር አሰጣጥ ልዩነት
4. የቃላት ቅደም ተከተል ልዩነት
5. የቃላት ወይም የፊደላት ጭማሬና ቅነሳ
6. የቃላት አወቃቀር ልዩነት፣ ለምሳሌ ብዙ ቁጥር ወደ ነጠላ ወይም ሁለት ወይም የተለዩ ለውጦች መቀየር፣ አንስታይ ጾታ የሆነ ወደ ተባዕታይ ጾታ መቀያየር ይታይባቸዋል፡፡
7. የቃላት አረባብ ወይንም አሰባበር ነጥቦች ልዩነት ናቸው፡፡[19]

[19] *www.alfatihonline.com/en/articles/***ahruf***.htm*

በአንድ መለኮታዊ በሚባል መጽሐፍ ቅጅዎች እንዲህ አይነት ልዩነኖች የሚገኙ ከሆነ በየቅጅዎቹ የሚገኘው መልእክት የተለያየ እንዲሆን ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡ እስኪ ከተዘረዘሩት ከሰባቱ የልዩነት ነጥቦች መካከል ሁለቱን እንደ ምሳሌ ወስደን እንገምግም፡፡ በመጀመሪያ በዋርሽ እና በሃፍስ ቅጅዎች መካከል ያለውን የምእራፎችን የቁጥር አሰጣጥ ልዩነት እንመልከት፡-

| በዋርሽ እና በሃፍስ ቅጅዎች ምእራፎ የያዙት ቁጥሮች ብዛት[20] | | |
|---|---|---|
| ምእራፍ | የሃፍስ ቅጅ | የዋርሽ ቅጅ |
| ሱረቱል አል-በቀራ /ምእራፍ 2/ | 286 | 285 |
| ሱረቱል አል-ማኢዳ /ምእራፍ 5/ | 120 | 122 |
| ሱረቱል አል-ተውባ /ምእራፍ 9/ | 129 | 130 |
| ሱረቱል አር-ሩም /ምእራፍ 30/ | 60 | 59 |
| ሱረቱል አል-ኒሳዕ /ምእራፍ 4/ | 176 | 175 |
| ሱረቱል ሳድ /ምእራፍ 38/ | 88 | 86 |

በአጠቃላይ በሁለቱም ቅጅዎች በ114ቱ ሱራዎች ያሉ ቁጥሮች ብዛት በዋርሽ 113 ቢስሚላህን ሳይጨምር 6214 ያህል ሲሆን በሃፍስ ደግሞ 112 ቢስሚላህን ሳይጨምር 6236 ቁጥሮች ይገኛሉ፡፡[21] ኢማም ኢብን ካሲርም በአንቀጾቹ ብዛት ያለውን ልዩነት በተፍሲራቸው የመጀመሪያ ቅጽ መግቢያ ላይ በዝርዝር ገልጸውት እናገኛለን፡፡ ታዲያ እነ ኡስታዝ ሳዲቅ (አቡ ሀይደር) በአንቀጾቹ ቁጥር መለያየት ዙሪያ እንዲህ አይነት ማነጻጸሪያዎችን ሲያዩ "የቁርአንን ምእራፎች አንቀጽ ያዋቀረው ሰው ነው፤ ስለዚህ እንደ ችግር ሊታይ አይገባም" ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ያላቸውን የእውቀት ድህነት በግልጽ ያሳያል፡፡ የነቢዩን ሐዲሳት ቢያውቁ ኖሮ አደራጀቱም ራሱ ወህይ መሆኑን ባወቁ ነበር፤ ንግግራቸውም ቁጥብ ይሆን ነበር፡፡[22] አላህ ዘንድ ካለው ከመጽሐፎች እናት ጋር ተመሳሳይ የአንቀጽ ብዛትን የያዘው የቁርአን ቅጅ የትኛው ነው?

ሁለተኛው ምሳሌ የአናባቢ ሥርአተ ነጥቦች፣ የፊደላትና የቃላት ልዩነትን የተመለከተ ይሆናል፡፡ ቁርአን አላህ ዘንድ ካለው የመጽሀፍቶች እናት (ሱረቱል

---

[20] *Layth Al-Shaiban, Which Qran?, www.free-minds.org/sites/default/files/WhichQuran.pdf*

[21] *Ibid*

[22] *Imam Al-Qurtubi, Tafseer Al-Qurtubi, translated by Aisha Bewley, Dar Al Taqwa Ltd, London 2003, vol 1 page 60.*

አዝ-ዝኹሩፍ 43 ፡ 3-4) ከሚባለው መጽሐፍ እየተቀዳ ለነቢዩ የተሰጠ መጽሐፍ እንደሆነ ተነግሮለታል፡፡ በእንዲህ አይነት ማንነት ያለው መጽሐፍ ከሆነ ምንም ዓይነት ችግር ሊገኝበት አይገባም፤ ሆኖም ግን አልሆነም፡፡ በቅጅዎቹ መካከል ግልጽ የሆነ የአናባቢ ሥርአተ ነጥቦች፣ የፊደላትና የቃላት ልዩነቶች እንዳሉ የእስልምና ምሑራኑ እየተናገሩ ነው፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ካሉ መልእክቱ እንደዛው መለያየቱ የማይቀር ነው፡፡ ይህም አላህ ለሰዎች ማስተላለፍ የፈለገው የትኛውን ነው? ብለን እንድንጠይቅ ያስገድዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኋላ የምመለስበት ቢሆንም የአናባቢ ስርዓተ ነጥቦቹም ቢሆኑ ከነቢዩ እና ከከሊፋዎቹ ሞት በኋላ ሌላ ሰው የጨመራቸው እንጂ የወህዩ አካል አለመሆናቸውን ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

| የሃፍስ ቅጅ | የዋርሽ ቅጅ |
|---|---|
| ሱረቱል አል-ፋቲሃ 1 ፡ 4 مَٰلِكِ ማአሊክ ተብሎ ሲነበብ ትርጉሞ ባለቤት ማለት ሲሆን | ሱረቱል አል-ፋቲሃ 1 ፡ 3 مَلِكِ መሊክ ተብሎ ሲነበብ ትርጉሙ ደግሞ ንጉሥ ማለት ነው |
| ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 125 وَٱتَّخِذُوا ሲነበብ ወተሂዙ ሲሆን ትርጉሙ አድርጉ ነው | ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 124 وَٱتَّخَذُوا ሲነበብ ወተሂዙ ሲሆን ትርጉሙ አደረጉ ነው |
| ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 259 نُنشِزُهَا ሲነበብ ነንሽዙሃ ሲሆን እንደምናስነሳ ተብሎ ተተርጉሟል | ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 258 نُنشِرُهَا ሲነበብ ነንሽሩሃ ሲሆን ትርጉሙ እንደምንዘረጋ የሚል ነው |

በዚህ ከመዝጋቴ በፊት ግንዛቤያችሁን ሊያሰፋ የሚችል ነገር ልናገር፡፡ ከሃያ ዘጠኙ የጥንት ጽሑፉት መካከል ታዋቂ የሆነው የአብዱላህ ኢብን መስኡድ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህ ሰው የቁርአኑ አስተማሪ ተብለው በነቢዩ ከተመረጡ አራት ሰዎች መካከል አንዱና ፊተኛው ነው፡፡[23] ታዲያ የዚህ ሰው ቁርአን ከከሊፋ ኡስማንና አሁን ላይ ካሉት የቁርአን ቅጂዎች ጋር በንጽጽር ሲታይ በሱራዎች ብዛት፣ በምእራፎች አሰዳደር፣ በቃላት እና በመሳሰሉት ከፍተኛ ልዩነት እንደ ነበረው የታሪክ መዛግብቱ ይናገራሉ፡፡ እናም የከሊፋ ኡስማንን ቁርአን ፈጽሞ አይቀበልም ነበር፡፡ የታሪክ መዛግብቱ በሁለቱ ቅጅዎች መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ ሲናገሩ ለምሳሌ በሱረቱል አል-በቀራ ብቻ 101 ልዩነቶች እንደሚታይባቸው ይናገራሉ፡፡[24] እንግዲህ በአንድ ምእራፍ ውስጥ ይህንን ያክል ልዩነት የሚታይ ከሆነ በ114 ምእራፎች ውስጥ ምን ያክል ልዩነት ሊኖር

[23] *Bukhari, vol 6, No. 521*

[24] *Ahmad von Denffer, Ulum al Qur'an, page 83*

እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ፡፡ በሁለቱ ሰዎች ቅጅዎች ይህንን ያክል ልዩነት ከተገኘ በሃያ ዘጠኞቹ ደግሞ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቡት፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ ከሞቱ ከሃያ ዓመታት በኋላ፣ ከሊፋ ኡስማን ቁርአንን በተመለከተ በሶሪያ ሙስሊሞችና በኢራቅ ሙስሊሞች መካከል አደገኛ ልዩነት መከሰቱን በሰማበት ወቅት፣ ዛይድን ከመዲና፣ ሌሎች ሦስት የመካ ዝዬን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎችን ከመካ በመምረጥ፣ ቁርአን የወረደው በመካ የአረብኛ ዘዬ ስለሆነ፣ በቁሬይሾች የአረብኛ ዘዬ እንዲጻፍ አድርጓል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ደግሞ ቁርአን የወረደው በመካ ዝዬ ብቻ ሳይሆን በሰባቱ የአረብኛ ዝዬ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ማነው ውሸታሙ? አላህ? ገብርኤል? ነቢዩ ሙሐመድ? ወይስ ከሊፋ ኡስማን? ማነውስ ነቢይ? ነቢዩ ሙሐመድ ወይስ ኡስማን?
- ከሊፋ ኡስማን በሚፈልገው ዝዬ ካጻፈ በኋላ ሌሎቹን የቁርአን ቅጅዎች በእሳት እንዲጋዩ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ የቁርአኑን ቅጅዎች በእሳት የማቃጠሉ አላማ፣ በቅጅዎቹ መካከል ያለውን ችግር ለማስወገድና ለሁሉም አንድ ቅጅ ብቻ እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ ነበር፡፡ ሆኖም ከእርሱ ሞት በኋላ በእሳት እንዲቃጠሉ ያደረጋቸው ቅጅዎች ተመልሰው ሕይወት ዘርተው ይኸውና እኛ እጅ ደርሰዋል፤ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? በዚህ የአላህ ጥበቃ መገለጫው ምንድን ነው? ምናልባት እንደገና በሕይወት መገኘታቸው የአላህ ጥበቃን ያሳያል ሊባል ከቻለ ከከሊፋ ኡስማን ሊጠብቀው ለምን አቃተው?
- በዓለም ዙሪያ አገልግሎት በመስጠት ላይ ስላሉት የቁርአን ቅጅዎችና እነርሱን ስለጻፉ ሰዎች ብዙ ተብሎላቸዋል፡፡ በአንጻሩ በቁሬይሽኛ ዘዬ ስለተዘጋጀው የከሊፋ ኡስማን የቁርአን ቅጅ በእጅ የሚጨበጥ ታሪክ አልተገኘም፡፡ ቅጅውም በምድር ላይ የለም፤ ለምን? የከሊፋው የቁርአን ቅጅ የት ገባ? በዚህስ የአላህ ጥበቃ እንዴት ሊገለጽ ይችላል?
- ከሊፋ ኡስማን በእሳት ያጋየው ከነቢዩ ሙሐመድ አንደበት እያደመጡ ለምን እንደ ወረደ ምክንያቱን ሳይቀር የሚያውቁ ሰዎች የጻፏቸውን የቁርአን ቅጅዎችን ነው፤ በአንጻሩ አሁን ላይ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉትን የቁርአን ቅጅዎች ያስተማሩ ሰዎች እና ከእነርሱ ተምረው ቅጅዎቹን በመጽሐፍ መልክ ያዘጋጁት ሰዎች ነቢዩ ሙሐመድና ሱሃባዎቹን በአካል የሚያውቁ ከእነርሱም የተማሩ አይደሉም፡፡ የከሊፋ ኡስማን ቁርአን ለመረጃ ያህል በሌለበት፣ ከነቢዩ ሙሐመድ ያለተማሩ ሰዎች ያዘጋጁት ቁርአን እንዴት ትክክለኛና እንከን የለሽ ተብሎ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል? ለነቢዩ ሙሐመድ ከወረደው ቁርአን ጋር ምንም አይነት ልዩነት የሌላቸው፣ ፍጹም ተመሳሳይ ለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ ማቅረብ ይቻላል?
- በከሊፋ ኡስማን ትእዛዝ በቅጅዎቹ ላይ የተፈጸመው በእሳት የማቃጠል ክፉ ሥራ፣ የተፈራውን ስጋት ማስወገድ አልቻለም፤ ታዲያ ቁርአኑ የአላህ ቃል፣ የከሊፋ ኡስማንም አድራጎት የአላህ ፈቃድ፣ ነበረበት ብሎ

ለመናገር ያስደፍራል? ነቢዩ በሕይወት በነበሩበት ወቅት፣ ከሊፋውን ለዚህ ሥራ እንዲነሳሳ ያደረገው አይነት ችግር ተከስቶ ነበር፤ አላህና ነቢዩ ሙሃመድ በሰባት የአረብኛ ዘዬዎች እንዲነበብ በማድረግ መፍትሄ አበጅተውለት ነበር፡፡ እንግዲህ በዚህ ጉዳይ አላህ ነበረበት ተብሎ የሚታመን ከሆነ፣ ግጭቱ እንዴት ሊታረቅ ይችላል?

- በተሠራው ሥራ የአላህ ፈቃድ ከሌለበት ደግሞ፣ ቃሉን፣ የራሱን ተአምራት፣ ከሊፋ ኡስማን በድፍረት በእሳት ሲያቃጥል፣ አላህ ለቁርአኑ ጠባቂው ከሆነ ይህ ክፉ ሥራ ሲሠራ እንዴት ዝም ሊለው ቻለ?
- በዚህ የቁርአን የጉዞ ሒደት ውስጥ እየታየ ያለው፣ አንዱ ጉልበተኛ ሲመጣ የፈለገውንና የመሰለውን ሰርቶበት ሲያልፍ የሚከተለው ደግሞ የራሱን ድርሻ የተወጣበት እንደነበር ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው? በዚህ ሁሉ አላህ ምን ያደርግ ነበር?
- በእነዚህ የቁርአን ቅጅዎች የሚታየው ልዩነት፣ ቁርአን ልክ በሌለው መበረዝ፣ መሰረዝ፣ መደለዝ እና በሰዎች ጣልቃ ገብነት ውስጥ እየኖረ እዚህ ዘመን ላይ የደረሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ታዲያ የሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9 የአላህ የጥበቃ ቃል ኪዳን ያልተፈጸመና ቁርአን ከአላህ ጥበቃ ውጭ የኖረ መሆኑን በግልጽ አያሳይም ትላላችሁ?
- ቁርአንን ከመበረዝ፣ ከመሰረዝ፣ ከመደለዝ፣ ብሎም ከመጥፋት ጠባቂው አላህ ነው፤ ተብሎ እያለ፣ ከጥበቃው ውጭ የኖረ ከሆነ፣ ቁርአን የአላህ ቃል፣ ነቢዩም የአላህ መልእክተኛ ናቸው፤ ማለት ይቻላል? ይህስ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ አላህ መጽሐፍ ቅዱስን የመጠበቁን ኃላፊነት የሰጠው ለሰዎች ነው፣ የሚለውን ንግግራቸውን ዋጋቢስ አያደርገውም ትላላችሁ? እንደሚጠብቀው ቃል ገባለት የተባለው፣ እንደተባለው ካልተጠበቀና ቃላቸው እውነት ካልሆነ፣ ሌላው ንግግራቸው እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል? ይህንን የመሰለ ታሪክ ያለው መጽሐፍ ይዞ፣ ምንም ስለማያውቁት መጽሐፍ ቅዱስ መበረዝ አለመበረዝ ማውራትስ ይቻላል?

## 1.1.3. ቁርአን ሙሉ ያልሆነ (INCOMPLETE) መሆኑ

በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን ስለ ቁርአን አኗኗር ሐዲሳቱ የተዘበራረቁ አሳቦችን ዘግበው እናገኛለን፡፡ ሆኖም ገዥ የሆነው አሳብ "በመጽሐፍ መልክ ባለመደራጀቱ በተበታተነ መልኩ ይኖር ነበር" የሚለው ነው፡፡ ከነቢዩ ሞት በኋላ የሃይማኖቱን አመራር ከሊፋ አቡበከር ሰዲቅ ተረከቧል፡፡ ከያማማ ጦርነት በኋላ ኡመር ኢብን አል-ኸታብ የቁርአኑ ህልውና አሰጋው፤ ተረት እንዳይሆን ፈራ፡፡ እናም የተበታተነውን ቁርአን በማሰባሰብ በመጽሐፍ መልክ የማዘጋጀት ሥራ እንዲጀመር ለአቡበከር አሳብ አቀረበ፡፡ ለዚህ የሰጠው ምክንያት "ከእስልምና መስፋፋት ጋር በተያያዘ በሚደረጉ ጦርነቶች ቁርአንን በቃላቸው የሚያወቁ

ሰዎች እየሞቱ ስለሆነ ቁርአኑ ከነአካቴው ሊጠፋ ነው" ሚል ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ከሞቱ በኋላ በነቢዩ ጦር በግድ እስልምናን ተቀብሎ የነበረው አብዛኛው የአረቢያ ሕዝብ እስልምናን በመተው ወደ ቀደመው ሕይወቱ ተመልሶ ነበር፡፡ ይህንን ወገን ከሊፋ አቡበከር ጦር ሰብቆ ያማማ በተባለው ቦታ ላይ ጦርነት ገጥሞ ነበር፡፡ እናም በዚያ ጦርነት ቁርአኑን በቃላቸው ያውቁ የነበሩ ወይም ሃፊዘል ቁርአን የሆኑ ቁጥራቸው ከ450-700 የሚደርስ የነቢዩ ተከታዮች ተገድለዋል፤ ያውቁት የነበረውን ቁርአን ይዘውት ተቀብረዋል፡፡ ይህ ነበር ስለ ቁርአኑ ህልውና ለኡመር የስጋት ምንጭ የሆነበት፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው የመስፋፋት ጦርነት ደግሞ፣ ከሞት የተረፉት ሃፊዘሎች እንዳይሞቱና ከነአካቴው ቁርአኑ እንዳይጠፋ፣ የማሰባሰብ ሥራው ቶሎ ብሎ እንዲጀመር ማሳሰቢያውን ለወቅቱ ከሊፋ አቅርቧል፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4679**

> አቡበከር ሲናገር፣… ኡመር መጥቶ እዲህ አለኝ፤ ሕዝቡ ያማማ ላይ በተደረገው ጦርነት በደረሰው ከፍተኛ ጉዳት (ሃፊዘል ቁርአኑን የሆኑ 450 ሰዎች ሞት) ስቃይ ደርሶበታል፡፡ ስለዚህ ካላሰባሰብከው በስተቀር በሌሎች ወደፊት በሚኖሩ ውጊያዎች ቀሪዎቹ በቃላቸው ቁርአኑን የሚያውቁ ይሞቱና አብዛኛው ቁርአን ይጠፋል ብዬ እፈራለሁ፡፡ ስለዚህ ብታሰባስበው የሚል አሳብ አለኝ፤ አለኝ፡፡ አቡበከር ጨመረም፣ ለኡመር፡- እንዴት የአላህ መልእክተኛ ያልሰሩትን ሥራ እኔ እሰራለሁ? አልኩት…[25]

ከብዙ ውትወታ በኋላ በቀረበው አሳብ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ በስምምነቱ መሠረት ቁርአንን ከተበታተነበት የማሰባሰብ ሥራው ቢጀመርም፣ አብዛኛው የቁርአን ክፍል ጠፍቶ ስለነበር በነቢዩ ዘመን የወረደውን ሁሉንም የቁርአኑን ክፍሎች ማግኘት ግን አልቻሉም፡፡ የቁርአን በርካታ ክፍሎች ስለመጥፋታቸውና ማሰባሰብ የተቻለው በጣም ጥቂቱን ብቻ መሆኑን ታማኝ የሆኑት ሃዲሳትና የተለያዩ የቁርአን ሙፈሲሮች ሱሃባዎችንና ከሊፋዎችን ምንጭ አድርገው እማኝነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የእማኝነታቸውን ቃል ከራሱ ከከሊፋ ኡመር ልጅ ከአብዱላህ ኢብን ኡመር ልጀምር፡-

> ኪታብ ፋዛኢል አል-ቁርአን ቅጽ 2፣ ገጽ 135
>
> አብዱላህ ኢብን ኡመር ሲናገር፡- ከእናንተ መካከል ሙሉውን ቁርአን እንዳገኘ የሚናገር የቁርአኑ አጠቃላይ ይዘት ምን ያህል እንደነበር

---

[25] *Al-Bukhari, Muhammed ibn Ismaiel, Sahih Al-Bukhari\ translated by Muhammad Muhsin Khan, Darussalam Publishers and Distributors, Riyadh - Saudi ArabiaRiyadh, 199, vol 6 page 156*

እውቀት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛው ቁርአን ጠፍቷል፤ ይልቁን የቀረውን ወይንም ያለውን አግኝቸዋለሁ ቢል ይሻላል፡፡[26]

አቡ ጃፍር እንዲህ ሲናገር ሰምቻልሁ፡- "ከአሊ ኢብን አቢ ታሊብና በኋላም ከኢማሞቹ በስተቀር ውሸታም ካልሆነ በስተቀር ከአላህ ዘንድ እንደ ወረደ ሙሉውን ቁርአን እንዳሰባሰበ ሊናገር የሚችል አንድም ሰው የለም፡፡"[27]

እንደ ኢብን ነዲም ዘገባ የአሊ ኢብን አቢ ታሊብ ቁርአን በከሊፋ ኡስማን ተቃጥሏል፤ በአሁኑ ቁርአን ውስጥ ያሉ አምስት ሱራዎች አልነበሩትም፣ ሌላም ሌላም፡፡ በሌላ ተያያዥ ሐዲስ ከሊፋ ኡመርም እንዲህ ተናግሯል፡-

**አል-ኢትቃን፣ ፊ ኡሉም አል-ቁርአን ቅጽ 1፣ ገጽ 88**

ኡመር ሲናግር ነቢዩ እንዲህ አሉ፤- ቁርአን 1,027,000 ፊደላትን የያዘ ነው፡፡ ማንም ብድራትን አስቦ የሚያነባቸው ሰው በገነት በእያንዳንዱ ፊደሎቹ ልክ የገነት ሴቶችን ያገኛል፡፡ …[28]

**አል-ኩላይኒ አል-ካፊ ቅጽ 2፣ 14 ፡ 28**

አቡ አብደላ /አል-ሳዲቅ/ ሲናገር፡- ገብርኤል ወደ ነቢዩ ሙሐመድ ያመጣው ቁርአን 17,000 አንቀጾች ነበሩት፡፡[29]

እነዚህ ሐዲሳት በሁለቱ ታላላቅ የእስልምና ክፍሎች፣ ማለትም በሱኒ እና በሺአ ኢማሞች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ የሺአ ኢማሞች ነቢዩ ሙሐመድ ከሞቱ ከስድስት ወራት በኋላ፣ በከሊፋ አሊ የተጻፈው የቁርአን ቅጅ ይህንን ያክል ፊደላት ይዞ እንደ ነበር ይናገራሉ፡፡ ከሊፋ ኡመር እንደተናገረው በመጀመሪያ ነቢዩ ሙሐመድ ከገብርኤል ተምረው ያስተላለፉትና ተበታትኖ ተቀምጦ የነበረው ቁርአን 1,027,000 ፊደላት ይዟል፤ ይህም በ17,000 አንቀጾች የታቀፈ ነበር፡፡ አሁን በዚህ ጊዜ የሚገኘው ቁርአን ደግሞ ከ267,033[30] ፊደላት ያልበለጠ እንደሆነ፤ ይህም በ6,666 አንቀጾች እንደ ታቀፈ የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ አንዳንዶች ይህንን 6,666 የሚለውን አሃዝና የፊደላቱን ቁጥር ጭምር አይቀበሉም፡፡ የማይቀበሉት ወገኖች የአንቀጾቹን ቁጥር በ6,000 እና በ6,348

---

[26] *http://www.shiapen.com/comprehensive/tahreef/sunni-reports-deletions-quran.html*

[27] *A Shi'ite Encyclopedia,Version 2.0 October 1995 Revised January 2001*

[28] *http://www.shiapen.com/comprehensive/tahreef/sunni-reports-deletions-quran.html*

[29] *Sheykh Muhammad Bin Yaqoub Al-Kulayni, Kitabe Al Kafi V 2, CH 14 H 28*

[30] *Sayyid Saeed Akhtar Rizvi, WAHHABIS' FITNAH EXPOSED, Bilal Muslim Mission of Tanzania, Tanzania 1997, page 43-44*

መካከል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ልዩነቱ በመቶኛ ሲገለጽ በፊደል 74% ማለትም የቁርአኑ 3/4ኛ በአንቀጽ ደግሞ ከ60.8% እስከ 62.66% ማለትም 2/3ኛ ያህሉ የቁርአን ክፍል ጠፍቷል፡፡

በቁርአን ቃላትና ፊደላት ብዛት ዙሪያ ያለውን የተመሰቃቀለና የተዘበራረቀ የኡለማዎች አመለካከት ሙፈሲር ኢማም ኢብን ካሲር በተፍሲር መጽሐፋቸው አስፍረውልን ይገኛል፡-

> ተፍሲር ፍሲር ኢብን ካሲር ቅጽ 1 ገጽ 35-36
>
> ቅዱስ ቁርአን ያቀፋቸው አያቶች ቁጥር 6,000 ያህል ነው፡፡ ሆኖም በቁጥሮቹ ዙሪያ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ቁጥሩ 6,000 ነው ሲሉ፣ ሌሎች 204 አያት ይጨምራሉ፡፡ ከነዚያ ሌላ ያሉ 214 አያት ይጨምሩበታል፡፡ በተጨማሪ ሌሎች 219 አያት ይጨምራሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ 225 አያት ወይም 226 አያት ይጨምራሉ፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ያሉት ደግሞ 336 አያት ይጨምራሉ፡፡ አል-ብያን በሚል ርእስ አቡ አምር አድ-ዳኒ ከጻፉት መጽሐፍ የወሰዱት [31]

እንደ ሙፈሲር ኢማም ኢብን ካሲር ዘገባ በቁርአን ፊደላት ቁጥር ብዛት ያለው የአመለካከት ልዩነት ከዚህ የተለየ አይደለም፡-

> ተፍሲር ኢብን ካሲር ቅጽ 1 ገጽ 36
>
> ስለ ቅዱስ ቁርአን ቃላትና ፊደላት ብዛት አል-ፋድል ቢን ሻዛን ሲናገር፣ አታ ቢን ያሳር እንዳለው፣ ቁርአን 77,439 ቃላትን ይዟል አለ፡፡ አብደላህ ቢን ካቲር ሲናገር፣ ሙጃህዲን እንዳለ፣ በእኛ አቆጣጠር የቁርአኑ ፊደላት ቁጥር ብዛት 321,180 ያህል ነው ብሏል፡፡ በተጨማሪ አል-ፋድል ሲናገር፣ አላ ቢን ያሳር እንዳለው፣ ቁርአን 323,015 ፊደላትን የያዘ ነው ብሏል፡፡ ሳልም አቡ ሙሐመድ አል-ሃማኒ ጨምሮ አል-ሃጃጅ የቁርአኑን ሀፊዘሎች ሰብስቦ ቁርአን ስንት ፊደሎችን በውስጡ እንዳቀፈ ንገሩኝ አላቸው፡፡ እነርሱም እኛ የቆጠርነው 340,740 ፊደሎችን ነው አሉት፡፡[32]

አሁን ላይ 267,033 ፊደላት ካለው ቁርአን ጋር በንጽጽር ሲታይ፣ ከእነዚህ ሰዎች አቆጣጠር ጋር ከፍተኛ ልዩነትና የቁርአን ቃላት መጥፋት ይታይበታል፡-

- በሙጃህዲንና ከእርሱ ጋር ባሉት ሰዎች አቆጣጠር ከቁርአኑ ላይ እስከ 54,1147 የሚያክል ፊደላት ጠፍተዋል፡፡

---

[31] *Imam Abu Al-Fida Ismail Ibn Kathir, Tafsir Ibn Kathir, maktaba Dar-us-salam, Lebabon 2003, vol 1, page*

[32] *Ibid page 36*

- በአላ ቢን ያሳር አቆጣጠር 55,982 የሚያክሉ ፊደላት ከዚህ ቁርአን ሳይካተቱ ጠፍተዋል ማለት ነው፡፡
- አል-ሃጃጅ አሰባስቦ የቁርአኑን ቁጥር እንዲነግሩት በጠየቃቸው ሃፊዘሎች አቆጣጠር ደግሞ 73,707 ያክል የሚሆኑ ፊደላት በዚህ ቁርአን ሳይካተቱ ለጥፋት ተዳርገዋል፡፡

የቁርአኑ አንቀጾች ስለ መጥፋታቸው ከሊፋ ኡመር ብቻ ሳይሆን፣ የነቢዩ ሙሐመድ የተወደደች ሚስታቸው አይሻም የሚከተለውን ብላለች፡-

ሱናኢብኑ ማጃህ ቅጽ 3፣ ቁጥር 1944

የራጂም (አመንዝራን በድንጋይ በመውገር መግደል) እና ለአቅመ አዳም የደረሰን ሰው አስር ጊዜ ስለ ማጥባት በወረደ ጊዜ ተጽፎ የነበረው በፓፓይረስ (ቅጠል) ላይ ነበር፡፡ ከትራሴ በታች አስቀመጥኩት፣ ነቢዩ በሞቱበት ወቅት፣ በእርሳቸው ሞት ተጨናንቀን ነበር፣ ያኔ ፍየል ገባች እና ፍየል የፓፒረስ ቅጠሉን በላችው፡፡ አይሻ የተናገረችው፤[33]

ስለ ሱረቱል አል-አህዛብ አሁንም ከሊፋ ኡመር እንዲህ ብሏል፡-

ሙህታዛር ካንዝ አል-ኡማል ቅጽ 2 ገጽ 2፣ ሱና ማሊክ ሙዋታ 41 ፡ 8

ሁዘይፋህ ሲናገር፡- ኡመር በሱረቱል አል-አሕዛብ ውስጥ ስንት አንቀጾች ይገኛሉ? ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ሰባ ሁለት ወይም ሰባ ሶስት አንቀጾች አልኩት፡፡ እርሱም ሱረቱል አል-አሕዛብ እንደ ሱረቱል አል-በቀራ 287 አንቀጾችን እንደያዘው እረጅም ነበር፤ በዛም ውስጥ አመንዝራን በድንጋይ በመውገር መቅጣትን የሚገልጸው አንቀጽ ነበር አለ፡፡ ኢብን ማርዳውያህ የዘገበው፤[34]

ስለ ሱረቱል አል-አሕዛብ አሁንም አይሻ እንዲህ ብላለች፡-

ሱረቱል አል-አሕዛብ በነቢዩ ዘመን ሲቀራ 200 አንቀጾች ነበሩት፣ ነገር ግን ኡስማን ቁርአኑን ሲጽፍ፣ አሁን በዚህ ጊዜ ካለው በላይ የሆኑትን ሊያገኝ አልቻለም፡፡ አቡ ኡቤይድ፣ ኢብን አንባሪና፣ ኢብን ማርዳውያህ ከአይሻ የሰሙት (አስ-ሱዩቲ አል-ኢቲቃን ቅጽ 2 ገጽ 25፣ ተፍሲር ዱር አል-መንሱር ቅጽ 5 ገጽ 180)[35]

---

[33] *Imiim Muhammad Bin Yazeed Ibn Majah Al-Qazwini, Sunan ibn majah, translated by Nasiruddin al-Khattab, Maktaba Dar-us-Salam, Ryadh 2007, vol 3 page 113-114*

[34] *Sayyid Saeed Akhtar Rizvi, WAHHABIS' FITNAH EXPOSED, Bilal Muslim Mission of Tanzania, Tanzania 1997, page 44-45*

[35] *Ibid page 44*

በአሁኑ ቁርአን ውስጥ ያለው ሱረቱል አል-አሕዛብ የያዛቸው አንቀጾች ብዛት 72 ብቻ ነው፡፡ በዚህም ከሱረቱል አል-አሕዛብ 215 ያህል አንቀጾች መጥፋታቸውን እንገነዘባለን፡፡ በከሊፋ ኡስማን ትእዛዝ ቁርአን ለሁለተኛ ጊዜ ይሰባሰብ በነበረበት ወቅት ሱረቱል አል-አሕዛብ የመጥፋት አደጋ ገጥሞት እንደ ነበር፣ አይሻ ብቻ ሳትሆን፣ በማሰባሰብ ሥራው ለሁለተኛ ጊዜ የተሳተፈው ዛይድ ቢን ሳቢትም የተናገረውን ኢማም ቡኻሪ[36] ዘግበውታል፡፡

ሱረቱል አል-ተውባህም 3/4ኛ ክፍሉ የጠፋበት መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡-

> ሁዛይፋ አል-ያማኒ እንዲህ አለ፡- "ያ ሱራ-አል-ታውባህ ብላችሁ የምትጠሩት የቁጣ ምእራፍ ነው፡፡ በአላህ! ሳያዋርደው ማንንም አይተውም፤ እናም የምታነቡት እኛ እናነብ ከነበረው አንድ አራተኛውን ብቻ ነው፡፡" አድ-ዱር አል-ማንሱር ቅጽ 3፣ ገጽ 208፤ አል-ኢትቃን ቅጽ 2፣ ገጽ 34[37]

> ማሊክ እንዲህ አለ፡- "... ሱራት ባራአት (ሱራ አል-ተውባህ) በርዝመቱ ሱራት አል-በቀራህን ያክል ነበር ወይም የተቀራረበ ነበር፡፡ እናም የተወሰነው ክፍል ጠፍቷል፤ ከዚህም የተነሳ ቢስሚላህ በጠፋውና በቀሪው በመካከል አልተጻፈም፡፡" (ተፍሲር አል-ቁርጡቢ ሱረቱል አል-ተውባህ ቅጽ 8፣ ገጽ 62)[38]

ቁርአን ለትውልድ ያለምንም እንከን መተላለፍ ያለመቻሉን ጉዳይ ሐዲሳቱ በዚህ ብቻ አላበቁም፡፡ አቡ ሙሳ ለጉብኝት ወደ ባስራ በተላከበት ወቅት፣ በባስራ ከነበሩ ቁጥራቸው ሦስት መቶ ከሚደርሱ ሃፊዘሎች ጋር ሲነጋገር በነበረበት ወቅት የቁርአኑ አካል የሆኑ ሁለት ሱራዎች እንደጠፉና የሚያስታውሰው ከአንዱ ሁለት አንቀጾችን ብቻ እንደሆነ፣ የአንዱ ሱራ አንቀጾች ብዛት ከሱረቱል አል-ተውባህ አንቀጾች ብዛት ጋር እኩልና ተመሳሳይ እንደነበር ተናግሯል፡-

> ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 3፣ ቁጥር 2419

> የነቢዩ ሙሐመድ ተከታይ የሆነው አቡ ሙሳ አሻሪ እንደዘገበው፤ በአንቀጾቹ ብዛት በቅደም ተከተሉ ከአል-ተውባህ ጋር የሚመሳሰል ሱራ እንቀራ ነበር፡፡ ነገር ግን እረስቸዋለሁ፤ አሁን ከእርሱ የማስታውሰው ይህንን አንቀጽ ብቻ ነው፤ "የአደም ልጆች ሁለት በረከት የተሞሉ ሸለቆዎች አሉት፣ አሁንም ሦስተኛ ይመኛል፤ የሰውን ጨጓራ የሚሞላ ከአሸዋ በስተቀር ምንንም የለም፡፡" ሌላው እንቀራው የነበረው ሱራ ደግሞ፣

---

[36] *Sahih Al-Bukhari vol 6, #4784 page 265*

[37] *WAHHABIS' FITNAH EXPOSED, page 45*

[38] *http://www.shiapen.com/comprehensive/tahreef/sunni-reports-deletions-quran.html*

> ከሙሳቢሃት ሱራዎች አንደ አንዱ የሚሆን አንቀጾች ያለውና የሚመሳሰል ነው፡፡ ነገር ግን እረስቸዋለሁ፤ ከዚያ አሁን የማስታውሰው ይህንን አንቀጽ ብቻ ነው፤ "እናንተ ያመናችሁ ሆይ፤ የማትሰሩትን ነገር ለምን ትናገራላችሁ? (አል-ሶፋ (የሰልፍ ምዕራፍ) 61 ፡ 2)፣ ሰውን ሁሉ በራሪውን ስራውን በአንገቱ አስያዝነው፤ ለእርሱም በትንሳኤ ቀን የተዘረጋ ሆኖ የሚገኘው የሆነን መጽሐፍ እናወጣታለን፡፡ (አል-ኢስራ (የሌሊት ጉዞ ምዕራፍ) 17 ፡ 13)[39]

"የአደም ልጆች ሁለት በረከት......" የሚለውን አንቀጽ የያዘው ሱራ የቁርአን ውስጥ አልተካተተም፡፡ ተመሣሣይ እንኳን አልተገኘለትም፤ ጠፍቷል ያለው በሐዲሱ ውስጥ ታሪኩ ብቻ ነው፡፡ ይህንን የጠፋ የቁርአን ክፍል ኢብን መሱድና ኡቤይ ቢን ካብ[40] በራሳቸው የቁርአን ቅጅ ውስጥ አካተውት እንደነበር ይነገራል፡፡ ከመጥፋት የተረፉት የሌላኛው ሱራ ሁለት አንቀጾች ተበታትነው አንዱ "እላንት ያመናችሁ ሆይ፤ የማትሰሩትን ነገር ለምን ትናገራላችሁ?(الَّذِينَ يأَيُّهَا) ءَامَنُواْ لِمَ تَقُولُونَ لاَ مَا تَفْعَلُونَ የሚለው <u>**በአል-ሶፍ 61 ፡ 2**</u> ላይ ሰፍሮ ሲገኝ ሌላው ደግሞ "ሰውን ሁሉ በራሪ ስራውን በአንገቱ አስያዝነው፣ ለርሱም በትንሳኤ ቀን የተዘረጋ ሆኖ የሚገኘው የሆነን መጽሐፍ እናወጣለን፡፡"وَكُلَّ إِنْسَنٍ أَلْزَمْنَـهُ طَـئِرَهُ فِى عُنُقِهِ وَنُخْرِجُ لَهُ يَوْمَ الْقِيَـمَةِ كِتَابًا يَلْقَـهُ مَنْشُوراً የሚለው <u>**በአል-ኢስራ 17 ፡ 13**</u> ያለ ክፍላቸውና ያለ አላህ ፈቃድ ቁርአኑ ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ይህ ሲጠቃለል ከዚህ አቡ ሙሳ ጠፋ ካለውና ከከሊፋ ኡመር ከሱረቱል አል-አሕዛብ ጠፋ ካለው ቁጥር ጋር <u>**ከ345 አንቀጾች**</u> በላይ የሆኑና ሁለትና ከዛም በላይ ሱራዎች አሁን ባለው ቁርአን ውስጥ ሳይካከቱ የጠፉ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ከሊፋ ኡመር በመጀመሪያው ቁርአንን የማሰባሰብ ሥራ ላይ ስለነበረው ሁኔታ በተናገረበት ወቅት ያኔም ቢሆን ቁርአን ሙሉ እንዳልነበር እንድናስተውል አድርጓል፡፡

> ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4481
>
> ኡመር ሲናገር፣ ኡቤይ በቁርአን እውቀቱ ከሁላችን የተሻለ ነው፡፡ ሆኖም ከሚቀራቸው የቁርአን ክፍሎች የተወሰኑትን ትተናቸዋል፡፡ ኡቤይ እኔ ይህንን ከነቢዩ አፍ የወሰድኩት ስለሆነ አንድንም ነገር አልተውም አለ፡፡ ነገር ግን አላህ ይህንን ብሏል፡- “ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ፣ ከርሷም የሚበልጥን ወይም ብጤዋን

---

[39] *Sahih Muslim, vol 3 page 93*

[40] *http://www.shiapen.com/comprehensive/tahreef/sunni-reports-deletions-quran.html*

እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ (ቻይ) መሆኑን አታውቅምን?” (አል-በቀራህ 2 ፡ 106)[41]

ኡቤይ ቢን ካብ፤ በቁርአን እውቀቱ ከሌሎች ሦስት ሰዎች ጋር በነቢዩ ሙሐመድ ለአስተማሪነት የተመረጠና ከዛይድ ቢን ሳቢት ጋር ለነቢዩ ይወርድ የነበረውን ወህይ(ራዕይ) ጸሐፊ የነበረ ሰው ነው፡፡ ታዲያ ከሊፋ ኡመር ሌሎች ሰዎች ስለ ቁርአን ሚሰጡትን ምስክርነት ተቀብሎ የዚህን ሰው ቁርአናዊ መረጃዎች አለመቀበሉ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አስቡት፡፡ በዚህ ወቅት ከዛይድ ጋር በመሆን መስጊድ በር ላይ ቁርአኑን ሲያሰባስቡ ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106ን ምክንያት በማድረግ ቁጥራቸው በውል ማይታወቅ ብዛት ያላቸው የቁርአን አንቀጾች ከቁርአን አካልነታቸው ተወግደዋል፡፡ ለዚህ እራሱ ከሊፋ ኡመር በአንደበቱ "ቁርአን 17,000 አንቀጾች አሉት" በማለት ያስተላለፈው ሐዲስ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን በዚህ ዘመን ባለው ቁርአን ያሉት የቁርአን አንቀጾች 6,666 ወይም ከዚህ በታች ናቸው፡፡ ኢብን ካቲር የዘገቡት የተዘበራረቀው የቁርአን ፊደላትና ቃላት ቁጥር ሳይረሳ ማለት ነው፡፡

ከሊፋ ኡመር **ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106ን** በመጥቀስ የሰጠው ምክንያት ከኡቤይ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከሁለተኛው የቁርአን አሰባሳቢ ከከሊፋ ኡስማን ጭምር ይጋጫል፡፡ ከሊፋ ኡስማን በሻሪና ተሻሪ አንቀጾች ላይ የነበረው አመለካከት እንደ ከሊፋ ኡመር አልነበረም፡ ያንንም በአል-ቡኻሪ እንዲህ ሰፍሮ ይገኛል፡-

> **ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4530**
>
> አል-በቀራ 2 ፡ 240ን በተመለከተ ኡስማን ቁርአኑን በሚያሰባስብበት ወቅት እንዲህ አልኩት፣ ይህ አንቀጽ በሌላ አንቀጽ ተሽሯል፤ ታዲያ የቁርአኑ አካል አድርገህ ለምን ትጽፈዋለህ? ኡስማንም የወንድሜ ልጅ ሆይ እኔ አንድንም ነገር ከቀድሞ ቦታው አልቀያይርም አለኝ፡፡ ኢብን አዝ-ዙቤይር እንደተናገረው[42]

ተመልከቱ **ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 240** የተሻረው በአንቀጽ **ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 234** ሲሆን፣ አንዱ ሻሪ ሌላው ተሻሪ፣ ሁሉም በቁርአኑ ውስጥ አሉ፡፡ በሁሉም የቁርአን ሱራዎች ውስጥ ማለት ይቻላል ሻሪና ተሻሪ አንቀጾች በአንድነት ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በሻሪና ተሻሪነት ምክንያት አንቀጾች ወጥተው ተጥለዋል፣ የአመለካከት ልዩነትንም ፈጥሯል፡፡ ታዲያ ይህ በከሊፋ ኡመር፣ በኡቤይ ቢን ካብና በከሊፋ ኡስማን መካከል የሚታየው የአመለካከት ልዩነት በቁርአን ንጽህና ላይ ሌላ ጥያቄ በውስጣችን ይፈጥራል፡፡ እንደ **አል-**

---

[41] *Sahih Al Bukhari, vol 6 page 28*
[42] *Sahih Al Bukhari, vol 6 page 53*

ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4987[43] ከሊፋ ኡስማን ቁርአኑን ያዘጋጀው፣ በከሊፋ አቡበከር ዘመን ከሊፋ ኡመርና ዛይድ ቢን ሳቢት ካሰባሰቡት የቁርአን ቅጅ ነው፡፡ እነዚህ ሃይማኖቱን የመሩና ያስተማሩ፣ የነቢዩ የቅርብ ሰዎች፣ እንዲህ ባለ ልዩነት የነበሩ ከሆነ፣ ከላይ በተጠቀሰው ሐዲስ የተላለፈው የቁርአን አሰባሰብ ዜና ውድቅ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በከሊፋ ኡመርና በዛይድ የመጀመሪያው የማሰባሰብ ሥራ ወቅት፣ ተሻሪ የሆኑት አንቀጾች እየተለዩ ከቁርአኑ ጥራዝ ውስጥ ተወግደዋል፤ ስለዚህ ሁለተኛው ላይ በምንም አይነት ሁኔታ ሻሪና ተሻሪ አንቀጾች በአንድነት መገኘት አይኖርበትም፡፡ ሻሪውና ተሻሪው አንቀጾች መገኘት ካለባቸው ደግሞ፣ ኡቤይ ቢን ካብ ያመጣቸው የቁርአን አንቀጾች ጥቅስ ተጠቅሶ ውድቅ መደረግ አልነበረባቸውም፡፡ ነገር ግን የሆነው ከሊፋ ኡመር አል-በቀራን ጠቅሶ ይጥላል፤ ከሊፋ ኡስማን ደግሞ የተጣለውን አንስቶ የቁርአኑ አካል በማድረግ አካቶት ይገኛል፡፡ ስለዚህ የቁርአን አሰባሰብ የአላህ ፈቃድና የነቢዩ አስተምህሮ ዋጋ ያጡበት፣ የሰዎች አሳብና ፈቃድ የነገሰበት፣ እንዳሹ ሲሄድ፣ የሚመጣው የራሱን አመለካከት እያስፈጸመበት የኖረ መጽሐፍ ነበር፡፡ ይህም በቁርአን ተአማኒነት ላይ የወደቀ ጥቁር ነጥብ ነው፡፡ በሱሃባዎቹ መካከል በአሳብ መለያየቱ፣ በእነዚህ ሰዎች ብቻ የሚያበቃ አልነበረም፤ የሚለያዩበት አሳብም ቁጥሩ እጅግ በርካታ ነው፡፡ በዚህ ላይ ግንዛቤያችሁን ያሰፋ ዘንድ በሁለቱም ቁርአንን የማሰባሰብ ሥራ ወቅት ዋና ሰራተኛ ስለነበረው ዛይድ ቢን ሳቢት አንዳንድ ጥያቄዎችን ላንሳ፡-

- ❖ በሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106 መሰረት ኡቤይ ያመጣቸው የቁርአን አንቀጾች ውድቅ ከተደረጉ፣ ሌሎቹ ሱሃባዎች ያመጧቸውም ይህ እጣ እንደሚገጥማቸው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በእነርሱም ላይ ተግባራዊ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ታዲያ አሁን ባለው ቁርአን ውስጥ ያሉት ሻሪና ተሸሪ የሆኑ አንቀጾች የቁርአኑ አካል ተደርገው መካተታቸው የሱሃባዎቹን አንድ ልብ፣ ለአንድ መለኮታዊ አላማ ይሠሩ የነበሩ መሆናቸውን ያሳያል? ይህስ ቁርአን እዚህ ዘመን ላይ ላለው ትውልድ ያለምንም ጉድለት ደርሷል ብሎ በድፍረት ለመናገር ያስችላል?
- ❖ ሁሉም ቅጅዎች ተመሳሳይ ናቸው ከተባለ፣ ከሊፋ ኡመር ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106ን የጠቀሰው ኡቤይን ለመቃወም በማሰብ ብቻ ነበር? ለምን? ኡመር የራሱን ሰዋዊ ስሜት ለማስፈጸም የአላህን ቃል ከተጠቀመ ቁርአን ያለምንም ችግር እዚህ ዘመን ላይ ደረሰ ማለት አይቻልም፡፡ ታዲያ አሁን ቁርአን ውስጥ ያሉት ሻሪና ተሻሪ አንቀጾች በሙሉ ድሮም ቢሆን ቁርአኑ ውስጥ ተካተው ነበር ማለት ነው? ወይስ ከሊፋ ኡመር ሻሪና ተሻሪ አንቀጾች ላይ የነበረው አመለካከቱ ተጥሶ በኋላ በሁለተኛው የማሰባሰብ ሥራ ወቅት የተካተቱ ናቸው? አዎን ከሆነ መልሱ፤ የከሊፋ ኡመር አመለካከት የተጣሰው በየትኛው የቁርአን ጥቅስ

[43] *Ibid vol 6 page 425*

መሠረት ነው? ወይስ በሕይወት ስላልነበር ለምን ብሎ የሚጠይቅ ሰው ስለሌለ ይሆን?

- ❖ በመጀመሪያው ቁርአንን የማሰባሰብ ሥራ ስለ ብቃቱ የመሰከረለት ሰው ያመጣቸውን የቁርአኑን አንቀጾች ጥቅስ ጠቅሶ ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡ በአንጻሩ ስመጥር ያልሆኑት ሰዎች ያመጡትን ተቀብሎ ቁርአኑን አዘጋጅቷል፡፡ ሥራው ሙሉ የሰው ፈቃድ ጣልቃ ገብነት ይታይበታል፡፡ እንግዲህ የማሰባሰቡ ሒደት እንዲህ ከነበር ቁርአን ምን ያህል ከመጥፋት፣ ከመበረዝ፣ ከመደለዝ ጽድት ያለ አስተማማኝ የአላህ ቃል ነው ብሎ መቀበል ይቻላል?
- ❖ የተጨበጠ አስተማማኝ መረጃ ሳይኖር፣ በጭፍን ሁሉም የቁርአን ቅጅዎች ተመሳሳይ ናቸው፣ እንደሚባል ይታወቃል፡፡ ያኔ ዛይድ ከከሊፋ ኡመር ጋር ከመስጊድ በር ላይ ተቀምጦ ቁርአኑን በሁለት ምስክሮች እያራጋገጠ ሲያሰባስብ ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106ን መሠረት በማድረግ የጣሉትን ተሻሪ አንቀጽ በኡስማን ትዕዛዝ በተዘጋጀው ቅጅ ውስጥ እንደገና ሲያሰፍረው ምን ማለቱ ነበር? ይህስ የከሊፋ ኡስማን ቁርአን የተዘጋጀው በከሊፋ አቡበከር ከተዘጋጀው ነው፣ የሚለውን የሐዲስ ዘገባ የሚቃረን አይሆንም?
- ❖ ከዚህ ቁርአንን የማሰባሰብ ታሪክ የሚታየው፣ ሥራው በዘፈቀደ ይከናወን የነበርና የከሊፋዎችም ሥልጣን ወሰን ያልነበረው፣ የፈለጉት የሚደረግላቸው ሰዎች እንደ ነበሩ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ምስቅልቅሎሽ ውስጥ የኖረው ቁርአን እንዴት ታማኝ ሊባል፣ ሰውም የሕይወቱ መመሪያ መርህ አድርጎ ሊይዘው ይችላል?

በዚህ ላይ ሌላው ተጨማሪ ሐዲስ የቁርአን አካል የነበሩ ሌሎች ሁለት ሱራዎች ከቁርአኑ ሳይካተቱ ቀርተው የመጥፋታቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን የተመለከተው ሐዲስ እንዲህ የሚል ነው፡-

> "ኡቤይ ኢብን ካብ በነበረው የእራሱ የቁርአን ቅጅ ሁለት ሱራዎች ሱራ አል-ሁላ እና ሱራ አል-ሂፍድ የተባሉትን ጨምሮ ይዞ ነበር፡፡" (አል-ኢትቃን ገጽ 86-87)[44]

እነዚህ ሁለት ሱራዎች፣ በሱራነታቸው የቁርአኑ አካል እንደሆኑ የታመ ነው፤ በአንዱ በኡቤይ ቢን ካብ ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎች ሦስት የነቢዩ ሙሐመድ ሱሃባዎችና የራሳቸውን ቁርአን ባሰባሰቡ በአቡ ሙሳ፣ በኢብን አባስና በከሊፋ አሊም ጭምር ይታወቃሉ፡፡ አራቱ ሱሃባዎች ሁሉም ለራሳቸው ባሰባሰቡት የቁርአን ቅጅ ውስጥ እነዚህን ሁለት ሱራዎች፣ የቁርአኑ አካል አድርገው አካተዋቸው እንደነበር የታሪክ መዛግብቱ ያሳያሉ፡፡ የሱራዎቹ ይዘት አንዱ

[44] *WAHHABIS' FITNAH EXPOSED, page 45; Ahmed Von Denffer, Ulum al Qur'an, The Mushaf of Ubay bin Ka'b*

ሦስት አንቀጾች፣ ሌላው ደግሞ ስድስት አንቀጾችን የያዙ ነበሩ፡፡ እንግዲህ አራቱ ሰዎች በአንድነት ሊሳሳቱ አይችሉም፣ ከዛይድም ይልቅ ለነቢዩ በጣም ቅርበት ያላቸው፣ እስልምናንም በመቀበል ቀደምት ናቸው፡፡ አንድ የቁርአን አንቀጽ የቁርአኑ አካል ሆኖ እንዲካተት የሁለት ሰዎች ምስክርነት እንዲያገኝ የሚጠይቀውን መስፈርትም አሟልተዋል፡፡ ግን ደግሞ ከቁርአን አካልነታቸው ወጥተው ተጥለዋል፡፡

## 2. ቁርአን የሱ አካል ያልሆኑ ሱራዎችንና አንቀጾችን አቅፎ መያዙ

ቁርአንን ለህዝቡ ለማስተማር ስለተመረጡት ሰዎች ኢማም አል-ቡኻሪ የሚከተለውን አስፍረዋል፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4999**

> አብደላ ቢን ኡመር፣ አብደላ ቢን መስኡድን ጠቀሰና እንዲህ አለ፡ የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ የሰማሁለትን ያን ሰው ምን ጊዜም እወደዋለሁ፡፡ ከእነዚህ አራት ሰዎች ቁርአንን ተማሩ፣ አብደላ ቢን መስኡድ፣ ሳሊም፣ ሙአዝና ከኡቤይ ቢን ካብ አሉ፡፡ ማስሪቅ የተናገረው ሐዲስ ነው[45]

ቁርአን የተበረዘና ንጹህ ያልሆነ ስለመሆኑ፣ የእስልምና የመረጃ ምንጮች የሚያቀርቡት ሌላው መረጃ፣ የራሱ አካል ያልሆኑ ሱራዎችንና አንቀጾችን በውስጡ አካቷል የሚል ነው፡፡ እነዚህ ለቁርአን አስተማሪነት ከተመረጡት መካከል የሆኑት፣ ቁርአን የራሱ አካላል ያልሆኑ ሱራዎችንና አንቀጾችን በውስጡ አቅፎ ስለመያዙ፣ የታመነ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

አብደላ ኢብን መስኡድና ከሊፋ አሊ እራሳቸው ባዘጋጁት፣ ቁርአን አሁን ካሉት 114 የቁርአን ሱራዎች የተወሰኑትን ባለማካተት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ኢብን መስኡድ ሱረቱል አል-ፋቲሃን (የመክፈቻይቱ ምዕራፍ)፣ ሱረተል አል-ፈለቅን (የተፈልቃቂው ምዕራፍ)/ 113ኛ/ እና ሱረቱል አል-ናስን (የሰዎች ምዕራፍ)/114ኛ/ እነዚህ ዱአዎች እንጂ የቁርአኑ አካል አይደሉም ብሏል[46]፡፡ ከሊፋ አሊ ደግሞ ሱረቱል አል-ፋቲሃ (የመክፈቻይቱ ምዕራፍ)፣ ሱረቱል ረድእ (የነጎድጓድ ምዕራፍ) /13ኛ/፣ ሱረቱል አል-ኑር (የብርሃን ምዕራፍ) /24ኛ/፣ ሱረቱል አል-ተህሪም (የማውገዝ ምዕራፍ) /66ኛ/ እና ሱረቱል አል-አለቅ (የረጋ ደም ምዕራፍ) /96ኛ/ የቁርአኑ አካል አይደሉም በማለት እራሱ ባዘጋጀው ቁርአን

[45] *Sahih Al-Bukhari vol 6 page 432*

[46] *Ahmed Von Denffer, Ulum al Qur'an, The Mushaf of Ibn Mas'ud;*

ውስጥ አላካተታቸውም[47]፡፡ በተለይ አብዱላህ ኢብን መስኡድ የሰጠው ምስክርነት እውነት መሆኑን በአጽንኦት የገለጸው እንዲህ በማለት ነበር፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 5002**

በአላህ! ከእርሱ በቀር ሌላ ሊመለክ የሚገባው የሌለ! በቁርአን ውስጥ ከወረደው የአላህ ቃል ውስጥ፣ የት ቦታ እንደወረደ የማላውቀው የለም፡፡ ደግሞ በቁርአን ውስጥ ከወረደው የአላህ ቃል ውስጥ፣ ስለማን እንደወረደ የማላውቀው የለም፡ ስለ አላህ ቃል ከእኔ የበለጠ የሚያውቅ ካለ የሚኖርበት ቦታ ግመል የሚደርስበት ከሆነ ወደ እርሱ እንደመምሄድ ይህንን አውቃለሁ፡፡[48]

ይህን በመሰለ ሰው/ኢብን መስኡድ/ የቁርአን አካል አይደሉም ስለተባሉት ሱራዎች ሌላ ተቃራኒ ሐዲስ ከሳሂህ አል-ቡኻሪ ላይ ላስነብባችሁና የተወሰኑ ጥያቄዎችን አነሳለሁ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4976-77**

ኡቤይ ቢን ካብን አቡ አል-ሙንዛር ሆይ፤ ወንድምህ ኢብን መስኢድ እንዲህና እንዲህ ይላል (ስለ ሁለቱ ሙአዊዛት ሱራዎች ሱራ 113 እና 114 (የቁርአኑ አካል አይደሉም) ስል ጠየቅሁት፡፡ ኡቤይም ስለእነርሱ የአላህን መልእክተኛ ጠይቄአለሁ፣ እንዲህም ብለዋል፤ እነርሱ የወረዱት ለእኔ ነው፤ እኔም ቀርቻቸዋለሁ (የቁርአኑ አካል እንደሆኑ) ስለዚህ የአላህ መልእክተኛ እንዳሉት እኛም እንላለን፣ ሲል ጨምሮ ተናገረ፡፡ ዚር ቢን ሁባኢሽ የተናገረው[49]

ወደ ጥያቄዎቹ ስመለስ፡-

- በመጀመሪያ የሐዲስ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ዘገባዎች ለምን እርስ በእርስ ሊቃረኑ ቻሉ? ኢማሙ ሐዲሱን ሲያሰባስቡ ይህንን ተቃርኖ አላስተዋሉም ነበር ማለት ነው?
- ውድ አንባቢ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ሁሉም ከሊፋዎች፣ በየዘመናቱ የነበሩ ኡለማዎች፣ ተቀባይነት ያላቸው የሐዲስ ዘጋቢዎች የመሰከሩላቸውና የተቀበሏቸው እውቅ የነቢዩ ሱሃባዎች ናቸው፤ እነዚህ ታማኝ ሱሃባዎች፣ የቁርአኑ አካል አይደሉም በተባሉት ሱራዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ እርሰዎ የየትኛውን ሱሃባ አመለካከት ይቀበላሉ? የኡቤይን

---

[47] *Theodor Nöldeke, The History of the Qur'ān, page 220*

[48] *Sahih Al-Bukhari vol 6 page 433*

[49] *Ibid page 419-420*

ወይንስ የኢብን መስኡድን? ስለተቀበሉት አመለካከት ትክክለኛነት የሚያቀርቡት የተጨበጠ ማስረጃስ ምንድን ነው?

- ኢብን መስኡድና ኡቤይ ቢን ካብ ህዝቡን ቁርአን እንዲያስተምሩ ነቢዩ ሙሐመድ የመረጧቸውና ከሊፋ አሊም ቢሆን የመጀመሪያ ሙስሊም ነው፡፡ ሁሉም ለቁርአን የታመኑ ምስክሮች ናቸው፡፡ ሐዲሳቱን የሞላው የእነርሱ ምስክርነት ነው፡፡ እንዲህ ሆነው እያለ፣ በታመኑበት በቁርአን እነርሱ መስማማት ካልቻሉ፣ የቁርአንን ታማኝነት ገደል የሚከተው አይሆንም ይላሉ? ለትውልድስ ያለምንም እንከን መተላለፍ የቻለ መጽሐፍ ነው፤ ብሎስ መቀበል ይቻላል?
- ሌላው ኡቤይ ይቀራቸው ከነበሩት መካከል፣ አንዳንዶቹን በአቡበከር ትዕዛዝ በተጀመረው የመጀመሪያው ቁርአንን የማሰባሰብ ሥራ ወቅት ውድቅ ተደርገውበታል፡፡ በአንጻሩ በአሁኑ ቁርአን ውስጥ የተካተቱትን ኢብን መስኡድ ሦስቱን ሱራዎች፣ ከሊፋ አሊ ደግሞ አምስት ሱራዎችን አስመልክቶ ጥያቄ ካነሱና የቁርአኑ አካል አይደሉም ካሉ ሌላው የሚታመነው ምንጭ ማን ሊሆን ይችላል? ይህስ በቁርአኑ ታማኝነት ላይ ትልቅ ጋሬጣ መሆኑ አይደለምን? ቁርአን ያልተበረዘና የሰው እጅ ያልገባበት ነው፤ ብሎ ለመናገር ከዚህ በኋላ ይደፍራሉ?
- የነቢዩ ሙሐመድ ሱሃባዎችና የቁርአኑ መምህራን የሆኑት፣ ነቢዩ ካለፉም በኋላ እምነቱን የመሩ ከሊፋዎች፣ ቁርአኑ ሲወርድ ኢብን መስኡድ እንዳለው አብረው የነበሩ፣ ለምን እንደወረደ ምክንያቱን ሳይቀር የሚያውቁ ሰዎች እራሳቸውን አስታርቀው መሄድ ያልቻሉበትን ቁርአን እንዴት እርስዎ ታማኝ ነው ብለው ሕይወትዎን ሰጡት? ደግሞስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በመበረዝ አለመበረዝ ጉዳይ ለማወዳደር እንዴት አሰቡ?

ሌላው የቁርአን አካል ያልሆኑት፣ በእስልምና ምሁራን ዘንድ ለአሥራ አራት ክፍለ ዘመናት ግራ አጋቢ ሆነው የቆዩና እስካሁን ድረስ አነጋጋሪ ሆነው ያሉት ሱረቱል አል-ተውባህ (የንስሓ ምዕራፍ) 9 ፡ 128-129 ናቸው፡፡ እነዚህ አንቀጾች፣ በምሁራኑ ዘንድ፣ በልዩ መጠሪያቸው የሐሰት አንቀጾች /false verses/ አንዳንዴም የሰይጣን አንቀጾች በመባልም ይጠራሉ ፡፡

**ሱረቱል አል-ተውባህ 9 ፡ 128-129**

ከነሳችሁ የሆነ፣ ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የሆነ፣ በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ በምእመናን ርህሩህ አዛኝ የሆነ መልእክተኛ፣ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡ ቢያፈገፍጉም አላህ በቂዬ ነው ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፣ በእርሱ ላይ ተጠጋሁ፣ እርሱም የታላቁ አርሽ ጌታ ነው በላቸው፡፡

እነዚህ ሁለቱ አንቀጾች የቁርአኑ አካል እንዳልሆኑ በእስልምናው ምሁራን ዘንድ ለምን እንደሚታመን ምክንያቶችን ያስቀምጣሉ፡-

- አንድ አንቀጽ የቁርአን አካል ነው፣ ተብሎ ተቀባይነት የሚያገኘው የሁለት ሰዎችን ምስክርነት ማግኘት ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ሐዲሳቱ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> ሂሻም ቢን አርዋን ከአባቱ ሰምቶ የተናገረው ሙስሊሞች በያማማ በተሰው ጊዜ፣ አቡበከር በመስጊድ መግቢያ ኡመር ቢን ኸታብንና ዛይድ ቢን ሳቢትን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ ማንም እናንተ ማስታዎስ ያልቻላችሁትን የቁርአን አንቀጽ ይዞ ከመጣ ሁለት ሰዎችንም ካስመሰከረ ተቀበሉት[50]፤ ይህ የሆነው በርካታ ቁጥር ያላቸው ቁርአኑን በልባቸው የሚያውቁ የነቢዩ ተከታዮች በያማማ ላይ በመገደላቸው ነበር፡፡

በዚህ መስፈርት መሰረት ለአል-ተውባህ (የንስሓ ምዕራፍ) 9 ፡ 128-129 የቀረበው ምስክር አንድ ብቻ ስለነበር፤ የመስፈርት አለመሟላት ስለታየበት ነው፡፡

- የቁርአን አንቀጾች ቦታ የሚወሰነው በአላህ ሆኖ ሳለ፣ ለእነዚህ አንቀጾች ቦታ የወሰነላቸው ሰው መሆኑ፡፡ አንቀጾቹ በመካ የወረዱ ሆነው ሳለ፣ ተመድበው የተገኙት ግን በመዲና ሱራ ውስጥ ነው፡፡ ለዚህም አዲስ አንሳራዊ ሙስሊም የሆነው ሁዘኢማንን ከሊፋ ኡስማን ጠይቆት ቦታውን እንደወሰነው ይታወቃል፡፡ አንቀጾቹም የተገኙት ከዚህ ሰው ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡[51]
- ስለ አንቀጾቹ የተሳከረ ሐዲሳዊ ዘገባዎች መሰጠቱ ሌላው ምክንያት ነው፡፡ ሱና አቡ ዳውድ ኡቤይ ቢን አል-ተውባህ በማጻፍ ላይ ሳለ፣ አንቀጽ 127 ላይ ደርሶ 128ን ሲቀጥል፣ ይጽፉለት የነበሩት ሰዎች ሱራው እንዳበቃ ሲነግሩት፣ እነርሱ እንደተሳሳቱ ነግሯቸው አንቀጽ 128 እና 129 ሲጨምር ሲያሳይ፤ ሳሂህ አል-ቢኻሪ ዛይድን በመጥቀስ ሁዘኢማ ከተባለ ሰው ላይ ብቻ ያገኘው መሆኑን ይናገራል፡፡[52]
- ኡቤይና ዛይድ ለነቢዩ ሙሐመድ ይወርድ ለነበረው ወህይ ጸሐፊዎች ስለሆኑ ቁርአን በወረደ ጊዜ ይመዘግቡ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ ሐላፊነት ላይ ኖረው ሁለቱ ጸሐፊዎች የሚሰጡት አሳብ የተሳከረ መሆኑ አንቀጾቹን ተአማኒነት አሳጥቷቸዋል፡፡
- በእስልምና ምሁራን ዘንድ የቁርአን ተአምራዊ ቁጥር በሚባለው በቁጥር 19 ብዜት ስሌት ሲሰላ እነዚህ ሁለት አንቀጾች የዚህን የስሌት ስርአት

---

[50] *Muhammad Mustafa Al-Azami, The history of the quranic text From Revelation to Compilation, Uk Islamic academy, ENGLAND 2003, page 80*

[51] *Sahih al Bukhari vol 6, #4679, page 156*

[52] *Ibn Abu Dawud vol.2, 30, Sahih al Bukhari vol 6, #4679, page 156*

የሚያዛቡ ሆነው ተገኝተዋል[53]፡፡ ስለዚህ የተደረሰበት መደምደሚያ ቁርአን ከእነዚህ ሁለት አንቀጾች ውጭ ነው የሚል ሆኗል፡፡ ታዲያ ቁርአን አልተበረዘም ብሎ ለመናገር እንዴት ያስደፍራል?

አንድ ሌላ ከቁርአን አንቀጾች ውጭ ነው ተብሎ በመታሰቡ የእስልምና ምሁራኑን በአመለካከት ከፋፍሎ የሚገኘው ቢስሚላህ ነው፡፡ ይህ አንቀጽ ከሱረቱል አል-ተውባ በስተቀር በሌሎቹ 113 ሱራዎች ውስጥ ይገኛል፡፡ በሱረቱል አል-ተውባ ላይ የነበረ ቢሆንም፣ ያልተገኘው እርሱም እንደ ሌሎቹ አንቀጾች በመጥፋቱ ነው ይላሉ፡፡ አብዛኛው ምሁራን በዚህ ይስማማሉ፡፡ ከዚህ የተለየ አመለካከት ያላቸውም አሉ፡፡ ሆኖም 114ቱን ቢስሚላህ በተመለከተ በምሁራኑ መካከል ያለውን የተለያየ አመለካከት ኢማም ኢብን ካሲር በተፍሲራቸው ውስጥ እንዲህ አስፍረውታል፡-

**ተፍሲር ኢብን ካቲር ቅጽ 1፣ ገጽ 60**

በሌላ በኩል ማሊክ፣ አቡ ሃኒፋህና የእነርሱ ተከታዮች ሲናገሩ ቢስሚላህ የፋቲሃም ሆነ የየትኛውም የቁርአን ሱራ አካል አይደለም፤ ብለዋል፡፡ ዳውድ ቢስሚላህ የሱራዎቹ አካል ሳይሆን፣ ከእነርሱ ውጭ የሆነ፣ በሱራዎቹ መጀመሪያ ላይ ያለ፣ የተለየ አያት ነው፤ ብሏል፡፡ ይህንን አሳብም አህመድ ቢን ሐምባሊ ይደግፊዋል፡፡[54]

ሌላ ተጨማሪ ሐዲስና የኢማሞችን ንግግሮች ላስነብባችሁ፡-

ተፍሲር ኢብን ካቲር ቅጽ 3 ገጽ 331

"በመጨረሻ የወረደው ሱራ ሱረቱል በራህ /ሱረቱል አል-ተውባህ/ ነው፡፡ ቢስሚላህም በሱራው መጀመሪያ ላይ አልተጻፈም፣ ምክንያቱም በከሊፋ ኡስማን ትዕዛዝ የቁርአኑ ቅጅ በሚዘጋጅበት ወቅት ሱሃባዎች አለመጻፋቸው ነው፡፡" "የአህለል ሱናው እውቅ ኢማም የሆኑት ኢማም ማሊክ ሲናገሩ፡- ቢሰሚላህ የሱረቱል በራህ /ሱረቱል አል-ተውባ/ መጀመሪያ አይደለም፤ ምክንያቱም **የሱረቱል በራህ የመጀመሪያ ክፍል በጠፋ ወቅት፣ ቢስሚላህ ከእርሱ ጋር አብሮ ጠፍቷል፡፡** በዚህ ወቅት ኡስማን፣ ነቢዩ፣ ሱረቱል በራህ፣ የሱረቱል አንፋል አካል ይሁን፣ አይሁን፣ አልነገሩንም አለ፡፡"[55]

**ሱና አቡ ዳውድ ቅጽ 1፣ ቁጥር 786-787**

---

[53] *Dr Rashad Khalifa, Quran - The Final Testament, Smashwords Edition, 1989 Appendix 24 - Tampering With the Word of God, http://www.submission.ws*

[54] *Tafsir Ibn Kathir vol 1, page 60*

[55] *Tafsir Ibn Kathir vol 3, page 331*

**ጃሚ አት-ትርሚዝ ቅጽ 5, ቁጥር 3086 393-394**

የአላህ መልእክተኛ ሱረቱል በራህ የሱረቱል አንፋል አካል መሆኑንና አለመሆኑን ሳይነግሩን ሞቱ፡፡[56]

እስኪ በዚህ በተመሰቃቀለ የቁርአን ታሪክ ላይ የተወሰኑ ጥያቄዎች ልጠይቅ፡-

- ❖ እነዚህ የታወቁ የሃይማኖቱ ምሁራን እንዳሉት፣ ቢስሚላህ የቁርአኑ አካል ካልሆነ በቁርአኑ ውስጥ ሰፍሮ እንዲገኝ ያደረገው ማን ነው? ለምን? ይህንን የማድረግ ስልጣን ያለው ማን ነው? የስልጣኑስ ምንጭ ከየት ነው? አንዱ ተነስቶ ይህንን ይጨምራል፣ ሌላው ያኛውን ይቀንሳል፤ ይህም ቁርአን ለትውልድ ያለምንም እንከን እዚህ ዘመን ላይ መድረስ አለመቻሉን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ እንዲህ ከሆነ ቁርአን ሳይበረዝ፣ ሳይሰረዝ፣ ሳይደለዝና ሳይጠፋ በአጠቃላይ በአላህ ጥበቃ ሥር ኖረ ለማለት እንዴት ይቻላል?
- ❖ የኢማም አት-ትርሚዝ የሐዲስ ዘገባ አል-ተውባ በሱራነት መልክ ቁርአን ውስጥ ስለመገኘቱ ጥያቄ ውስጥ እያስገቡን ነው፡፡ አል-ተውባ እራሱን የቻለ ሱራ ካልሆነ አሁን ባለበት መልኩ መኖር የቻለው በከሊፋ ኡስማን በጎ ፈቃድ ነው ማለት ነው?
- ❖ በሱረቱል አል-ተውባህ ውስጥ የነበር ቢስሚላህ 3/4ኛው የምዕራፉ ክፍል ሲጠፋ አብሮ ጠፍቷል፡፡ ይህንንም ኢማም ማሊክ አረጋግጠውልናል፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ እየታወቀ ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9 ሁሌ እየተጠቀሰ ስለ አላህ ጥበቃ ለምን ይወራል?
- ❖ በእስልምና መሪዎቹና ምሁራኑ መካከል ቢስሚላህ ነበረው ግን ጠፍቷል የሚልና አልነበረውም የሚሉ ሁለት አሳቦች እንዳሉ እያየን ነው፤ ከሁለቱ አሳቦች አንጻር ጥያቄዎችን ላንሳ፡- ከ114ቱ የቁርአን ሱራዎች ቢስሚላህ የሌለው በዚህ ሱራ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ታዲያ ሱራው ቢስሚላህ እንደነበረው አሁን ላይ እንዴት ሊታወቅ ቻለ? የሱረቱል አል-ተውባ ቢስሚላህ ከሁሉ ተለይቶ ብቻውን እንዴት ጠፋ? የሌሎቹ እንዴት ተገኘ? ነው ወይስ ከሊፋ ኡስማን እንዳለው ሱረቱል አል-ተውባ እራሱን የቻለ ሱራ ሳይሆን ሁለት ቢስሚላህ ያለው የሱረቱል አንፋል አካል መሆኑ ነው?
- ❖ ብዙ የተወራላቸው የቀድሞዎቹ ሃፊዘሎችና የነቢዩ ሙሐመድ ሱሃባዎች ቁርአኑን በማሰባሰብ ሥራቸው ወቅት በሱረቱል አል-ተውባ ላይ ቢስሚላህ ብሎ መጀመርን እንዴት ሊረሱት ቻሉ? ዛይድስ ቢሆን ያኔ ወህይ ሲጽፍ ሳለ ይህንን አንቀጽ ማስፈሩን አያስታውስም ነበር? ወይንስ

[56] *Abu Dawud Sulaiman bin Ash'ath, Sunan Abu Dawud, Maktaba Dar-us-Salam Riyadh-2008 vol 1page 466-467; Muhammad lbn Eisa At-Tirmidhi, Sunan At-Tirmidhi, Maktaba Dar-us-Salam, Riyadh2007, vol 5 page 393-394*

ይህ አንቀጽ የጠፋው ዛይድ ቁርአኑን በመጽሃፍ መልክ አሰባስቦ ከጨረሰና ዘመን ካለፈ በኋላ ነበር?

- ከሊፋ ኡስማን እራሱ ካዘጋጀው ውጭ ያሉት ሁሉም የቁርአኑ ቅጅዎች እንዲቃጠሉ ስለአደረገ፣ ሱረቱል አል-ተውባ ቢስሚላህ እንደነበረውና እንዳልነበረው የሚገልጽ ማስረጃ ማግኘት አይቻልም፡፡ ታዲያ አሁን ያሉት ኡለማዎች ይህ ሱራ ቢስሚላህ እንደነበረውና እንዳልነበረው እንዴት ሊያውቁ ቻሉ? ለአመለካከታቸው የሚያቀርቡት መረጃ ምንድን ነው? በዚህ ውስጥ ለቁርአን ጠባቂው አላህ ነው እንደተባለው ሁሉ ያደረገለትን ጥበቃ ማየት ችለዋል? ቁርአን በአላህ የተጠበቀና እንከን የለሽ ነው ብሎ ማመንም ሆነ ማሰብስ ይቻላል?
- የመጀመሪያዎቹ የነቢዩ ሱሃባዎች ቢስሚላህ የቁርአኑ አካል እንደሆነ ካወቁ፣ በሃፍስ ቁርአን ውስጥ ሱረቱል አል-ተውባ ላይ ቢስሚላህ ሳይካተት ሲያዩት መረሳቱን በማሳወቅ ተመልሶ እንዲካተት ለምን አላደረጉም? አሁን ላይ ያሉት ኡለማዎችስ በሱራው ውስጥ ቢስሚላህ እንደነበር ካመኑ፣ ለምን አሁን በመጻፍ የሱራው አካል አላደረጉትም?
- ለዚህ ግራ ግብት ላለው ነገር ተጠያቂው ማን ነው? ቁርአኑስ የማን ነው? አላህ ለቁርአኑ ጠባቂው ከሆነና የእራሱ እውነተኛ ቃል ከሆነ፣ ይህ ሁሉ ሊፈጠር ይገባል ብለው ያምናሉ? ምክንያቱም አላህ ፍጹም አምላክ ስለሆነ፣ ሥራው በፍጹምነቱ የሚከናወን ስለሚሆን ምንም አይነት እንከን ሊገኝበት አይችልም!
- ውድ ሙስሊም ወገኔ የቁርአን ገሃድ ታሪክ እንዲህ ከሆነ፣ የአላህ ቃል ነው፣ በሚለው እምነት ጸንተው መቆም ይችላሉ? አሁን ቆም ብሎ ማስተዋልና የቆሙበትን እምነት ትክክለኛነት መመርመርን ይጠይቃልና ያድርጉት ስል አሳቤን አቀርባለሁ፡፡

# 3. ቁርአን የራሱ አካል ያልሆኑ ተጨማሪ ቃላትን በውስጡ ይዟል

በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ የጎላ ተቀባይነት ያለው የነቢዩ ሙሐመድ የሐዲስ መጽሐፍ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቁርአን የራሱ አካል ያልሆኑ ተጨማሪ ቃላትን በውስጡ አቅፎ መያዙን አስመልክቶ ሱረቱል አል-ለይል(የሌሊት ምእራፍ) የተባለውን ሱራ ጠቅሶ የሚከተለውን ዘግቦ እንመለከታለን፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4944**

የአብዱላህ ኢብን መስኡድ ተከታዮች ወደ አቡ ዳርዳእ መጡ፤ እነርሱ ወደ እርሱ ቤት ከመድረሳቸው በፊት እርሱ ፈልጓቸው ሄደና አገኛቸው፡፡ ከዛም ጥያቄ ጠየቃቸው፤ ከመካከላችሁ እንደ አብዱላህ

ኢብን መስኡድ ቁርአኑን የሚቀራ ማን ነው? ሲል ጠየቀ፤ አልቃማን አመላከቱት፡፡አል-ቃማንም ጠየቀው፤ እንዴት ነበር አብዱላህ ኢብን መስኡድ ሱረቱል አል-ለይልን የሚቀራው? አለው፡፡ አል-ቃማም ሲመልስ፤ **"በወንድና በሴት"** አለው፡፡ አቡ ዳርዳእም ነቢዩ በዚህ መልክ ስቀራ እንደሰሙኝ አረጋግጫለሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች "ወንድና ሴትን በፈጠረው አምላክ" ብዬ እንድቀራ ይፈልጋሉ፡፡ እኔ እነርሱን አልከተልም፡፡ ኢብራሂም የተናገረው [57]

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 5 ቁጥር 3761**

አቡ ዳርዳእ በተጨማሪ "በሌሊቱ(በጨለማው) በሚሸፍን ጊዜ" በማለት የሚጀምረውን ሱራ አብዱላህ ኢብን መስኡድ እንዴት ነበር የሚቀራው? ሲል ጠየቀ፡፡ ከዚያም በፊቱ ቀራሁለት፡-

> "በሌሊቱ በሚሸፍን ጊዜ፣ በቀኑም በተገለጸ ጊዜ፣ በወንድና በሴት፡፡"

ያኔ አቡ ዳርዳእ በአላህ! ነቢዩ ይህንን ሱራ በዚህ መልኩ እንድቀራ አደረጉኝ እርሳቸውም እንዲሁ ሲቀሩ ሰምቻቸዋለሁ፡፡ አል-ቃማ የተናገረው ሐዲስ ነው[58]

ይህ ሲጠቃለል ሱረቱል አል-ለይል (የሌሊት ምዕራፍ) 92 ፡ 1-3 በኢብን መስኡድና በተከታዮቹ ዘንድ የሚታወቀው፡-

"በሌሊቱ በሚሸፍን ጊዜ በቀኑም በተገለጸ ጊዜ በወንድና በሴት፡፡"

በማለት የሚቀጥል ሲሆን፣ አሁን በዚህ ዘመን ባለው የሃፍስ ቁርአን ቅጅ ደግሞ እንደሚከተለው አስፍሮት ይገኛል፡-

**ሱረቱል አል-ለይል (የሌሊት ምዕራፍ) 92 ፡ 1-3**

በሌሊቱ እምላለሁ (በጨለማው) በሚሸፍን ጊዜ በቀኑም በተገለጸ ጊዜ ወንድንና ሴትን በፈጠረውም (አምላክ እምላለሁ)፡፡

وَاللَّيْلِ إِذَا يَغْشَىٰ وَالنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ وَمَا خَلَقَ الذَّكَرَ وَالْأُنثَىٰ

በሱረቱል አል-ለይል የተጠቀሱ አንቀጾች ውስጥ ሰፍረው የሚገኙት **በፈጠረው አምላክ** የሚሉትን ቃላት የአሁኑ ቁርአን በመጨመር ይዞ ይገኛል፡፡

---

[57] *sahih Al Bukhari vol 6, page 394*

[58] *Ibid vol 5, page72*

## 4. ከከሊፋ ኡስማን ሞት በኋላ፣ በቁርአን ላይ የደረሱ ሁለት አደጋዎች

### ሀ. ቁርአን ለሁለተኛ ጊዜ በእሳት ቃጠሎ መውደሙ

ቁርአን ከአላህ እንደ ወረደና ጠባቂው አላህ እንደሆነ፣ ቢነገርለትም እንደ ነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ዘገባ የደረሰበት ችግር ከዚህ በፊት በተገለጹት የሚያበቃ አልሆነም፡፡ ቀድሞ በከሊፋ ኡስማን የተፈጸመው ቁርአኑን የማቃጠል ተግባር ሳይበቃ፣ ከከሊፋዎች ሞት በኋላ ሌላ አንድ ማን አለብኝ ባይና ስሙን ከቁርአን ጋር በተያያዘ በታሪክ መዝገብ ላይ ማስፈር በፈለገ ሰው፣ እንደገና በእሳት የመቃጠል እጣ ወድቆበታል፡፡ **በሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9** የተገለጸው የአላህ ጥበቃ የት እንደ ደረሰ ባይታወቅም እንደገና ለእሳት የመዳረግ እጣ የወደቀበት፣ እንደ ቀድሞው ሁሉ፣ ወደፊትን በመስጋት ነው፡፡ ሲጀመር ሊያተርፈው ባይቻለውም ከሊፋ ኡመር መጥፋቱን ሰጋ፤ ሁዛይፋ ኢብን አል-የመኒ ሰጋ፤ ከሊፋ ኡስማን አሁንም ስጋት በስጋት ሆነ፤ ከዚህም በኋላ ሌላ የስጋት ሰው መርዋን ኢብን አል-ሃካም የሚባል በውክልና መዲናን ያስተዳድር የነበር ሰው፣ የድርሻውን ሊወጣበት ተነሳ፡፡

ይህ ሰው በእሳት ያቃጠለው፣ በከሊፋ አቡበከር ትዕዛዝ፣ ከሊፋ ኡመርና ዛይድ ቢን ሳቢት ያዘጋጁትን የመጀመሪያውን ቁርአን ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ያነሳሳው ሃፍሳ ዘንድ የተቀመጠው የቁርአን ቅጅ፣ በሕይወት ከኖረ፣ በኋለኛው ዘመን የሚመጣው ትውልድ በከሊፋ ኡስማን ከተዘጋጀው ቁርአን ጋር በማነጻጸር ሌላ ችግር ሊያስነሳ ይችላል ብሎ ስለሰጋ ነበር፡፡ ይህንን በሃፍሳ ዘመን ማድረግ ሞክሮ ሳይችል ቀርቷል፡፡ ከእርሷ ሞት በኋላ ወንድሟን በማስገደድ ከተቀመጠበት ወስዶ በመቀዳደድ በእሳት አቃጥሎታል፡፡ የዚህን ሰው አድራጎት ኢማም ኢብን አቢ ዳውድ ኪታብ አል-መጻሒፍ በተባለው መጽሐፋቸው ታሪኩን አስቀምጠውታል፡፡ እኚህ ሰው ሱና አቡ ዳውድ የተባለውን እውቅ የሱኒዎች የሐዲስ መጽሐፍን የጻፉ ሰው ልጅ ናቸው፡፡ እንዲህ አሉ፡-

> ሳሊም ኢብን አብዱላህ ኢብን ኡመር ሲነግረኝ "መርዋን ወደ ሃፍሳ መልእክተኞችን ላከ፡፡ ማለትም እርሱ በጊዜው ሙአውያን ወክሎ የመዲና አስተዳዳሪ ነበር፡፡ ነገር ግን እርሷ ለእርሱ ለመስጠት አልፈለገችምና ከለከለችው፡፡" ሳሊም ቀጠለና ሃፍሳ ሞተች፤ እኛም ከቀብር ከተመለስን በኋላ መርዋን ለአብዱላ ኢብን ኡመር የቁርአኑን መጽሐፍ እንዲልክለት ማስገደጃ ላከለት፤ ወዲያውም አብዱላህ ኢብን ኡመር ላከለት፡፡ ከዛም መርዋን መልእክተኞቹን አዘዛቸው፣ እነርሱም ቀዳደዱት፤ እንዲህም አለ፣ ይህንን ያደረግኩበት ምክንያት ወደፊት ከጊዜ በኋላ፣ የማያምኑ ሰዎች መጽሐፍቱን በተመለከተ ክህደትን

እንዳይፈጽሙ በማለት ብቻ ነው፡፡ ከዛም እነርሱ ቀዳደዱትና አቃጠሉት፡፡ አቡ ኡቤይድ የተናገረው[59]

ሱና ኢብን አቢ ዳውድ ኪታብ አል-መጽሐፍ

ቁርአን ለሰው ልጆች ደህንነት ከዘለአለሙ አምላክ የተላከ መገለጥ እንዳልሆነ፣ በጉልህ የሚያሳዩ መረጃዎችን እስካሁን ሐዲሳቱ ሲያስነብቡን ቢቆዩም፣ አሁንም አንድ ጨምረውልናል፡፡ እነርሱን መሠረት በማድረግም ይህንን ሰው ድርጊቱን እንዲፈጽም በአነሳሳው ምክንያትና አጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ አንዳንድ ጥያቄዎችን እስኪ ልጠይቅ፡-

- የከሊፋ ኡስማን የቁርአን ቅጅ የተዘጋጀው ከሊፋ አቡበከር ካዘጋጀው ቁርአን እንደነበር የአል-ቡኻሪ ዘገባ ያስረዳል፡፡ ሐዲሱ እውነት ከሆነ በከሊፋ ኡስማን በተዘጋጀውና በመጀመሪያው በከሊፋ አቡበከር በተዘጋጀው የቁርአን ቅጅ መካከል ልዩነት ሊኖር አይችልም፡፡ ማርዋን ሁለቱም የቁርአን ቅጆዎች የተዘጋጁት በአንድ ሰው ዋና አዘጋጅነት መሆኑን እያወቀ በመካከላቸው ልዩነት ይፈጠራል ብሎ እንዴት ሰጋ? ልዩነቱ ካለም እንዴት ሊኖር ቻለ? አንዳንድ የነቢዩ ሱሃባዎች አዘጋጁ ለሥራው በነበረው ብቃት ስላልተማመኑ የተዘጋጀው የቁርአን ጥራዝ ከችግር የጸዳ ሊሆን እንደማይችልም ስላመኑ፣ የተቃውሞ ድምጽ አሰምተዋል፡፡ እርሱም ይህንን የሱሃባዎቹን ስጋትና እምነት ይጋራ ስለ ነበር ይሆን? ሁኔታው እንዲህ እንዲታሰብ ያስገድዳል፡፡
- በሁለቱ ቅጅዎች መካከል ልዩነት እንደ ነበር ካወቀ ደግሞ፣ በጊዜው እንደ ሌሎቹ ማለትም እንደ ኢብን መስኡድ "ጥያቄ አለኝ" ማለት ለምን አልቻለም? እንዲህ በማድረግስ ለአላህና ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ ያለውን ታማኝነት ለምን አላሳየም? ምናልባት ድምጹን ያልሰማነው ስላልተዘገበ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና የከሊፋ ኡስማንን ቅጅ አሜን ብሎ መቀበልና በከሊፋ አቡበከር የተዘጋጀውን ወዲያው መጣል ብሎም በእሳት ማቃጠል ለምን አስፈለገው?
- ደግሞስ በሁለቱ ከሊፋዎች ዘመን ስለተከናወነው፣ ቁርአንን በአንድ ጥራዝ ስለማሰባሰቡ ሥራ የተሰጡትን የተለያዩ ሐዲሳት እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? የዚህ ሰው ድርጊት የሁሉንም የነቢዩን ሱሃባዎች ታማኝነት፣ የቁርአንን ከችግር የጸዳ መሆን፣ እንዲሁም የሐዲሳቱን ዘገባዎች እውነትነት ጥያቄ ውስጥ አይከታቸውም ትላላችሁ?
- የሃይማኖቱ የእምነት መመሪያ ስለሆነው መጽሐፍ ያለውን የታሪክ እውነታ የሚመጣው ትውልድ እንዳያውቅ፣ ሐቅን ከእርሱ መደባበቅና

---

[59] *Gabriel Sawma, The Qur'an: Misinterpreted, Mistranslated, and Misread. The Aramaic Language of the Qur'an, page 84; Dr. William Campbell, The Qur'an and the Bible in the light of history and science, Middle East Resources, 2002; Theodor Nöldeke, The History of the Qurʾān, page 306-307*

ትውልዱን መፍራት ለምን አስፈለገ? ትውልዱ ያለውን ታሪካዊ እውነታ እንዳያውቅ መደረጉ፣ በቁርአንና በሃይማኖቱ እውነተኛነት ላይ ጥላ አያጠላበትም ትላላችሁ?

❖ አላህ ጠባቂው ነው፣ በተባለለት ቁርአን ላይ ከነቢዩ ህልፈት በኋላ፣ ሱሃባዎቹ እንዲህ የተመሰቃቀለ ሥራ የሠሩት፣ አላህ ፈቅዶላቸው ነው፤ ብለው ያምናሉ? መልስዎት አዎን ከሆነ ለምን? በሱረቱል አል-ሒጂር 15 ፡ 9 እንደተባለው የቁርአን ጠባቂውና ባለቤቱ አላህ እራሱ ከሆነና ውስጡም ምንም አይነት እንከን የሌለበት ከሆነ፣ ከትውልዱ ታሪኩን መደበቅ ለምን አስፈለገው? እንዲህ አይነት የድብብቆሽ ጨዋታ በሰው ልጆች መካከል የተወገዘ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ከሆነ፣ ከአላህ ባህሪ ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል?

❖ ውድ አንባቢ፤ ሙስሊም ነዎት? ከሆኑ እንዲህ ምስቅልቅል ባለና ከትውልድ በተደበቀ ታሪክ ውስጥ የሚኖረውን ቁርአን፣ እርስዎ እንዴት ትክክለኛና የእውነተኛው አምላክ ቃል ነው፣ ብለው ማመን ቻሉ? ወይንስ ይህንን የተደበቀ ከመጋረጃው ጀርባ ያለውን ታሪኩን አያውቁም ነበር?

## ለ/ ከሊፋ ኡስማን ባዘጋጀው ቁርአን ላይ የተደረገ ስረዛና ድለዛ

ኢብን አቢ ዳውድ አሁንም "ኪታብ አል-መጽሐፍ" በተሰኘው መጽሐፋቸው አላህ ጠባቂው ነውና ምንም እንከን እንደማይወጣለት በሚነገርለት ቁርአን ውስጥ፣ የተፈጸመውን የመሰረዝና የመደለዝ ተግባር ዘግበዋል፡፡ እንዲሁም የቁርአኑ አካል ያልሆኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው አዲስ ቃላት የመጨመራቸውንም ታሪክ ዘግበው አድርሰውናል፡፡ ይህንን የፈጸሙት ከ694-714 ዓም የኢራቅ አስተዳዳሪ የነበረው አል-ሐጃጅ ዩሱፍ እና ኡቤይዱላህ ቢን ዚያድ የተባሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ከእነርሱ በፊት የነበሩት እንዳደረጉት ሁሉ እነዚህም በቁርአኑ ታሪክ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው የፈለጉ ይመስላል፡፡ ኢብን አቢ ዳውድ አል-ሐጃጅ ቁርአን በከሊፋ ኡስማን የተቃጠለው ተቃጥሎ፣ የተረፈው ለአርባና ሃምሳ ዓመታት ያክል አገልግሎት እየሰጠ ባለበት ሰአት ላይ፣ ተነስቶ ሊስተካከል እንደሚገባው ስለአመነ፣ ከውስጡ በተለያዩ ሱራዎች ላይ አስራ አንድ ያክል የቃላት ማስተካከያ አድርጎለታል ብለዋል፡፡

> አቡበከር ሲናገር … አባቴን ያሰው ማን ነው? ስል ጠየቅሁት፣ እርሱም አባድ ኢብን ሱሃይቡ ከአውፍ አቢ ጃሚላ ሰምቶ የነገረን አል-ሐጃጅ ቢን ዩሱፍ ከኡስማን መጽሐፍ አስራ አንድ ፊደሎችን ቀይሯቸዋል አለን፤ እነርሱም፡-
>
> በሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2 ፡ 259
> በሱረቱል አል-ዝህሩፍ (የጌጣጌጥ ምዕራፍ) 43 ፡ 32
> በሱረቱል አል-ማኢዳ (የማዕድ ምዕራፍ) 5 ፡ 48
> በሱረቱል ዩኑስ (የዮናስ ምዕራፍ) 10 ፡ 22

በሱረቱል ዩሱፍ (የዮሴፍ ምዕራፍ) 12 ፡ 45
በሱረቱል ሙሚኒን (የምእምናን ምዕራፍ) 23 ፡ 85-89
በሱረቱል አል-ሹዐራ (የባለ ቅኔዎች ምዕራፍ) 26 ፡ 116 በኑህ ታሪክ
በሱረቱል አል-ሹዐራ (የባለ ቅኔዎች ምዕራፍ) 26 ፡ 167 በሉጥ ታሪክ
በሱረቱል አል-ለዚና ከፋሩ 47 ፡ 15
በሱረቱል አል-ተክዊር (የመጠቅለል ምዕራፍ) 81 ፡ 24 ባሉት ላይ ስረዛና ድለዛ ተደርጓል፡፡[60]

እንደገናም በኡቤይዱላህ ቢን ዚያድ ስለተጨመሩ 2000 ፊደላት የሚከተለውን ዘግበዋል፡-

ያዚድ አል-ፋሪስ ሲናገር፤ ኡቤይዱላህ ቢን ዚያድ ቁርአን ውስጥ ተጨማሪ 2000 ፊደላትን አስገብቷል…[61]

## 5. ቁርአን ከአላህ ውጭ ከሆኑ ምንጮች መቀዳቱ

ነቢዩ ሙሐመድ ነቢይነታቸውን ካወጁበት ቀን ጀምሮ፣ የተለያዩ ወገኖች ቁርአን የአምላክ ቃል ከሆነ ለምን ይህ? ለምን ያኛው? በማለት ሲጠይቁ ኖረዋል፡፡ ስህተት ነው የሚሉትን፣ ለአምላክ ባህሪ አይመጥንም የሚሉትን፣ ሁሉ እያነሱም ጠይቀዋል፤ ተነጋግረዋል፤ ተከራክረዋል፡፡ የቁርአን አስተምህሮዎችና የመልእክቶቹ ምንጭ ማንነትም እንደ ሌሎቹ የመነጋገሪያ ነጥቦች ሁሉ አንዱ አጀንዳ ነበር፡፡ ቁርአን ስለራሱ ከአላህ ዘንድ የወረደ እንደሆነ ሲናገር፣ ሞጋቾቹ አይደለም ይላሉ፤ ታሪክና ሳይንስ እንዲሁም የነቢዩ ሐዲሳት ደግሞ ከአላህ ውጭ ከሆነ ምንጭ የተቀዳ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ፡፡ ከአላህ ውጭ ለቁርአን በምንጭነት ከሚጠቀሱት ሁለቱ፡-

### ❖ የቅድመ እስልምና ባለቅኔዎች የቅኔ መድብሎች

በእስካሁኑ ንባባችሁ ሱረቱል **አል-ሒጅር** 15 ፡ 9 የቁርአን ጠባቂው አላህ እንደሆነ ቢናገርም በአንጻሩ ሌሎቹ የእስልምና የመረጃ ምንጮች አባባሉን ውድቅ እንዳደረጉት አንብባችኋል፡፡ እነዚያው የመረጃ ምንጮች አሁንም ቁርአን በውስጡ ከቀደምት የአረብ ባለቅኔዎች የቅኔ መድበል ውስጥ በቀጥታ ቃል በቃል የተቀዱ የግጥም ስንኞችና አስተምህሮዎችን አካትቶ እንደያዘ ያስረዳሉ፡፡

---

[60] *Ibn Abi Dawud, Kitab al-Masahif, p.117, http:www.answering-islam.org/authors/gilchrist/quran/chapter5.html*

[61] *Muhammad Mustafa al-Azami, The History of Quranic text From Revelation to Compilation, UK Islamic academy leiceste, England 2003 page 133. Ibn Abi Dawud, Kitab al-Masahif, p.117*

ከዚህም የተነሳ ያዳምጣቸው የነበረው ማህበረሰብ ለነቢይነታቸውና ለሚያስተላልፉት ትምህርት ቀና አመለካከት አልነበረውም፡፡ ማህበረሰቡ ነቢዩ ሙሐመድን እንዴት ይመለከታቸው እንደነበር ቁርአን በተለያዩ ሱራዎች ውስጥ በዝርዝር አስፍሮት ይታያል፡፡ ከበርካታ አስተያየቶቻቸው መካከል እነዚህን እናገኛለን፡-

ሱረቱል አል-አንቢያ (የነቢያት ምዕራፍ) 21 ፡ 5

«በእውነቱ (ቁርኣኑ) የሕልሞች ቅዠቶች ነው፡፡ ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ **<u>ቅኔን ገጣሚ</u>** ነው፡፡ የቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልክተኛ ከኾነ) በተዓምር ይምጣብን» አሉ፡፡

بَلْ قَالُوا أَضْغَاثُ أَحْلَامٍ بَلِ افْتَرَاهُ بَلْ هُوَ شَاعِرٌ فَلْيَأْتِنَا بِآيَةٍ كَمَا أُرْسِلَ الْأَوَّلُونَ

ሱረቱል አል-ሷፍፋት (የተሰላፊዎቹ ምዕራፍ) 37 ፡ 36

እኛ **<u>ለዕብድ ባለቅኔ</u>** ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር፡፡

وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُو آلِهَتِنَا لِشَاعِرٍ مَّجْنُونٍ

ቁርአን ሲነበብ አድማጭ የነበረው ህዝብ "ቅኔን ገጣሚ" "እብድ ባለቅኔ" ይላቸው የነበረውና ትምህርታቸውን ያቃልል የነበረው ከሦስት ምክንያቶች የተነሳ እንደ ነበር ከመረጃዎቹ መመልከት ይቻላል፡-

## 1. ከባለ ቅኔዎች የቅኔ መድበል ቃል በቃል የተወሰዱ ቃሎች፣ አባባሎችና መልእክቶች ቁርአኑ ውስጥ በመገኘታቸው

ነቢዩ ሙሐመድ ከቅድመ እስልምና ባለ ቅኔዎች የቅኔ መድብል ውስጥ፣ በርካታ ቅኔዎች ተነቦላቸው ካደመጡ በኋላ እነዚህ ቅኔዎች ሰልመዋል ይሉ እንደነበር ሱና ሻማኢል አት-ትርሚይዝ 36 ፡ 232 ማብራሪያ ላይ ተዘግቦ ይገኛል፡፡

ሻማኢል ቲርሚዝ ምዕራፍ 36፣ ቁጥር 002 (232)

ማብራሪያ፡- … ኡመያህ ቢን አቢስ-ሳኡለት እውነትን በቅኔዎቹ የገለጸ እውቅ ባለቅኔ ነበር፤ በመጨረሻው ዘመን ያምን ነበር፡፡ ሆኖም የአላህ ምህረት ከእርሱ ጋር አልነበረም፤ እድለቢስ ሆኖ እስልምናን አልተቀበለም ነበር፡፡ ነቢዩም ስለ እርሱ እንዲህ አሉ፡- "የእርሱ ቅኔዎች

እስልምናን ተቀብለዋል ልቡ ግን አልተቀበለም፡፡" ስለእርሱ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ በሐዲስ ቁጥር ስምንት ላይ ተሰጥቷል፡፡[62]

እንግዲህ ሕዝቡ ራሱ የሚያውቃቸው እነዚያ የቅድመ እስልምና ቅኔዎች የሰለሙ ከሆኑ፣ የቁርአኑ አካል የማይሆኑበት፣ መልእክታቸውም የማይካተትበት ምን አይነት ምክንያት ሊኖር ይችላል? አልፎ ተርፎም በእናታቸው በኩል የሥጋ ዘመዳቸው የሆነን የቅድመ እስልምና ዘመን እውቅ ባለቅኔ ኡመያህ ቢን አቢስ-ሳኡለትን እስልምናን ሳይቀበል ሙስሊም ነው፣ ማለት ይቻላል ይሉ እንደነበር አቡ ሁሬይራ ተናግረዋል፡፡

**ሱና ሻማኢል አት-ትርሚዝ 36 ፡ 8 (238)**

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 6፣ ቁጥር 5885-5887**

አንድ ሰው ከነቢዩ ጋር ቁጭ አለ፤ ነቢዩ ከኡመያህ ኢብን አል-ሳላት ቅኔዎች የምታውቀው አልህን? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እርሱም አዎን ሲል መለሰ፡፡ እስኪ ከዚያ የተወሰኑትን ተቀኝልኝ አሉት፡፡ አንድ መስመር ተቀኘ፡፡ሌላ መስመር ተቀኘ፡፡ ጨምር አሉት፡፡ መቶ ያክል የግጥም መስመሮችን አነበበና ጨረሰ፡፡ ነቢዩም ኡመያህ እስልምናን ለመቀበል የቀረበ ነበር አሉ፡፡ አምር ቢን ሻሪድ ከአባቱ ሰምቶ የተናገረውና አቡ ሁሬይራ በተጨማሪ የተናገሩት ሐዲስ ነው[63]

እስኪ በሌላ ሐዲስ ከአንደበታቸው ስለሚወጣው ቃል እርሳቸውና አላህ የተናገሩትን ላስነብባችሁ፡-

**ሱና አቡ ዳውድ 19 ፡ 3646**

እንዳስታውሰው በማሰብ ከአላህ መልእክተኛ አፍ የምሰማውን ማንኛውንም ነገር እጽፍ ነበር፡፡ ቁሬይሾች ግን እንዲህ በማለት እንዳልጽፍ ከለከሉኝ፤ "እርሱ ፍጡር ሰው ስለሆነ፣ በቁጣም በደስታም ይናገራል፤ ታዲያ አንተ ዝም ብለህ ትጽፋለህ?" እኔም መጻፍ አቆምኩ፡፡ ለአላህ መልእክተኛም አሳወቅኳቸው፡፡ እርሳቸውም በእጣታቸው ወደ አፋቸው በማመልከት፣ነፍሴን በእጁ በያዘው! ትክክለኛ የሆነ ብቻ ከዚህ ይወጣልና ጻፈው አሉኝ፡፡ አብዱላህ ኢብን አምር ኢብን አል-አስ የተናገረው[64]

---

*[62] Imaam Abi 'Eesaa Muhammad bin 'Eesaa bin Sorah At-Tirmiai, Shamaail-Tirmizi, Translated by Muhammad bin 'Abdurrahmaan Ebrahim, page 232*

*[63] Shamaail Tirmize page 240; sahih Muselim vol 6, page 112-113*

*[64] Sunan Abu Dawud vol 4, page 209-210*

አላህም እንዲህ ብሎላቸዋል፡-

**ሱረቱል አል-ነጅም (የኮከብ ምዕራፍ) 53 ፡ 4**

እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራዕይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡

إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَىٰ

እንግዲህ ነቢዩ ሙሐመድ የራሳቸውንና የባለ ቅኔዎችን ቅኔ ይቀኙ ከነበር፣ ስለ ባለ ቅኔዎች የቅኔ መድበል ይህንን የመሰለ አመለካከት ከነበራቸው፣ ቁርአኑ ሲሰባሰብ የነበረው ከአንደበታቸው ይወጣ ከነበረው ቃል ሁሉ ከሆነ፣ ቁርአን ከባለ ቅኔዎቹ ቅኔ ጋር ላለመቀላቀሉ ማስረጃ ሊያቀርብ የሚችል የለም፡፡ የሕዝቡም ምላሽ እንዲያ ሊሆን የቻለው ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከቀደሙትና በዛው ዘመን ይኖሩ ከነበሩ ባለቅኔዎች የቅኔ መድብል ውስጥ ቃል በቃል የተቀዱ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ የግጥም ስንኞች የቁርአኑ አካል ተደርገው ተወስደው ስለነበር ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ ቃል በቃል ከቅኔ መድብሎቻቸው ቅኔዎችን በመውሰድ፣ የቁርአኑ አካል ያደረጉባቸው ባለቅኔዎች እነማን ናቸው? ከቅኔ መድበሎቻቸው ቃል በቃል የተወሰዱትና የቁርአኑ አካል የተደረጉት አንቀጾች የትኞቹ ናቸው? ትሉ ይሆናል፡፡ በዚህኛው ዘመን አምላካችን ለአረቡ ዓለም የምስራቹ ወንጌል ሰባኪ እና በርካታ ሙስሊም አረቦችን ከጌታችንና ከመድሐኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እያስተዋወቁ የሚገኙት ግብጻዊው የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን አባት፣ አባ ዘካርያ፣ ለበርካታ ዓመታት ባደረጉት ጥናት "source of Islam, the pre-islam poetry, hanifian, sabian rites" በተሰኘው ጽሁፋቸው ምንጭ ጠቅሰው የሚከተለውን ብለዋል፡፡ እኔም በአባባላቸው ስህተት አልባ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ሐዲሳትንም አያይዤ አቀርባለሁ፡-

## ሀ. ባለቅኔው ኤምር አል-ቁየስ

ይህ ባለቅኔ ከነቢዩ ሙሐመድ መወለድ ከሠላሳ ዓመታት በፊት ከዚህ ዓለም እንዳለፈ አባው ይገልጻሉ፡፡ አባ ዘካርያ ከዚህ ባለቅኔ የቅኔ መድብል ውስጥ ቃል በቃል በነቢዩ ሙሐመድ የተወሰዱና የቁርአኑ አካል የተደረጉ የባለቅኔው ቅኔዎች ጥቂቶቹ በሚከተሉት ሱራዎች ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል[65]፡-

ሱረቱል አል-ቀመር (የጨረቃ ምዕራፍ) 54 ፡ 1፣ 29፣ 31
ሱረቱል አል-ዱሃ (የረፋድ ምዕራፍ) 93 ፡ 1-2
ሱረቱል አል-አንቢያ (የነቢያት ምዕራፍ) 21 ፡ 96

---

[65] አባሪ 1

ሱረቱል አስ-ሳፍፋት (የተሰላፊዎች ምዕራፍ) 37 ፡ 61

## ለ. ባለቅኔው ኡመያህ ኢብን አል-ሳላት

ይህ ባለቅኔ በሳውዲ አረቢያ ጣይፍ ከተማ ይኖር የነበር የነቢዩ የእናታቸው የሥጋ ዘመድ ነው፤ ከናዝራውያን ባለቅኔዎች መካከል አንዱ እንደነበር አባ ዘካርያ ይናገራሉ፡፡ ጨምረውም ይህም በናዝራውያን ባለቅኔዎች የቅኔ መድበል ገጽ 227 ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡ ስለዚህ ሰው ሌሎች ኢስላማዊ መረጃዎች መካ ላይ በአራት ሰዎች የተመሰረተው የሃኒፋህ ሃይማኖት አስተሳሰብ ተከታይም እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሰው እምነቱ አህዳዊ የሆነና በመጨረሻው ዘመን ፍርድ የሚያምን ነበር፡፡ ከነቢዩ ሙሐመድ የእምነት መሰረት ጋር ተመሳሳይ እምነት ቢኖረውም፣ እርሳቸው በኖሩበት ዘመን እየኖረ ለነቢይነታቸው የተንበረከከ ሰው አልነበረም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድም ከዚህ ባለቅኔ የቅኔ መድበል ውስጥ በርካታ ቅኔዎች ተነበውላቸው ካደመጡ በኋላ፣ እርሱ እስልምናን ሳይቀበል ቅኔዎቹ ግን እስልምናን ተቀብለዋል፣ ይሉ እንደነበር ኢማም አት-ትርሚዝ **በሱና ሻማኢል አት-ትርሚዝ 36 ፡ 232፣ 238** እና ኢማም ሙስሊም **በሳሂህ ሙስሊም 28 ፡ 5685-87** መዘገባቸውን ማስነበቤን እንዳትዘነጉ፡፡

ከዚህ ባለቅኔ የቅኔ መድበል ውስጥ ቃል በቃል በነቢዩ ሙሐመድ ተወስደው የቁርአኑ አካል ከተደረጉ በርካታ የባለቅኔው ቅኔዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው በማለት አባ ዘካርያ ይዘረዝራሉ[66]፡-

ሱረቱል ሉቅማን (የሉቅማን ምዕራፍ) 31 ፡ 10
ሱረቱል አሽ-ሹራ (የመመካከር ምዕራፍ) 42 ፡ 51
ሱረቱል አል-ሃሽር (ከአገር የማውጣት ምዕራፍ) 59 ፡ 24
ሱረቱል አል-አንአም (የቤት እንስሳት ምዕራፍ) 6 ፡ 103
ሱረቱል አል-ሙእሚኒን (የምእምናን ምዕራፍ) 40 ፡ 7

### 2. ለቅድመ እስልምና ቅኔዎች የነበራቸው ፍቅርና ቅኔን ጠላቶቻቸውን ለመመከቻ መጠቀማቸው

ነቢዩ ሙሐመድ አንዴ ወደ አላህ እንዲህ ሲሉ ጸለዩ አሉ አቡ ዳውድ፡-

**ሱና አቡ ዳውድ ቅጽ** 1፣ 764፣ 775

የአላህ መልእክተኛ አላህ ታላቅ ነው! ምስጋና ለእርሱ ይሁን! ክብር በጠዋት በማታ ለአላህ ይሁን! እያሉ ሦስት ሦስት ጊዜ ሲናገሩ

[66] አባሪ 2

ሰማቸው፡፡ ከዛም ከተረገመው ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ! ከሰይጣን እስትንፋስ፣ ከአክታውና ከክፉ አሳቡ በአላህ እጠበቃለሁ! አሉ፡፡አምርም የሰይጣን አክታ ቅኔ ነው፤ እስትንፋሱም ትእቢት ሲሆን፣ ክፉ አሳቡ ደግሞ መራራ ቂጣ ነው፤ በማለት ተናግሯል፡፡[67]

አላህም እንዲሁ ነቢዩንና ቅኔን በተመለከተ የሚከተለውን ተናግሮ ነበር፡-

**ሱረቱል ያሲን (የያሲን ምዕራፍ) 36 ፡ 69**

(ሙሐመድን) ቅኔንም አላስተማርነውም፡፡ ለእርሱም አይገባውም፡፡ እርሱ (መጽሐፉ) መገሰጫና ገላጭ ቁርአን እንጅ (ቅኔ) አይደለም፡፡

وَمَا عَلَّمْنَاهُ الشِّعْرَ وَمَا يَنبَغِي لَهُ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ وَقُرْآنٌ مُّبِينٌ

እንግዲህ አላህ ይህንን ሲናገር፣ እርሳቸውም ያንን የመሰለ ጸሎት ሲያደርሱ፣ ተከታዮቻቸውና ቁርአኑ ሲወርድ የሚያደምጡት ተቃዋሚዎቻቸው ሰምተዋል፡፡ ሆኖም አላህ እንዲጠብቃቸው የጸለዩበትን፣ የሰይጣን አክታ ነው ያሉትን፣ አላህም ለሙሐመድ አይገባም ያለውን፣ ከቅድመ እስልምና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቅኔዎች፣ ተከታዮቻቸው በፊታቸው ሲቀኙ በደስታ ያዳምጧቸው ነበር፡፡ የኡመያህን ተቀኝልኝ እያሉ ማስቀኘታቸውንና የሰጡትን አስተያየት ከዚህ በፊት አይተናል፡፡ እርሳቸው ነቢይ ነኝ ብለው፣ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ ሲሆኑ፣ አድማጮቹ ከሐዲ እየተባለ የተፈረጀው ሕዝብ፣ ቢንቃቸው፣ ቢያጣጥላቸው ምኑ ላይ ይሆን ስህተቱ?

**ሱና ሻማኢል አት-ትርሚዝ 36 ፡ 3-6፣ ቁጥር 6**

ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ከአንድ መቶ በላይ ስብሰባዎችን አብሬያቸው ተካፍያለሁ፡፡ በስብሰባዎቹ ሱሃባዎች ቅኔዎችን ይቀኙ፣ ደግሞም ከቅድመ እስልምና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ታሪኮች ይናገሩ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የአላህ መልእክተኛ እየሳቁ በዝምታ ያዳምጡ ነበር እንጅ አልከለከሏቸውም፡፡ ጃብር ኢብን ሳሙራህ የተናገረው ሐዲስ ነው[68]

ነቢዩ እንዳሉት ቅኔ የሰይጣን አክታ ነው!፤ ቅኔ ለነቢዩ የማይገባ፣ አላህም ያላስተማራቸው ነገር ነው፡፡ የሰይጣን ከሆነ፣ የአላህ ከሆነ ነገር ጋር በምንም ሁኔታ ሕብረት ሊኖረውና ጥቅም ላይ ሊውል አይገባም፡፡ ሆኖም ይህንን የሰይጣን አክታም እንደ ጂሐድ ቀስት ቆጥረው ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር ሲተጋተጉበት ታይተዋል፡፡ አንዴ በመካ መስጊድ ቁሬይሾች ነቢዩን አናስገባም

---

[67] *Sunan Abu Dawud vol 1, page 453 and 459-460*

[68] *Shamaail Tirmize page 233-239*

ባሉ ጊዜ፣ ሃሰንና ኢብን ራውሃ የተባሉትን ባለቅኔዎች "ገብርኤል ከእናንተ ጋር ነው" በማለት በቅኔ መልስ እንዲሰጣቸው ያበረታቱ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አላህ የተናገረውን እራሳቸው ነቢዩ ስለ ቅኔ የተናገሩትን ያልዘነጋው ኡመር ያንን ሲያደርጉ ከለከላቸው፡፡ ነቢዩ ግን ምን እንደተናገሩ የረሱ ይመስለኛል፣ ቅኔ የጂሐድ አንዱ የጦር መሳሪያ ነው፤ ተው አትከልክላቸው ብለውታል፡፡

**ሻማኢል ትርሚዝ ም 036፣ ቁጥር 005 (235)**

> *... ኡመር አስቆመውና እንዲህ አለ፡- "ኢብን ራዋሃህ ሆይ! የአላህ መልእክተኛ ባሉበትና በአላህ መስጊድ ቅኔዎችህን ታነበንባለህን?" የአላህ መልእክተኛም እንዲህ አሉ፡- "ኡመር ሆይ ተወው፤ እነዚህ የቅኔ ስንኞች በእነርሱ ላይ ብዙ ቀስቶችን ከማዝነም ይልቅ ብርቱዎች ናቸው፡፡"*[69]

ይህ የነቢዩ ሁኔታ የተምታታ መሆን፣ ነቢዩን ተቀባይነት ያሳጣ ሆኗል፡፡ ህዝቡ እርሱ ባለ ቅኔ ነው ሲሉ፤ አይ አይደለም፣ አይገባውም አለ አላህ በማለት፣ መንፈሳዊ ሊያስመስሉ ይሞክራሉ፡፡ እራሳቸውን ሊጠቅማቸው በሚችል ሁኔታ ውስጥ ሲያገኙት ደግሞ፣ አይ ይህማ በማለት የቀደመውን ንግግራቸውን ይሽሩታል፡፡ ይህ የሚያሳየው ነቢዩ የአላህ መልእክተኛ ቁርአንም የአላህ መልእክት አለመሆናቸውን ነው፡፡ ቁርአኑም ሆነ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር የመነጨው ከአላህ ሳይሆን፣ ከልባቸው ነበር፡፡

## 3. እራሳቸው ቅኔ ይቀኙ ስለነበር

የሚቃወማቸው ማሕበረሰብ እንዲያ የመሆኑ ሌላው ምክንያት፣ ስለ ቅኔ ከላይ የተባለውን ሁሉ ያሉና የተናገሩ ሰው፣ የአላህን ቃል ጥሰው፣ የራሳቸውንና የሌሎችን ባለቅኔዎች ቅኔ ሲያነቡና ሲቀኙ ይደመጡ ስለነበር ነው፡፡ ቃሉ የሚለው ሌላ፣ ተግባራቸው ሌላ፤ ይገርማል፡፡ የእስልምና ምሁራን ነቢዩ ሙሐመድ በሕዝቡ ዘንድ ልማድ የሆነውን ቅኔን ይቀኙ ነበር ወይ? ተብለው ሲጠየቁ፣ አንድና ወጥ የሆነ መልስ አይሰጡም፡፡ አንዳንዶቹ ሱረቱል ያሲን 36 ፥ 69ን በመጥቀስ አላህ ስለከለከላቸው አይቀኙም ነበር ይላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሐዲሳቱን ዋቢ በማድረግ፣ የራሳቸውን ቅኔ ይቀኙ፣ ከቅድመ እስልምና ባለቅኔዎች የቅኔ መድበል ሲነበብላቸው ያዳምጡ እንደነበር ይናገራሉ፡፡ ከዚህ አልፎ ተርፎ ራሳቸው የባለቅኔዎችን ቅኔ ይቀኙም እንደነበር ይናገራሉ፡፡ በዚህ ላይ ሚስታቸው አይሻ የሰጠችውን የምስክርነት ቃል ኢማም አት-ትርሚዝ ዘግበውታል፡-

**ሱና ሻማኢል አት-ትርሚዝ 36 ፥ 1-4**

---

*[69] Shamaail Tirmize page 238*

የአላህ መልእክተኛ ቅኔ ይቀኙ ነበርን? ሲል አይሻን ጠየቀ፣ ስትመልስ አዎ ለምሳሌ አንዳንዴ የአብዱላህ ቢን ራውሃን፣ አንዳንዴ የሌሎቹን ባለቅኔዎች ቅኔ፣ አንዳንዴም እነዚህን የታራፋህን የቅኔ ስንኞች ይቀኙ ነበር ……..፡፡[70]

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ነቢዩ የራሳቸውንና የሌሎቹን ባለቅኔዎች ቅኔ ይቀኙ የነበረው የሚከተለውን የአላህን ቃል በመጣስ ነበር፡-

**ሱረቱል ያሲን (የያሲን ምዕራፍ) 36 ፡ 69**

(ሙሐመድን) ቅኔንም አላስተማርነውም፡፡ **ለእርሱም አይገባውም፡፡** እርሱ (መጽሐፉ) መገሰጫና ገላጭ ቁርኣን እንጅ (ቅኔ) አይደለም፡፡

وَمَا عَلَّمْنَاهُ الشِّعْرَ وَمَا يَنبَغِي لَهُ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ وَقُرْآنٌ مُّبِينٌ

አድማጭ የነበረው ሕዝብ ጅማሬ ላይ እንደተገለጸው እብድ በለ ቅኔ ይላቸው የነበረው፣ እንዲህ ዝብርቅርቅ ያለ ነገር በመመልከቱ ነበር፡፡

## 5. ከሃኒፋ/ሁናፋ/ ሃይማኖት አስተምህሮ

ሃኒፋ የሚለው ቃል የሃይማኖት ስያሜ መሆን የጀመረው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ላይ በሶሪያ የነበሩ ክርስቲያኖች፣ አረባውያን ጣኦት አምላኪዎችን በዚህ ቃል መጥራት በጀመሩበት ወቅት ነበር፡፡ የምስራቃውያን የቋንቋና ባህል ተመራማሪዎች ሃኒፋ የሚለው ስያሜ ሃናፋ ከሚል የሲርያክ ሥርዎ ቃል የተወሰደ ሆኖ ትርጉሙ የተዘበራረቀበት፣ ግራ የገባው፣ አድሎኛ፣ ወስላታ፣ እምነት የማይጣልበት፣ ቅንነት የጠፋበት ማለት ነው ይላሉ[71]፡፡ ጃዋድ አሊ የተባሉ ኢራቃዊ የእስላምና ምሁር ቃሉ በአራማይስጥ አምላክ የለሽ፣ አታላይ፣ ግብዝ፣ ከሃዲ፣ የሰውን አሳብ የሚያጣምምና ወደ ጥፋት የሚመራ ማለት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ፣ በተለይም ነቢዩ ሙሐመድ በነቢይነት ከመገለጣቸው በፊት የነበሩ፣ ስያሜው አብርሐም ይከተለው የነበር ሃይማኖት ስያሜ መሆኑንና እነርሱም ያንን ሃይማኖት እንደሚከተሉ የሚናገሩ ሰዎች ተነሱ፡፡ እነዚህ ከቁሬይሽ ጎሳ የሆኑ ጥቂት ሰዎች፣ በመካ የነገሰውን የጣኦት አምልኮ እየተቃወሙ የአብርሃምና የቀደሙት ነቢያት ሃይማኖት የሆነው የሃኒፋ ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ ይናገሩ ነበር፡፡ ከዚህ አቋማቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ስደት እንደደረሰባቸው የነቢዩ ሙሐመድ የታሪክ መጽሐፍት ያስገነዝባሉ፡፡ ነቢዩ

---

[70] *Shamaail Tirmize page 231-234*

[71] *Arthub Jeffeby, The Foreign Vocabulary Of The Qur'an, Oriental Institute Baroda 1938, page 112-115*

ሙሐመድም ከእስልምና በፊት የዚህ ሃይማኖት ተከታይና የአስተሳሰቡም አራማጅ ነበሩ፡፡ በመካ የዚህ ሃይማኖት መስራች የነበሩ አራት ሰዎች፡-[72]

- ዛይድ ቢን አምሩ ቢን ናፋኢል
- ዋራቃ ቢን ናኡፋል
- ኡቤዱላህ ቢን ጃሃሽ
- ኡስማን ቢን አል-ሁዋይሬዝ ይባላሉ፡፡

እነዚህ አራት ሰዎች ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ከልጅነታቸው ጀምሮ የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ በኋላም በተለያዩ ሁኔታዎችና በሃይማኖት ጉዳይ ሳይቀር እየተገናኙ ይመካከሩና ይደጋገፉ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ሁሉም ሉአይይ በተባለ የነቢዩ ሙሐመድ ቅድመ አያት ዘር ሃረግ ውስጥ የተገኙ ሰዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ዋራቃ ቢን ናኡፋልና ኡስማን ቢን አል-ሁዋይሪዝ የሚስታቸው የኸድጃ የስጋ ዘመዶች ሲሆኑ፣ ኡቤይዱላህ ቢን ጃሃሽ ደግሞ፣ የነቢዩ የአክስታቸው ልጅና የሚስታቸው የኡም ሃቢባ የቀድሞ ባል ነበር፡፡ ሁሉም ሃይማኖታዊ ተጽእኗቸውን ከልጅነታቸው ጀምሮ በነቢዩ ላይ ማሳደር የቻሉ ነበሩ፡፡ ይህንን የሚያሳይ አንድ ሐዲስ ላስነብባችሁ፡-

> በመጀመሪያ ከጣኦት አምላኪነቴ የገሰጸኝና እነርሱን ማምለክ የከለከለኝ ዛይድ ቢን አምሩ ቢን ናፋይል ነው፡፡ ከዛይድ ቢን ሃሪሳ ጋር ከጣይፍ ስንመጣ በመካ በላይኛው ክፍል ዛይድ ቢን አምሩ ነበርና በእርሱ በኩል አለፍን፡፡ ቁሬይሾቹ ዛይድ ቢን አምሩን ሃይማኖታቸውን ለሚተውት ልዩ ምሳሌያቸው ነበር፡፡ ስለዚህ እርሱ ከመካከላቸው ወጥቶ ሄዷል፡፡ እኔም ከእርሱ ጋር ቁጭ አልኩ፡፡ ዛይድ ቢን ሃሪሳ ለጣኦቶቻችን የተሰዋ ስጋ በሻንጣ ተሸክሞ ነበር፡፡ እናም እኔ በጊዜው ልጅ ነበርኩና ለዛይድ ቢን አምሩ አቅርቤለት እንዲህ አልኩት "አጎቴ ከዚህ ምግብ ትንሽ ብላ"፤ ሲመልስልኝም "እውነት ይህ እነዛ ለጣኦቶቻቸው ከሰውት የተወሰደ ነው" አለኝ፡፡ እንደሆነም ነገርኩት፤ እርሱም የወንድሜ ልጅ ሆይ፤ የአብዱል ሙጧሊብን ሴት ልጆች ከጠየቅሃቸው እንዲህ አይነት ምግብ እንደማልበላ ይነግሩሃል፤ ይህንን የማድረግ ፍላጎቱ የለኝም፤ አለኝ፡፡ ከዛም የጣኦት አምልኳቸውንና መስዋእታቸውን እያንቋሸሸ በመናገር ስለ ጣኦት አምላኪነቴ ገሰጸኝ አለ፡፡[73]

የዚህን ተመሳሳይ ሐዲስ በሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 5፤ ቁ 3826[74] ላይ ያገኙታል፡፡

---

[72] *Muhammad Mohar Ali, Sirat Al-Nabi and the Orietalists, King Fahd complex for the printing of the holy Quran, Medina 1997, vol 1 page 323-324; sira Ibn Ishaq page 99*

[73] *https://my.vanderbilt.edu/.../Chapter-Nineteen.-Muhammad-and-the-Beginnings-of-Islam, Sira Ibn Ishaq Translation by Guillaume 1956, p. 26.*

[74] *Sahih Al-Bukhari vol 5, page 63*

ኢ.ማም ሙስሊምና ኢ.ማም ኢ.ብን ካቲር በተፍሲራቸው ዋራቃ በዛን ወቅት ክርስትናን የተቀበለና አዲስ ኪዳንን/ኢ.ንጅልን/ ከሂብሩ ወደ አረብኛ ቋንቋ የተረጎመ ሰው እንደነበር ዘግበውለታል[75]፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ በሂራ ዋሻ የመጀመሪያውን ራዕይ ሲቀበሉ የመጣው እንግዳ ቁርአኑን እንዲያነቡ ሦስት ጊዜ ማጅራታቸው ላይ እየረገጠ ባሰቃያቸው ወቅት፣ ሚስታቸው ኸድጃ ለችግሩ መፍትሂ ለማግኘት ስትል የወሰደቻቸው ወደዚህ ሰው ነበር፡፡ ከእርሱም ሞት በኋላ ለሦስት ዓመታት የራዕይ መቋረጥ አጋጥሟቸው ነበር[76]፡፡ በዚህ ወቅት ወደ ገደል እራሳቸውን ወርውረው ለመግደል ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገው ነበር[77]፡፡ ከእርሱ የተማሩትን ለሱሃባዎቻቸው እያስተላለፉ ነበር እንዴ፣ ራዕይ ወረደልኝ ይሉ የነበረው?

በትንሹም ቢሆን፣ ሐዲሱ ላይ እንዳያችሁት፣ ዛይድ ቢን አምሩ ለነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖታዊ ትምህርት ብቻ አስተማሪ አልነበረም፡፡ የአረብኛ መጻፍና ማንበብም አስተማሪያቸው እንደነበር አባ ዘካርያ ጨምረው ይናገራሉ፡፡ የአባ ዘካርያ ንግግር እውነት መሆኑንና እንደሚባለው ነቢዩ ሙሐመድ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሰው እንዳልነበሩ የሚያረጋግጥ ሐዲስ በሳሂህ አል-ቡኻሪ ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል[78]፡፡

ሃኒፋ የሚለውን የሃይማኖት መጠሪያ እስልምና ወርሶ ለራሱ መጠሪያ ማድረጉ፣ ነቢዩ ሙሐመድ በእነዚህ ሰዎች በተለይም በዛይድ ቢን አምሩ ተጽእኖ ስር ይኖሩ እንደነበር ያመላክታል፡፡ በእምነት አንቀጾቻቸውም ቢሆን፣ ፍጹም ተመሳሳይ መሆናቸው ነቢዩ ከእነዚህ ሰዎች በቀዷቸው አስተምህሮዎችና የእምነት አንቀጾች ቁርአኑን ለማጣበባቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ የሚመሩትን እስልምናን ከአብርሃም ጋር ለማያያዝ ሃኒፋ የሚለውን ቃል 12 ጊዜ ቁርአን ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ለአብነት ያክል የሚከተሉትን የቁርአን አያዎች ይመልከቱ፡፡

ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2 ፡ 135
ሱረቱል አሊ-ኢ.ምራን (የኢ.ምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ) 3 ፡ 19፣ 95
ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 125 ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ውድ ወገኖች! ምንም ብዙ ማለት ቢቻልም፣ እዚህ ላይ ላቁምና እንዳነበባችሁት ይህ ሁሉ እየተነገረን ያለው በክርስቲያኖች ወይንም በአይሁዶች አይደለም፡፡ ራሳቸው እስልምና አንድ ብሎ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከዚህ ዘመን ድረስ

---

75 *Sahih al-Bukhari vol 1 page 46-48; tafir ibn kathir sura 96:1-3.*

76 *Sahih al-Bukhari vol 1 page 48*

77 *Ibn kathir, Al-sira Al-Nabawiyya, the life of Muhammad, Translated by Professor Trevor Le Gassick, Garner Publishing Limired, London 2006, vol 1 page 279-280*

78 *Sahih al-Bukhari vol 5, # 3826, page 101; Sahih al-Bukhari vol 3, #2699, page 506*

ያሉ፣ የተከበሩ የእስልምና ከፍተኛ ምሁራን ናቸው፡፡ እዚህ እስከምንደርስ ድረስ መግቢያ ላይ ከጠቀስኳቸው ውጭ አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አልጠቀስኩም፤ ሁሉም በሙስሊሙ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው መጽሐፎቻቸው ላይ ባሰፈሩት ዘገባ ያደረሱን ነው፡፡ ውድ አንባቢ! ቁርአንን በተመለከተ እስካሁን ድረስ ካነበቡት የተረዱትንና የደረሱበትን የግምገማ ማጠቃለያ ልጠይቅዎት እፈልጋለሁ፡-

- ❖ ከዚህ ቀደም ይህንን የቁርአንን ታሪክ ሰምተው ያውቃሉ?
- ❖ እስካሁን ድረስ ባነበቡት በአላህ ማንነትና በቁርአን ታሪክ መካከል መጣጣም ይታያል ብለው ያምናሉ?
- ❖ ቁርአን ከአላህ ለነቢዩ ሙሐመድ የተሰጠ ራዕይ ነው ከተባለና አላህም ጠባቂወው ነኝ ካለ እንዳለው ትክክለኛ ጥበቃ ተደርጎለታል ብለው ያምናሉ?
- ❖ ደግሞስ ያልተበረዘ፣ ያልተሰረዘ፣ ያልተደለዘ የአላህ ቃል ነው፣ ብለው ለመናገር ከዚህ በኋላ ይደፍራሉ?
- ❖ ሙስሊም ከሆኑ፣ የመጣው ሰው ሁሉ በየአጋጣሚው የሚወደውን የፈጸመበትን ቁርአን፣ የሕይወት መመሪያዎት አድርገው ሊይዙት እንዴት ቻሉ? ከዚህ በኋላ የአላህ ቃል ነው፤ ብለው በእርሱ በማመን ሊከተሉትና የሚያዘውን በመተግብር የዘለአለም ሕይወት በማግኘት ጀነት እገባለሁ ብለው ተስፋስ ሊጥሉበት ይችላሉ? አሁን ቆም ብለው ማሰብ ሊጀምሩ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

## 1.2. መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተበረዘ ተባለ?

ሳሂህ የሆኑት የሐዲስ መጽሐፍት በአንዳንድ ዘገባቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተበረዘ ያወሩት ለምን እንደሆነ ቀጥለን እስኪ እንመልከት፡፡ እንደ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ዘገባ ተበረዘ የሚለውን ቃል የተናገሩት ነቢዩ ሙሐመድ አልነበሩም፤ ኢብን አባስና ከሊፋ ኡመር ናቸው፡፡ ይህንን ሲሉ አላህ በተለያዩ የቁርአን ሱራዎች ስለ ቀደሙት መጽሐፍትና ስለ መጽሐፉ ሰዎች ከተናገረው ጋር መጋጩታቸውን አለማስተዋላቸው የሚገርም ነው፡፡ ግጭቶቹን ሁሉ ማሳየት አሁን አስፈላጊ ባይሆንም የተወሰኑ ናሙናዎችን ማሳየት ግን ይኖርብኛል፡፡ ቁርአን ስለራሱና ስለ ቀደሙት መጽሐፍት /ስለመጽሐፍ ቅዱስ/ የሚከተለውን ካለ እነርሱ ምን ቤት ናቸው?

**ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ) 3 ፡ 3-4**

> ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት <u>የሚያረጋግጥ ሲኾን</u> መጽሐፉን (ቁርኣንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ፡፡ ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል፡፡ (ከቁርኣን) በፊት ለሰዎች መሪ አድርጎ

(አወረዳቸው)፡፡ ፉርቃንንም አወረደ፡፡ እነዚያ በአላህ ተዓምራቶች የካዱ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አላቸው፡፡ አላህም አሸናፊ የመበቀል ባለቤት ነው፡፡

نَزَّلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَأَنزَلَ التَّوْرَاةَ وَالْإِنجِيلَ مِن قَبْلُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَأَنزَلَ الْفُرْقَانَ ۗ إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا بِآيَاتِ اللَّهِ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌ ۗ وَاللَّهُ عَزِيزٌ ذُو انتِقَامٍ

**ሱረቱል አል-አንአም (የቤት እንስሳዎች ምዕራፍ) 6 ፡ 92**

«አላህ (አወረደው)» በላቸው፡፡ ከዚያም በውሸታቸው ውስጥ የሚጫወቱ ሲኾኑ ተዋቸው፡፡ ይህም ያወረድነው የኾነ ብሩክ፣ ያንንም በፊቱ የነበረውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው፡፡ የከተሞችን እናት (መካን) እና በዙሪያዋ ያሉትንም ሰዎች ልታስጠንቅቅበት (አወረድነው)፡፡ እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የሚያምኑት እነርሱ በሶላታቸው ላይ የሚጠባበቁ ሲኾኑ በርሱ ያምናሉ፡፡

وَهَٰذَا كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ مُبَارَكٌ مُّصَدِّقُ الَّذِي بَيْنَ يَدَيْهِ وَلِتُنذِرَ أُمَّ الْقُرَىٰ وَمَنْ حَوْلَهَا ۚ وَالَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِالْآخِرَةِ يُؤْمِنُونَ بِهِ ۖ وَهُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ

ሌላው ነቢዩ የሚወርድላቸው ራዕይ ከአላህ ዘንድ መሆኑን አያምኑም ነበር፡፡ "አላህም" በጥርጣሬ ሲከበቡ ስላያቸው በሱረቱል ዩኑስ 10 ፡ 94 ላይ በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን፣ የመጽሐፉን ሰዎች ጠይቅ በማለት አዟቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡

**ሱረቱል ዩኑስ (የዮናስ ምዕራፍ) 10 ፡ 94**

ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን፣ እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፡፡ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል፡፡ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን፡፡

فَإِن كُنتَ فِي شَكٍّ مِّمَّا أَنزَلْنَا إِلَيْكَ فَاسْأَلِ الَّذِينَ يَقْرَءُونَ الْكِتَابَ مِن قَبْلِكَ ۚ لَقَدْ جَاءَكَ الْحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ الْمُمْتَرِينَ

❖ እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ከሆነ አላህ ስለ ቁርአንና ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ተልእኮ ይህንን ሁሉ ማለት ነበረበትን? መጽሐፍቱ የተበረዙ ከሆኑ ትክክለኛ የአላህ ቃል መሆናቸውን ለማረጋገጥ መልእክተኛዬን ላኩ ከማለት ይልቅ መበረዛቸውን ለምን አልወቀሰም? ማስተካከያ ማድረግ፣

ሰዎቹ የሚታረሙበትንና ወደ አላህ የሚመለሱበትን ምክር መስጠት አይሻልም ነበር?

❖ አላህ ቁርአንን ያወረድኩት ነቢዩ ሙሐመድንም መላኬ የቀደሙትን መጽሐፍት ላረጋግጥ ነው፤ ሲል፣ ሱሃባዎቹ ደግሞ የቀደሙት መጽሐፍት ተበርዘዋል፣ ልክ አይደሉም የሚሉ ከሆነ፣ ማነው ትክክለኛ? አላ ወይስ የነቢዩ ሱሃባዎች? ይህንን የሚጣረስ ነገር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

❖ ነቢዩም ሆኑ ሱሃባዎቹ ስለ ቀደሙት መጻሐፍት ተበረዙ ብለው ሲናገሩ የዘነጉት ሌላውን የቁርአን ክፍል መቃረናቸውን ነው፡፡ አንዱን ገነባን ሲሉ ሌላውን በማፍረስ ሥራ ላይ ይጠመዳሉ፡፡ የመጽሐፉ ሰዎች መጽሐፋቸው ከተበረዘና ትክክለኛ መረጃ ከእነርሱ ማግኘት የማይቻል ከሆነ፣ አላህ በሱረቱል ዩኑስ 10 ፡ 94 የማስተላለፉ አስፈላጊነት ምኑ ላይ ነው? የተበረዘ መጽሐፍ የያዘ ወገን መረጃ ይጠየቃል ወይስ ስለክፉ ስራው ሊወቀስ ይገባዋል?

❖ ሱሃባዎቹ አንድን ነገር ሲናገሩ፣ ከአላህ ቃል ጋር መጋጨቱንና አለመጋጨቱን ቅድሚያ መመርመርን ለምን አልፈለጉትም? ይህስ ነቢዩና ቁርአን ከአላህ ዘንድ የተላኩ ናቸው፣ የሚባለውን ስብከት ጥርጣሬ ውስጥ አይጥለውም ትላላችሁ?

❖ ቁርአን ምን እንዳለ ሳያስተውሉ በመናገር እርስ በእርሱ የሚያቃርኑት ከሆነ የሚናገሩትና የሚሰጡት የትኛውም አሳብ እንዴት ተቀባይነት ሊኖረው፣ ሰውም እነርሱንና እምነታቸውን ተቀብሎ የዘለአለምን ሕይወት ተስፋ አድርጎ አብሯቸው ሊጓዝ ይችላል?

❖ አላህስ ትክክለኛ ያልተዛባ መረጃ ማግኘት የማይቻልበትን ምንጭ ማመልከቱ ነቢዩን አጣብቂኝ ውስጥ መጣል አይሆንበትም? እንደተባለው ስለ ነቢዩ ነቢይነት ከመጽሐፉ ሰዎች መረጃ ከነበር፣ ለምን ሊቀበሏቸው አልቻሉም? ይህንን ያለው አላህ እራሱ ከሆነ፣ ከመመስከር ይልቅ "በሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 150 ሃይማኖታችንን ይክዳሉ፣ ቂብላችንን ግን ይከተላሉ እንዳይሉ" በማለት ሌላ የሚቃረን ነገር መናገር ለምን አስፈለገው? ሃይማኖታዊ ልዩነት ካላቸው አንዱ ለሌላው ምስክር ሊሆን የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ ሊኖር አይችልም፡፡ ይህንን ማስተዋል አልቻለምን?

❖ ሌላው ሱረቱል አል-በቀራ 1 ፡ 150ን ከሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 89-90 ከተገለጸው አሳብ ጋር እንዴትስ ማስታረቅ ይቻላል? ይህንን ሁሉ እየሠራና እየተናገረ ያለው አላህ ነውን?

❖ በተጨማሪ ነቢዩ ሙሐመድም ሆኑ፣ ኢብን አባስና ኡመር እንዲሁም በዚህ ዘመን ያሉ ተከታዮቻቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ነው፣ ብለው ካመኑ፣ ነቢዩ ከራሳቸው ጋር እና ከቁርአን ጋር በመጋጨት ተልእኳቸውን ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ ማድረጋቸው እንዴት ይታያል? እንዲህ አይነት እርስ በእርስ መጣራረስ ከአንድ የአላህ ነቢይ የሚጠበቅ ይሆናልን?

እነዚህ ወገኖች የአላህን ቃል የሚያስጥስ እንዲህ አይነት አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገቡ ምን አስገደዳቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተበረዘ ሊባል ቻለ? ብለን ብንጠይቅ፣ ለዚህ መልስ ይሆን ዘንድ የተለያዩ ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በአማኙ ህዝብ መካከል የተፈጠረው ግራ መጋባት ነው፡፡ የሚከተሉት የቁርአንና የሐዲሳት ክፍሎች የነበረውን ሁኔታ ግልጽ ስለሚያደርጉት፣ እነርሱን በመመልከት መፍረድ ይቻላል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ መዲና ከገቡ በኋላ የነጅራን ክርስቲያኖችና የመዲና አይሁዳውያን ሙስሊሞችን ወደ ሃይማኖታቸው መጋበዝ ጀምረው ነበር[79]፡፡ ስለ አብርሃም ሃይማኖት ማንነትም ክርክሮች ጦፈው ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ሙስሊሞቹ ወደ እነዚህ ሃይማኖቶች የመሳብ አዝማሚያ አሳይተው ነበር፡፡ ውይይቱና ክርክሩ የጦፈ ንጽጽራዊ ክርክር እንደነበር የቁርአን አንቀጾቹ አስባብ ያመላክታል፡፡ ተገዶም ይሁን ወዶ ወደ እስልምና የገባው ሕዝብ የመጽሐፉን ሰዎች /አይሁዶችንና ክርስቲያኖቹን/ ስለ መጽሐፋቸው በጠየቀ ቁጥር የነቢዩ ሙሐመድ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እየተቃረነ እንዳለ ያስተውሉ ነበር፡፡ ስለ እምነታቸው ግራ መጋባት ውስጥ ወድቀዋል፡፡ በዚህ ወቅት ነቢዩ ሙሐመድ የመጽሐፉ ሰዎችን አስተምህሮ እንዳይክዱ ቁርአናቸው ሊፈራርስና የመጽሐፉ ሰዎች ያሉት እውነት ሊሆን ነው፤ እንዳይቀበሉት ነብይነታቸውን በአንዴው ከእጃቸው ሊወጣ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጉድ የሚያወጣቸውን መናገር ነበረባቸውና እንዲህ አሉ፡-

> ሐዲስ ሚሽካት አል-ሙሳቢህ ቅጽ 1፣ ቁ 68[80]
> ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 9፣ ቁ 7362
> ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 9፣ ቁ 7542
> የመጽሐፉ ሰዎች ተውራቱን በሂብሩ ቋንቋ እያነበቡ፣ ለሙስሊሞቹ በአረብኛ ተርጉመው ያብራሩላቸው ነበር፤ የአላህ መልዕክተኛም ለሙስሊሞቹ እንዲህ አሉ፡- የመጽሐፉን ሰዎች አትመኗቸው፣ እመኗቸውም፤ ነገር ግን እንዲህ በሏቸው፤ በአላህ እናምናለን፣ በእኛም በተወረደው እናምናለን፣ በናንተም በተወረደው እናምናለን በሉ አሉ፡፡ አቡ ሁሬይራ የተናገረው

“አላህም” የሚከተለውን አንቀጽ በማውረድ ተባብሯቸዋል፡-

> **ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ) 3 ፡ 84**
>
> «በአላህ አመንን፡፡ በእኛ ላይ በተወረደውም (በቁርኣን)፣ በኢብራሂምና በኢስማዒልም፣ በኢስሓቅም፣ በያዕቆብም፣ በነገዶችም ላይ በተወረደው፤ ለሙሳና ለዒሳም ለነቢያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው (አመንን)፡፡

---

[79] *Asbāb al-Nuzūl, sura 3:83-84, page 37; Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, sura 3:83-84, page 64*

[80] *Al-Haj Maulana Fazlul Karim, Mishkat Ul Masabih, Darul-Ishat, Pakistan Karachi 1994, vol 1 page 141; Sahih al Bukhari vol 9, page 277 and 388*

ከእነርሱ መካከል አንድንም አንለይም፡፡ እኛ ለእርሱ ታዛዦች ነን» በል፡፡

قُلْ آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ عَلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَالنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ

ሌላው ለተመሳሳይ ሁኔታ የወረደው የቁርአን አንቀጽ ደግሞ እንዲህ ይላል[81]፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 136**

«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ፡፡

قُولُوا آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ

ሱባዎቹም በትብብር የገነቡትን "ሃይማኖት" ድንገት የእባይ ካብ ሊሆን እንደሆነ ሲመለከቱ ከገባበት ማጥ ውስጥ ለማውጣት ማለት የነበረባቸው ይህንኑ ሆነና እንዲህ አሉት፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 9፣ ቁ 7522-7523፣ ገጽ 377**

ኢበን አባስ እንዲህ አለ፤ እንዴት የመጽሐፉን ሰዎች ስለ መጽሐፋቸው ትጠይቃላችሁ? በእናንተ ዘንድ የአላህ መጽሐፍ (ቁርአን) ከአላህ ከወረዱት መጽሐፎች ሁሉ የቅርብ የሆነና ባልተበረዘ ሁኔታ በንጽህና ያለውን አታነቡምን? ኢክሪማ የተናገረው ሐዲስ ነው

ይህንን ሲሉ ግን ስለሚሉት እጃቸው ላይ ምንን አይነት መረጃ አልነበራቸውም፡፡ አላህም በሕዝቡ መካከል ስለ "ሃይማኖቱ" የተፈጠረው ግራ መጋባት፣ እርሱንም እንደ ነቢዩና ተከታዮቻቸው ያስደነገጠው ይመስላል፤ እናም የማስፈራሪያ መልእክቶችን ማኽጎድጎድ፣ ሙስሊሞች ከመጽሐፉ ሰዎች ጋር የነበራቸውን የዝምድና እና የወዳጅነት የግንኙነት መስመሮች መበጣጠስ ጀመረ፡፡ ይህንን ሲያደርግ እራሱን እየተቃረነ፣ ቁርአኑንም እርስ በእርሱ እያጋጨና በማንነቱ ላይ

---

[81] *Asbāb al-Nuzūl, sura 2: 135-136, page 9; Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, sura 2:135-136 p 23*

በርካታ ጥያቄ የሚያስነሱበትን ነገሮች እየፈጸመ እንዳለ ያስተዋለ አይመስልም፡፡ እስኪ አንብቡት፡-

**ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ) 3 ፡ 100**

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ መጽሐፉን ከተሰጡት ሰዎች ከፊሉን ብትታዘዙ ከእምነታችሁ በኋላ ከሓዲዎች አድርገው ይመልሱዋችኋል፡፡*[82]

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِن تُطِيعُوا فَرِيقًا مِّنَ الَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ يَرُدُّوكُم بَعْدَ إِيمَانِكُمْ كَافِرِينَ

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማዕድ ምዕራፍ) 5 ፡ 51**

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፡፡ አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም፡፡*

**ሱረቱል አል-ኒሳዕ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 138-139**

*መናፍቃንን ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት ያላቸው መኾኑን አብስራቸው፡፡ እነዚያ ከምእምናን ሌላ ከሓዲዎችን ወዳጆች አድርገው የሚይዙ እነሱ ዘንድ ልቅናን ይፈልጋሉን? ልቅናውም ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው፡፡*

**ሱረቱል አል-ኒሳዕ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 144-145**[83]

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከምእምናን ሌላ ከሓዲዎችን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ፤ ለአላህ በናንተ ላይ ግልጽ ማስረጃዎችን ልታደርጉ ትፈልጋላችሁን? መናፍቃን በእርግጥ ከእሳት በታችኛው አዘቅት ውስጥ ናቸው፡፡ ለእነሱም ረዳትን አታገኝላቸውም*

*ግንዛቤያችሁን ለማስፋት፡-*

- *ነቢዩ ሙሐመድ የመጽሐፉን ሰዎች እመኗቸውም፣ አትመኗቸውም ብለው ማለታቸው፣ ቀድሞ አላህ በቃሉ ምን እንዳላቸው ስለረሱ ይሆን? በመልአኩ ገብርኤል ከተማሩት ቁርአን ውስጥ ከሰፈረው ቃል ጋር ማን ያስታርቃቸው? ካመጡት ቃል ጋር እየተጣረሱስ የአላህ መልእክተኛ መባል ይገባቸዋል? ቃሉንስ የአላህ ቃል ነው ማለት ይቻላል?*

---

*82 Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, sura 3:100, page 66*
*83 Tafsir Ibn Kathire sura 4:144-146*

- ❖ አላህ እራሱን ከራሱ ጋር የሚያቃርነው ምን ነገር መጣ? እውን እንዲህ ዝብርቅርቅ ያለ መልእክት እየላከልን ያለው እርሱ ነውን? እየተከናወኑ የነበሩት ተግባራት ሁሉ የአላህን ባህሪ የሚመጥኑ ባለመሆናቸው ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሌላውን ለሌላ ጊዜ ላቆየው፡፡

ሕዝቡ ከመጽሐፉ ሰዎች ጋር በሚኖረው ቆይታ፣ የቀደሙት ነቢያትን ማንነትና የአገልግሎታቸውን ታሪክ እያወቀ ሲሄድ፣ የነቢዩ ሙሐመድን የተልእኮ ሂደትና ተላከልህ የተባለውን መልእክት አጠቃላይ ሁኔታ፣ ከቀደሙት ነቢያት ተልእኮ ጋር የማነጻጸር፣ የመገምገምና የመፈተሽ ሥራ ውስጥ ገብቷል፡፡ ከዛም አላህ ይሉት የነበረውን እንዲህ በማለት ገልጾታል፡-

**ሱረቱል አል-ረዕድ (የነጎድጓድ ምዕራፍ) 13 ፡ 7**

እነዚያም የካዱት በእርሱ ላይ ከጌታው ተዓምር ለምን አልተወረደለትም? ይላሉ፡፡ አንተ አስፈራሪ ብቻ ነህ፡፡ ለሕዝብም ሁሉ መሪ አላቸው፡፡

وَيَقُولُ الَّذِينَ كَفَرُوا لَوْلَا أُنزِلَ عَلَيْهِ آيَةٌ مِّن رَّبِّهِ ۗ إِنَّمَا أَنتَ مُنذِرٌ ۖ وَلِكُلِّ قَوْمٍ هَادٍ

**ሱረቱል አል-አንቢያ (የነቢያት ምዕራፍ) 21 ፡ 5**

«በእውነቱ (ቁርኣኑ) የሕልሞች ቅዠቶች ነው፡፡ ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ ቅኔን ገጣሚ ነው፡፡ የቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልክተኛ ከኾነ) በተዓምር ይምጣብን» አሉ፡፡[84]

بَلْ قَالُوا أَضْغَاثُ أَحْلَامٍ بَلِ افْتَرَاهُ بَلْ هُوَ شَاعِرٌ فَلْيَأْتِنَا بِآيَةٍ كَمَا أُرْسِلَ الْأَوَّلُونَ

**ሱረቱል አል-አንአም (የቤት እንስሳዎች ምዕራፍ) 6 ፡ 8**

«በእርሱም (በሙሐመድ) ላይ መልአክ አይወረድለትም ኖሮአልን?» አሉ፡፡ መልአክን ባወረድንም ኖሮ (ባያምኑ በጥፋታቸው) ነገሩ በተፈረደ ነበር፡፡ ከዚያም አይቆዩም ነበር፡፡

ምን ይህ ብቻ በግርምት እንዲህም ይሉ ነበር፡- "ለዚህ ሰው የሚወርድለት ስለሴትና ስለ ጋብቻ ብቻ ነው? ስለ ሌላ አይወርድለትም?"[85] ይሉም ነበር፡፡

---

[84] *Tafsir ibn Kathir sura 21:5*

[85] *Asbāb al-Nuzūl, sura 13:38, page 99*

ሞጋቾቹ በትኩረት ከመከታተላቸው የተነሳ እንዲህም ይሉ ነበር፡-

> "ሙሐመድ ተከታዮችን በአንድ ነገር ሲያዛና ከዛ ተመሳሳይ ሲከለክላቸው እንደገናም ከዛ ፍጹም ተቃራኒ በሆነው ሲያዛቸው አላያችሁትምን? አንድ ቀን አንድ ነገር ይናገርና በተከታዩ ቀን የተናገረውን ይሽረዋል፡፡ ይህ ቁርአን ሙሐመድ የፈጠራት የራሱ ንግግር ሌላ ምንም አይደለችም፡፡ ቁርአን እርስ በእርሱ የሚቃረን ንግግር ነው፡፡"[86]

ይህንን ያሉት ነቢዩ አሁን ያዘዙትን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሲሽሩ፣ የጠዋቱን ምሽት ላይ ሲሽሩ ስለተመለከቱ ነው፡፡ እናም ቁርአኑ የእርሱ ፈጠራ እንጂ የአላህ ቃል አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ደርሰዋል፡፡ አላህም ለማስተባበል አልሞከረም፤ ይልቁንም በአምላክ ውስጥ የሌለንና ይኖራል ተብሎ የማይታመንን ባህሪ ለራሱ በመስጠት፣ ይባሱን አመሰቃቀለው፡፡

**ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2 ፡ 106**

> ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ፣ ከርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ (ቻይ) መኾኑን አታውቅምን?

مَا نَنسَخْ مِنْ آيَةٍ أَوْ نُنسِهَا نَأْتِ بِخَيْرٍ مِّنْهَا أَوْ مِثْلِهَا ۗ أَلَمْ تَعْلَمْ أَنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

ውድ አንባቢዎቼ፤ በዚህ በአላህና በነቢዩ ሙሐመድ ንግግር ላይ ያልገባኝ፡-

- ❖ አምላክን ከዚህ በላቀ ማንነቱ ስለምናውቀው ይህ ከሃሊነት ሊሆን አይችልም፡፡ ይሁንና እንዴ ያወረደውን አንቀጽ ከመለወጥ ይልቅ፣ እንደሚለውጠው ስለሚያውቅ የተሻለውን ለዋጩን አንቀጽ ቅድሚያ ለምን አልሰጠም? አሳቡን በየጊዜው የሚያስለውጥ ምን ነገር ቢኖር ነው? መጀመሪያውኑ ምርጡን መስጠት አይሻልም ነበር? ይህ አንቀጽ የወረደበት ምክንያት ምን እንደሆነ ከላይ አንብባችሁታል፤ እርሱም የነቢዩን ማንነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡
- ❖ አንድን ነገር መርሳት፣ በሰዎች ባህሪ ውስጥ የማይፈለግና በሌሎች ዘንድ ጥሩ አመለካከት እንዳይኖር እንደሚያደርግ አላህ ያውቃል፡፡ ታዲያ ይህንን እያወቀ መጀመሪያ ላይ አንድ ራዕይ ሰጥቶ፣ በኋላ ማስረሳት ለምን አስፈለገ? ጥቅሙስ ምንድን ነው? የአንቀጹ የመውረዱ ሌላው

86 *Asbāb al-Nuzūl, sura 2:106, page 6*

ምክንያት የነቢዩ ዝንጉነት እንደሆነ ይታወቃል፤[87] የሚበልጠው እንዲቀድም ለምን አላደረገም? መልእክተኛውን ዝንጉ ማድረግ ለምን አስፈለገው? ደግሞ ነቢዩ ስለእራሳቸው "እኔ እንደ እናንተው ሰው ስለሆንኩ እረሳለሁ፤ ስለዚህ ስረሳ እናንተ አስታውሱኝ" ካሉት ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 2፤ ቁጥር 1274፣ 1283

… ነገር ግን እኔ ሰብአዊ ፍጡር ነኝ፤ እናንተ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ፤ በረሳሁ ጊዜ አስታውሱኝ…….፡፡[88]

ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 106 ያለው አሳብ አምላካዊ እንዳልሆነ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው የሚከተለው ሐዲስ ነው፡-

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁ 2655 ገጽ 475

ሱናን አቡ ዳውድ ቅጽ 4፣ ቁ 3970 ገጽ 362

በምሽት አንድ ሰው ለጸሎት/ለሰላት/ ተነስቶ ሳለ ድምጹን ከፍ አድርጎ ቁርአን ይቀራ ነበር፡፡ ሲነጋም የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፤ የአላህ ምህረት በእርሱ ላይ ይሁን፤ ባለፈው ምሽት የረሳሁትን የቁርአኑን አንቀጽ አስታወሰኝ አሉ፡፡ አይሻ የተናገረችው ሐዲስ ነው

- የመጀመሪያውን አስወግዶ፣ የእርሱን ተመሳሳይ መስጠት፣ በቃሉ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ያኔም ሆነ አሁን ላይ ያለው ሕዝብ ምን እንዲማር ፈልጎ ይሆን፣ አላህ ይህንን ያደረገው? ይህስ በምን ሒሳብ ከሀሊነት /ሁሉን ቻይነት/ ሊባል ይችላል? በዚህ አድራጎቱ ሰው ከሀሊናቱን /ሁሉን ቻይነቱን/ ይገነዘባል፣ ወይስ በሚያየው ልዩ ባህሪ ግራ ይጋባል?
- ውድ አንባቢ፤ አላህ በእንዲህ አይነት ባህሪ የተሞላ አምላክ ነው፣ ብለው ያምናሉ?
- ከእነዚህ ሐዲሶች መርሳት የራሳቸው የነቢዩ ችግር እንጂ አላህ ስለሚያስረሳቸው የሚረሱ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡ ለመርሳት ሰው መሆን በራሱ በቂ ነው፤ ምክንያቱም "እኔም እንደናንተው ሰው ነኝ ስለዚህ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ" ያሉትን አንረሳም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሱራ 2 ፡ 106 ከአላህ ዘንድ የወረደ ቃል ሊሆን እንዴት ይችላል?

---

[87] *Jalal Al-Din Al-Mahaly & Jalal Al-Din As-Suyuti, Tafsir Al-Jalalayn, translated by Muhammad Anis Gad Khalil, Dar Al-Manarah, Egypt 2010,vol 1, page 61*

[88] *Sahih Muslim vol 2, page 65-69*

የቀደሙት ነቢያት በመልእክቶቻቸውና በትምህርታቸው ይህንን ቁርአን ላይ የሰፈረውን የአላህን ተለዋዋጭ ባህሪ አላሳዩንም፡፡ ነቢይነታቸው በእስልምና ሳይቀር የተመሰከረላቸው የቀደሙት ነቢያት ሁሉም አምላካቸውን ያገለግሉት የነበረው በሙሴ በኩል ለተሰጠው ሕግ ራሳቸውን እያስገዙ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ አላህ አንድም ጊዜ መጀመሪያ ላይ በሙሴ የተሰጠውን የሚሽር ቃል በሌሎቹ ነቢያት በኩል አልላከም፡፡ በራሱ በሙሴ በኩልም አንድም ጊዜ ተሻሻሪ መልእክቶችን አላወረደም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ላይ እንዳደረገው ሙሴን አንድም ጊዜ ቃሉን እንዲረሳ አድርጎት አያውቅም፡፡ ሌሎችንም ቢሆን ዝንጉ አድርጓቸው አያውቅም ነበር፤ ይልቁንም ከአፉ ስለሚዎጣ ቃሉ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

**ትንቢተ ኢሳይያስ** 55 ፡ 11

> ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፣ የምሻውን ያደርጋል፣ የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።

ስለ ዝንጉዎችም፡-

**መጽሐፈ ኢዮብ** 13 ፡ 16

> ዝንጉ ሰው በፊቱ አይገባምና …………

**መጽሐፈ ኢዮብ** 27 ፡ 8

> እግዚአብሄር ባጠፋውና ነፍሱን በለየ ጊዜ፤
>
> የዝንጉ ሰው ተስፋው ምንድር ነው?

ታዲያ ቃሉን የሚረሳ ሰው፣ በአላህ ፊት መሆን ካልቻለ፣ ለሰዎች መመሪያ ይሆን ዘንድ ለራሱ መልእክተኛ የሰጠውን መልእክት በማስረሳት፣ አገልጋዩ ከፊቱ እንዲርቅ እንዴት ያደርጋል? ይህ ሊታመን የሚችል አይሆንም፡፡ የቀደሙት ነቢያት የሕይወት መመሪያ፣ እንደሚከተለው እየተባለ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የኖረ የሕግ መጽሐፍ ነው፡-

**መጽሐፈ ኢያሱ** ፡ 1 ፡ 7-8

> ነገር ግን ጽና÷ እጅግ በርታ፣ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ÷ አድርገውም፣ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ÷ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፣ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል፣ ይከናወንልሃልም።

**መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ** 2 ፡ 2-3

እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ፤ በርታ ሰውም ሁን፣ የምታደርገውንና የምትሄድበትን ሁሉ ታከናውን ዘንድ፥ በሙሴ ሕግ እንደ ተጻፈ ሥርዓቱንና ትእዛዛቱን፣ ፍርዱንና ምስክሩንም ትጠብቅ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ፥ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ።

**የማቴዎስ መንጌል** 5 ፡ 17-19

እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር፣ ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር፣ ማንም ሰው፣ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን፣ የሚያስተምርም ማንም ቢሆን፣ እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።

## 1.3. ለመጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ፣ በአላህ፣ በነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳትና በሙፈሲሮች የተሰጠ ምስክርነት

ነገሩ አበው "በአንድ እራስ ሁለት ምላስ" እንደሚሉት እንደሚሆንባችሁ አምናለሁ፡፡ ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ፣ ነቢዩ ሙሐመድ፣ ሱሃባዎቹና አላህ ምን ያህል ራሳቸውን በመቃረን የሚናገሩ እንደሆኑ ታስተውሉ ዘንድ ስለቀደሙት መጽሐፍት አለመበረዝ፣ አለመሰረዝና አለመደለዝ ብሎም አለመጥፋት ከተናገሩት ሁለቱን ላስነብባችሁ፡፡ በመጀመሪያ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ የምስክርነት ቃል የሰጠው በሱረቱል አል-ማኢዳህ 5 ፡ 41-48 አላህ ነበር፡፡ ያንንም ነቢዩ ሙሐመድ “ተቀብለው” አስተላልፈውት አሁን ባለው ቁርአን ውስጥ ቃሉ ይገኛል፡፡ በቅድሚያ ይህ የቁርአን ክፍል ሊወርድ የቻለበትን ምክንያት በሚያትተው የነቢዩ ሐዲስ ልጀምር፡-

**ሱና ማሊክ ሙዋታ** 41 ፡ 1
**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ** 4፣ 4437 **ገጽ** 474-475
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ** 8፣ 82 ፡ 809

በዝሙት ኀጢአት የተከሰሱ አይሁድና አይሁዳዊት ወደ አላህ መልእክተኛ አቀረቡ፡፡ ነቢዩም እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው፤ በእናንተ በተወረደው በተውራቱ ለእንዲህ አይነት ኀጢአት የተወሰነው ቅጣት ምንድን ነው? ሲመልሱም ቀሳውስቶቻችን ቅጣቱን የገለጹልን ጥላሸት ፊታቸውን በመቀባት ማዋረድ ነው፤ አሉ፡፡ አብዱላ ኢብን ሰላማ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ፤ ተውራቱን እንዲያመጡ ንገሯቸው" አለ፤ ተውራቱም

መጣ፡፡ አንድ አይሁዳዊ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል በሚያዘው የአምላክ ቃል ላይ በእጁ በመሸፈን ምን እንደሚል ከፊት ያለውንና ከኋላ የሚከተለውን ማንበብ ጀመረ፡፡ ያኔ ኢብን ሰላማ አይሁዳዊውን እጅህን አንሳ አለው፡፡ በድንጋይ በመወገር መቅጣት የሚያዘው የአላህ ቃል ከእጁ በታች እንደነበር አየ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ሁለቱ ኀጢአተኞች በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዙ፤ ተወገሩም፡፡ ኢብን ኡመርም በተጨማሪ ሁለቱ ሲወገሩ፣ እንኪሞቱ አይሁዳዊው አይሁዳዊቷን ሲሸፍናት አይቻለሁ አለ፡፡ ኢብን ኡመር የተናገረው ሐዲስ

ሐዲሱ ላይ በግልጽ እንደሚታየው፣ በዛን ጊዜ በአይሁዳውያኑ እጅ የነበረው የተውራቱ መጽሐፍ የተበረዘ እንደነበር የሚጠቁም ምንም ነገር የለም፡፡ ነቢዩም በተከሳሾቹ ላይ እርምጃው እንዲወሰድባቸው ሲያደርጉ፣ ተውራቱ ላይ በሰፈረው የሕጉ ቃል መሰረት እንጂ፣ ለርሳቸው በወረደው በቁርአኑ ቃል አልነበረም፡፡ የጠየቁት የእናንተ ምን ይላል? በማለት ነበር፡፡ የሚገርመው አመንዝራን በድንጋይ በመውገር መቅጣትን የሚያዝ አንድም አንቀጽ በቁርአን ውስጥ አለመኖሩ ነው፡፡ አይሻ በዘገበችው ሐዲስ አንቀጹ የተጻፈበት የፓፓይረስ ቅጠል በፍየል እንደተበላ፣ ከዚህ የተነሳ ቁርአኑ ውስጥ እንዳልተጻፈ በመናገር የቁርአኑን በአላህ አለመጠበቅ አሳይታናለች፡፡

በፍርድ ሂደቱ ወቅት በአካባቢው የነበሩት አይሁዳውያን የሰጡት ምላሽም ሆነ፣ አንባቢው አይሁዳዊ በእጁ መሸፈኑ፣ ፍርዱ በተውራቱ መሰረት የሚፈጸም ከሆነ፣ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ስለሚያውቅ ነበር፡፡ ይህም ሰዎቹን ለማዳን ያደረገው እንጂ፣ የቀደሙትን መጽሐፍት መበረዝ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በእውነት ድርጊቱ ተፈጽሞ ከሆነ፣ ያኔ የተነበበው የተውራቱ ክፍል በዚህ ዘመን በእጃችን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለምንም ለውጥ ይገኛል፡፡ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቢመለከቱ ይደርሱበታል፡-

> ኦሪት ዘሌዋውያን 20 ፡ 10-21፣ ኦሪት ዘኍልቁ 5 ፡ 27፣ ኦሪት ዘዳግም 22 ፡ 21-27

**በሳሂህ ሙስሊም ቅጽ** 4፣ **ቁ** 4440 ላይ ነቢዩ ይህንኑ ችግር ለመፍረድ በተሰየሙበት ወቅት፣ ወዲያው ከአላህ የወረደላቸው የቁርአን ክፍል **ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማዕድ ምዕራፍ) 5 ፡ 41-48** እንደነበር ተዘግቧል፡፡ በዚህ የቁርአን ክፍል አላህ የተናገረው የቀደሙት መጻሕፍት ብርሃን ያለባቸው፣ ያልተበረዙ፣ ያልተደለዙ እውነተኛና ትክክለኛ መሆናቸው ብቻ ነው፡፡ አልፎ ተርፎም ሦስቱ ማለትም እስልምና፣ ክርስትና እና አይሁድ ተብለው በሃይማኖት መለያየታቸው እንኳን ቢሆን ከአላህ የተወሰነ እንደሆነ፣ እርሱም ትእዛዙን ማን በአግባብ እያከበረ እንዳለ ሊፈትናቸው እንደ ለያያቸው ይናገራል፡፡ እስኪ ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማዕድ ምዐእራፍ) 5 ፡ 43-48**

እነርሱም ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትኾን እንዴት ያስፈርዱሃል! ከዚያም ከዚህ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ! እነዚያም በፍጹም ምእምናን አይደሉም፡፡ እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በርሱም ላይ መስካሪዎች በኾኑት (ይፈርዳሉ)፡፡ ሰዎችንም አትፍሩ፡፡ ፍሩኝም፡፡ በአንቀጾቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ፡፡ አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሓዲዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ በእነርሱም ላይ በውስጧ «ነፍስ በነፍስ ዓይንም በዓይን አፍንጫም በአፍንጫ ጆሮም በጆሮ ጥርስም በጥርስ (ይያዛል)፡፡» ቁስሎችንም ማመሳሰል አለባቸው ማለትን ጻፍን፡፡ በእርሱም የመጸወተ (የማረ) ሰው እርሱ ለርሱ (ለሥራው ኃጢአት) ማስተሰሪያ ነው፡፡ አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው፤ እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው፡፡ በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡ የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፡፡ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው፡፡ ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን፡፡ በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ፡፡ እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል፡፡ ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፡፡ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)፡፡ በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡ በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል፡፡

እነዚህ አንቀጾች ተሽረዋል እንዳይባል አይሻ እንዲህ በማለት ተናግራለች፡-

አል-ሀኪም ሲናገር ጁባይር ቢን ኑፋይር እንዲህ አለ፡- አንዴ ሐጅ ፈጸምኩና አይሻን ጎበኘኋት፤ እርሷም እንዲህ አለችኝ፡- ጁባይር ሆይ አል-ማኢዳህን አንብበሃል ወይንም በቃልህ ሸምድደኸዋል? እኔም አዎን ስል መለስኩላት፡፡ እርሷም እርሱ በመጨረሻ የወረደ ሱራ ነው፡፡ ስለዚህ በእርሱ ውስጥ የምታገኘው የተፈቀደ ማንኛውም ነገር እንደተፈቀደ አስብ፤ ደግሞም ያልተፈቀደ ሆኖ የምታገኘው ማንኛውም ነገር እንዳልተፈቀደ አስብ አለችኝ አለ፡፡[89]

---

[89] *Tafsir Ibn Kathir sura 5,* "*The Virtues of Surah Al-Ma'idah;*"

አላህ ሊጠብቀው ቃል እንደገባለት የሚነገርለት ቁርአን በምን አይነት ምስቅልቅሎሽ ውስጥ እንደኖረ በትንሹም ቢሆን ተመልክተናል፡፡ በአንጻሩ ሰዎች እንዲጠብቁት በኃላፊነት የተሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እስካሁን ድረስ ያለምንም እንከን ተጠብቆ ይገኛል፡፡ እናም ቁርአንን ለማንገስ በሁለቱ መጽሐፍት መካከል ስለ መበረዝና አለመበረዝ፣ በአላህ ስለ መጠበቅና አለመጠበቅ ሱረቱል አል-ሒጅር (የሒጅር ምዕራፍ) 15 ፡ 9ን የመጠቃቀስ አመለካከት ፈጽሞ ትክክል አይደለም፡፡ የሁለቱ ሱራዎች /የሱረቱል አል-ማኢዳና የሱረቱል አል-ሒጅር/ የአወራረድ ደረጃም ቢሆን፣ ዳኢዎቹ የሚሉትን እንዲሉ በር ከፋች አይሆንም፡፡ ሱረቱል አል-ሒጅር 54ኛ ደረጃ ላይ በመካ የወረደ ሱራ ሲሆን ሱረቱል አል-ማኢዳ ደግሞ 114ኛ ደረጃ ላይ በመዲና የወረደ ሱራ ነው፡፡ ስለዚህ የዘመኑ ዳኢዎች በዚህ ጊዜ ላይ ተነስተው፣ አላህ ለሌሎቹ መጽሐፍት ሰውን ጠባቂ አድርጌአለሁ፤ ቁርአኑን ደግሞ እኔው እራሴው እጠብቀዋለሁ ብሏል ሊሉን በፍጹም አይችሉም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ የምስክርነት ቃል ከሰጡ የታወቁ የእስልምና ምሁራን መካከል የሦስቱን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንዱ ውሃብ ቢን ሙናቢህ ነው፤ ከኢብን ኢሻቅም የቀደመ የእስልምና ታሪክ ጸሐፊ ነበር፡፡ ስለቀደሙት መጻሕፍት ይዘት ተበርዘዋል አልተበረዙም ለሚለው ኢማም ኢብን ካቲር ለሱረቱል አሊ-ኢምራን 3 ፡ 78 ማብራሪያቸውን ሲሰጡ እንዲህ ብለው ነበር፡-

> ውሃብ ቢን ሙናቢህ እንዲህ አለ፡- "ተውራቱና ኢንጅሉ ከእነርሱ አንድም ፊደል ሳይጠፋ አላህ እነርሱን ባወረደበት ሁኔታ እስካሁን ድረስ አሉ፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ በመጨመርና የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ራሳቸው በጻፏቸው መጽሐፍት ሌሎቹን እንዲታመኑ በማድረግ ወደ ስህተት ይመራሉ፡፡ የአላህ መጽሐፍት እስከ አሁን ድረስ ተጠብቀዋል፤ ሊለወጡም አይችሉም፡፡"[90]

ምን ይህ ብቻ፤ ኢማም ኢብን ካሲር የኢብን አባስንም አመለካከት ጨምረው አስፍረዋል፡፡ አደራችሁን ኢብን አባስን በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዳትሉት፤ ዝም ብላችሁ አድምጡት፡-

> ኢብን አባስ እንዲህ አለ፡- "… ከአላህ ፍጥረት ቃላትን ከአላህ መጽሐፍት ሊያስወግድ (ሊያወጣ) የሚችል አንድም የለም፡፡ እነርሱ የለወጡትና የበረዙት ግልጽ ትርጉሙን ነው፡፡"[91]

---

[90] *Ibn Kathir, Tafsir Ibn Kathir Juz' 3 (Part 3), by Muhammad Saed Abdul-Rahman, MSA Publication Limited, 2009, vol 3 page 303-304*

[91] *Ibid page 303*

የዘመናችን ዳኢዎች ትልቁ ችግር እንዲህ እየሆነ እያዩ ከእነዚህ ቀደምት ኢማሞች ይልቅ እኛ እናውቃለን ማለታቸው ነው፡፡ ለማንኛውም እንደምመለስበት ተናግሬ በይደር ወዳቆየሁት አሳብ ልመለስ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የመበረዝ ሒደት ወይንም ዓይነት የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ፣ በቁርአን ጥቅሶች አስደግፌው በአምስት ነጥቦች ዘርዝረዋል፡፡ እስኪ ነጥቦቹን አንድ በአንድ እንመልከት፡፡ በእርግጥ እንደሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ተበረዘ ለማለት የወረዱ አንቀጾች ይሆኑ? የወረዱበት ምክንያትስ ያንን የሚያሳይ ነውን? አብረን እንመልከት፡-

## 1. የመጀመሪያው ክስ እውነትን ከውሸት መቀላቀልና እውነትን መደበቅ

በእነዚህ ሁለት ክሶች ሥር የተጠቀሱ አንቀጾች **ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 40-42፣ 146፣ ሱረቱል አሊ-ኢምራን 3 ፡ 71** ናቸው፡፡[92] የትኛውን እውነት ነው ከውሸት ጋር የተቀላቀለው? የተቀላቀሉትን እውነትና ውሸት አውጥተው ሊያሳዩን ይችሉ ይሆን? የተደበቀው እውነትስ የትኛው ነው የት ነው የተደመቀውስ? የተደበቀ ከሆነ የሆነ ቦታ ተሰወረ እንጂ አልጠፋም ማለት ነው፤ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ተበረዘ ለማለት ያስችላል? የእነዚህ የቁርአን አንቀጾች የኋላ ታሪክ ምን ያሳያል?

ኢብን ካሲር ሱራ 2 ፡ 42 ሲያብራሩ የተለያዩ ሱሃባዎች "እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ" ስለሚለው ሲያብራሩ የተለያዩ ሱሃባዎች የተናገሩትን አስደግፌው አቅርበዋል፡፡ ኢማም አል ቁርጡቢም የሰጡት ማብራሪያ ፍጹም ተመሳሳይ ነው[93]፡፡ "ቃታዳህ የተባለው ሰው እንዲህ ብሎ ነበር፡- "እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ" ማለት አይሁዳዊነትን እና ክርስትናን ከእስልምና ጋር አትቀላቅሉ ማለት ነው፡፡ "እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ" እስልምና የአላህ ሃይማኖት መሆኑን፣ ክርስትና እና አይሁዳዊነት ደግሞ ከአላህ ያልሆኑ ፈጠራዎች መሆናቸውን የምታውቁ ስትሆኑ ማለት ነው፤ አል ሃሰን አል ባስሪም ተመሳሳዩን አስተላልፏል" በማለት ጽፈዋል፡፡[94]

ኢብን አባስም ይህንን አንቀጽ ሲያብራራ፡- ""እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ" ማለት የሙሐመድን መገለጫ ከሐሰተኛው ክርስቶስ መገለጫ ጋር አትቀላቅሉ ማለት ነው" ብሏል፡፡[95]

**አያቶላ መሃዲ ፑያ እና ሰ.ቨ. ሚር አህመድ አሊ** በጋራ ባዘጋጁት ተፍሲር ስለ ሱራ 2 ፡ 40-42 እንዲህ ብለዋል፡- "አይሁዳውያኑን አላህ በቃል ኪዳናቸው

---

92 ሳዲቅ መሃመድ አህመድ፣ ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ)፣ ዲሬ ኢታሚ፣ 2003 ዓም፣ ገጽ 19-20

93 *TAFSIR AL-QURTUBI, vol 1 page 234*

94 *Tafsir Ibn Kathir sura 2 : 42*

95 *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, page 9*

ታማኞች እንዲሆኑ ያሳስባቸዋል፤ በዘዳ 26 ፡ 16-17፣ በዘዳ 18 ፡ 5፣ በዘዳ 18 ፡ 18-19 ነቢይ እንደሚያስነሳላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር፤ ይህም የተገባላቸው ቃል ነቢዩ ሙሐመድን ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ይህ የኪዳን ቃል ኢሳ ነው ይላሉ ሆኖም ኢሳ ራሱ በዮሐ 14 ፡ 16፣ 26 እና በዮሐ 16 ፡ 7-14 ባለው ላይ ስለእርሱ እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ ከቁርአን ቀድሞ በወረደው መጽሐፍ ተገልጾ እያለ ክርስቲያኖች ሌላ ቅርጽ ይሰጡና ይደብቁት ነበር፡፡ በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን የነበሩ ብዙ የአይሁድ መምህራንም በመጽሐፉ የሰፈረውን እውነተኛውን ቃል ያውቁ ነበር፤"[96] በማለት አብራርተዋል፡፡

ሌላው አንቀጽ ሱራ 3 ፡ 71 ነው፡፡ ስለዚህ አንቀጽም የተሰጡ ማብራሪያዎች አሉ፡፡ ማብራሪያው ከአንቀጽ 69 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 73 ባለው ይጠቃለላል፡፡ ኢብን አባስ ለዚህ አንቀጽ ለሱራ 2 ፡ 42 የሰጠውን ማብራሪያ በቀጥታ ተጠቅሞበታል፤ "የሐሰተኛው ክርስቶስን ባህሪ ከነቢዩ ሙሐመድ ባሕሪ ጋር ለምን ትቀላቅላላችሁ"[97] በማለት፡፡

አንቆቹ የወረዱበትን ምክንያት የዘገቡ አካላትም እንደገለጹት አንቀጾቹ የወረዱት ሙስሊሞችን ከእስልምና ለመመለስ የተደረጉ ጥረቶችን ለመመከት እንደሆነ ይገራሉ፡፡[98]

ውድ አንባቢ በዚህ ሁሉ ማብራሪያ ውስጥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መበረዝ የሚያሳይ ፍንጭ አንድም የለም፡፡ አያቱላዎቹ የጠቀሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ነቢዩ ሙሐመድ የተነገሩ አይደሉም፡፡ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ የሚናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ አንድም የለም፡፡ ነገር ግን አሉ ብለው ጠቃቅሰዋል፤ የጠቀሷቸው ደግሞ አብዛኛው ሙስሊም ዳኢዎች የሚጠቃቅሷቸውን ጥቅሶችን ነው፡፡ እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘና ስለ ነቢዩ ሙሐመድ የሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተደበቁ ከነበር ይናገራሉ ብለው የጠቀሷቸውን ጥቅሶች ማግኘት ባልቻሉም ነበር፡፡ ቁርአን ያለው ያልተደረገውን ስለሆነ ሊገያጇቸው ችለዋል፤ ይህ የሚያሳየው ቁርአን እየዋሸ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ የአላህ ቃል አይደለም ወደሚለው ሊመራን ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያም አላህ እንዲህ አይሳሳትምና፡፡

"የነቢዩ ሙሐመድን ባሕሪ ከሐሰተኛው ክርስቶስ ባህሪ ጋር መቀላቀል" የተባለውም ቢሆን በንግግር ደረጃ ሊሆን ቢችል እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የተካሔደ ስረዛና ድለዛ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ልድገመውና ስለ ነቢዩ ሙሐመድ የተነገረ አንድም ጥቅስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ ሊሰርዙ ሊደልዙ ሊቀላቅሉ አይችሉም፡፡ ክርስቲያኖቹ ከሐሰተኛው ክርስቶስ ጋር

---

[96] *Ayatullah Agha Mehdi Pooya and S.V. Mir Ahmed Ali, Tafsir Sura 1-5,translated by Mirza M. Pooya, ISLAMICMOBILITY.COM, 2013, page 76-78*

[97] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās page 62*

[98] *Asbāb al-Nuzūl page 35*

በመያያዝ ተናግረው ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ለሐሰተኛው ክርስቶስና ለአሠራሩ የሚሰጠውን መገለጫ በነቢዩ ሙሐመድና በቁርአኑ ውስጥ በማየታቸው ነው፡፡ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላልና፡-

**1ኛ የዮሐንስ መልእክት 4 ፡ 1-3**

> ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።

በዚህ መለኮታዊ ቃል መለኪያ መሠረት ነቢዩን ከሐሰተኛው ክርስቶስ ጋር ቢያነጻጽሩ ተሳሳቱ ሊባሉ አይገባም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛው ክርስቶስን የገለጠበት መግለጫ አሁን ላይ እስልምና የአላህ ሃይማኖት ቁርአንም የአላህ ቃል ስለመሆኑ ያረጋገጠበት ተአምር እንደሆነ የእስልምና ምሑራን በኩራት እየተናገሩት ያለ ጉዳይ ነው፤[99]

ዳኢ ሳዲቅ ሙሐመድ፣ ላለመደናገር ማመሳከር በተሰኘው መጽሐፉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ከውሸት ጋር ስለመቀላቀሉ "በሱረቱል ጣሃ (የጣሃ ምዕራፍ) 20 ፡ 87-90 ሳምራዊው የተባለው ሰው የሠራውን ሥራ፣ አሮን ሠራው ተብሎ በኦሪት ዘፀአት መጠቀሱ ነው፡፡"[100] በማለት ገልጿል፡፡ ይህ አባባሉ የቁርአንን መለኮታዊ ቃልነት ጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ችግር እንዳለበት አመላካች ሊሆን አይችልም፡፡ ሱረቱል ጣሃ (የጣሃ ምዕራፍ) 20 ፡ 87-90 ጠቅሶ "ይኸው መረጃዬ" ማለት ቁርአን በመቼታዊና በታሪካዊ ስህተቶች የተሞላ መጽሐፍ ለመሆኑ ቁልጭ ያለ መረጃ በእጅ እንደማቀበል ይቆጠራል፡፡

## 2. ሁለተኛው ክስ እውነትን መሸሽግ የሚል ነው

የመጽሐፍ ቅዱስ ሌላው ችግር ተብሎ የተጠቀሰው እውነትን መሸሸግ የሚል ነው፡፡ በዚህ ክስ ሥር ለማገናዘቢያ የተጠቀሰው የቁርአን ጥቅስ ሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 15 ነው፡፡

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 15**

---

[99] *http://www.universalunity.org/6.html*

[100] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 20

*የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ፤ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ፣ ከብዙውም የሚተው ሲሆን መልእክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ፡፡ ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡*

يَا أَهْلَ الْكِتَابِ قَدْ جَاءَكُمْ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمْ كَثِيرًا مِّمَّا كُنتُمْ تُخْفُونَ مِنَ الْكِتَابِ وَيَعْفُو عَن كَثِيرٍ ۚ قَدْ جَاءَكُم مِّنَ اللَّهِ نُورٌ وَكِتَابٌ مُّبِينٌ

- *በዚህ አንቀጽ ቁርአን የመጽሐፉ ሰዎች ከሚሸሽጉት ብዙውን የሚገልጽ ደግሞም ብዙውን የሚተው ተብሎለታል፤ ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሁን የሌለ የመጽሐፉ ሰዎች የሸሸጉት ነገር ግን ቁርአን የገለጸው ብዙው ምንድን ነው?*
- *ለዚህ የቁርአን አያት መውረድ ሰበቡ /ምክንያቱ/ ምንድን ነበር? የቀደሙት የእስልምና ምሑራን ስለዚህ ጉዳይ ምን ብለዋል?*
- *ሁኔታው እውን መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መሆኑን ያመለክታል? በዚህስ የማን ታማኝነት ይሆን ጎልቶ የሚታየው?*

*ይህንን አንቀጽ ለመጽሐፍ ቅዱስ መበረዝ እንደማሳያ የሚጠቅሱ ዳኢዎች ራሳቸውን እንደ ሊቅ ሊቆጥሩ አይገባም፡፡ ይልቁንም አላዋቂ መሆናቸውን፤ መጽሐፍቶቻቸውን ያወቁ ቢመስላቸውም ለእነርሱ እንግዳዎች መሆናቸውን፤ እንደ መሪዎቻቸው አፍቃሪ እስልምና እንጂ፣ ለእውነትና ለአላህ ፍቅር የሌላቸው መሆናቸውን ሊያውቁ ይገባል፡፡ እምነታቸውን እንዴት እንደሚጠብቁም ጭምር አያውቁም፤ እውነተኞችም አይደሉም፡፡ ለማንኛውም የእስልምና ከፍተኛ ምሁራንና ምስክሮች ስለዚህ አንቀጽ የሰጡትን ማብራሪያ እስኪ እንመልከት፡-*

***ኢብን አባስ** እንዲህ ብሏል፡- "(የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! መልክተኛችን) ማለት ሙሐመድ (በእርግጥ መጣላችሁ፣ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ) ማለት ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ባህሪና መገለጫ እና **<u>አመንዝራን በድንጋይ ስለመውገር</u>** የተላለፉትን ሕጋዊ መመሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን የምትሸሽጉትን ማለት ነው"[101] በማለት አብራርቷል፡፡*

***ኢማም ኢብን ካሲርም**፡- "አል-ሃኪም በራሱ የሐዲስ ስብስብ እንዳሰፈረው ኢብን አባስ እንዲህ አለ፡- "አመንዝራን ወገሮ በመግደል የሚክድ ሰው ሳያውቀው በቁርአን ይክዳል፤ አላህ እንዲህ እንዳለው፡- 'የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ፤ ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ፣ መልእክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ' እናም **<u>አመንዝራን በድንጋይ</u>***

[101] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās page 112-113*

**ወግሮ መግደል** ከሚደብቋቸው ነገሮች መካከል ነው፡፡” አል-ሐኪምም ይህ ትክክለኛ የሆነ የሐዲስ ሰንሰለት ነው እነርሱ ግን አልጻፉትም አለ፡፡"[102]

**ሁለቱ ጃላላይኖችም** ለአንቀጹ እንዲህ የሚል ማብራሪያ ሠጥተዋል፡- "(የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ) ማለት አይሁድና ክርስቲያኖች፣ (መልእክተኛችን በእርግጥ መጣላችሁ) ማለት ሙሐመድ፣ (ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ) ማለት ከቶራውና ከወንጌሉ ማለትም **አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደልና** ስለነቢዩ ሙሐመድ መገለጫ የተጻፈውን፡፡"[103]

**ኢማም ሰይድ ቁጡብ እና ሰይድ ሁሴይን ናስር** የተባሉት የእስልምና ምሑራን አንቀጹ የሚናገረው **አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል** የሚያዘውን የቶራውን ቃል ስለመደበቃቸው ነው የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡[104] የብዙ የእስልምና ምሑራን ማብራሪያ ተመሳሳይ በመሆኑ እዚህ ላይ ይብቃኝ፡፡

ውድ አንባቢ፤ እንደምትመለከቱት የመጽሐፉ ሰዎች እውነትን ሸሸጋችሁ የተባሉት አመንዝራን በድንጋይ እስከ ሞት ድረስ በመውገር መቅጣትን የሚያዘውን ሕግና ስለ ነቢዩ ሙሐመድ በተውራቱና በኢንጅሉ የሚገልጸውን እንደሆነ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በጥያቄ ልጀምረው፡-

- በመጀመሪያ ተሸሸጉ ማለት ምን ማለት ነው? አውጥታችሁ ጣላችሁት ማለት ካልሆነ፣ አንቀጹ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመበረዙ እንደማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ እንዴት ቻለ? ደግሞስ እነዚህ ሸሸጋችኋቸው የተባሉት ህግጋት አሁን ባለው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሉምን?
- መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለነቢዩ ሙሐመድ መምጣት የሚገልጽ ትንቢታዊ መልእክት እንደሌለ እናውቃለን፡፡ ሆኖም እናንተ ኸረ አለ ብላችሁ እንደምትጠቅሱም ጭምር የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ የሸሸጉት ከነበር፤ ታዲያ አለ ብላችሁ ጥቅስ የምትጠቅሱት ለምንድን ነው? እንዴት አገኛችሁትና ልታስረዱን ትሞክራላችሁ? እናንተ ጥቅሶቹ መኖራቸውን እርግጠኞች ከሆናችሁ አላህ ሸሸጋችሁት ብሎ በሐሰት ንጹህ ሰው እንዴት ይከሳል? ሙፈሲሮቹና ሱሃባዎቹስ የመጽሐፉን ሰዎች ሸሸጋችሁ ብለው ለምን ይወነጅላሉ?
- አላህና እናንተ ተቃርናችኋል፤ አላህ ተሸሽጓል ይላል፣ እናንተ አለ ትላላችሁ፤ ከእናንተና ከአላህ ሁሉን አዋቂው ማነው? ማን ይታመን? እናንተ ወይስ አላህ?

---

[102] Imam Ibn kathir, tafsir Ibn kathir(Abridged), translated by Safi ur-Rahman Al Mubarak Puri, Dar us salam, Riyadh 2003, vol 3 page 131-132

[103] Tafsīr al-Jalālayn, page 116

[104] Sayyid Qutb, In the Shade of Quran, vol 4 page 51; Seyyed Hossein Nasr, The study Quran : a new translation and commentary, HarperCollins Publishers, UK 2015, page 492

- ቁርአን የተሸሸገውን ገላጭ መጽሐፍ ከሆነ የመጽሐፉ ሰዎች የሸሸጉት የተባለው አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ በመግደል መቅጣትን የሚያዘው የሕግ አንቀጽ ቁርአን ውስጥ አለን?
- ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ አላህ ለምን ይዋሻል? ነቢዩ ሙሐመድ በአምንዝራውና በአመንዝራው ላይ ፍርድ ሲያስተላልፉ የቁርአን አንቀጽ ወርዶላቸው እንዳልነበር ያውቃል፡፡ ፍርዱ የተላለፈባቸው ተውራቱ ላይ በሰፈረው ፍርድ መሠረት ሆኖ ሳለ የምትሸሽጉትን ገላጭ እንዴት ይልላ?

የአላህን ማንነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ጥቅስ ይዞ የማያውቁትን ለመተቸት መነሳት አዋቂ ነን ባይ አላዋቂ መሆንን ያሳያል፡፡ ማስተዋል ብትችሉና እውነተኞች ብትሆኑ፣ ከዚህ አንቀጽ ውስጥ ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን፣ ነቢዩ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ አለመሆናቸውን በግልጽ መመልከት ትችሉ ነበር፡፡ ምክንያቱም ተሸሸገ የተባለው የተውራቱ መልእክት ያኔም ሆነ አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነበር፣ አለ፤ በአንጻሩ ገላጭ እና ተጠባባቂ በተባለው ቁርአን ውስጥ ግን የለም፡፡ ታዲያ ምኑን ይሆን የሚገልጠው? ምናልባት ክርክር አይታክቴ አይጠፋምና አንቀጹ ወርዶ ነበር ትሉ ይሆናል፡፡ አዎን! ወርዶ ነበር የሚሉ የሐዲስ ዘገባዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ እና ወርዶ ከነበር የት ገባ? ተብሎ ሲጠየቅ አኢሻህ ለዚህ መልስ አላት፡-

**ሱና ኢብን ማጃህ ቅጽ 3፣ 1944**

አኢሻህ እንዲህ አለች፡- "<u>**የአመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደልና አዋቂን አስር ጊዜ ጡት የማጥባት አንቀጽ ወርዶ**</u> ነበር፤ ወረቀቱም እኔ ዘንድ ከትራሴ ሥር ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛ በሞቱ ጊዜ በሞታቸው ተጨንቀን ሳለን በግ ገብታ በላችው፡፡" ሐዲሱ ሃሳን ነው[105]

ይህንን ሐዲስ ቀደም ብዬ አላህ ቁርአኑን በቃሉ መሠረት እንዳልጠበቀው ለማሳየት መጥቀሴን ታስታውሳላችሁ፡፡ አላህ የመጽሐፉ ሰዎችን "የምትሸሽጉትን" በማለት በሐሰት ከሶ፣ ገላጭ የሆነውን ቁርአንን ላኩላችሁ ብሏል፡፡ ይህንን ቢልም በላከው ቁርአን ላይ ሰፍሮ የሚገኘው "እነዚያ የሸሸጉት" እርሱ "ገለጥኩት" ያለው አንቀጽ ሳይሆን፣ የዚያ ፍጹም ተቃራኒ የሆነ ሕግ ነው፡፡ እርስ እረሱ የሚጋጭ ቃል ማለት ነው፡፡ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ቃል ደግሞ ከሌላ ምንጭ የተቀዳ ቢሆን እንጂ የአላህ ቃል ሊሆን አይችልም፡፡ እውን አላህ ሁለት ምላስ አለው? ወይንስ ሲናገር አያስተውልም? እንግዲህ አመንዝራ በድንጋይ ተወግራ ትገደል፣ ወይስ ንስሐ እስክትገባ ወይም ሞት ከአላህ ዘንድ እስኪመጣ ድረስ በቤት ውስጥ ትታሸግ? ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ በአንቀጾቹ እንዲህ በማለት አዟል፡-

---

105 *Sunan ibn-Majah vol 3, page 113-114*

**ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 15-16**

እነዚያም <u>ከሴቶቻችሁ</u> መጥፎን ሥራ (ዝሙትን) የሚሠሩ፣ በእነርሱ ላይ ከናንተ አራትን (ወንዶች) አስመስክሩባቸው፡፡ ቢመሰክሩም <u>**ሞት እስከሚደርስባቸው ወይም አላህ ለእነርሱ መንገድን እስከሚያደርግ ድረስ በቤቶች ውስጥ ያዙዋቸው (ጠብቁዋቸው)፡፡**</u> እነዚያንም <u>**ከእናንተ ውስጥ (ዝሙትን) የሚሠሩዋትን አሰቃዩዋቸው፡፡**</u> ቢጸጸቱና ሥራቸውንም ቢያሳምሩ ከእነርሱ ተገቱ (አታሰቃዩዋቸው)፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡

وَاللَّاتِي يَأْتِينَ الْفَاحِشَةَ مِن نِّسَائِكُمْ فَاسْتَشْهِدُوا عَلَيْهِنَّ أَرْبَعَةً مِّنكُمْ ۖ فَإِن شَهِدُوا فَأَمْسِكُوهُنَّ فِي الْبُيُوتِ حَتَّىٰ يَتَوَفَّاهُنَّ الْمَوْتُ أَوْ يَجْعَلَ اللَّهُ لَهُنَّ سَبِيلًا وَاللَّذَانِ يَأْتِيَانِهَا مِنكُمْ فَآذُوهُمَا ۖ فَإِن تَابَا وَأَصْلَحَا فَأَعْرِضُوا عَنْهُمَا ۗ إِنَّ اللَّهَ كَانَ تَوَّابًا رَّحِيمًا

- ውድ አንባቢ፤ መቼም ሴት ብቻዋን አታመነዝር፤ ታዲያ ስለ ወንዱ አመንዝራ አንዳች ያላለው ለምን ይሆን? ሴቷ ብቻ እንድትሰቃይ እንዴት ይበይንባታል? አዛኝነቱን ምኑ ነው የሚያሳይለት? አላህ አዛኝ ወይስ ፍርደ ገምድል አድሎኛ ዳኛ? አያችሁ ቁርአን እና ነቢዩ ሙሐመድ አላህ ኢ-ፍትሐዊ አምላክ ነው እያሉን ነው፡፡ እርሱስ ፍትሃዊ አምላክ ነው፤ ነቢዩ ሙሐመድ እና ቁርአን ግን ከአላህ ዘንድ የተላኩ ላለመሆናቸው ጎልተው ከተጻፉት ማስረጃዎች መካከል ይህ አንዱ ነው፡፡

ለወንዱ እስከ ምን እንደሚፈቅድለት ላስነብባችሁ፤ ምን ማለት እንደሆነ ማብራሪያውን እመለስበታለሁ፡-

**ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 24**

ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ፣ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡ ከዚሃችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ፣ ጥብቆች ኾናችሁ፣ ዝሙተኞች ሳትኾኑ <u>**በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ**</u>፡፡ ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች፣ መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን ስጧቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡

ውድ አንባቢ፤ የመጽሐፉ ሰዎች ምንም አላህና ነቢዩ ሙሐመድ በሐሰት እውነትን ሸሸጋችሁ ቢሏቸውም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክሱ ሐሰት ነው ይላል፡፡ ያኔም ሆነ ዛሬ የአላህን ፍትሐዊ አምላክነት እያረጋገጠ ተሸሸገ የተባለውን የሕግ ቃል እስከአሁን ድረስ በገጾቹ ጠብቆ ይዞ ይገኛል፡፡ ያም ሕግ ሴትና ወንድ ያለ

አድሎ እኩል ይዳኛሉ ከሚለው አምላካዊ የፍትህ አቋሙ ዝንፍ አላለም፡፡ ይህንንም ቅዱስ ቃሉን መጽሐፍ ቅዱሳችሁን እንዴ ከፈት አድርጉና የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ አረጋግጡ እላለሁ፡-

**ኦሪት ዘሌዋውያን** 20 ፡ 10-21
**ኦሪት ዘኁልቁ** 5 ፡ 27
**ኦሪት ዘዳግም** 22 ፡ 21-27

## 3. ሦስተኛው ክስ ቃላትን ከስፍራው መቀየርና ምላስን ማጣመም

በእነዚህ ሁለት የክስ ርእሶች የተጠቀሱ ቁርአናዊ አንቀጾች **ሱረቱል አሊ-ኢምራን** 3 ፡ 78፣ **ሱረቱል አል-በቀራ** 2 ፡ 75፣ **ሱረቱል አል-ማኢዳ** 5 ፡ 41 **እና ሱረቱል አል-ኒሳእ** 4 ፡ 46 ናቸው፡፡

የቁርአን ሙፈሲሮች (ተርጓሚዎች) ምን እንዳሉ እንመልከት፡-

የቁርአን አንቀጾች የወረዱበትን ምክንያት የሚዘግበው አስባብ አል-ኑዙል ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 75፣ ሱራ 3 ፡ 78፣ ሱራ 5 ፡ 41 የወረዱት ካብ ኢብን አል-አሽራፍ፣ ራፊ፣ ኪናናህ ኢብን አቡ-ሃቃይቅና ሁያይ ኢብን አህታብ የተባሉ የመዲና አይሁዶች በነቢዩ ሙሐመድ መገለጫ እና አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ መግደልን በሚያዘው የተውራቱ ህግ ላይ ስለፈጸሙት ለውጥ እንደሆነ ያትታል፡፡[106]

ሁለቱ ጀላላዎችም ለሱራ 2 ፡ 75፣ 3 ፡ 78፣ 4 ፡46 እና ለሱራ 5፡ 41 በሰጡት ማብራሪያ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰ የመዲና አይሁዶች በተውራቱ የነቢዩ ሙሐመድን መገለጫ ማጣመማቸውና ራኢና የሚል በአረብኛና በአራማይስጥ የተለያየ ትርጉም ያለውን ቃል በመናገር ያፌዙ እንደነበር፣ እንዲሁም አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል የሚያዘውን ደግሞ በሃይባር የሚኖሩና ቤይኑ ቁሬይዛ የተባሉት አይሁዶች ስለመደበቃቸው ይናገራል በማለት ማብራሪያቸውን ጽፈዋል፡፡[107]

ተፍሲር ኢብን አባስ ላይም ለሱራ ለሱራ 2 ፡ 75 አላህ ለሙሐመድ አይሁዶች በእርሱ ሊያምኑ እንደማይችሉ እንስገነዘበው፤ ለሱራ 3 ፡ 78 አሁንም ከላይ ስማቸው የተጠቀሰ የመድና አይሁዶች በተውራቱ ውስጥ የሐሰተኛው ክርስቶስን መገለጫ በማንበብ ተራው ሕዝብ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳለ እንዲያስቡ ያደርጉ እንደነበር፤ ለሱራ 4 ፡ 46 ደግሞ በስም የተጠቀሱ አይሁዳውያን የነቢዩን

---

[106] *Asbāb al-Nuzūl page 3,36,66*
[107] *Tafsīr al-Jalālayn page 14, 92-93, 119*

የባህሪ መገለጫ እንደለወጡና ከዛም በሳቸው ላይ በማፌዝ ራኢና ይሉ እንደነበር፤ እንዲሁም ለሱራ 5 ፡ 41 የቤይኑ ቁሬይዛ አይሁዶች አመንዝራን በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል የሚያዘውን የተውራቱን ሕግ ስለመደበቃቸው እንደሚገልጹ አብራርተዋል፡፡[108]

ኢብን ካሲርም፣ ሰይድ ሁሴን ናስር እንዲሁም ሌሎቹ ተመሳሳይ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡[109]

አሁንም እነዚህ አንቀጾች የቀደሙት መጽሐፍት ተበርዘዋል ብሎ ለማለት መግቢያ ቀዳዳ የሚሰጡ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ይህ አባባል በበርካታ ምክንያቶች ውድቅ ይሆናል፤ ከእነዚያም ጥቂቶቹን ማንሳት እችላሁ፡-

1) ይህ ሁሉ እየተባለ ያለው በቁርአንና በነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት መረጃ ላይ ተመስርቶ ነው፤ ሌላ ተጨማሪ የተጨበጠ ማሰረጃ አልቀረበም፡፡ ስለዚህ የቁርአንን መለኮታዊ ቃልነትና የነቢዩን የአላህ መልእክተኝነት በማስረጃ ማሳየት ስለማይችሉ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡
2) የተከሰሱት አካላት አይሁዳዊ ናቸው፤ የተከሰሱበት ክስ ደግሞ እራሱ የእግዚአብሔር ቃል እንዳያደርጉት ያዘዛቸውን ስለሆነ ለቃሉ ያላቸው አክብሮት ትልቅ በመሆኑ ይህንን ደፍረው ሊያደርጉት አይችሉም፡-

ኦሪት ዘዳግም 4 ፡ 1-2

አሁንም፥ እስራኤል ሆይ፥ እንድታደርጉአቸው በሕይወትም እንድትኖሩ፥ የአባቶቻችሁም አምላክ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱ፥ የማስተምራችሁን ሥርዓትና ፍርድ ስሙ። እኔ ያዘዝኋችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኋችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም፥ ከእርሱም አታጎድሉም።

ኦሪት ዘዳግም 12 ፡ 32

እኔ የማዝዝህን ነገር ሁሉ ታደርገው ዘንድ ጠብቅ፣ ምንም በእርሱ ላይ አትጨምር፥ ከእርሱም ምንም አታጕድል።

መጽሐፈ ምሳሌ 30 ፡ 5-6

የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ተፈትናለች፣ እርሱ ለሚታመኑት ጋሻ ነው። እንዳይዘልፍህ፥ ሐሰተኛም እንዳትሆን በቃሉ አንዳች አትጨምር።

---

[108] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās page 13,63,90,117*

[109] *The study Quran, sura 2:75, 3:78, 4:46, 5:41; tafsir Ibn kathir(Abridged), vol 1 page267-269, vol 2 page 195-196, vol 2 page 477, vol 3 page 177-183*

3) እነዚህ ሰዎች ይህንን የአምላካቸውን ቃል ጥሰው፣ ይህንን አደረጉ እንኳን ቢባል ነቢዩንም ሆነ አላህን እንዲሁም በየዘመናቱ የኖሩትን ዳኢዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ብሎ ለማለት አያስችላቸውም፡፡ ምክንያቱም አሁን በእጃችን ላለው መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ቅጅዎች የግሪክና የእብራይስጥ የመጀመሪያ ቅጅ መጽሐፍ ቅዱሳት እንጂ፣ የመዲና አይሁዶች እጅ የነበሩት መጻህፍት አይደሉም፡፡ ለዚህ ነው የኢስላም ታሪክ ጸሐፊው ኢማም ዋሃብ ሙናቢሃ "የአላህ ቃላት (መጽሐፍ ቅዱስ) አላህ ሲያወርዳቸው በነበረበት በቀደመው ሁኔታቸው አሉ፤ አልጠፉም፡፡" ማለት የቻሉት፡፡ ሙፈሲር ኢብን አቢ ሃቲም የውሃብ ሙናቢሃን አሳብ ለመሞገት ሞክረዋል፤ ሲሞግቱ እደተበረዘ ለማሳየት የሞከሩት በትርጉም ሥራዎች ላይ እንጂ በዋናው ቅጅ ላይ አይደለም አለመሆኑን ኢብን ካሲር አስነብበውናል፡፡ ኢብን ውሃብ ሙናቢሃ እየተናገረ ያለው እርሱ እጅ ስላለው መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ አለ "አዎን የአላህ መጻህፍት ተጠብቀዋል ፈጽሞ ሊለወጡ አይችሉም፡፡"[110] ይህ የሚያሳየው ያልተበረዘ ንጹህ መጽሐፍ ቅዱስ ከነቢዩ መሞት በኋላም ቢሆን ሙስሊሞች እጅ ይገኝ እንደነበር ነው፡፡

4) ሌላው እነዚህ አራት የመዲና አይሁዶች የአላህን የአላህ፣ "ራሳቸው የጻፉት" የተባለውን መጽሐፍ ደግሞ የራሳቸው እንደሆነ መግለጻቸው መጽሐፍ ቅዱስ ከእነርሱ ሥራ ተለይቶ ይኖር የነበር መሆኑን ያመላክታል፡፡ በዚህም ለአላህ ቃል የነበራቸውን አክብሮት አሳይተዋል፡፡ ይህም ከደፋሮቹ ከእነ ከሊፋ ኡስማን ይልቅ እውነተኞችና ታማኞች፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡ ስለዚህ ሊደነቁ እንጂ ሊከሰሱ አይገባም፡፡ ቁርአን ግን እንዲህ የኖረ መጽሐፍ አለመሆኑን ቀደም ብለን ተነመልክተናል፡፡ የተበረዘ፣ የተደለዘ፣ አብዛኛው ክፍሉ የጠፋ፣ ለትውልድ ያለምንም እንከን መተላለፍ ያልቻለ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህም መለኮታዊ ቃል ያለመሆን ማሳያ ነው፡፡

ተጨማሪ አንድ ምስክር ስጨምር ከሊፋ ኡመር ከተናገረው ላስነብባችሁ፡-

**ሐዲስ ሚሽካት አል-ሙሳቢህ ቅጽ** 1፣ 1 ፡ 93

ኡመር እንዲህ አለ፤ እጅግ ታላቅ ደስታን የፈጠረብንን ትምህርት ከአይሁዳውያኑ ሰማን፤ ታዲያ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰነውን ብንጽፈው እርስዎ ምን ይላሉ?...[111]

**ሐዲስ ሚሽካት አል-ሙሳቢህ ቅጽ** 1፣ 1 ፡ 121, 20w

---

110 *tafsir Ibn kathir(Abridged),vol 2 page 196*

111 *Al Hadis Mishkat Ul-Masabih, vol 1 page 153*

> ኡመር የተውራቱን ቅጅ በእጁ ይዞ ወደ አላህ መልእክተኛ መጣና እንዲህ አለ፤ የአላህ መልእክተኛ ሆይ ይህ የተውራቱ ቅጅ ነው፡፡ ምንም አልመለሱለትም፡፡ እርሱ ግን ማንበብ ጀመረ፤ በኋላ የነቢዩ ፊት ላይ መናደዳቸው መታየት ጀመረ፡፡ አቡበከርም ለነዛ ከምታዝንላቸው ለራስህ እዘን፤ የአላህ መልእክተኛ ፊት እንዴት እንደሆነ አታይምን? አለው፡፡ ኡመርም የነቢዩን ፊት ተመለከተና ከአላህና ከአላህ መልእክተኛ ቁጣ በአላህ እጠበቃለሁ፤ እኛ በአላህ ጌትነት በኢስላም ሃይማኖትና በሙሐመድ መልእክተኛነት ደስተኞች ነን አለ፡፡ ከዚያም በኋላ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- ሙሴ ወደ አንተ ቢመጣ፣ እርሱን ብትከተልና እኔን ብትተወኝ፣ በእውነት ከቀጥተኛው መንገድ ከመመራት ወደ ጥመት ትሄዳለህ፡፡ ሙሴ በህይወት ቢኖርና የእኔን ነቢይ መሆን ቢደርሰው እርሱ እኔን የከተል ነበር፡፡[112]

እነዚህ ሁለት ሐዲሶች ስለ ሁለቱ መጽሐፍትና በነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኝነት ላይ በርካታ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያደርጋሉ፤ አሁን ለጊዜው እርሱን እናቆየው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ደግሞ እንከን አልባና፣ የከሊፋውን ልብ መማረክ የቻሉ መልእክቶችን እንደያዙ፣ በመጽሐፍ መልክም ተጠርዘው ይገኙ እንደነበር ይታያል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ በከሊፋ ኡመር ሁኔታ እንዲያ የተበሳጩት የተበረዘ መጽሐፍ ይዞ ስላዩት አይደለም፡፡ እርሳቸውን ከመከተል ተመልሶ ወደ ይሁዲነት የገባ ስለመሰላቸው እንጂ፡፡ ገሃዱ እውነታ እንዲህ ሆኖ እያለ ከሊፋ ኡመርና መሰሎቹ ተገልብጠው የቀደሙት መጽሐፍት ተበርዘዋል ብለው ቢያወሩ፣ ደግሞም እንዲህ አሉ ተብሎ ቢወራላቸው፣ ማን ሊሰማቸው ይችላል? ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9 ጠቅሶ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል ስለ አላህ ጥበቃ ማውራት፣ ነቢዩ ሙሐመድና ቁርአን፣ በዚህም ላይ የተመሰረተው እስልምና ሃይማኖት፣ ከአላህ ዘንድ ለሰው ልጆች የተላኩ የደህንነት መንገዶች አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ በዘመኑ ሁሉ፣ በእስልምና ሃይላትም ሆነ፣ በሌሎች መኖሩን በማይፈልጉት ሃይሎች ብዙ ስደት ቢደርስበትም፣ እራሱ የቃሉ ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ ጠብቆት እንደኖረ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የእስልምና የመረጃ ምንጮቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃልም አንብባችኋል፡፡ በዘለአለም አምላክ ጥበቃ ሥር የሚኖር በመሆኑ የሰው እጅ በፊትም ይሁን አሁን በዚህ ዘመን ሲኖር፣ የመጀመሪያ ይዘቱን አላስለቀቀውም፡፡ በውስጡ በተቃዋሚዎቹ ስህተት የተባሉ የመጽሐፉ ክፍሎች፣ የመጽሐፉን ባሕሪ ሳያውቅ በገረፍታ ለሚያያቸው ስህተት በመምሰል ለመተቸት በር የከፈቱ አንዳንድ ሁኔታዎች እየታዩበት እንኳን፣ ከትችት እንዲድን የእርዳታ ሥራ የሠራ፣ እንደ ከሊፋ ኡስማን የደፈረ ደፋር የለም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቃሚ የሆነ ሰው፣ በጥናቱ ወቅት ለሚገጥሙት ችግር መሳይ ነገሮች፣ መፍትሔውን ለማግኘት ይችል ዘንድ፣

---

[112] *Al Hadis Mishkat Ul-Masabih, vol 1 page 175*

እንዲያመሳክርባቸው የቀድሞዎቹ ቅጅዎች ዛሬ ድረስ ተጠብቀውለት ይገኛሉ፡፡ እግዚአብሔር እራሱ ጠባቂው ስለሆነ ማንም አላቃጠላቸውም፡፡ ለዚህ ነው በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የግርጌ ማስታወሻ ላይ ስለ አንዱ አሳብ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ እዚህኛው ቅጅ ላይ እንዲህ ይላል፣ ከዛኛው ደግሞ እንዲህ ይላል፣ እየተባለ ዋናው አሳብ ሳይነካ መግለጫ የሚሰጠው፡፡ ይህም አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ የታማኝነቱ ልዩ መገለጫ ነው፡፡ ቁርአን ግን ለዚህ የታደለ መጽሐፍ አይደለም ፡፡ ማብራሪያና ማመሳከሪያ ሲጠየቅ የሚያቀርበው የአላህ ቃል የሆነውን፣ ነቢዩም ተጠባባቂና አረጋጋጩ ነኝ ያሉለትን የቀደሙትን መጻሕፍት ትክክለኛ የሆነውን አላህ ያውቃል/Allah knows the best/ በሚል መንፈሳዊ መሳይ የሽፋን ንግግር በመናገር፣ ምንም ሊታረቁ የማይችሉ፣ የራሳቸውን ከነፍሳቸው የወጣ ማላምት የሚናገሩ ኡለማዎችን አተረጓጎም ነው፡፡

በዚህ ዘመን ያሉት የእስልምና ዳኢዎች በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መጻሕፍትን በመያዝ የሚያነሱት የመበረዝ ክስስ እንዴት ይታያል? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል፡፡ ቀደም ብሎ እንዳነበባችሁት ሙፈሲር ኢብን አቢ ሃቲምም ውሃብ ሙናቢሃን ለመሞገት የሚከሩት ዋና ቅጅዎች ላይ ሳይሆን ትርጉሞችን በተመለከተ ነው፡፡ የዘመኑ ዳኢዎችም የነቢዩ ሙሐመድን ሱሃባዎች ንግግር ደጋፊ አድርገው መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል በማለት ጩኸት የሚያሰሙት በእነዚህ በተለያዩ ቋንቋዎች በተዘጋጁት መጽሐፍ ቅዱሳት ላይ ነው፡፡ ብረዛን በተመለከተ የሁለታችን ጥያቄዎች መሠረት የተለያዩ ናቸው፡፡ የእኛ በቁርአን መበረዝ ዙሪያ ያለን ጥያቄ የተመሠረተው በትርጉሞች ላይ ሳይሆን ከነቢዩ ሙሐመድ አፍ እየወጣ ተጻፈ ስለ ተባለለት የመጀመሪያው ቅጂ ላይ ነው፡፡ የእነርሱ ደግሞ መሠረቱ የትርጉም ሥራዎች ላይ ነው፡፡ በበኩር ቋንቋ ለተጻፉት ግን የእስልምና ምሑራኑ ላለመበረዛቸው የሰጡትን ምስክርነት አንብባችሁታል፡፡ ስለዚህ በእነዚህ የመከራከሪያ መሠረቶች መካከል ግዙፍ ልዩነት አለ፡፡ እንግዲህ ለእንዲህ አይነት ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ከፈለጉ መልሱ ያለው ጓዳቸው ውስጥ ነው፡፡ መልሱን የሚሻ ሰው በ147 ቋንቋዎች በሙሉና በከፊል ተተርጉመው ወደተሰራጩት የቁርአን ትርጉም መጻሕፍት መሄድና እነርሱን መፈተሽ የተሻለ ነው፡፡ የትርጉም ቅዱሳት መጽሐፍት የብረዛ ማሳያ መሆን ከቻሉ አሁንም በዚህ በኩል ቁርአን የተበረዘ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላሉ፡-

- ***የመጀመሪያው በአገራችን ቋንቋ የተዘጋጁት***

የእኛ አገር የእስልምናው ዳኢዎች የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ከ1879 ዓም እስከ 2000 ዓም ድረስ የታተሙትን የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች በማነጻጸር በመካከላቸው ያሉትን የቃላት ልዩነቶች፣ የተለወጡ ቃላትን፣ ቋንቋ ባለው የማደግ ባህሪ ምክንያት በአንዱ ሲኖር በሌላው አለመኖራቸውን እንዲሁም የትየባ ችግሮችን በማንሳት ተበርዟል ይሉናል፡፡ እንግዲያውስ ቁርአንም ኢትዮጵያ ውስጥ ተበርዟል፡፡ ብረዛውን የፈጸመው ደግሞ ነጃሽ አሳታሚ ድርጅት ነው፡፡ ይህ አሳታሚ በአማርኛ ቁርአንን ከሦስት ላላነሰ ጊዜ አሳትሟል፡፡

የመጀመሪያው በሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ እና በሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳቢቅ የተተረጎመው፣ ሁለተኛው በ1997 የታተመው ባለ 11 ጥራዙ ቁርአን፣ ሦስተኛው በኋላ የታተመው ባለ 4 ጥራዙ ቁርአን፡፡ አንድ የቁርአን አንቀጽ እንውሰድና ብረዛው ምን እንደሚመስል እንመልከት፡-

**ሱረቱል አል-ሐጅ (የሐጅ ምዕራፍ) 22 ፡ 52**

ከመልክተኛና ከነቢይም ከአንተ በፊት አንድንም አላክንም ባነበበ (እና ዝም ባለ) ጊዜ ሰይጣን በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚጥል ቢሆን እንጅ፡፡ ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ያስወግዳል፡፡ ከዚያም አላህ አንቀጾቹን ያጠነክራል፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡

ይህ በ1961 ዓም በነሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ ተተርጉሞ በ1993 ዓም በድጋሚ በታተመው የአማርኛ ቁርአን ሰፍሮ የሚገኝ ነው፡፡ ሳውዲ አረብያ ውስጥ በአራት ጥራዞች ተዘጋጅቶ ለአማርኛ ተናጋሪዎች በነጻ በመሰራጨት ላይ ባለው የአማርኛ ቁርአን ይኸው አንቀጽ እንዲህ ሰፍሯል፡-

ሱረቱል አል-ሐጅ (የሐጅ ምዕራፍ) 22 ፡ 52

ከአንተ በፊት አንድም ነቢይ ወይም መልእክተኛ አላክንም አንዳች ነገር በተመኘ ጊዜ ሰይጣን በምኞቱ ላይ (ከንቱ ነገር) የጣለበት ቢሆን እንጂ፡፡ ግና አላህ ሰይጣን የጣለውን (ከንቱ ነገር) ያስወግዳል፡፡ ከዚያም መልእክቱን (ይበልጥ) ያጸናል፡፡ አላህ አዋቂ ጥበበኛም ነው፡፡

በተለያየ ወቅት በተለያዩ ሰዎች ተዘጋጅተው በአንድ አሳታሚ በታተሙት በእነዚህ ሁለት የቁርአን የትርጉም ሥራዎች የሚታየውን ልዩነት እንመልከት

| የ1961 እና የ1993 እትም | አዲሱ ባለ አራት ጥራዝ እትም |
|---|---|
| ባነበበና ዝም ባለ ጊዜ የሚለው | አንዳች በተመኘ ጊዜ በሚል ተተክቷል |
| በንባቡ ላይ (ማጥመሚያን ቃል) የሚለው | በምኞቱ ላይ (ከንቱ ነገር) በሚል ተተክቷል |
| ወዲያውም የሚለው ወጥቶ | ግን የሚል ቃል ገብቷል |
| አላህ የሚለው ሲኖር | አላህ የሚለው ወጥቶ ከንቱ ነገር የሚል ሐረግ ተጨምሯል፡፡ |
| አንቀጾቹን ያጠነክራል የሚለው ወጥቶ | ምልእክቱን ይበልጥ ያጸናል በሚል ተተክቷል |

የትኛው ነው ትክክለኛ የአላህ ቃል? እንግዲህ ውድ አንባቢ፣ ይህ በሁለቱ ወቅቶች በታተሙት በአማርኛ የቁርአን ትርጉም መጽሐፍት መካከል የሚታየው

ይህንን የመሰለ ዝብርቅርቆሽ ምን ይባላል? ይህን የመሰለው ሥራቸው ትክክለኛ ነው፣ ከተባለ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሱን ሥራዎች መበረዝ የሚያሰኘው ምን ይሆን? ይህስ ማንነታቸውን ቁልጭ አድርጎ አያሳይም ትላላችሁ?

ከዚህም ተጨማሪ መጽሐፍቶቹን አግኝታችሁ መቅድሞቻቸውን ብታነቡ፣ ላለመደናገር ማመሳከር በማለት ብዙ የተናገሩት የአገራችን የተጨበጨበላቸው ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቻቸው፣ እንዲሁም አህመድ ዲዳትና ደቀ መዝሙሮቹ እነ ዶ/ር ዛኪር ምን ያክል ለራሳቸው፣ ለአንባቢዎቻቸው፣ ለመላው ሙስሊም ማሕበረሰብና ከሁሉም በላይ ለአምላካቸው ታማኞች አለመሆናቸውን ትመለከታላችሁ፡፡ እንዲሁም በጽንፈኝነትና በጭፍን ጥላቻ ተሞልተው፣ የማያውቁትን በማውራት ላይ እንዳሉ ማስተዋል ትችላላችሁ፡፡

## ❖ ሁለተኛው የተለያዩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሳት፡-

ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ብሎ ለማውራት እንደ መረጃ የሚጠቅሱት በተለያየ ዘመን የተተረጎሙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የተመለሱ መጽሐፍ ቅዱሳትን በመያዝ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ከዚህ በፊት እንዳልኩት ቁርአንን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተከሰተውን የትርጉም ችግር ካለማወቅ፣ ወይንም እያወቁ አላውቅም በማለት የሚሰሟቸውን ግራ ለማጋባት የሚያደርጉት ሰይጣናዊ ተግባር ነው፡፡ እስኪ አንድ የቁርአን ወስደን ቁርአንን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ በተረጎሙ የተለያዩ ሰዎች አንቀጹን እንዴት እንደ ተተረጎመ፣ እንዲሁም የቁርአን መዝገበ ቃላት ለአንዳንድ ቃላት የሰጠውን ትርጓሜ አያይዤ ላስነብባችሁ፡-

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 73**

**እነዚያ «አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጅ ሌላ የለም፡፡ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል፡፡**

لَّقَدْ كَفَرَ الَّذِينَ قَالُوا إِنَّ اللَّهَ ثَالِثُ ثَلَاثَةٍ ۘ وَمَا مِنْ إِلَٰهٍ إِلَّا إِلَٰهٌ وَاحِدٌ ۚ وَإِن لَّمْ يَنتَهُوا عَمَّا يَقُولُونَ لَيَمَسَّنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا مِنْهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ

**ቁርአንን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሲመልሱት አንቀጹን እንዲህ ብለውለታል፡-**

In the Shad of the quran, sayyid Qutb, vol 4, Sura 5:73

**Unbelievers** indeed are those who say: "**God is the third of a trinity**." Of certain, there is no god save the One God. Unless they desist from so saying, grievous suffering will surely befall those of them who are unbelievers.

By Shaykh Mufti Taqi Usmani Sura 5:73

Surely, **disbelievers** are those who say, .**Allah** is the third of the **three**. while there is no god but One God. If they do not desist from what they say, a painful punishment shall certainly befall such disbelievers.

By Khazain —ul-Hidayat Sura 5: 73

Undoubtedly, those are **infidels** who say, 'Allah is third of the **three Gods**, and there is no God but the one God. And if they desist not from what they say, then a painful torment shall surely befall to those who will die as infidels

Yusuf Ali Sura 5: 73

They do **blaspheme** who say: **Allah** is one of in a **Trinity**: for there is no god except One Allah. If they desist not from their word (of blasphemy), verily a grievous penalty will befall the blasphemers among them

By Muhammad Asad Sura 5:73

Indeed, the **truth deny** they who say, "Behold, **God** is the third of a **trinity**" - seeing that there is no deity whatever save the One God. And unless they desist from this their assertion, grievous suffering is bound to befall such of them as are bent on denying the truth.

By Grand Shaykh, Professor Hasan Qurbullah Sura 5: 73

indeed those who say: `**Allah** is the third of the **Trinity**` became **unbelievers**. There is but one God. If they do not desist in what they say, a painful punishment will afflict those of them that disbelieve.

**እንደምትመለከቱት፡- ካፉራ (كَفَرَ) የሚለው ቃል፡- Unbelievers, disbelievers, infidels, blaspheme, truth deny ተብሎ ተተርጉሟል፡፡**

**አላህ (اللَّهَ) የሚለው፡- Allah, God ተብሎ ተጽፎ እንመለከታለን**

**ሳሊሱ ሳላሳቲን (ثَالِثُ ثَلَاثَةٍ) የሚለውን፡-** third of the three Gods, third of a trinity, one of in a Trinity, third of the three Gods, third of the three **እየተባለ ተመልሷል፡፡ በዚህ የተርጓሚዎቹ ዓይን የክርስትናን ስነመለኮታዊ አስተመህሮ ላይ እንደሆነ ይታያል፡፡ ሙፈሲሮች ከተናገሩት፡-**

ኢብን አባስ፡- "(እነዚያ «አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ) ማለት ይሄ የማርቆሳውያን ንግግር ነው፤ እነርሱ አብ፤ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በማለት ይናገራሉ..."[113]

ኢብን ካሲርም ይህንኑ የኢብን አባስን አሳብ ደግመውታል[114]፤ ሁለቱ ጀላላዎች ደግሞ አሁንም የክርስቲያን ክፍሎችን እንደሚመለከት ተናግረዋል፡፡[115] ይሁንና ይህ ሁሉ ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ቁልጭ አድርገው ከሚያሳዩት በርካታ የቁርአን አንቀጾች መካከል አንዱ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ ምን ሊሆኑ ይችሉ ይሆን?

እስኪ አሁን ደግሞ A Basic Dictionary of Islam የተሰኘው መዝገበ ለአንዳንድ ቃላት የሰጠውን ትርጉም እንመልከት፡-

> "ኩፍር (ካፋራ)፡- ማለት መደበቅ፣ አላህን አለመቀበል መቃወም ማለት ነው፤ አለማመን የማወጅ ተግባር ነው፡፡ አላማኝ የሆነ ሰው ካፊር ይባላል፡፡ በቁርአን ውስጥ ቃሉ የሚያመለክተው ጣኦት አምላኪወችን እና አምላክ የለም ባዮችን ነው፡፡ በመሰረቱ የቃሉ ትርጉም መሸፈን ወይንም መደበቅ ማለት ነው፡፡ ኩፍር እውነትን መካድ ነው፤ ወይም የአላህን ሕግ መከላከል ወይንም መጣስ ማለት ነው፡፡ ኩፍር ማለት ግልጽ የሆነ ክህደት እንጂ ግብዝ ማለት አይደለም፤ ግብዝ እርሱ/እርሷ በአንድ ነገር ማመን የመሰከረ/ች ነገር ግን ከልብ ያልተቀበለ/ች ማለት ነው፡፡ ... የጽንፈኝነት አንዱ መጥፎ ባህሪ "ተክፊር" በሌሎች ላይ ካፊር የሚል መለያ መለጠፍ ነው፤ ለምሳሌ የተወሰኑ ጽንፈኛ የሱኒ ሙስሊሞች ሺአዎችን ካፊሮች እንደሆኑ አድርገው ይመለከቷቸዋል፤ የተወሰኑ ሙስሊሞች አይሁዶችን እና ክርቲያኖችን ካፊሮች እንደሆኑ ያስባሉ፡፡ ይህ የማይረባ አስተሳሰብ ነው፤ አይሁዳዊ፣ ክርስቲያን እና ሙስሊሞች የሚል ስያሜ ያላቸው ሁሉም በአንድ እውነተኛ አምላክ ያምናሉ፣ ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት ያምናሉ፣ እንዲሁም ከሞት በኋላ ባለ ፍርድ ያምናሉ፡፡ ታክፊር የሚለውን ተመልከት
>
> ታክፊር፡- ሌሎችን በማጋራት ወይንም በካፊርነት የመወንጀል ልማድ ነው፡፡ የተለያዩ አሳቦችን እና ስሚቶችን የማያቻችል እንዲሁም የተፈቀዱ ነገሮችን ከልክ ያለፈ ክልከላ የሚያደርግ የጽንፈኝነት ምልክት ነው፡፡ ለምሳሌ ጽንፈኞች አዘውትረው ክርስቲያኖችን እና አይሁዶችን ካፊሮች በማለት ይገልጿቸዋል፤ ሆኖም ቁርአን አህል አል-ኪታብ ወይም የመጽሐፉ ሰዎች ብሎ ይጠራቸዋል፡፡ እንዲሁም በእውነተኛው አንድ

---

[113] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, page 123*

[114] *tafsir Ibn kathir(Abridged),vol 3 page 234-235*

[115] *Tafsīr al-Jalālayn, page 125*

አምላክ እንደሚያምኑ እና መጽሐፍት እንደተቀበሉ እውቅና ይሰጣቸዋል፡፡"[116]

ውድ አንባቢ ቁርአን እንዴት እንደተበረዘ አስተዋሉ ይሆን? ቁርአንንና አላህን፣ እንዲሁም በየዘመናቱ የኖሩትንና ያሉትን ምሑራን በተመለከተም የተወሰ ግንዛቤ ያስጨብጠናል፡፡ ከነዚያም አራት ነጥቦችን ማንሳት እችላለሁ፡-

1) ቁርአን ምን ያህል እርስ በእርሳቸው በሚቃረኑ አሳቦች የተሞላ መጽሐፍ እንደሆነ፤ የቁርአኑ አላህም እርስ በእርስ የሚጋጭ ነገር የሚናገር አምላክ መሆኑ፤ከዚህ የተነሳ በምሑራኑ መካከል እንኳን አንድነት የለም፡፡ ይህም የእውነተኛው አምላክ ቃል አለመሆኑ ያሳያል፡፡
2) ቁርአን የአላህ ቃል መሆኑ ቀርቶ ከነቢዩ ሙሐመድ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ማንም ያለከልካይ የሚፈነጭበት ለጥ ያለ ሜዳ መሆኑንና፣ ግለሰቦች የራሳቸውን ስሜትና ፍላጎታቸውን የሚያንጸባርቁበት፣ ባለቤት የለሽ ነጻ መድረክ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡
3) ቁርአን ምንም አላህ ሊጠብቀው ቃል በመግባቱ እንከን አልባ ነው፣ ቢባልለትም ለትውልድ ያለምንም እንከን መተላለፍ ያልቻለ፣ የተበረዘ፣ የተሰረዘ፣ የተደለዘና የጠፋ መሆኑን ያሳያል፡፡
4) በመዝገበ ቃላቱና በቁርአን ተርጓሚዎቹ መካከል ከታየው መለያየት የምንገነዘብ የትርጉም ሥራዎቹ የተሰሩት ክርስትናን እና ክርስቲያኖችን ለማጥቃት ባለሙ ጽንፈኞች መሆኑን ነው፡፡

ሌላውን ትርጉም እስኪ እንመልከት፤ ሳሊሱ ሳላሳቲን (ثَالِثُ ثَلَاثَةٍ) (thalithu thalathatin) የሚለውን ሐረግ፣ Trinity ብለው መተርጎማቸው በርካታ ስህተቶችን መፈጸማቸውና ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን በግልጽ ያሳዩበት ሆኗል፡-

- የኢስላም መዝገበ ቃላት "Allah:- the Muslim term for God, the Almighty One" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ Allah የሚለው ስም በራሳቸው በተርጓሚዎቹና በመዝገበ ቃላቱ God በሚል የእንግሊዝኛ አቻ የስም ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ God የሚለው ስም እንደ ክርስትና በተዋሐደ አንድነት የሚኖረውን አምላክ የሚወክል ስም ነው፡፡ በተጨማሪ ከላይ ክርስቲያኖች፣ አይሁዶችና ሙስሊሞች አንድ እውነተኛ የሆነውን አምላክ በጋራ እንደሚያመልኩ ተገልጿል፡፡ እንግዲህ ተርጓሚዎቹ ክርስቲያኖች ካፊሮች ናቸው ብለው ካመኑ፣ Allah የሚለውን ስም God በሚለው መተካታቸው ትልቅ ስህተት ነው፡፡ God በተዋሐደ አንድነት የሚኖር

[116] Ruqaiyyah Waris Maqsood, Abasic Dictionary of Islam, goodword books, India 2007, page 127 and 211-212

አምላክ ሲሆን Allah ግን ነጠላ አንድ አምላክ ነው፤ ስለዚህ ስሞቹ መተካካት የሚችሉ አይሆኑም፡፡ ለዚህ ይመስላል ፓኪስታንና ማሌዥያ አሁን አሁን Allah የሚለውን በእንግሊዝኛ God መተርጎምን እንደ አገር በሕግ ወንጀል ያደረጉት፡፡ ስለዚህ የኢስላም መዝገበ ቃላቱ ሦስቱም አንድ አምላክ ያመልካሉ የሚለው አባባል ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል፡፡ ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅሎሽ ተጠያቂው ማን ነው ትላላችሁ?

- ጽንፈኝነታቸው አስገድዷቸው እንዲህ ሲተረጉሙ፣ ከራሱ ከሚተረጉሙት ከቁርአን ጋር ትርጉማቸው አለመጋጨቱን አለመፈተሻቸው ይገርማል፡፡ የሁሉም ተርጓሚዎች ትርጉም ስለክርስቲያኖችና ስለአይሁዶች እምነትና ስለመጽሐፍቶቻቸው ትክክለኛነት ከተናገረባቸው በርካታ የቁርአን አንቀጾች ጋር ይጋጫል፡፡ እነዛን አንቀጾች ችላ ብሎ ካፊሮች ናቸው ብሎ ማለት፣ ማንን መቃረን እንደሆነ አያስተውሉምን? እንግዲህ ይህንን የመሰለ ከአላህ እና ከቁርአን ጋር የሚቃረን የትርጉም ሥራ ይዞ፣ ቁርአን አልተበረዘም እንዴት ሊባል ይችላል?
- ማስተዋላቸውን ምን ወሰደው? ሥላሴ ብለው ሲተረጉሙት ቁርአን የአላህ ቃል ላለመሆኑ ለክርስቲያኖቹ ማስረጃን በእጃቸው ማስጨበጥ መሆኑን እንዴት አላስተዋሉም? እስኪ የሁለት ሙፈሲሮችን ትርጉም ላስነብባችሁ፡-

ኢብን አባስ ሱራ 5 ፡ 73፡- "(እነዚያ «አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ) ማለት ይሄ የማርቆሳውያን ንግግር ነው፤ እነርሱ አብ፤ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በማለት ይናገራሉ..."

ሁለቱ ጃላላዎች ደግሞ ይህንኑ አንቀጽ እንዲህ ብለው አብራርተውታል፡- "እነዚያ «አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ" ማለት አማልክት፣ አላህም ከእነርሱ አንዱ ነው፤ ሁለቱ አማልክቶች ኢየሱስና እናቱ ማርያም ናቸው" ብለዋል፡፡

ሁለቱ ሙፈሲሮች ስለሥላሴ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ተመሳሳይ እውቀት የላቸውም፡፡ ምን ይህ ብቻ አላህም ራሱ ለክርስቲያኖቹ አስተምህሮ እንግዳ ነበር፡፡ ኢንን አባስ ትክክለኛውን ሲጠቅሱ አላህ በሱራ 5 ፡ 116 እና ጃላላዎቹ የተሳሳተን ሥላሴ ይገልጻሉ፡፡ እውነተኞች ከሆኑ ለምን ተመሳሳይ መናገር አልቻሉም፡፡ ይህ የሚያሳየው ቁርአን በበጥልቅ ብረዛ ውስጥ ያለና የእውነተኛው አምላክ ቃል አለመሆኑን ነው፡፡

**ሱረቱል አል-ማኢዳ 5 ፡ 116**

አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን?» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡ …

وَإِذْ قَالَ اللَّهُ يَا عِيسَى ابْنَ مَرْيَمَ أَأَنتَ قُلْتَ لِلنَّاسِ اتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيْنِ مِن دُونِ اللَّهِ…

- ❖ አሁንም የትርጉም ሥራቸው የአላህን ማንነት ሳይሸራረፍ በትክክል መግለጹን ለመፈተሽ አለመሞከራቸው ሌላው የተገለጠ ስህተታቸው ነው፡፡ አላህ ሁሉን አዋቂ ሆኖ ሳለ በቁርአን እና በተርጓኒዎቹ ግን ሁሉን አዋቂ እንዳልሆነ እያሳዩን ነው፡፡

ውድ አንባቢ እንግዲህ እነዚህን የቁርአን ትርጉም መጽሐፍት አንቀበልም የቁርአንን መበረዝ አያንጸባርቁም ካሉ፣ (እንደሚሉ የታወቀ ነው) ለመጽሐፍ ቅዱሱም ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለ ቁርአን መበረዝ ስንናገር ከነቢዩ ሙሐመድ ስለተላለፈው የመጀመሪያው ቅጅ እንጂ አሁን ስላሉት የቁርአን የትርጉም መጽሐፍት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ አሁን በዚህ ዘመን ላይ በአረብኛ ቋንቋ ተጽፎ የሚገኘው ቁርአን ሌሎቹን የትርጉም ሥራዎች ማረምና ማስተካከል የሚችል ሥልጣን ያለው የመጀመሪያው ቁርአን አይደለም ነው እያልን ያለነው፡፡ ይህንን ስናገር ከላይ እንዳያችኋቸው ተርጓሚዎችና የዘመኑ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች እንደሆኑ እራሳቸውን እንደሚቆጥሩት ዳኢዎች በጭፍን ጥላቻና የሃይማኖት ጽንፈኝነት ተውጨ እንዳልሆነ አይታችኋል፡፡ አንደኛ ሁለተኛ እየተባሉ በሚጠቀሱ በርካታ ኢስላማዊ የመረጃ ምንጮች ተደግፌ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደ ቁርአን እንዲህ የተዘበራረቀበት አይደለም፡፡ በጌታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ወንጌልን በምድር ዙሪያ ለማዳረስና ሰዎች የአምላካቸውን ቃል በቋንቋቸው ያለምንም ችግር ይረዱት ዘንድ ታስቦ ወደ 2500 በሚደርሱ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፡፡ ሆኖም በሥራ ወቅት አንዳንድ ግድፈቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ በቁርአንም የትርጉም ሥራ ወቅትም ሊያጋጥም የሚችል ነው፡፡ ነገር ግን የማረምና የማስተካከል ስልጣን ያላቸው በበኩር ቋንቋው የተጻፉ ቅጅዎች በቃሉ ባለቤት ተጠብቀው፣ እስከአሁን ድረስ ያለምንም ችግር በሕይወት ስለሚገኙ የተፈጠረውን ችግር ማስተካከል ይቻላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚፈልግ ሰው በበኩር ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ቢያስፈልገው አሁን ማግኘት ይችላል፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባና በእግዚአብሔር በራሱ የሚጠበቅ መጽሐፍ ለመሆኑ አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡

ማጠቃለያ፡- የቀደሙት መጽሐፍት ተበርዘዋል፣ ተብሎ በነቢዩ ሙሐመድ፣ ብሎም በከሊፋ ኡመርና በአባስ እንዲሁም በተከታዮቻቸው እየተነዛ የነበረውና ያለው ክስ የሐሰት ክስ እንጂ እውነትነት የነበረውና ያለው አይደለም፡፡ እስካሁን ባየናቸው በቁርአንም ሆነ በሐዲሳቱ መልእክቶች ክሳቸውን አሳማኝ እንዲሆን

ሊያግዛቸው የሚችል ምንም መረጃ ማቅረብ አለመቻላቸው ታይቷል፡፡ እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ስለሆነ፣ የእግዚአብሄር ቃል አይደለም፣ የሚለው የዘመኑ የእስልምና የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ ነን ባዮቹ የመደምደሚያ አሳብ ምንም ሊያስኬድ አይችልም፡፡ ደግሞም በትክክል ጥናት ተደርጎበት የተደረሰበት ድምዳሜ ሳይሆን የጭፍን ተሚጋቾች ከንቱ የስም ማጥፋት ወሬ መሆኑ ግልጽ ሆኗል፡፡ በዚህ ሥራቸው የሚንጸባረቀው የተከበረው አምላክ ባህሪ ሳይሆን፣ የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት የሆነው የሰይጣን ሥራ ነው፣ ብል ተሳሳትክ ሊለኝ የሚችል አለ አልልም፡፡

ውድ አንባቢ፤ በእስካሁኑ ንባባዎት መጽሐፍ ቅዱስ የዘለአለሙ አምላክ ያልተበረዘ፣ ንጹህ፣ ለሰዎች ሁሉ ደህንነት የተሰጠ ሕያው ቃል መሆኑን በበቂ ሁኔታ የተገነዘቡ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ተበረዘ ተብሎ ለተወራው ሐሰተኛ ክስ አሳማኝ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ እውነተኛነታቸው ብቻ በቁርአኑና በሃዲሳቱ ጎልቶ ተመስክሮለት አይተዋል፡፡ ስለዚህ ለዘለአለም ህይወትዎ ደህንነት ትክክለኛ አመራር ያገኙበታልና አምነው ይጠቀሙበት፤ የሚሰጥዎትንም ምክር ይስሙት እላለሁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ሲናገር፡-

> ወደ ሮሜ ሰዎች 3 ፡ 23
>
> ልዩነት የለም፤ ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡፡

ደግሞም

> ወደ ሮሜ ሰዎች 6 ፡ 23
>
> የኀጢአት ደምወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘለለም ህይወት ነው፡፡ ይላል

ስለዚህ ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ነው፡፡ አንድም ጻድቅ የለም ከተባለ፣ እርስዎም ኀጢአተኛ ነዎት፡፡ የኀጢአት ደሞዝ ደግሞ የዘላለም ሞት ነው፡፡ ቢሆንም ዛሬ ለእርስዎ እድል አለ፡፡ የሚወድዎት አምላክ ቅዱስ እግዚአብሔር ለዘላለም እንዳይሞቱ አስተማማኝ የደህንነት መንገድ አዘጋጅቷል፡፡ እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ያገኛል፤ ለዘላለምም በደስታ ከአምላኩ ጋር በገነት ይኖራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ መንጌል ላይ ሲናገር፡-

> የዮሐንስ ወንጌል 3 ፡ 16

በእርሱ የሚያምን ሁሉ፣ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ፣ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ሁሉ እንዲሁ ወዶአልና፡፡

ውድ አንባቢ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ በእግዚአብሔር እጅግ የተወደዱ ሰው መሆነዎትን ምን ያክል ያውቃሉ? ወሰን በሌለው ፍቅር ይወደዎታል፡፡ ታዲያ በዘረጋለዎት የጽድቅ መንገድ በኩል ወደ አፍቃሪዎት፣ ወደ አምላክዎት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ያለዎት ጊዜ አሁን ነው፡፡ ይህንን ጊዜ ይጠቀሙበት፤ የዘለአለም ሕይወት ያገኛሉ፡፡

2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6 ፡ 2

በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ፣ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ÷ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ÷ የመዳን ቀን አሁን ነው።

በሌላ መንገድ ወደ ገነት መግባትና ወደ ዘላለሙ ደስታ መድረስ አይችሉም፡፡ ወደ እግዚአብሔር የመድረሻ መንገድ ስለ ኀጢአተኞች መስቀል ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ የተከፈለውን ዋጋ ማመን ነው፡፡ የተሰጠዎትን ጊዜ ሳይጠቀሙ ወደ ገሃነመ እሳት እንዲወርዱ ፈጽሞ አይፈልግም፡፡ ገሃነመ እሳትን ያዘጋጀው ለሰይጣንና ለሰራዊቱ ብቻ እንጂ ለሰው ልጆች አይደለም፡፡

የማቴዎስ ወንጌል 25 ፡ 41

በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን÷ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።

ታዲያ ለሰው ልጆች ካልሠራው ለምን የውመል ቂያማ ወደ ገሃነመ እሳት ይልካቸዋል? ይሉ ይሆናል፡፡ ሰዎች ወደ ገሃነም የሚሄዱት በራሳቸው ፈቃድ ነው፡፡ ዛሬ እርስዎ እየሰሙት ያለውን ይህንን የሕይወት መንገድ ለመቀበልና በእርሱ ለመሄድ ባለመፈለጋቸው ነው፡፡ በተሰጣቸው እድሜ ከሕይወት ይልቅ ከኀጢአት ጋር አብሮ ለመኖር ሙጥኝ በማለታቸው ነው፡፡ ወደ ገነት የሚያደርሰው ብቸኛው መንገድ አንድ ነው፤ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመታዘዝና በእርሱ የተከፈለውን ዋጋ ለመቀበል፣ ከእርሱም ጋር ለዘላለም በደስታ ለመኖር የሚፈልግ ሰው ቢኖር ወደዚያው ወደተዘጋጀው የዘላለም ደስታ ያለከልካይ መግባት ይችላል፡፡ ይፈልጋሉ??

የዮሐንስ ወንጌል 14 ፡ 6

ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

በዚህ የሕይወት መንገድ ለመሄድ፣ እውነትን ለማመን ሕይወትንም ለማግኘት ከፊለጉ የሚጠየቁት እጅግ ቀላል ነገር ነው፡፡ ባሉበት ሆነው ከልብ የሆነ ውሳኔና የንስሐ ጸሎት መጸለይ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ውሳኔ ሲያደርጉና የንስሐ ጸሎት በጸለዩበት ወቅት ወዲያው የኀጢአት ይቅርታን ይቀበላሉ፤ አፍቃሪዎት ከእርስዎ መስማት የሚፈልገው ይህንን ብቻ ነው፡፡ ወዲያውም የመንግሥተ ሰማይ አባል በመሆን የእግዚአብሔር ልጅነትን መብት ይቀበላሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ምን ይፈልጋሉ? ዋስትና ያለው ሕይወት መኖር ይጀምራሉ፤ ከዚህ ዓለም ሲያልፉ የሚገቡበትን ሰማያዊ ቤት እየናፈቁ በደስታ ይኑሩ፡፡ ይህንን ሕይወት ለመቀበል ፈቃደኛ ነዎት? ከሆኑ አሁን ከልበዎት ሆነው አምላክዎትን እንዲህ ይበሉት፡-

- እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ አመሰግናለሁ፡፡
- ያለማዎቅ ከፍቅርህ እርቄ የኖርኩ ኀጢአተኛ ሰው ነኝ፡፡ ለፍቅርህ ምላሽ ሳልሰጥ በራሴ መንገድ ተጉዤ አሳዝኘሃለሁ፤ በድያለሁ፡፡ አሁን መጣሁ ተቀበለኝ፡፡
- በልጅህ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ
- ስለኀጢአቴ ሲል መስቀል ላይ መሞቱን መቀበሩን አምናለሁ
- በሦስተኛውም ቀን ሞትን አሸንፎ ከሞት መነሳቱን አምናለሁ
- ሰይጣንን ሥራውን ዓለምን እክዳለሁ
- ለአንተ ተሸነፍኩ ና ወደ ልቤ ግባ ልጅህ አድርገህ ተቀበለኝ
- አመሰግናለሁ፡፡

ወዳጄ፤ እንኳን ደስ ያለዎት! ከዚህ በኋላ የአምላክዎትን ቃል መጽሐፍ ቅዱስን የሕይወት ምግብ ነውና ያንብቡ ይታዘዙት፡፡

# ሙግት ሁለት

## መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አዕምሮ ሊቀበለው የማይችላቸውን አሳቦች መያዙ

እራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ ቆጥረው ለሙግት የተነሱት የእስልምና ዳኢዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል ከሚለው መሞገቻቸው ቀጥለው የሚያነሱት ይህንን ክስ፦ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም፤ ምክንያቱም የሰው አዕምሮ ሊቀበላቸው የማይችላቸውን አሳቦች በውስጡ ይዟል" የሚል ነው፡፡ ዳኢ ሳዲቅ ሙሐመድ "ላለመደናገር ማመሳከር"[117] በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ ለዚህ መሞገቻው እንደ ማስረጃ የጠቀሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉት፤

- በጠላት ከበባ ምክንያት በተከሰተው ብርቱ ርሃብ ልጇን ቀቅላ ከጎደኛዋ ጋር የበላችውን እናት ታሪክ መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 6 ፡ 26-29

- የአባት እድሜ ከልጁ እድሜ በሁለት ዓመት ያነሰ የመሰለበት ታሪክ
  መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 21 ፡ 16-20
  መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 22 ፡ 1-2

- ነቢዩ ሕዝቅኤል የሰውን አይነ ምድር እንደ ምግብ ተጠቅሞ ትንቢታዊ መልእክቱን እንዲያስተላልፍ የታዘዘ የመሰላቸው ክፍል
  ትንቢተ ሕዝቅኤል 4 ፡ 9-12

- ሴት ልጅ በወር አበባ ጊዜዋ መደረግ ስለሚገባው የመንጻት ሥርአት ሕግን በተመለከተ የተሰጠው ትእዛዝ
  ኦሪት ዘሌዋውያን 15 ፡ 19-22

- በወገኖቹ መካከል ለራሱ ስም ማስጠሪያ የሚሆን ዘር ሳይተካ ለሞተ እስራኤላዊ ስሙ እንዲጠራ ለማድረግ የሚችን ሚስት ስለማግባት የተሰጠውን ሕግ በተመለከተ
  ኦሪት ዘዳግም 25 ፡ 5-10

- የነቢዩ አህያ ለነቢዩ እብደቱን ትነግረው ዘንድ የሰው ቋንቋ ተጠቅማ መናገሯን በተመለከተ
  2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2 ፡ 16

---

117 ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 33-41

- በምሳሌያዊ አገላለጽ ዛፎችን ለንግሥና እያወያየ ለሰዎች መልእክቱን በማስተላለፍ የተዋጣለትን የኢዮአታምን ታሪክ በተመለከተ
  *መጽሐፈ መሳፍንት* 9 ፡ 7-13

- በጸታ ፍቅር ምሳሌ ቅኔን በመቀኘት መልእክቱን ያስተላለፈውን የንጉሥ ሰለሞንን መኃልይ የተመለከተ
  *መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን* 7 ፡ 1-9

- ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው ደብዳቤ ላይ ስለተጠቀመው የመዝጊያ መልእክት
  2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4 ፡ 9-13

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የያዙት መልእክት የሰው አዕምሮ ሊቀበላቸው የማይችል አስቸጋሪ ታሪኮችና መልእክቶች ናቸው ይላሉ፡፡ በመሠረቱ ይህ አመለካከታቸው ከመሰሎቻቸው ውጭ ባሉ ሰዎችም ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል አመለካከት ነው ብዬ አላምንም፡፡

- ❖ ታዲያ የአምላክ ሁሉን ቻይነት ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ ከሰው አዕምሮ ያለፈ ነገር ማድረጉ ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?
- ❖ እውን እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የያዙት መልእክት ለሰው አዕምሮ የሚከብዱ ናቸውን? አንድን መልእክት ከአላህ ነው፣ ለማለት የግድ የሰው አዕምሮ ሊቀበለው የሚችል ሊሆን ይገባልን? ይህ አመለካከታቸው ቁርአናዊ ድጋፍ ያለው ነውን?
- ❖ ዓለማችን ባለፉት ዘመናትም ሆነ፣ በዚህ ዘመን፣ በአንዱ ሰው የፈጠራ ሥራ ተገርመን ሳንጨርስ፣ ሌላ አስገራሚና አስደናቂ ነገር የሚታይባትና የሚሰማባት መድረክ ሆናለች፡፡ እንግዲህ መለኪያው የሰው አዕምሮ አቀባበል ከሆነ በአምላክና በሰው መካከል የሚኖረው ልዩነት ምን ሊሆን ይችላል?
- ❖ ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ አመለካከታቸውን **ከሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 87** ጋር እንዴት ሊያስታርቁ እንደሚችሉ ይገባሩን? የሰው ልጅ በአብዛኛው በአላህ ፈቃድ ደስ ብሎት ሲያጨበጭብ ታይቶ አይታወቅም፡፡ ከገነት የተባረረው እኮ በአላህ ትዕዛዝ ደስተኛ ባለመሆኑ ነበር፡፡ አሁን ምን መጣና መልእክቱን የሰው አዕምሮ መቀበል አለመቀበል ለአላህ ቃል መለኪያ ሊሆን ቻለ? ቁርአንን የአላህ ቃል ነቢዩ ሙሐመድንም የአላህ መልእክተኛ አድርገው የተቀበሉት አዕምሯቸው ሊቀበለው የሚችል መልእክት ይዘው ስለመጡ ነውን?

**ሱረቱል አል-በቀራ** 2 ፡ 87

ሙሳንም መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው፡፡ ከበኋላውም መልክትኞችን አስከታተልን፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው፡፡ በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው፡፡ <u>ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን?</u> ከፊሉን አስተባበላችሁ፣ ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡

ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ፣ በዚህ አንቀጽ እየነገረን ያለው ሰዎች ከአላህ የሆነውን መልእክተኛና መልእክት መቀበል አለመቀበል በነፍሳቸው ፈቃድ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ነው፡፡ የሚወዱትን ይቀበላሉ፣ የማይወዱትን ይጥላሉ፡፡ ከመጀመሪያው አባት ከአዳም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጅ በአላህ ትዕዛዝ ፈንድቆ ደስታውን ሲገልጽ ታይቶ አይታወቅም፤ የቁርአንም ንግግር ይኸው ነው፡፡ አዕምሮው ነገሮችን ይቀበል ዘንድ ካስፈለገ ከስሜቱ፣ ከፍላጎቱ፣ እውነት ካለው ከእምነቱ ጋር በጥብቅ መማከርን ይፈልጋል፡፡ እውነት ነው ብሎ የያዘው እምነቱ ከአላህ እውነት ጋር ሲነጻጸር እውነት ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ከላይ የተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ የአላህ ንግግር ከሰዎች ፍላጎት ጋር ሊጣጣም የማይችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልና የሰውም አዕምሮ ሊገፋው እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ እንግዲህ ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሰፈሩት መልእክቶች ያቀረቡት መሞገቻ ተገቢ ሊሆን አይችልም፤ ቁርአናዊ መሠረትም የለውም፡፡ ያንንም እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስንመለከት አብረን የምንመለከተው ይሆናል፡፡

እንግዲህ ግራ የተጋቡ ኃይሎች እንዳሉት አምላክን አምላክ ያሰኘው በሰው አዕምሮ ልክ ተናግሮ መገኘቱ ከሆነ፡-

1) የአምላክ ነገር የሰው አዕምሮ ሊቀበለው በሚችለው ልክ ብቻ ተለቋል ማለት ይሆናል፡፡ ይህ አመለካከት ሰው የአምላክ ነገር ከአእምሮው ልክ ያለፈ ስላልሆነ እርሱን በቀላሉ ማረጋገጥ ስለሚችል የእምነት ልዩነቶች መፈጠር አልነበረባቸውም ወደሚል መደምደሚያ ሊያደርሰን ነው፡፡ ይህም ደግሞ **ከሱረቱል አል-ማኢዳ** 5 ፡ 48 እና ከሌሎች ተመሳሳይ የቁርአን አንቀጾች ጋር በቀጥታ ይጋጫል፤ ከእስልምና የእምነት መሠረቶች መካከል አንዱ ከሆነው ከቀድር ጋርም የሚጋጭ ይሆናል፡፡
2) እንደ እነዚህ ወገኖች አመለካከት አንድ የእምነት መጽሐፍ የሁሉን ቻይ አምላክ ቃል ነው ለመባል የሰው አዕምሮ ሊቀበለው መቻልና በውስጡ በቀላሉ ሊታመኑ የሚችሉ አሳቦችን መያዝ ሊኖርበት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ ከተባሉት የሰው አእምሮ ሊቀበላቸው ከማይችላቸው አሳቦች ይልቅ አላህ አጥጋቢ ምክንያት ያልሰጠባቸው፣ በቀደሙት መጻሕፍት ማረጋገጫ ያላገኙ፣ ለአዕምሮ የማይመቹ ቁጥራቸው በርካታ አሳቦች ቁርአኑን አጨናንቀዋል፡፡ የነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳትም በመሰል ሐሳቦች ተሞልተው፣ ሙስሊሙ እጅ

ይገኛሉ፡፡ ታዲያ ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ራሳቸው ማረጋገጣቸው አይደለምን?

3) ሰው አዕምሮው ሊቀበለው በሚችለው ልክ የአምላክን ነገር ማወቅ አለበት ከተባለ፣ የአላህ ፍላጎት ለሁሉም ሰው ግልጽ ስለሚሆን በእምነት ልዩነት ምክንያት አሁንና ከዚህ በፊት የታዩት የሃይማኖት ግጭቶች፣ ዘግናኝ የሆኑ ግድያዎች ሊኖሩ አይችሉም ነበር፡፡ ነገር ግን ሳይሆን ቀርቶ ሰዎች ትክክለኛ እኔ እንጂ አንተ አይደለህም እየተባባሉ እርስ በእርስ እንዲጣረሱ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ስንት እንደገደለ፣ ስንት ውድመትም እንዳስከተለ ራሱ እስልምና ያውቀዋል፡፡

4) የአምላክ ቃል የሰው አዕምሮ ሊቀበለው በሚችለው አሳቦች መሞላት አለበት ከተባለ፣ ሙስሊሞች ሙስሊም የሆኑት አላህ አዕምሯቸው ሊቀበለው የሚችለውን መልእክቶች ብቻ አስይዞ ቁርአንን ስላወረደው ነው ማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ እንግዲያውስ የቢሊዮኖች አዕምሮ በመረጃ ሊቀበላቸው የማይችላቸውን መልእክቶች ቁርአን በውስጡ አጭቆ ስለያዘ አልተቀበሉትምና የአምላክ ቃል አይደለም ማለት ነው፡፡ ለዚህ ምን ይላሉ? መልስ የለም፡፡

ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ ይህን የመሞገቻ ነጥብ ሲያነሱ የእስልምና ሃይማኖት መጽሐፍትን ዙሪያ መለስ ሳይመረምሩ ለመሆኑ ነጋሪ አያስፈልግም፡፡ ክርስትናን ለማጣጣል አዋጭ መንገድ በስሏቸው ከሆነ ተሳስተዋል፡፡ ከዚህ ይልቅ የማደናገር ተግባራቸውን ቆም አድርገው "አልገባንምና አስረዱን" ቢሉ ለዘላለማቸው ጉዞ መስተካከል አንድ እርምጃ ይሆንላቸው ነበር፡፡ የሰው አዕምሮ ሊቀበላቸው የማይችላቸው የቁርአን መልእክቶች ውስጥ ጥቂት ምሳሌዎችን ላንሳ፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 259**

*ወይም ያንን በከተማ ላይ እርሷ በጣራዎችዋ ላይ የወደቀች ስትኾን ያለፈውን ሰው ብጤ (አላየህምን?)፡- «ይህችን (ከተማ) ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል?» አለ፡፡ አላህም ገደለው፣ መቶ ዓመትን (አቆየውም)፡፡ ከዚያም አስነሳው፡- «ምን ያህል ቆየህ?» አለው፡፡ «አንድ ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየሁ» አለ፡፡ «አይደለም መቶን ዓመት ቆየህ፡፡ ወደ ምግብህና ወደ መጠጥህም ያልተለወጠ ሲኾን ተመልከት፡፡ ወደ አህያህም ተመልከት፡፡ ለሰዎችም አስረጅ እናደርግህ ዘንድ (ይህንን ሠራን)፡፡ ወደ ዐፅሞቹም እንዴት እንደምናስነሳት ከዚያም ሥጋን እንደምናለብሳት ተመልከት» አለው፡፡ ለርሱም (በማየት) በተገለጸለት ጊዜ፡- «አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን ዐውቃለሁ» አለ፡፡*

ይህ ክፍል ከአይሁድ አፈ ታሪኮችና ከአፖክሪፋ መጽሐፍት የተቀዳ ይመስላል፡፡ ከዚህና በዙሪያቸው ከነበሩት አይሁዳውያን የተነሳ "በጀሮው ተደገመችለት"

የሚለውን የተቃዋሚዎቻቸውን አባባል አምኖ ለመቀበል አስገዳጅ ይሆናል፣ ብዬ አምናለሁ፡፡ ከተወሰነ ልዩነት ውጭ ፍጹም ተመሳሳይ የሆነ የአንድ ተቀራራቢ ዘመን ታሪክ በተረፈ ኤርምያስ ምእራፍ 9 (ገጽ 895-896) ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ የቁርአን አንቀጽ የተተረከለት ሰው በተረፈ ኤርምያስ በተገለጸው ዘመን በባቢሎን ምድር በምርኮ ይኖር የነበርና በመጋቢት 1/ 458 ዓዓ ላይ ከዛ በመውጣት ከወገኖቹ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ስለተመለሰው ፀሐፊና ካህኑ እዝራ ነው፡፡ ምንም አንድ የአይሁድ ካህን የትንሳኤ ሙታን ጉዳይ፣ ያውም የሰዎች ከሞት መነሳት ሳይሆን (የትኛው ከተማ እንደሆነ ባይታወቅም) የከተማ ሞቶ መነሳት ጥያቄ ሆኖበት ከአላህ የማረጋገጫ ጥያቄ ጠየቀ መባሉ፣ ከአይሁዳዊነቱ አንጻር አስገራሚና ከአላህ እንደበት ቃሉ ላለመውጣቱ አመላካች ነው፡፡ ቢሆንም፡-

- ❖ አላህ የአንድን ከተማ ትንሳኤ ጥያቄ ለመመለስ ሲል ጠያቂውን ሰው በመግደል ከመቶ አመት በኋላም በማስነሳት ጥያቄውን መመለሱ ምን ማለት ይሆን? እውን አላህ ስለ ከተማ ትንሳኤ እየተጠየቀ ስለ ሰው የተጠየቀ ይመስል ጠያቂውን ገድሎ በማስነሳት የማይገናኝ መልስ የሚመልስ ይመስላችኋል? ይህንን ጉዳይ የትኛው አዕምሮ ይሆን ሊቀበለው የሚችለው?
- ❖ መቶ አመትስ ማቆየቱ ለምን አስፈለገ? ከዚያ ያነሰ ጊዜ በቂ አይሆንም ነበር?
- ❖ እንደ ካህንነቱ የትንሳኤ ሙታንን ትምህርት ገና ድሮ አምኖበት ለህዝብ እያስተማረ የነበር መሆኑን አላህ አያውቅም? ከተማ በሰው በጎ ፈቃድ የሚገነባ እንጂ፣ አላህ በታምራት የሚሠራው አይደለም፡፡ እዝራስ ከተማ የሰው በጎ ፈቃድ ውጤት መሆኑን እያወቀ እንዲህ አይነት ጥያቄ የሚጠይቅ ይመስላችኋል? በአላህ ተአምራት የተፈጠረ፣ ከእርጅናውም በአላህ ተአምር የታደሰ ከተማ እንደሌለ ሁሉም ሰው ምስክር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡
- ❖ ከእስልምና የኢማን መሠረት አንጻር ሲታይ፣ አላህ ትንሳኤ አለ ብሎ ያስተማረው ነቢዩ ሙሐመድም ተልኬአለሁ ያሉት ለከተማዎች ትንሳኤ ወይንስ ስለ ሰዎች ትንሳኤ ሙታን?

የአይሁድ አፈ ታሪኮች ሰንበትን እንጨት በመልቀም የሻሩ ሰዎች ወደ ጦታነት እንደተቀየሩ፣ በሔኖክ ዘመን የነበሩ ኀጢአተኞች አላህ ፊታቸውን ወደ ዝንጀሮ ፊት እንደቀየረው፣ ታልሙዱም በባቢሎን ግምብ ሥራ ተሳታፊ የነበሩትን ሰዎች ወደ ጦጣነት እንደቀየራቸው ይናገራል[118]፡፡ ቁርአንም ከዚህ አፈ ታሪክ በመቅዳት የተወሰነ ማሻሻያ አድርጎለት እንደመገለጥ ያቀረበው አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው ታሪክ እነሆ፡-

---

[118] *Louis Ginzberg, The Legends Of The Jews, The Jewish Publication Society of America 1928, vol 6 page 84-85*

ሱረቱረል አል-በቀራ 2 ፡ 65

እነዚያንም ከእናንተ ውስጥ በቅዳሜ ቀን (ዐሣን በማጥመድ) ወሰን ያለፉትንና ለነሱ «ወራዳዎች ስትኾኑ ዝንጀሮዎች ኹኑ» ያልናቸውን በእርግጥ ዐወቃችሁ፡፡

ሱረቱል አል-አእራፍ (የአዕራፍ ምዕራፍ) 7 ፡ 166

ከእርሱም ከተከለከሉት ነገር በኮሩ ጊዜ ለእነሱ «ወራዶች ዝንጀሮች ኹኑ አልን፤» (ኾኑም)፡፡

ስለ እነዚህ ሁለት ቁጥሮች በተሰጠው ተፍሲር ላይ እንደሚታየው ወደ ተባለው መተላለፍ ወይም ፈተና ሰዎቹን የመራቸው ራሱ አላህ እንደሆነ ተመልክቷል[119]፡፡ እነዚህ የምድያም ሰዎች ከወንዞቻቸው ኣሣዎችን አጥምደው በመያዝ እንዳይመገቡና ርሐባቸውን እንዳያስታግሱ አንድ ሳምንት ሙሉ ደብቆ አቆይቶ በሰንበት ቀን ከተደበቁበት እንዲወጡ አድርጓል፡፡ ስድስት ቀናት ሲመላለሱ ሰንብተው ቢያጡ ሰባተኛው ላይ ተጨማሪ ሙከራ አደረጉ፣ አገኙም፡፡ እንግዲህ በርሐብ የቆየ ሕዝብ ሊሆን ይችላል፡-

- ❖ አሣዎቹ በተለቀቁበት ቀን አጥምደው ቢበሉና ርሐባቸውን ቢያስታግሱ ጥፋቱ ምን ላይ ነው? ዝንጀሮ ከማድረግ ይልቅ በቶራው የተደነገገውን ፍርዱን ለምን አልፈጸመባቸውም? የእነዚያ ዝንጀሮዎች ዝርያ አሁን በአካባቢው ላይ ይኖር ይሆን? ይህንንስ የትኛው አእምሮ ይሆን ሊቀበለው የሚችለው? አይደለም የሌላውን የእስልምና ምሁራኑን አዕምሮ የተፈታተነ ጉዳይ ነው፡፡
- ❖ አላህ እነርሱን እንደ ጥፋኛ ቆጥሮ ዝንጀሮ በማድረግ መቅጣቱ ፍትሃዊ አምላክ ያሰኘዋል? በዚህ ሁኔታ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ የያኔው አላህ አሁንም አልተለወጠምና በዚህ ዘመን ሰንበት ሻሪዎቹ በዝተዋልና ለምን ብዙ የሰው ዝንጀሮዎችን ማየት አልቻልንም? ይህስ አል-አድል ነው፤ ያለውን ማንነቱን ያጎላል ወይስ ይቃረናል? ከተውሂድ አስማ ወሲፋት ጋር ያለው ተዛምዶ እንዴት ይታያል?
- ❖ ውድ አንባቢ ይህን ቁርአናዊ ታሪክ ምን ያክል የሰው አዕምሮ ሊቀበለው ይችላል ይላሉ? እርስዎ ህንን ሲሰሙ ምን አሉ?
- ❖ የሰንበት ጉዳይ ቁርአናዊ ሳይሆን የተውራት ሕግ ነው፡፡ ስለዚህ ተውራቱ ሰንበትን መሻር ስለሚያስከትለው ቅጣት ምን ይላል? ይህ የተፈጸመባቸው ሕዝቦች እነማን ናቸው? ይህ አይነቱ ሕግና ፍርድ የሚመለከታቸው ወገኖች ነበሩ ወይንስ አልነበሩም?

---

[119] *Ibn Kathir, Stories of the Quran, translated by Ali As-Sayed Al-Halawani, Dar Al-Manarah, Egypt 2001, page 188-194*

ውድ አንባቢ ሆይ፤ ለሰው አዕምሮ የማይመቹ ግን ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ እንደድንቅ ቆጥረው የሚሰብኳቸውን ቁርአናዊ ታሪኮችን አልጨረስኩም፡፡ -

ሱረቱል አል-ነምል (የጉንዳን ምዕራፍ) 27 ፡ 18

በጉንዳንም ሸለቆ በመጡ ጊዜ አንዲት ጉንዳን «እናንተ ጉንዳኖች ሆይ! ወደ መኖሪያዎቻችሁ ግቡ፡፡ ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ የማያውቁ ሲኾኑ አይሰባብሩዋችሁ» አለች፡፡

ሱረቱል አል-ነምል (የጉንዳን ምዕራፍ) 27 ፡ 20-24

…………. (ወፉ) ዕሩቅ ያልኾነንም ጊዜ ቆዬ፡፡ አለም «ያላወቅከውን ነገር አወቅኩ፡፡ ከሰበእም እርግጠኛን ወሬ አመጣሁልህ፡፡ «እኔ የምትገዛቸው የኾኑትን ሴት፣ ከነገሩም ሁሉ የተሰጠችኝ አገኘሁ፡፡ ለእርሷም ታላቅ ዙፋን አልላት፡፡ «እርስዋንም ሕዝቦችዋንም ከአላህ ሌላ ለፀሐይ ሲሰግዱ አገኘኋቸው፡፡ ሰይጣንም ለእነሱ ሥራዎቻቸውን ሸልሞላቸዋል፡፡ ከእውነተኛውም መንገድ አግዷቸዋል፡፡ ስለዚህ እነሱ (ወደ እውነት) አይምመሩም፡፡»

ውድ አንባቢ ሆይ፤ ይህም ተአምርና መገለጥ ተብሎ ቢነገርለትም በአይሁዳውያኑ የአዋልድ መጽሐፍ ሰፍሮ የሚገኝ ታሪክ ነው[120]፡፡ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በእንዲህ አይነት ሥራዎች ነቢዩ ሙሐመድ ጥሩ የሚባል ባለሞያ ናቸው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ ሐዲሳቱን ጥቂት ማገላበጥ ይበቃል፤ የአሹራን፣ የሮመዳንን፣ የመቃብር ቅጣትን የመሳሰሉትን ታሪኮች በጥቂቱ መመልከት በቂ ነው፡፡ ለማንኛውም፡-

- ጉንዳን የሰለሞንንና የሰራዊቱን ማንነት አውቆ ለወገኖቹ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ ሲባል የትኛው የሰው አዕምሮ ሊቀበለው ይችላል?
- የእኛ የዝናብ ወፍ፣ የፈረንጆቹ ሁፒዮ ከኢየሩሳሌም በመነሳት ምድረ በዳውን እያቆራረጠ ብዙ ሽህ ኪሎ ሜትሮችን በመብረር ንግስተ ሳባ ያለችበት ከተማ መድረሱ፣ ከድፍን የሳባ ቆነጃጂት መካከል እርሷን መለየት ቻለ መባሉን የማን አዕምሮ ሊቀበለው ይችላል?
- በዚህ ሳያበቃ ጣኦት አምልኮን መለየት ቻለ፤ ብቻም አይደለም፤ የቀናውን መመራትና በሰይጣን መንገድ ላይ መሆንን ለይቶ ማወቅ ቻለ መባሉንስ የትኛው አዕምሮ ይቀበለዋል? ይህ ሁሉ ከአላህ አንደበት በመልአኩ ገብርኤል በኩል የተላለፈ መለኮታዊ ቃል ይመስለዎታል?
- ቆይ እንስሳት ከሰው ከሚለዩበት መሰረታዊ ነገሮች መካከል አንዱ ይህ አሁን ስለ እንስሳዎቹ የሚነገረን ነገር አይደለምን? ቁጥር ስፍር

[120] *Rev. W. St. Clair Tisdall, The Original Sources Of The Qur'an, Society For Phomoting Christian Knowledge, London 1905, Page 80-93*

ከሌላቸው ጉንዳኖችና ሁፒዎች መካከል መናገር የሚችሉትስ ይህ አንዱ ሁፒዩና አንዱ ጉንዳን ብቻ ነበሩ? ወይንስ ሁሉም መናገር ይችላሉ?

- ሳይንስ ይህንን በሰማበት ቀን ምን አለ? የማንስ አዕምሮ ይህንን ዜና አምኖ ሊቀበል ይችላል? የሳዲቅና የመሰሎቹ አዕምሮ ይህንን ከተቀበለ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ላይ ሲደርስ ምነው ዳተኛ ሆነባቸው?

ዳኢ ሳዲቅ ሙሐመድ በተለያዩ የዳዕዋ መድረኮች በሰጣቸው ትምህርቶችና በጻፈው መጽሐፍ ነቢዩ ሙሐመድ ለነቢይነታቸው ስለተሰጣቸው ተአምራት ዘርዝሯል፡፡ ከዘረዘራቸው መካከል እንዲህ የሚለው ይገኛል፡-

> "የአላህ መልእክተኛ የጁምአ ኹጥባ የሚያደርጉት የተምር ግንድ በመደገፍ ነበር፡፡ ሚንበር ከተሰራላቸው በኋላ ግን ያንን የተምር ግንድ ትተው ወደ ተሰራላቸው ሚንበር ሲመጡ ያ የተምር ግንድ እንደ ግምል መንሰቅሰቅ ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ወደ እርሱ በመምጣት እጃቸውን ሲያሳርፉበት ወዲያው ጸጥ አለ፡፡ (ቡኻሪ፣ ናሳኢና ትርሚዝ የዘገቡት ሐዲስ)"[121]

- ውድ አንባቢ የተምር ዛፍ ልክ ግመል እንደሚያለቅስ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ሲባል የሰው አዕምሮ እንዴት ሊያምን ይችላል? ይህንን አምኖ የተቀበለው የዳኢ ሳዲቅ አዕምሮ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ሲሰማ ይህ የማይታመን ነው ማለቱ አይገርምም? ይህንን ታማኝ አዕምሮ ነው ትሉታላችሁ?

በሱረቱል አል-ካህፍ (የዋሻው ምዕራፍ) 18 ፡ 60-65 ደግሞ ሙሴና ኢያሱ በጉዞ ላይ እያሉ ምሳ በልተው የተረፈ የተጠበሰ የአሳ ግማሽ ነበር፡፡ ይህ የተጠበሰና ከምሳ የተረፈ ግማሽ አሳ ማንም ሳያየው ወንዝ ውስጥ በመግባት እነርሱን መንገድ መሪ ሆኖ እንደተገኘ ይነግረናል[122]፡፡

- እንግዲህ የመንገድ ስንቅ፣ ከምሳ የተረፈ የተጠበሰ የአሳ ግማሽ ከተቀመጠበት ቅርጫት ውስጥ ወጥቶ ባህር ውስጥ ዘሎ በመግባት እነ ሙሴን መንገድ መራ ሲባል፣ በሰው አዕምሮ ውስጥ እንዴት ተቀባይነት ማግኘት ይችላል? ልቀጥል? ይብቃኝ፤ ለአብነት ያክል ይኸው በቂ ይመስለኛል፡፡

የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥና የሚነሱባቸውን ጥያቄዎች መመለስ የማይችሉባቸውን የቁርአንና የሐዲሳቱን ታሪኮች አዕምሯቸው አምኖ ተቀብሎ፣ የአምላክን ባህሪ ሳይጋፉና ሳያዛባ እውነት

---

[121] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 149-150

[122] *Stories of the Quran, page 58-61*

የተገለጸበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች መቀበል እንደተሳናቸው ሳይ በጣም ተገረምኩ፡፡ ይሁንና እንዲህ እየሆኑ ያሉት ጽንፈኝነታቸው አስገድዷቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እኛም የሰላም መልእክተኞችና ሰዎች ሁሉ ከዘላለም ጥፋት ይድኑ ዘንድ የሚወደው አምላክ አገልጋዮች ነን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ስለራሱ ለሚነሱ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ መስጠት የሚችል የአምላክ ቃል በመሆኑ ግራ ያጋባል ለሚሏቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች ሁሉ አጥጋቢ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡

## 2.1. መጽሐፈ ነገስት ካልእ 6 ፡ 26-29

> የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥር ላይ በተመላለሰ ጊዜ፣ አንዲት ሴት ጌታዬ ንጉሥ ሆይ÷ እርዳኝ ብላ ወደ እርሱ ጮኸች። እርሱም፦ እግዚአብሔር ያልረዳሽን እኔ እንዴት እረዳሻለሁ? ከአውድማው ወይስ ከመጥመቂያው ነውን? አለ። ንጉሡም ምን ሆነሻል? አላት እርስዋም፦ ይህች ሴት ዛሬ እንድንበላው ልጅሽን አምጪ ነገም ልጄን እንበላለን አለችኝ። ልጄንም ቀቅለን በላነው፣ በማግሥቱም እንድንበላው ልጅሽን አምጪ አልኋት ልጅዋንም ሸሸገችው ብላ መለሰችለት።

እንዲህ ያለ አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለውን ነገር ያቀፈ የአላህ ቃል ሊባል እንዴት ይችላል? በማለት ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አዕምሯቸው ሊቀበለው ባይችልም አንድ በማስተዋል የሚያነብ አንባቢ ክፍሉን በሁለት መንገድ ሊመለከተው እንደሚችል አስባለሁ፡፡

## ሀ. ከወላጃዊ ባህሪ ጋር በተያያዘ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእናት ስብእና ጋር በተያያዘ ሲታይ የእናትነት አንጀቷ ሞቶ ልጇን ቀቅላ ለመብላት፣ ነገም የሌላ ሰው ልጅ ለመድገም እንዴት ማሰብ ቻለች? ብሎ መገረም ይቻላል፡፡ ሆኖም ከዚህ አለፍ ብለን እንድናስብ ሊያደርገን ግን አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ልጇን የበላች ብቸኛዋ እናት ይህች ብቻ ስለሆነች፤ ሌላዋ የሌላ ልጅ ስጋ ነው የበላችው፡፡ ታሪካቸው በዚህ መጽሐፍ ያልተዘገበ የሰው ስጋ የሚበሉ ሰዎች አሉ፤ ነበሩ አያስደንቅም፡፡ ሁለተኛም ዓለም ወላጆችና ልጆች ባላቸው የስሜትና የመንፈስ ትስስር መለኪያ ስንለካ እንዴት የሚያሰኙና የሚያስገርሙ በርካታ ክስተቶች አሳይታናለች፤ በታሪክ መዛግብቶችዋም አስነብባናለች፡፡ የሚገረም እየተገረመ፣ አንዳንዱም የማይታመን እያለ ምላሹን እየሰጣት አልፎታል፡፡

በቁርአን እና በነቢዩ ሙሐመድ የሐዲስ መጽሐፍት ውስጥ የአረብ ወላጆች ምን ያደርጉ እንደነበር ተተርኳል፡፡ በወቅቱ የነበረውን የምግብ እጥረት ለመቋቋምና ነፍሳቸውን ለማቆየት እጃቸው ላይ ያለችውን ምግብ እንዳይጋሯቸው በማሰብ

ልጆቻቸውን ስለ ምግብ ይገድሏቸው ነበር[123]፡፡ የቁሬይሽ እና የኹዛአህ ጎሳ አባላት ለሴት ልጅ ከነበራቸው የተዛባ አመለካከት የተነሳ ሴት ልጅ በተወለደችላቸው ቁጥር ያለ ምንም ርህራሄ፣ የልጅነት የለቅሶ ድምጻቸው ሳይረብሻቸው ከነ ሕይወታቸው ይቀብሯቸው ነበር[124]፤ በማለት ድሮን ዛሬ ላይ ላለነው ይነግሩናል፡፡ እንግዲህ፡-

- እናቶቻችን ለልጆቻቸው ያላቸውን ልዩ ፍቅር በአይናችን ያየን፣ በመንፈሳችን ያጣጣምን እኛ፣ ይህንን የሐዲሳቱን ዘገባ እንዴት አዕምሯችን አምኖ ሊቀበልልን ይችላል? ወላጅ ልጅን ከነ ሕይወቱ ሊቀብር አይችልም፤ በፍጹም ሊታመን አይችልም ልንል እንችላለን፤
- ዳኢ ሳዲቅና መሰሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሊታመንላቸው ካልቻለ፣ ይህን የራሳቸው መጻሕፍት የያዙትን ታሪክ እንዴት አዩት? በዚህም ግራ ገብቷቸው ይሆን? ወይንስ ምንም ነቢዩ ሙሐመድ የመጀመሪያው ሰው ባይሆኑም፣ ይህን ድርጊት ስለተቃወሙና የትምህርታቸው አካል ስላደረጉት፣ እንዲህ የሚያደርጉ ገነት እንደ ማይገቡ ስለ ሰበኩ፣ የአላህ መልእክተኛ እንደሆኑ እራሳቸውን ካሳዩበት አንዱ ስለሆነ፣ አግራሞትን ሳይፈጥርባቸው የነቢዩን ነቢይነት ብቻ ሊያሳያቸው ቻለን?
- ሳዲቅና መሰሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ አዕምሯቸው አላምን ያላቸው በዘመናቸው ሁሉ ይህንን ሲሰብኩ በምን ስሜት ውስጥ ሆነው ሰበኩት? ታዲያ ያኔ አዕምሯቸው ጥያቄ አለኝ አላላቸውም ነበር? ካላላቸው የመጽሐፍ ቅዱስን እንዴት መዋጥ አቃታቸው?

በቅድመ እስልምና የኖሩ የአረባውያን ወላጆች ድርጊት ለእኛ ሊታመን የሚችል ስላልሆነ፣ ለእኛ አዕምሮ ስለከበደ ብቻ አላህ ያወረደውን ቃል የአላህ ቃል አይደለም ለማለት አያስችለንም፡፡ ታሪኩ እኛን ቢያስገርመንና ቢያሳዝነን እንጂ፣ ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ለማሳየት ማስረጃ ልናደርገው አንችልም፡፡ በቁርአንና በነቢዩ ሙሐመድ መልእክተኛነት ላይ ያለው ጥያቄያችን የተመሠረተው በሌላ መመዘኛ ላይ ነው፡፡ ያንንም በተወሰነ መልኩ ቀደም ብዬ አሳይቻለሁ፡፡

## ለ. የእምነት መጽሐፍ ስለሆነ ከተናጋሪው ከእግዚአብሔር ከመለኮታዊ አላማው አንጻር ሊመለከተው ይችላል

ሁለተኛ ከቅዱሳት መጽሐፍት ተግባራት መካከል አንዱና ዋንኛው አምላክንና ሰዎችን ማገናኘት ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ሰውና አምላክ የሚነጋገሩባቸው አገናኝ ድልድዮች ናቸው፡፡ ሰው የአምላኩ ፈቃድ ምን እንደሆነና ከእርሱም ጋር ለመኖር ምን ማድረግ እንዳለበት እውቀት የሚያገኘው ከእነዚህ መጻሕፍት

---

[123] *Tafsir Ibn Kathir, vol 6 page 512, sura 6 : 151, sura 17 : 31*

[124] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, page 302*

ነው፡፡ በተጨማሪ ባለመታዘዝ መንገድ ቢጓዝ የሚያገኘው ጉዳትም የተገለጸው በዚያው ነው፡፡ አምላክ እነዚህን እውቀቶች ለማስጨበጥ የቀደሙት ሰዎች ከእርሱ ጋር በመታዘዛቸው የተጠቀሙና እርሱን ትተው ሌላ በማምለካቸው የከሰሩትን ሰዎች የሕይወት ታሪክ በምሳሌነት ሊጠቀም ይችላል፡፡ ይህን የመሰለው ገለጻ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን ውስጥ በጉልህ የታየ ጉዳይ ነው፡፡

የአምላክን ፈቃድ በማወቅ መታዘዝን ፈልጎ እውቀት ለማግኘት መጽሐፍቱን የሚጠቀም ሰው በራሱ ግንዛቤ ልክ መዝኖ ያልመሰለውንና ለመቀበል ያዳገተውን ነገር ይህ የማይታመን ስለሆነ፣ የአምላክ ቃል አይደለም እንዲል ከመጽሐፍቱ ፈቃድ አይሰጡትም፡፡ ይልቁንም ተረጋግቶ "ለምን ሆነ?" ብሎ በመጠየቅ ከሰዎቹ ስህተት በመማር የራሱን ሕይወት ከተመሳሳይ ስህተትና አደጋ እንዲጠብቅ ይመከረዋል፡፡ መልካም ምሳሌ የሚሆን ከሆነም ፈለጉን እንዲከተል ያሳስበዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ቃሉ እውነተኛ የአምላክ ቃል መሆኑን ከልቡ እርግጠኛ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ቅድሚያ መጽሐፉ ከእግዚአብሔር እንደሆነና እንዳልሆነ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ለምን? እንዴት? መቼ? በማለት በመጠየቅ እዲጀምር ይመክራል፡፡ ምናልባት ግልጽ ቢያደርግልኝ ከቁርአን አንድን አንቀጽ እንመልከት፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 65**

> እነዚያንም ከእናንተ ውስጥ በቅዳሜ ቀን (ዐሣን በማጥመድ) ወሰን ያለፉትንና ለነሱ «ወራዳዎች ስትኾኑ ዝንጀሮዎች ኹኑ» ያልናቸውን በእርግጥ ዐወቃችሁ፡፡

وَلَقَدْ عَلِمْتُمُ الَّذِينَ اعْتَدَوْا مِنكُمْ فِي السَّبْتِ فَقُلْنَا لَهُمْ كُونُوا قِرَدَةً خَاسِئِينَ

በዚህ አንቀጽ ሰው ዝንጀሮ ሆነ፣ የሚለው ዜና መሠረታዊ ችግር ያለበትና የሰው አዕምሮ ሊቀበለው የማይችል ዜና ነው፡፡ ሆኖም ለሰሚ ግራ ቢሆንም፣ ለምርመራ የሚያነብ 'ሰው ወደ ዝንጀሮነት ተቀየረ' መባሉን አዕምሮው መቀበል ስላልቻለ 'ቁርአን የአላህ ቃል አይደለም' ማለት አይችልም፡፡ አላህ አጥፊንና ለቃሉ የማይታዘዝን በፈለገው መልኩ የመቅጣት መብት አለው፤ ለምን ይህንን አደረግህ? ሊለው የሚችል የለም፡፡ ነገር ግን የሕይወት አካል ለማድረግ ቁርአኑ የአላህ ቃል መሆኑንና አለመሆኑን ከመመርመር መጀመር ተገቢ ይሆናል፡-

- ሕዝቡ እንዲህ አይነቱ ፍርድ የደረሰበት በምን ምክንያት ነው? አላህ በዚህ አይነት ሁኔታ ለመቅጣት ያነሳሳው ምን አይነት ኀጢአት ቢሠሩ ነው?
- ቅጣቱስ ከአላህ በህሪ ጋር ያለው ተዛምዶ ትክክል ነውን?

- ይህ ተውራታዊ እንጂ ቁርአናዊ ሕግ አይደለም፡፡ ስለሆነ ተውራቱ ለሰንበት ተላላፊዎች ያዘዘው ቅጣት እንዲህ አይነት ቅጣት ነበርን? በእነ ሙሴ ዘመንስ በዚህ መልክ የተቀጣ ሰው ነበርን?
- አላህ በታሪኩ ውስጥ እንዴት ተገልጧል? የቀደሙት ነቢያት እርሱን የገለጹበት መንገድና በታሪኩ ውስጥ የተገለጸበት መንገድ ተመሳሳይ ነውን? የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን በመጠየቅ የመመርመርና የመተቸት መብትን መጽሐፉ በሙላት ይፈቅድለታል፡፡

ይህንን መንገድ ወጥቶ ለመተቸት የሚነሳ ሁሉ ከመሳሳት አይተርፍም፡፡ እራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩት ወገኖችም በስህተት አዘቅት ውስጥ ሰጥመዋል፤ የተሳሳተም ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት በሞከሩበት ሥራዎቻቸው ለአላህም ሆነ ለሕዝባቸው ታማኞች አለመሆናቸው በግልጽ አሳይተዋል፡፡ ለምን ይሆን ይህን የመሰለ ታማኝነት የጎደለው ሥራ ለማከናወን የተበረታቱት? ብዬ ስጠይቅ እነዚህን መልሶች አግኝቻለሁ፡-

1) "እኔ ብቻ ትክክል ስሆን ሌላው ሁሉ ስህተት ነው፡፡" በሚለው የጽንፈኛ አባዜ የተጠቁ በመሆናቸው ነው፡፡

አበው "ሞኝ ያሸንፋል፣ እንዴት? ቢሉ እምቢ ብሎ፡፡" ያሉት አይነት ነው፡፡ እውነተኛ ነኝ ስላሉ ብቻ እውነተኛ አይኮንም፡፡ እውነት የተጨበጠ ምስክርና አሳማኝ ማስረጃ አለው፡፡ ሰው ስለሚያምነው ከመናገሩ በፊት እምነቱ በእውነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ ግዴታው ነው፡፡ ይህን ሳያደርግ ብዙ ቢያወራ፣ እምነቱ እውነት አለመሆኑን በተጨባጭ መረጃ የሚያውቁ ወገኖች ሊስቁበት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች አድርገው የሚቆጥሩ ወገኖች እየሆኑ ያሉት እንዲህ ነው፡፡ የሃይማኖታቸው መሠረት የሆኑት ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት እውነት ናቸው፣ ስለተባሉ ብቻ የሰሙትን አምነው የሚጓዙ እንጂ፣ ላመኑበት እውነትነት ማስረጃ ኖሯቸው በዚያ ላይ የተመሠረቱ ወገኖች አይደሉም፡፡ እውነተኞች እንደሆኑ ለማሳየት የሚጥሩት ሌላውን ሐሰተኛ በማስመሰል ውስጥ እንጂ የራሳቸውን እውነት በመዘርዘር አይደለም፡፡ ስለሚከተሉት እምነት እውነተኛነት ተጨባጭ መረጃ ማቅረብ ለእነርሱ ተራራን እንደመውጣት ነው፡፡

2) በሌሎች ሃይማኖቶች መጽሐፍት ይቅርና በራሳቸው ቁርአን ውስጥ አንዱ ከሌላው እየተቃረነም ቢሆን፣ አላህንና ኀጢአትን፣ እንዲሁም አላህ ስለ ኀጢአት ያለውን አቋም በትክክል አለማወቃቸው

ሐዲሳቱም ሆኑ ቁርአን፣ የአላህን ባህሪ፣ ለኀጢአትም ያለውን አቋም በግልጽ መዝግበው የያዙ አይደሉም፡፡ እናም በአመኙ ውስጥ እንዲህ አይነት ስሜት

ቢፈጠር የሚገርም አይሆንም፡፡ ይህ ችግር የዳኢዎቹ ብቻ ሳይሆን፣ የነቢዩም ጭምር ነበር፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 9፣ # 7487**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- ገብርኤል ወደ እኔ መጣና የምስራች አበሰረኝ፡፡ ያም ማንኛውም ሰው ከአላህ ሌላ ሌላን ካላጋራ ቢሞትም ገነት ይገባል አለኝ፡፡ እኔም ስርቆት ቢፈጽም? ደግሞም ዝሙት ቢፈጽም ይገባልን? ስል ጠየቅሁት፡፡ እርሱም አዎን፤ ቢሰርቅም ዝሙትም ቢፈጽምም ይገባል አለኝ፡፡[125]

- ወገኖቼ የገሃነም ሰዎች ሥራ የተባለው ይህ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? እነዚህን ኀጢአቶች መፈጸም ከገነት የማያስቀር ከሆነ የሸሪአን ሕግ በእነዚህ ላይ መደንገግ ለምን አስፈለገ? አላህ እንዲህ አይነት ሥራ የሠራውን ገነት የሚያስገባ ከሆነ፣ ቁርአን ተቃርኖ በተቃርኖ መሆኑ አይደለምን? ለምን ይሆን አላህና ነቢዩ ሙሐመድ ይህንን ማስተዋል ያልቻሉት?
- መልአኩ ገብርኤልስ ቢሆን እየመጣ የሚያስተምራቸው የቁርአን ቃል ምን እንደሚል ዘንግቶት ይሆን፣ የምስራች ተብዬ የኀጢአት ማበረታቻ ዜና የተናገረው?
- ገብርኤል ይህንን ካላቸው፣ ለምን ይሆን ታዲያ ነቢዩ ራሳቸው ጀነት ለመግባታቸው እርግጠኛ ያልሆኑት? እናንተም የእስልምናው ዳኢዎች እርግጠኞች አይደላችሁም፤ መላው ሙስሊም ማሕበረሰብ እርግጠኛ አይደለም፤ ለምን?

3) ሌላው በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ያለውን ልዩነት በቁርአን መነጽር ተመልክተው ድምዳሜ መስጠታቸው

እነርሱም እንደሚያምኑት በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ለምሳሌ አዳምን እንውሰድ፤ አዳም ያለኀጢአት፣ ሞት ለሌለበት ደስታ ተፈጥሮ በገነት ይኖር እንደ ነበር፣ ይህ ንጹሕ ሰው በሰይጣን ተታሎ ከመኖሪያው እንደተባረረበ ሁለቱም መጽሐፍት ይታወቃል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ሞት እንደ ነገሠበት ሲናገር ቁርአን ሞት አብሮት እንደተፈጠረ ያወራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለዚህ ሞት ለነገሠበት ሰው ያለውን ጥልቅ ፍቅር፣ እንደገናም የሚድንበትን መንገድ እንዳዘጋጀለት፣ ይህንን መንገድ የወደደ ሰው ወደ ገነት ተመልሶ ከአምላኩ ጋር በደስታ እንደሚኖር የተናገረበት፣ አምላክ እራሱን ለሕዝቡ የገለጠበት የኪዳን መጽሐፍ ነው፡፡ ቁርአን ግን አላህ ለፈተና የፈጠረውን፣ ከመፈጠሩም በፊት የገሃነም ወይም የገነት ሰው መሆኑን

---

[125] *Sahih al-Bukhari vol 9, page 352*

የወሰነበትን፣ ተስፋ ቢስ ሰው ለማስፈራራትና ለማስጠንቀቅ የተላከ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ በሁለቱ መካከል ያለ እጅግ ግዙፍና ሊገናኝ የማይችል ልዩነት ነው፤ የአላማም፣ የተልእኮም ዝምድና የላቸውም፡፡ እንዲህ ሆኖ እያለ መጽሐፍ ቅዱስን በቁርአን መነጽር ለመመልከት መሞከር ይህ ነው የማይባል ስህተት ይሆናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ባህሪና ለኀጢአት ያለውን አቋም ሳይሸራርፍና ሳያቃርን በግልጽ የሚናገር የአምላክ ቃል ነው፡፡ ቁርአን ደግሞ ለኀጢአት ያለውን አቋም በግልጽ ያላስቀመጠ፣ የሚያቃርንና እራሱ የአምላክ ቃል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሌለው መጽሐፍ ነው፡፡ እንዲህ በመሆኑም አንባቢ የታሪክ ፍሰቱን ተከትሎ በመሄድ መልእክቱን በመረዳት ሞጋች ነገሮችን እንዳያነሳ ለማድረግ ታስቦ የተሰደረ፣ በወረደበት ቅደም ተከተል፣ ሳይሆን በተዘበራረቀ መልኩ በኢራቃዊው በሃፍስ የተጠረዘ መጽሐፍ ነው፡፡ የኢራቃዊውን የሃፍስን ስም የጠቀስኩት አሁን ያለው ቁርአን በከሊፋ ኡስማን የተዘጋጀው ባለመሆኑ ነው፡፡ ይህንን በመጀመሪያው ገጾች በምስል አስደግፌ ባቀረብኩት ላይ ማስነበቤን አትዘነጉትም ብዬ አስባለሁ፡፡ ስለዚህ ይህንን ውል የጠፋበትን በጭፍን የሚከተሉ፣ በእርሱም ታንጸው ያደጉ በመሆናቸው ታማኝነት የጎደለው ማንነታቸው ሊታይ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡

አንዱ ሱራ በሱራዎች አቀማመጥ የአወራረድ ቅደም ተከተል ያለበት ደረጃና በአሁኑ ቁርአን ውስጥ የሚገኝበትን ምዕራፍ እንዴት እንደሆነ ናሙና ላሳያችሁ፡፡ እንዲያውም በሌሎቹ ሱሃባዎች የቁርአን ቅጅ ምን አይነት ደረጃ እንደነበረው አያይዤ ባሳያችሁ ጥሩ አይመስላችሁም?

| ሱራ | የወረደበት ቦታ | ምእራፍ በአሁኑ በቁርአን | በተለያዩ ሱሃባዎች ቁርአን የነበረው ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በኢንብ መስኡድ | በኡቤይ ቢን ካብ | አሊ ኢብን አቡ ጣሊብ | በኢብን አባስ |
| አል-ፋቲሃ | መካ | 1 | አይቀበልም | 1 | አይቀበልም | 6 |
| አል-በቀራ | መዲና | 2 | 1 | 2 | ጁዝ 1፣ ተቁ 1 | 84 |
| አሊ-ኢምራን | መዲና | 3 | 3 | 4 | ጁዝ 2፣ ተቁ 1 | 86 |
| አል-ማኢዳ | መዲና | 5 | 6 | 7 | ጁዝ 4፣ ተቁ 1 | 108 |
| አል-አንአም | መካ | 6 | 5 | 5 | ጁዝ 5፣ ተቁ 1 | 52 |
| አል-አዕራፍ | መካ | 7 | 4 | 6 | ጁዝ 6፣ ተቁ 1 | 37 |
| አል-አለቅ | መካ | 96 | 86 | 70 | አይቀበልም | 1 |
| አል-ቀለም | መካ | 68 | 68 | 56 | ጁዝ 5፣ ተቁ 11 | 2 |
| አል-ሰመድ | መካ | 111 | -- | 102 | ጁዝ 3፣ ተቁ 10 | 7 |
| አል-ናስ | መካ | 114 | አይቀበልም | 106 | አይቀበልም | 114 |

ዳኢ ሰዲቅ ሙሐመድ በዛው "ላለመደናገር ማመሳከር" በተሰኘው መጽሐፉ የቁርአንን ሱራዎችና አንቀጾች ቅደም ተከተል የማስያዙ ሥራ የተሰራው አላህ ባሳያቸው መሰረት በራሳቸው በነቢዩ ሙሃመድ እንደሆነ፣ ይህ አሁን ያለው

ይዘት ያኔ በነቢዩ ዘመን የተከናወነ እንደሆነም ይናገራል[126]፡፡ ይህ በራሱ በቁርአን የአላህ ቃልነትና በነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛነት ላይ እንዲሁም በቁርአን ንጽህና ላይ ብርቱ ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል፡፡ ያንንም በተወሰነ መልኩ ሠንጠረዡን ስታዩ ያስተዋላችሁት ይመስለኛል፡፡ ይሁንና እንዲያ ከሆነ ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ፡-

❖ መጀመሪያ የወረደው ሱረቱል አል-አለቅ ወይንስ የቁርአኑ 114 ሱራዎች ማውጫ? ማውጫ ቀድሞ የወረደ ካልሆነ፣ የሚወርደውን አንቀጽ ይህን ከዚህኛው፣ ያ ደግሞ ከዚያኛው ይሁን፣ በማለት መደልደል እንዴት ቻሉ? የወረደው የሱራዎቹ ማውጫ ከሆነ ደግሞ፣ አንብብ እየተባሉ በሂራ ዋሻ በእንግዳቸው የተገደዱት ሱረቱል አል-አለቅን ነበር ተብሎ ለምን ይዋሻል?
❖ ከዚህ በተቀራኒው ያስብ የነበረው ከሊፋ አሊ የራሱን ቁርአን ነቢዩ ከሞቱ ከስድስት ወራት (ሦስት ቀናትም የሚሉ አሉ) በኋላ ባዘጋጀበት ወቅት የአወራረዱን ቅደም ተከተል ጠብቆ አዘጋጅቶ ነበር[127]፡፡ ታዲያ ነቢዩ በሕይወት እያሉ ካዘጋጁት ይህ የመጀመሪያ ሙስሊም፣ ከሌሎቹ ይልቅ ለነቢዩ ቅርበት ያለው ሰው እንዴት እንዲያ ሊያዘጋጅ በቃ?
❖ የቁርአን አሰባሰብና አሰዳደር ታሪኮች እንደሚያሳዩት እንዲህ አይነቱ መለያየት ያለው በዚህ ሰው ባቻ ሳይሆን የራሳቸውን ቁርአን ባዘጋጁ ሱሃባዎች ሁሉ ነው፤ ሰንጠረዡም የሚያሳየው ያንን ነው፡፡ መለያየቱም የሚብሰው የቁርአን አስተማሪዎች ተብለው በነቢዩ በተሾሙትና የእርሳቸው የግል ጸሐፊ ነበሩ በተባሉት ሰዎች መካከል ነው፡፡ ቅደም ተከተሉ የተሠራው በነቢዩ በራሳቸው ከሆነ፣ ሁሉም ሱሃባዎች በጉዳዩ መለያየታቸውን ምን አመጣው?
❖ ከሊፋ ኡስማን በሰዎች እጅ የሚገኙ ሌሎች የቁርአን ቅጅዎችን በእሳት የማጋየቱ አንዱ ምክንያት ይህ ላለመሆኑ ምን ማስረጃ አለ? ሁሉም በነቢዩ ዘመን የተከናወነ ከነበር፣ ተጨማሪው የሱሃባዎቹ ሥራ ለምን አስፈለገ?
❖ የነቢዩ ሙሐመድ ጸሐፊዎች ነበሩ የተባሉት ሁሉም ለነቢዩ ራዕይ መውረድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከእርሳቸው ጋር አብረው የነበሩ ሰዎች አልነበሩም፡፡ ለምሳሌ ዛይድ ቢን ሳቢት ነቢዩ ሙሐመድ ከመካ ተሰደው መዲና በገቡበት ወቅት ገና 11 ዓመት ያልሞላው ሕጻን ነበር፡፡ ከሊፋ አሊ ግን እንደ ልጅ በቤታቸው ያደገ ሁሉ ሲሆን፣ አብሮ የነበር ሰው ነበር፡፡ ሆኖም ሁለቱም ቁርአኑን በማዘጋጀቱ የተለያየ መንገድ ተከትለዋል፡፡ ታዲያ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ የተናገሩት በምን መንገድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል?

---

126 ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 82

127 *The History of the quran, part 4, page 45; Theodor Nöldeke, The History of the Qur'ān, page 221*

ሌላው አላህ ባሳያቸው መሠረት ነቢዩ አደረጉት ብሎ ማለት ግን አላህን ሰዎችን የሚፈራ አምላክ ስለሚያስመስለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ቁርአን በተለያዩ መስፈርቶች ሲፈተሽ በስህተቶችና በተቃርኖዎች የተጣበበ መሆኑ ይታወቃል፤ የአላህ ቃል ለመሆኑም ራሳቸው ነቢዩ ሙሐመድም ሆኑ በየዘመናቱ የነበሩ የሃይማኖቱ ምሁራን የተጨበጠ ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ድርጊቱ የተፈጸመው የእስልምና ተቃዋሚዎችን ትችትና ስሕተት ፍለጋን በመፍራት ውሉን እንዳያገኙት ለማድረግ ታስቦ መሆኑን አምኖ መቀበል የተሻለ ነው፡፡ ቁርአንም ሲወርድ በነበረበት ዘመን ስለነበረው የተቃዋሚዎች ስህተቶችን ነቅሶ የማውጣትና የአላህ ቃል አለመሆኑን አጉልቶ የማሳየት ሥራቸውን እንዲህ ገልጾት ይታያል፡-

**ሱረቱል አሊ-ኢምራን 3 ፡ 7**

እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሐፉን ያወረደ ነው፡፡ ከእርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የኾኑ አንቀጾች አልሉ፡፡ እነሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው፡፡ ሌሎችም ተመሳሳዮች አልሉ፡፡ እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን ለመፈለግና ትችቱን ለመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ፡፡ (ትክክለኛ) ትችቱንም አላህ ብቻ እንጅ ሌላ አያውቀውም፡፡ በዕውቀትም የጠለቁት «በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው» ይላሉ፡፡ የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሰጽም፡፡

هُوَ الَّذِي أَنزَلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ مِنْهُ آيَاتٌ مُّحْكَمَاتٌ هُنَّ أُمُّ الْكِتَابِ وَأُخَرُ مُتَشَابِهَاتٌ ۖ فَأَمَّا الَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمْ زَيْغٌ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَابَهَ مِنْهُ ابْتِغَاءَ الْفِتْنَةِ وَابْتِغَاءَ تَأْوِيلِهِ ۗ وَمَا يَعْلَمُ تَأْوِيلَهُ إِلَّا اللَّهُ ۗ وَالرَّاسِخُونَ فِي الْعِلْمِ يَقُولُونَ آمَنَّا بِهِ كُلٌّ مِّنْ عِندِ رَبِّنَا ۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّا أُولُو الْأَلْبَابِ

ውድ አንባቢ፤ እንዲህ መያዣ መጨበጫ የሌለው ቁርአን ከፍጥረት ጅማሬ በመጀመር በዘመን ፍጻሜ ጻድቃን በገነት ከአምላካቸው ጋር የዘለአለሙን ደስታ ኑሮ መኖር ሲጀምሩ፣ ኀጢአተኞችም ከሰይጣን ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ሲገቡ በማሳየት ከሚደመድም፣ ማንንም ሳይፈራ ታሪካዊ ቅደም ተከተልን ጠብቆ ከዘገበ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዴት ማወዳደር ይሞከራል?

4) የቁርአንን ስነ አፈታት ስርዓት እንደሚጠብቁት ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ስነ አፈታት ስርዓት አለመጠበቃቸው ሌላው ችግራቸው ነው

አምላክ ኀጢአተኛን በፈለገው መልኩ የመቅጣት ሙሉ ስልጣን እንዳለው ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እናም መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 6 ፡ 26-29 የተገለጸችው እናት ‘ልጇን እንዴት በላች ይላል? አላምንም እናት ልጇን ልትበላ አትችልም’ ሳይሆን መባል ያለበት ለምን በላች? በሙሴ ከተሰጠው ህግ ጋር ያለው ቁርኝት

ምን ይመስላል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ያለ አምላካችን ቃል ምስክር ምንም ነገር አልተከናወነም፡፡

ጊዜው ንጉሡና ሕዝቡ በሙሴ የተሰጠውን የአምላካቸውን ሕግ መታዘዝና እርሱን ማምለክ ትተው ኢዮርብአም የሄደበትን ጠማማ መንገድ የተከተሉበት ወቅት ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ፊት አጸያፊ የሆነውን የጥጃ ጣኦት አምልኮ ያከናወኑ ነበር፡-

**መጽሐፈ ነገስት ካልዕ** 3 ፡ 1-3

በይሁዳም ንጉሥ በኢዮሣፍጥ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ ኢዮራም በእስራኤል ላይ በሰማርያ መንገሥ ጀመረ፥ አሥራ ሁለትም ዓመት ነገሠ። በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ ነገር ግን አባቱ ያሠራውን የበኣልን ሐውልት አርቆአልና እንደ አባቱና እንደ እናቱ አልነበረም። ነገር ግን እስራኤልን ባሳታቸው በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት ተያዘ ከእርሱም አልራቀም።

ቁርአንም እንደሚያምነው ይህ አይነት አምልኮ ከዚያ በፊት ብዙዎችን ለቅስፈት አብቅቷል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድና ተከታዮቻቸውም የብዙዎችን ነፍስ ለማጥፋትና ወደ ገሃነመ እሳት ለመላክ እንደ ምክንያት ተጠቅመውበታል፡፡ /ሱረቱል ጣሃ 20 ፡ 88/

**መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ** 12 ፡ 28-31

ንጉሡም ተማከረ፥ ሁለትም የወርቅ ጥጆች አድርጎ። እስራኤል ሆይ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል፣ ከግብጽ ምድር ያወጡህን አማልክቶችህን እይ አላቸው። አንዱን በቤቴል፥ ሁለተኛውንም በዳን አኖረ። ለአንዱ ጥጃ ይሰግድ ዘንድ ሕዝቡ እስከ ዳን ድረስ ይሄድ ነበርና ይህ ኃጢአት ሆነ። በኮረብቶቹም ላይ መስገጃዎች ሠራ፥ ከሌዊ ልጆች ካይደሉ ከሕዝብ ሁሉ ካህናትን አደረገ።

እስራኤል በዚህ አይነት ኃጢአት እንዳይገኝ እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ በሙሴ በኩል አስጠንቅቆ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡-

**ኦሪት ዘፀአት** 20 ፡ 1-6

እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ። ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥

አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።

በእስራኤል ዘንድ ይህ ትእዛዝ ተጥሶ አምላካቸውን ትተው ጣኦትን አንተ አምላካችን ነህ ሲሉ እንመለከታለን፡፡ በዚህ የጣኦት አምልኮ ኀጢአት ቢገኙ ደግሞ የአምላካቸውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰዋልና በዚህ ምክንያት ሊገጥማቸው ያለውን የቅጣት አይነት ሙሴ ዘርዝሮ ነግሯቸው ነበር፡-

**ኦሪት ዘዳግም** 28 ፡ 15፣ 53

*ገር ግን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ሁሉ ባትጠብቅ ባታደርግም፥ እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይመጡብሃል ያገኙህማል።... ጠላቶችህም ከብበው ባስጨነቁህና መከራ ባሳዩህ ጊዜ፣ አምላክህ እግዚአብሔር የሚሰጥህን **የሆድህን ፍሬ የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ሥጋ ትበላለህ**።*

**ኦሪት ዘሌዋውያን** 26 ፡ 27-30

*እስከዚህም ድረስ ባትሰሙኝ፥ በእንቢተኝነትም ብትሄዱብኝ፥ እኔ ደግሞ በቍጣ እሄድባችኋለሁ፣ ስለ ኃጢአታችሁም ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ። **የወንዶች ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ የሴቶች ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ**። የኮረብታ መስገጃዎቻችሁንም አፈርሳለሁ፥ የፀሐይ ምስሎቻችሁንም አጠፋለሁ፥ ሬሳችሁንም በጣዖቶቻችሁ ሬሳዎች ላይ እጥላለሁ ነፍሴም ትጸየፋችኋለች።*

እንግዲህ የሆነው የእስራኤል ሕዝብ የአምላካቸውን ትእዛዛት በመጣሳቸውና የጣኦት አምልኮን ሙጥኝ በማለታቸው የዚህ እርግማን ፍጻሜ በእነርሱ ላይ ሊመጣ ችሏል፡፡ የእርግማኑን ቃል ለማስፈጸም የሰማርያ ከተማ በሶሪያ ወታደሮች እንድትከበብ ተደረገ፡፡ የከተማዋ የቅጥር በሮችም ተዘጉ፤ ማንኛውም እንቅስቃሴ ተቋረጠ፤ ንግዶች ቆሙ፣ ወደ እርሻ መሄድ ስለ ቀረ፣ የምግብ ፍጆታ አቅርቦት ተቋረጠ፡፡ ቢኖርም ዋጋው በቀላሉ የሚቀመስ አልነበረም፤ ርሃቡ ጸና፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር፤ የእናትነት ስብዕናዋ የሞተባት እናት ልጇን ቀቅላ ለመብላትና በሕይወት ለመኖር ከጓደኛዋ ጋር የተማከረችው፡፡ የምትገርም እናት፤ እንዴት አሳቡስ መጣላት?

ውድ አንባቢ ፍርዱን ወደ እርስዎ ላምጣው፡፡ ይህ ራሳቸውን እንደ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚያስቡት ወገኖች "አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው" ያሉት ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስን ታማኝነት አያረጋግጥም ይላሉ? ይልቁንም የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነቱን የሚያደምቁ፣ የሚሰጣቸው ምክንያቶች አሳማኝ የሆኑ፣

ለኀጢአት ትክክለኛ ትርጉም የሰጡና እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ ያለውን ግልጽ አቋም የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህንን አይነት የመለኮታዊ ቃል ባህሪ ቁርአን ውስጥ ማየት ፈጽሞ አይችሉም፤ ምክንያቱም የዘለአለሙ አምላክ የአላህ ቃል አይደለምና፡፡

## 2.2. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 21 ፡ 16-20

*….መንግሥ በጀመረ ጊዜ የሠላሳ ሁለት ዓመት ጕልማሳ ነበረ፥ በኢየሩሳሌምም ስምንት ዓመት ነገሠ ማንም ሳያዝንለት ሄደ በዳዊትም ከተማ እንጂ በነገሥታት መቃብር አልቀበሩትም።*

**መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ** 22 ፡ 1-2

*…የይሁዳ ንጉሥ የኢዮራም ልጅ አካዝያስ ነገሠ። አካዝያስም መንግሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው አርባ ሁለት ዓመት ነበረ፥ በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ እናቱም ጎቶሊያ የተባለች የዘንበሪ ልጅ ነበረች።*

*የማይታመነው የአባት እድሜ ከልጅ እድሜ በሁለት ዓመት አንሶ መገኘቱ ነው፤* ብለዋል[128]፡፡

*በእርግጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የስነ አፈታት ስርዓት ውጭ ሆኖና በሌላኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያለውን የዚህን ዘገባ አካል ሳያነብ እነዚህን ሁለት የነገስታት ታሪክ ዘገባዎችን ለሚያይ ግራ አጋቢ ይመስላሉ፡፡ በቅንነት ለሚያነብ ደግሞ ልጅ ከአባቱ በእድሜ ሊበልጥ እንደማይችል ተፈጥሮ ስለምትነግረው ችግሩ ችግር ከተባለ እንዲህ አይነት ስህተት የተከሰተበትን ምክንያት ሊገምት ይችላል እንጂ ግራ ሊጋባ አይችልም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ስነ አፈታት ስርዓት ውስጥ ሆኖ የሚያነብ እውነተኛ ሰው በነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ የሚመለከተው በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራና ከእርሱ ጋር በተያያዘ የሠሩ የቀደሙ አባቶችና አሁን እየሠሩ ያሉ ምን ያህል እውነተኞችና ታማኞች መሆናቸውን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለተጠያቂነት ያበቃው ይህ ጥቅስ እንከ አሁን ድረስ በመጽሐፉ ሰዎች ሳይታወቅ ቀርቶ እዚህ የደረሰና ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ የሚያስቡት አሁን ላይ ያገኙት መስሎ እንዳይሰማቸው ላሳስብ እወዳለሁ፡፡ የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ ስልጣኑ ተከብሮና ተጠብቆ እንጂ ይህ ኢምንት ስህተት እንዳለ በእኛ ዘንድ ቀድሞውንም የታወቀ መሆኑን ሊገነዘቡ የገባል፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ* 40 **ክፍለ ዘመናትን** *ያስቆጠረ የእድሜ ባለጸጋ ነው፡፡ ይህ ድንቅ መጽሐፍ የተጻፈበት የመጀመሪያው ብራና ሲያረጅ በአዲስ እየተገለበጠ*

---

[128] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 34

ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ተደርጓል፤ በዛ ሁኔታ አልፎ እኛ ዘመን ላይ ደርሷል፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅትና በትርጉም ሥራ ጊዜ ከቋንቋዎች ባህሪና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ዋጋቸው ተአማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊከቱ የማይችሉ ስህተቶች ተፈጥረዋል፡፡ በተለይ በእስራኤልና በነገስታቶቿ ታሪክ ውስጥ አንዳንድ የቁጥርና የስም ልዩነቶች ተከስተዋል፡፡ ቢሆንም እንደተባለው ፈጽሞ ግራ አጋቢ ሊሆኑ የሚችሉ ግን አይደሉም፡፡ በእግዚብሔር ጥበቃ ሥር ያለ በመሆኑ ችግሮች የተባሉትን መፍታት ይቻል ዘንድ ቀደምት ቅጅዎች እንደ ቁርአን አልተቃጠሉም ዛሬም ድረስ በሕይወት አሉ፡፡ እነርሱን በመጠቀም ለችግሩ ምላሽ ማግኘት ይቻላል፡፡

የዚህን "ሊታመን የማይችል" ተብሎ የተጠቀሰውን የአባትና የልጅ እድሜ ጉዳይ ለመፍታት እሩቅ ሳንሄድ ሌላም ሳያስፈልግ መልሱን እዛው የመጽሐፉ ሌላኛው ክፍል ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ እንዲህ ይላል፡-

**መጽሐፈ ነገስት ካልእ 8 ፡ 26**

*መንገሥ በጀመረ ጊዜ አካዝያስ የሃያ ሁለት ዓመት ጕልማሳ ነበረ በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ። እናቱም ጎቶልያ የተባለች የእስራኤል ንጉሥ የዘንበሪ ልጅ ነበረች።*

የተፈጥሮው ሕግ ነውና የልጅ እድሜ ከአባት አይበልጥም፡፡ እናም አባት በጊዜው የአርባ አመት ጎልማሳ ነበር፡፡ ልጁ ወደ ዙፋን ሲመጣ የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት እንደ ነበር ይታያል፡፡ ይህ ስህተት ታዲያ እንዴት ተፈጠረ? ማለታችሁ አይቀርም፡፡ ሁለቱ ቁጥሮች ማለትም 42 እና 22 በዕብራይስጥ የቁጥር አጻጻፍ ስርአት ተቀራራቢ ቅርጽ አላቸው፤ (a similarity of the numeral letters, מב, forty two, for כב, twenty two)[129] በቁም ጽሁፎች ከብራና ወደ ብራና ሲገለበት በአጻጻፍ የተፈጠረ ስህተት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ችግሩ ከላይ በተመለከተው መልኩ ስለተፈታ ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝነት ሳንካ ሊሆን ከቶውን አይችልም፡፡

## 2.3. ትንቢተ ሕዝቅኤል 4 ፡ 9-12

*አንተም ስንዴንና ገብስን ባቄላንና ምስርን ጤፍንና አጃን ወደ አንተ ውሰድ፥ በአንድ ዕቃም ውስጥ አድርገህ እንጀራ ጋግር በጐድንህ እንደ ተኛህበት ቀን ቍጥር ሦስት መቶ ዘጠና ቀን ትበላዋለህ። የምትበላውም በሚዛን በየቀኑ ሀያ ሀያ ሰቅል ይሁን፥ በየጊዜው ትበላዋለህ። ውኃውንም በልክ የኢን መስፈሪያ ከስድስት እጅ አንድን እጅ ትጠጣለህ፥ በየጊዜው*

---

[129] *John Gill, Exposition of the entire bible, published in1748-1763, 1809, E-SWORD bible software.*

ትጠጣዋለህ። እንደ ገብስ እንጐቻም አድርገህ ትበላዋለህ፥ ከሰውም በሚወጣ ፋንድያ በፊታቸው ትጋግረዋለህ።

የማይታመነው ነገር አላህ ነቢይን የሰውን ፋንድያ እንደ ምግብ እንዲጠቀም ማዘዙ ነው፡፡[130]

አንድን ምንባብ በትክክል አንብበው ሳይጨርሱ አላማ የለሽ የመከራከሪያ አሳብ ማንሳት እያገለገሉት ያሉ የመሰላቸውን አላህን አለመፍራት ነው፡፡ ደግሞም በሰሚም በአንባቢም ትዝብት ውስጥ የሚጥል ይሆናል፡፡ እኛ ነን ትክክል ለሚሉበት ሃይማኖታቸው እንዲሁም ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ ታማኝ ምስክር አለመሆናቸውንም ያሳያል፡፡ ይህንን የማይታመን ያሉትን የትንቢት መልእክት የሚያነቡ ወገኖቻቸውም በእውነት ይታዘባሉ፡፡ ውድ አንባቢ፤ እባክዎን መጽሐፍ ቅዱስ ከአቅራቢያዎት ካለ **ትንቢተ ሕዝቅኤል 4 ፡ 9-17** ያለውን ክፍል አንዴ ከፍተው ያንብቡትና ትዝብተዎትን ይስጡበት፤ ጭፍን ክርስትናን የማጥላላት ዘመቻ ነው፡፡

ለመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ መልስ የሚሆነውን መስጠት ይኖርብኛል፡፡ የትንቢቱ ቃል የኢየሩሳሌም ሕዝብ ከሠሩት ኀጢአት የተነሳ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊሆንባቸው ስላለው የአምላካቸው ቁጣውንና ቅጣት ይናገራል፡፡ ነቢዩ መልእክቱን ድራማዊ በሆነ መልኩ እንዲያስተላልፈው በእግዚአብሔር ቃል ሲታዘዝም እንመለከታለን፡፡ በዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ ቀን ሕዝቡ ከሚደርስባቸው የምግብና የውሃ እጦት፣ በባእድ ምድር ከመበተናቸው የተነሳ እንዴት ከመልካሙ ኑሯቸው እንደሚጎድሉ፣ ከቅድስናው እንደሚረክሱ ለማሳየት ነው፡፡ በዚያን ወቅት ማገዶም ስለሚጠፋ በሚያረክሰው ነገር ምግባቸውን እንደሚያበስሉ እንዲያሳይ ሲታዘዝ እንመለከታለን፤ መልእክቱን በሰው አይነ ምድር ምግቡን እያበሰለ ማስተላለፍ ነበረበት፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል ይህን ማድረግ እንዳያረክሰው ስለፈራ ለእግዚአብሔር ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት **ቁጥር** 15 ላይ የሰው አይነ ምድር ከመጠቀም ይልቅ ከእንስሳት በሚገኝ ኩበት ማገዶውን ቀይሮ እንዲጠቀም ሲፈቀድለት እናያለን፡፡ መልካም የሆነው አምላክ የሰውን አይነ ምድር እንዲበላ ነቢዩን በፍጹም አላዘዘም፡፡ ኡስታዝ ሳዲቅ ለአድማጮችዎት እና ለአንባቢዎችዎ ታማኝነትዎ እንዲገለጥ በማስተዋል የማንበብ ችሎታዎትን ለማሻሻል የንባብ ት/ቤት ይግቡ ስል እመክራለሁ፡፡

## 2.4. ኦሪት ዘሌዋውያን 15 ፡ 19-22

ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው። መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው፤

[130] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 35

የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው። የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።

የማይታመነውና አእምሮ የማይቀበለው፡-

- ሴት ልጅ እንዴት ሰባት ቀን በመርገም ትቀመጣለች?
- እንዴትስ ደግሞ የተኛችበት፣ የተቀመጠችበትንና መኝታዋን የነካ ሰው ሊረክስ ይችላል?
- ለእርኩሰትስ ማወራረጃ ደግሞ ገላውን በውሃ ታጥቦ ልብሱንም አጥቦ እስከ ምሽት መርከስ ለምን?[131]

ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩት ወገኖች ስለ እስልምና እውነተኛነት ለመመስከር ከመሞከራቸውና ሌላውን ከመተንኮስ ይልቅ ራሳቸው ለረሳቸው እውነተኞች መሆናቸውን ቢያረጋግጡ መልካም ነበር፡፡ ያን ቢያደርጉ ለሚሰሟቸውና ለሚያነቧቸው ሁሉ ትክክለኛና የሚታመን መረጃ ማቅረብ ባልተቸገሩ ነበር፤ ታማኝነት ከራስ ለራስ ይጀምራል፡፡ ሆኖም በዚህ ሙግታቸው ለአምላካቸውና ለሚሰሟቸው፣ ብሎም ወክለው ለሚናገሩለት ለእስልምና ሃይማኖት፣ ለእምነቱ ተከታይ ማሕበረሰብ ጭምር ታማኝነት የጎደለው ማንነታቸውን በጉልህ ሲያሳዩ በጣም ያሳፍራል፡፡ ምናልባት እንዲህ የሆኑት፡-

- ❖ ከ99 በመቶ የሚሆነው ሙስሊም ስለ እምነቱ መጻህፍት ያለው እውቀት ጥቂት ከማንበብ ያልዘለለ ስለሆነ ይሆናል፡፡ ከዚህ ቁጥር በርካታው ጭራሹን ቁርአንን ማንበብ የማይችል፣ በሚሰማው ብቻ የሚጓዝ ህዝብ ስለሆነ፤ ከዚህ ጋር ራሳቸውን ሲያነጻጽሩ ከሌላው ሰው ይልቅ የበቁ አዋቂ አድርገው ስለቆጠሩ
- ❖ ሙስሊሙ ማሕበረሰብ ለአረብኛ ቋንቋ እንግዳ በመሆኑ፣ የሌላውም እምነት ተከታይ ስለ እስልምና መጻሕፍት ለማወቅ የሚያሳየውን አለመነሳሳት ተመልክተው ሁኔታውን ለራሳቸው ለማስጨብጨብ ሊጠቀሙበት ፈልገውም ይሆናል

ያምሆነ ይህ አሁን ተደናግሮ ሌላውን ማደናገር ይበቃል፤ እንዲህ መቀጠል የለባቸውም፡፡ እውነት አደባባይ ላይ መነገር አለበት፡፡ አዕምሮ ሊቀበለው የማይችል ባዮቹ መጽሐፍ ቅዱስ በወር አበባ ላይ ስላለች ሴትና ከእርሷ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ሁኔታዎች ያስተላለፈውን መልእክቶች ለመተቸት ሲነሱ ነቢዩ ሙሐመድ የወር አበባ ላይ ያለችን ሴት በተመለከተ ለሰጡት ፈትዋ

---

131 ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 35-36

እንግዳ ናቸው ልበል? ነቢዩ ሙሐመድ ውሃን በተመለከተ የተናገሯቸውን ሐዲሳት አላነበቡም ይሆን?

እንግዲህ ለነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት እንግዳ ከሆኑ ደግሞም ካልሰሙና እነርሱን ካላነበቡ እኔ ላስነብባቸው መሰለኝ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 305**

ከነቢዩ ጋር ሐጅ ለመሄድ ጉዞ ጀመርን፣ ሶሪፍ ላይ ስንደርስ የወር አበባዬ መጣ፡፡ ነቢዩ ወደ እኔ ሲመጡ እያለቀስኩ ነበር፤ ለምን ታለቅሻለሽ? ብለው ጠየቁኝ፡፡ እኔም ምንም እንኳን ሐጅ ለማድረግ ብፈልግም በዚህ ዓመት ማድረግ አልችልም ስል መለስኩላቸው፡፡ ከዛም ይህ አላህ በአደም ሴት ልጆች ላይ የወሰነው ነገር ነው፤ ስለዚህ ያሰብሽውን ሐጅ ፈጽሚ፡፡ ነገር ግን ንጹሕ እስከትሆኚ ድረስ ካእባውን መዞር አትችይም አሉኝ፡፡ አይሻ የተናገረችው[132]

- ❖ አይሻ በወር አበባዋ ምክንያት ንጹሕ ካልነበረች፣ በንጹሕ ተቃራኒ ሁኔታ ላይ መሆኗ ግልጽ ነው፤ ያም እርኩስ የሚባለው ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታዋ ወደ "ተቀደሰው" ስፍራ ለአምላኳ ለመስገድ እንዳትሄድ ተከልክላለች፤ ማንኛዋም በወር አበባ ላይ ያለች ሙስሊም ሴት ሐጅ ማድረግ ስትችል፣ ከኡምራና ከመስጊድ ብሎም ከጀምአ ሰላት ሁሉ ትከለከላለች፡፡ ለምን ተከለከለች? ምናልባት ሐጁንም የፈቀዱት በጣም የሚያፈቅሯት፣ በስድስት ዓመት ያጯትና በዘጠኝ ዓመት እድሜዋ ላይ ክብሯን የሰጠቻቸው ሐጻኗ ሚስታቸው ስላለቀሰችባቸው አንጀታቸው አልችል በሎ ይሆን? እንዲህ ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱሱ ስርዓት ለአዕምሮ እንዲከብድባቸው የሚያደርገው ምኑ ነው?
- ❖ ነቢዩ አይሻን "ንጹህ እስካልሆንሽ" ብለዋታል፤ የምትነጻው እንዴት ነው? መንጻቷ ስንት ቀናት ይወስድባታል? በምን ትነጻለች? ለመንጻትስ ምን ማድረግ ይኖርባታል?

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 306**

ፋጢማ ቢንት አቡ ሁባኢሽ ለአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለች፤ የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከደም መፍሰስ ንጹህ አልሆንኩም፡፡ ታዲያ ሰላት መስገድ ላቁምን? የአላህ መልእክተኛም ሲመልሱ፣ አታቁሚ ይህ ደም መፍሰስ፣ ከደም ስር እንጂ የወር አበባ አይደለም፡፡ ስለዚህ ትክክለኛው

[132] *Sahih al-bukhari vol 1, page 211*

የወር አበባሽ መፍሰስ ሲጀምር ሰላት አቁሚ፡፡ የወር አበባሽ በቆመ ጊዜ ደግሞ በውሃ ታጠቢ፣ ሰላት ማድረግሽንም ጀምሪ፡፡[133]

- ❖ የወር አበባ ላይ ያለች ሙስሊም ሴት ከሰላትና ከጾም የመታገዷ ምክንያት ምንድን ነው? የወር አበባ ምን ቢሆን ነው? አላህ ራሱ በእነርሱ ላይ የወሰነው ነገር ከሆነ፣ እንደገና ከሰላት የሚያርቃቸው እንዴት ሊሆን ይችላል? አላህ ያዳላል ማለት ነውን?
- ❖ ለምን በውሃ መታጠብ አስፈላጊነቱ ተገለጸ? የግል ንጽህናዋ ጉዳይ ስለሆነ፣ እራሷ ያለ ነጋሪ አታውቀውምን?

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 304**

አንዴ የአላህ መልእክተኛ የኢድ አልፊጥር ሰላት ለመስገድ ወደ መስጊድ ሄዱ፡፡ ከዛም በሴቶች በኩል በማለፍ እንዲህ አሉ፤ ሴቶች ሆይ ስጦታን ስጡ እኔ እንዳየሁት የገሃነም እሳት አብዛኛው ገቢዎች የሆናችሁት እናንተ ናችሁ፡፡ እነርሱም የአላህ መልእክተኛ ለምን ይህ ሆነ? አሏቸው፡፡ ሲመልሱም ሁሌ የምትራገሙና የባሎቻችሁን ውለታ ዘንጊዎች ስለሆናችሁ ነው፡፡ እኔ እንደ እናንተ በጣም የእውቀትና የሃይማኖት ጉድለት ያለበት ማንንም አላየሁም፡፡ በእናንተ በአንዳንዶቹ ጥንቁቅ የሆነው ወንድ ወደ ጥመት ይመራል፡፡ ሴቶቹም የአላህ መልእክተኛ በእኛ ያለ የእውቀት ጉድለት ምንድን ነው? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እርሳቸውም የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል አይደለምን? አሉ፤ ሴቶቹም ልክነው አሉ፡፡ እርሳቸውም በእውቀት ጎደሎ ማለት ይህ ነው፡፡ ደግሞስ ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ጾምና ሰላት ማቆሟ እውነት አይደለምን? ሴቶቹም አዎን አሉ፡፡ እርሳቸውም በእምነት ጎደሎ ማለት ይህ ነው፤ አሉና መለሱ፡፡[134]

- ❖ እውን ሴቶች ከወንድ ያነሱ ጎደሎዎች ናቸው? አላህ እነርሱን እንደ ጎደሎ ይመለከታቸዋል? ወይስ ነቢዩና የቁሬይሾች የወንድ የበላይነት አስተሳሰብ?
- ❖ ይህ ደግሞ ፈልገው ያመጡት ማንነት ካልሆነና አላህ የወሰነባቸው ከሆነ፣ የወሰነባቸውን ሆነዋልና ጎደሎዎች ለምን ይላቸዋል? በህዝቡ እንዲከበሩ ያላደረገው ለምንድን ነው? ጉድለት ካለባቸው የሆኑትን የሆኑት በእነርሱ ስህተት ሳይሆን፣ የሠራቸው ያደረጋቸውን ነው የሆኑት፤ ይህ የሚያስጠይቀው አላህን ነው፤ ታዲያ አላህ እንዲህ ፍርደ ገምድል ነው፣ ማለታቸው ነውን? በሥራውስ ፍጹም አይደለም?

---

[133] *Ibid vol 1, page 212*

[134] *Sahih al-bukhari vol1, page 210*

**ሱና አን-ናሳኢ ቅጽ 1፣ 1 ፡ 752**

ቃታዳህ እንዲህ አለ፤ ጃብር ቢን ዛይድን ሰላትን ዋጋቢስ የሚያደርግ ምንድን ነው? አልኩት፡፡ እርሱም በወር አበባ ላይ ያለች ሴትና ውሻ ብሎ ኢብን አባስ ሲናገር ሰምቻለሁ፤ ያህያም እንዲህ ብሏል፡፡ ሹባህም ይህ የታወቀ ዘገባ ነው ሲል ተናግሯል፡፡ ቃታዳህ የዘገበው ሐዲስ ነው[135]

- ❖ ምን ቢሆን ክቡር ሴት እንደ ውሻ ትቆጠራለች? እንደ አህያ መቆጠሯንም አልረሳሁም፡፡ የወር አበባ ላይ ያለች ሴት ከራስዋ አልፋ የሌላውን ሰው ሰላት ልክ እንደ ውሻ ዋጋቢስ የምታደርግ ከሆነ፣ ያለችበት ሁኔታ በአላህ ፊት ምን አይነት ትርጉም ቢሰጠው ነው? ይህንን አምኖ ኡዱ የሚያደርግ፣ የሚያስተምር አዕምሯቸው የመጽሐፍ ቅዱስን የመንጻት ስርአት ሲያነብ ለምን ይከብዳል አለ? እውነተኞችና እውነትን ፈላጊዎች ስላልሆኑ ነው፡፡
- ❖ ነቢዩ በትንሹ ዘጠኝ ሚስቶች እያሏቸው የወር አበባ ላይ ያለችውን ሚስት ወሲብን በሚቀሰቅስ መልኩ ይተሻሹ/fonedle/ ይሳሳሙ ነበር፡፡ የወር አበባ ላይ ካልሆኑት ሚስቶቻቸው ጋር ማደርና የፈለጉትን ማድረግ እየቻሉ ጅናባ ላይ ካለችው ጋር እንዲያ መሆናቸው እንደ ኀጢአት አልታየም፡፡ (**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ** 1፣ **ቁ** 297-302፤ **ሱና አን-ናሳኢ ቅጽ** 1፣ **ቁ** 373-376) የወር አበባ ላይ ያለች የነቢዩ ሚስት ነቢዩን እንደ ውሻዋ አታረክሳቸውምን? ወይስ ለእርሳቸው አይሰራም? በዚህ ምክንያት ይሆን ዳኢ ሳዲቅ የመጽሐፍ ቅዱሱን አዕምሮው አልቀበልለት ያለው?
- ❖ ምንም ነቢዩ ሙሐመድ አንዴ የፈጂር ሰላት ላይ ጁኑብ መሆናችን እረስተው ከነጅናባቸው ለሰላት ቆመው ቢያውቁም፣ ስለኡዱ ማድረግና ጅናባን ስለማንጻት በውሃ እንዲፈጸም መታዘዙ ለምን ይሆን? ውሃ እንዲህ ጥቅም ከሰጠ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የውሃ አገልግሎትና የመንጻት ስርዓት የማይታመን መባሉ ለምን ይሆን?

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 275**

አንዴ ለሰላ አዛን ታዘነና መስመሮች ተስተካክለው ቆመናል፡፡ የአላህ መልእክተኛም ከቤታቸው ወጥተው መጡና መስገጃቸው ላይ ቆሙ፤ ጅናባ ላይ መሆናቸውን አስታወሱ፡፡ ከዛ እኛን በቦታችን ላይ እንድንቆይ አዘዙንና ለመታጠብ ሄዱ፡፡ በጭንቅላታቸው ላይ ውሃ አፍስሰው ተመለሱና አላሁ አክበር አሉ፤ ሁላችንም ከእርሳቸው ጋር ሰላታችንን ሰገድን፡፡[136]

---

[135] *Ahmad bin 'Ali - An-Nasai, Sunan An-Nasai, translated by Niisiruddin al-Khattiib, Dar-us-Salam, Riyadh-2007, vol 1, page 443*
[136] *Sahih al-Bukhari vol 1 page 198*

❖ ለነቢዩ ወንጀል መታጠቢያ ውሃ አገልግሎት ከሰጠ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የመንጻት ሕግ በውሃ እንዲጠቀሙ ማዘዙ እንዴት የማይታመን፣ አዕምሮ የማይቀበለው ሊባል ቻለ? እነርሱ ውሻና የወር አበባዋ ላይ ያለች ሴት ስትነካቸው የግድ በውሃ ኡዱ ማድረግ ካስፈለጋቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያንን ሲያዝ፣ ስህተት የሆነባቸው እንዴት ነው? የነቢዩ ሙሐመድና የቁርአን ሲሆን ልክ ይሆናል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ደግሞ፣ ለአዕምሯቸው ሸክም ይሆናል፤ ይገርማል። ውድ አንባቢ፤ እነዚህ ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች አድርገው የቆጠሩ ወገኖች እውነተኞችና ታማኞች ናቸው ብለው ያስባሉ?

የቁርአናዊው ሕግጋቶች ከአምላክ መለኮታዊ ማንነት ላይ ተነስተው ኀጢአትንና ጽድቅን የሚፈርጁ ስላልሆኑ ለጥያቄዎቹ መልስ የሚኖራቸው አይመስለኝም። ቁርአን አላህን የሰዎች የኀጢአት ምንጭ አድርጎ ስለሚያስተምር፣ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ፍትሐዊ መሠረት የለውም። አላህ ራሱ አንዱን ኀጢአተኛና የጀሃነም ሰው እንዲሆን፣ ሌላውን ደግሞ የጻድቃንን ሥራ በመሥራት ጀነት እንዲገባ የወሰነ ፈጣሪ በሆነበት ምን መልስ ይኖራል?

**ሱረቱል አል-ኢስራዕ (የሌሊት ጉዞ ምዕራፍ) 17 ፡ 83**

በሰውም ላይ ጸጋችንን በለገስን ጊዜ (ከምስጋና) ይዞራል። ጎኑንም (ከእውነት) ያርቃል። ችግርም በነካው ጊዜ ተስፋ ቆራጭ ይኾናል።

وَإِذَا أَنْعَمْنَا عَلَى الْإِنسَانِ أَعْرَضَ وَنَأَىٰ بِجَانِبِهِ ۖ وَإِذَا مَسَّهُ الشَّرُّ كَانَ يَئُوسًا

**ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 39**

እነዚያም በአንቀጾቻችን ያስዋሹ፣ ደንቆሮች፣ ድዳዎችም በጨለማዎች ውስጥ ያሉ ናቸው። አላህ ማጥመሙን የሚሻውን ሰው ያጠመዋል። መምራቱን የሚሻውንም ሰው በቀጥተኛ መንገድ ላይ ያደርገዋል።

وَالَّذِينَ كَذَّبُوا بِآيَاتِنَا صُمٌّ وَبُكْمٌ فِي الظُّلُمَاتِ ۗ مَن يَشَإِ اللَّهُ يُضْلِلْهُ وَمَن يَشَأْ يَجْعَلْهُ عَلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ

መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ አይደለም። ኀጢአትንና ጽድቅን፣ ሕግንና ፍትሕን፣ በስርዓት ስፍራ ስፍራቸውን በማስያዝ፣ ትክክለኛ ዳኝነትን የሚሰጥ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር አምላክም እንደ አምላክነቱ ባሕሪው ሳይጋጭ፣ ያለ አድሎ ፍትሐን በእኩል ሲያሰፍን ይታይበታል። ኃጢያት በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትርጓሜ አግኝቷል፤ ሕግም የመሰጠቱ አላማ በግልጽነት ተቀምጧል።

በሁለቱ መጽሐፍት ሕግ የመሰጠቱ አላማ ስንመለከት ተመሳሳይ አይደለም። ሁለቱም መጽሐፍት ላይ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን አታድርጉ ያላቸውን

በመተላለፋቸው ከገነት መባረራቸውን ያስተምራሉ፡፡ ልዩነቱ የሚጀምረው ከዚህ በኋላ ባለው ሒደት ላይ ነው፡፡ ቁርአን ካለንበት እውነታ ጋር በሚቃረን መልኩ መልእክቱን ያስተላልፋል፡፡ በተወሰኑ ሱራዎቹ የመላእክትንና የአላህን፣ የሰይጣንንና የአላህን፣ እንዲሁም የአዳምን ቃለ ምልልሶች ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ያስነብባል፡፡ ከዛም አዳም በሰይጣን ተታሎ የአላህን ትእዛዝ በመተላለፍ ከገነት ተባረረ ይለናል፡፡ በዚህ የድሮ ታሪክ የአላህን ማንነት የቀደሙት ነቢያት ካስተማሩት በተቃራኒ በማሳየት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባውና፤ እንደገና ወደ አዳምና ሔዋን መልሶን አዳም ንስሐ ገብቶ አላህም ምህረት አደረገለት ብሎን ሌላ የጥያቄ ናዳ ይጭነናል[137]፡፡

- ❖ አዳም ንስሐ ስለገባ አላህ ምህረት ካደረገለት፣ ወደወጣበት ወደ ገነት ተመልሶ የጀመረውን የደስታ ኑሮ እንዲቀጥል ለምን አልፈቀደለትም? ይህንን ካላደረገለት መህረት አደረገለት ለማለት ይቻላልን? ምህረት ማለት ምን ማለት ነው? የአላህ ምህረት የሚታወቀው ሰዎችን ጀነት በማስገባቱ ነው፡፡ መላው ሙስሊም አላህን ተስፋ የሚያደርገው በምህረቱ ጀነት ያስገባኛል ብሎ አይደለምን?
- ❖ እንደ እስልምና የመረጃ ምንጮች ዘገባ፣ አላህ ኀጢአት እንደሠሩ ባልና ሚስቱን ከገነት አባሯቸዋል፡፡ ያንን ከመሰለ ደስታ አስወጥቶ የላካቸው በተለያየ የምድር አቅጣጫዎች፣ ሚስቱን ሳውዲ አረቢያ ጅዳ፣ ባልን ደግሞ ሕንድ ነበር፡፡ ከ200 ዓመታት በኋላ አረፋ ተራራ ላይ እንደተገናኙ ይናገራሉ[138]፡፡ በተገናኙበት በአረፋ ተራራ ላይ አሁን ሐጅ ስርአት ይፈጸምበታል፡፡ ይህ ቅጣት ነው የሚባለው ምህረት? ምህረት አደረገለት ከተባለ ለአንድ ቀን አይደለም ለዘመናት በብቸኝነት መንከራተትን ምን አመጣው? ምህረት እንዴት ነው የሚተረጎመው? ምህረትና አላህ እንዲህ ከሆኑ፣ አላህን ማን እንበለው? ከአስማ ወሲፋት ጋር እንዴት እናስታርቀው?

መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ አደለም፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ኀጢአትን የሚቀጣ አምላክ ነው፤ ደግሞም ሩህሩህና ፍቅር ምሕረትንም የተሞላ አምላክ ነው፡፡ እነዚህን ባህሪዎቹን በማይጣረስና ለሁሉም መልስ በሚሆን መልኩ ከገነት እንዳባረረው ይነግረናል፡፡ እንደ ቁርአን ምህረት አደረገለት ብሎን አንከራተተው አይልም፡፡ አታድርግ የተባለውን በማድረግ ለአምላክ አለመታዘዙን ገልጧል፤ ይህም ኀጢአት ስለሆነ፣ ከገነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተባሯል፡፡ ኃጢአት ቢያደርግ ባይታዘዝ የሚከተለውን ጥፋት ነግሮት አስጠንቅቆት ስለ ነበር ኃጢአቱን በፈጸሙበት ወቅት የተባለው ጥፋት ሁሉ አገኛቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው፣ እርግማኑ በሁለቱ ላይ ብቻ ሳይቆም ወደ ልጆቻቸው

---

[137] ሱራ 2 ፡ 30-38

[138] *Abu 'Abd Allah Muhammad Ibn Sa'd, KITAB AL-TABAQAT AL-KABIR,* [http://www.soebratie.nl/religie/hadith/IbnSad.html](http://www.soebratie.nl/religie/hadith/IbnSad.html)*, Volume 1, Parts 1.3.42*

ወርዶ እስከ አሁን ድረስ በእኛም ሕይወት ውስጥ እየሠራ ይገኛል፡፡ አንባቢ ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ካለዎት የሚከተሉትን ጥቅሶች ከሁለቱ መጽሐፍት በማንበብ በየትኛው መጽሐፍ የተዘገበው በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ትክክለኛ ፍጻሜ እያገኘ እንዳለ ትዝብተዎትን ይስጡበት፡-

> መጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት 2 ፡ 16 እስከ ኦሪት ዘፍጥረት 3 ፡ 24
> ቁርአን ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 30-38

አንተ ባልከው መንገድ አላህ መሐሪና ፍቅር ከሆነ፣ አዳምን ለምን ከገነት አባረረው? ትሉ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ራሱን ስለማይቃረን ሲሆን፣ ሁለተኛው ስለሚወደው ነበር፡፡ በመሆኑም በሰይጣን የተታለለው ሰው፣ በገነት ውስጥ ቢኖር እንደገና የመታለል አደጋ ይገጥመው ስለነበር ነው፡፡ አምላኩን እየታዘዘ በነበረበት ሕይወቱ የሕይወትን ዛፍ ፍሬ ቢበላ ችግር አልነበረውም፡፡ በኀጢአት ውስጥ ሆኖ ቢበላው፣ ለዘላለም የዘላለም ኀጢአተኛ ሆኖ፣ ለዘለአለም ይሞት ነበር[139]፡፡ ይህ እንዳይደርስበትና ተስፋው እንዳይጨልም ከገነት መባረር ነበረበት፡፡ ከገነት መባረሩ ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም ምን ያህል ጥልቅ ፍቅር እንዳለው፣ አብዝቶ እንደሚጠነቀቅለትና ምህረቱን እንዳበዛለት ያሳያል፡፡ የአዳምን መጥፋት ያልፈለገው፣ ምህረተ ብዙ አምላክ፣ ከሚስቱ ጋር ከገነት ሲያባርረው፣ የደህንነት ተስፋን ሰጥቶታል፡፡ ለሰይጣን ደግሞ ከሴቲቱ የሚወለደው እራስ እራሱን እንደሚቀጠቅጠው ነግሮት ቀን ተቀጥሮለት ሸኝቷቸዋል[140]፡፡

ለአዳም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ፈልጎ፣ እግዚአብሔር አምላክ ሥራውን ሲጀምር፣ የሔደው ወደ አባታችን አብርሐም ነው፡፡ አብርሐምን ለሥራው ሲጠራው ሊያደርግ ያለውን እቅዱንና ለሰው ልጆች ያለውን የመዳን ተስፋ ዝርዝር ነግሮታል፡፡ እርሱም ይህንን ሲሰማ ጅማሬውን በሙሉ ልብ ተቀብሎ አምላኩን ለመከተል ወስኖ እንዲሔድ ወደተነገረው ስፍራ ወደ ከነዓን ምድር በእምነት ተጉዟል፡፡ ከ430 ዓመታት በኋላ አብርሐም ብዙ ልጆችም ሆነውለት ከባርነት ምድር ከግብጽ ወጥተው ወደ ተስፋው ምድር ወደ ከነዓን በመጓዝ ላይ ሳሉ፣ እግዚአብሔር በሲና ተራራ በሙሴ በኩል ለሕዝቡ የመተዳደሪያ ሕግ ሲሰጣቸው እናያለን፡፡ አላማው፡-

- የሰው ልጆችን ከዘለአለም ጥፋት ማዳን
- እግዚአብሔር አምላካችን የሰው ልጆችን የሚወድ አምላክ ስለሆነ በመካከላቸውም መኖር እጅግ ደስ ያሰኘዋል፡፡ ሆኖም ቅዱስ ነውና ኀጢአት ባለበት መገኘት አይሆንለትም፡፡ ስለዚህ ከሰው ልጆች ጋር ለመኖር የሚያስችለውን ሁኔታ ለመፍጠር ሕዝቡ የአምላኩን ፈቃድ ምን

139 *Keil & Delitzsch, Keil and Delitzsch commentary on bible, published in 1866-1891, on Genesis 3:22-24*
140 ዘፍጥረት 3፡ 15

እንደሆነ አውቆ እንዲኖር የመተዳደሪያ ሕግ መስጠት አስፈላጊ ስለሆነ ኦሪት ዘፀአት 25 ፡ 8-9

- በመካከላቸው ሲኖር ደስ እያለው እንዲኖር፣ እግዚአብሔርን እንዲያውቁትና እርሱን በመፍራት እንዲኖሩ ለማስተማር፣ ወደ ዕብራውያን ሰዎች 10 ፡ 1
- የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጉልቶ በማሳየት፣ በእርሱ ነጸብራቅ የሰው ልጆች ኀጢአተኝነታቸውን እንዲያውቁና የይቅርታን አስፈላጊነት፣ እንዲሁም የኩነኔን አደገኛነት ተመልክተው፣ ንስሐ በመግባት ደህንነትን እንዲያገኙ ለማድረግ፡፡ ወደ ሮሜ ሰዎች 7 ፡ 7-11

ሰው ምህረት እንደሚያስፈልገውና እርሱንም ከሚምር ከእግዚአብሔር ያገኝ ዘንድ፣ ቅድሚያ ኀጢአተኛ መሆኑን ማወቅ አለበት፤ ያንንም የሚነግረው ሕግ ነበር፡፡ ስለዚህ የሰውን ኀጢአተኝነት ከሚያስገነዝቡት ሕግጋቶች መካከል፣ ይህ የወር አበባን በተመለከተ የተሰጠው የመንጻት ስርአት አንዱ ነው፡፡ የወር አበባ ጉዳይ በጉልህ ሕግ ተጽፎለት፣ የመንጻትም ስዓት ተደንግጎለት የሚታየው የእስራኤል ልጆች በጉዞ ላይ እያሉ በሲና ምድረ በዳ ላይ ነበር፡፡ ይህ ጊዜ እስራኤል ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር በቅርብ መኖር የጀመረበት ወቅት ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ ጀምሮ እስከዛ ጊዜ ድረስ ምንም ሲባል አናይም፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ እግዚአብሔር አምላክ በሕዝቡ መካከል እንዲገኝ ራሳቸውን ሕጉ እርኩስ ከሚለው ነገር ርቆ መኖር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአምላካቸው ልመናቸውን ለማሰማት፣ የአምልኮ ስርአታቸውን ለመፈጸም ሲሄዱ፣ በሥራ ቦታቸው ሁሉ ተቀድሰው እንዲኖሩ የአምላካቸው ሕግ ይመክራል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር አስፈላጊው ከኃጢአት የተለየ ሕይወት መሆኑ ሁላችንንም ያስማማናል ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ **በኦሪት ዘሌዋውያን** 15 ፡ 19-22 የተጠቀሰው ከወር አበባ የመንጻት ሕግ፣ በቀጥታ የሚመራን ወደ **ኦሪት ዘፍጥረት** 3 ፡ 16-17 ወዳለው የአዳምና የሔዋን አዲስ ሕይወት ጅማሬ፣ የእርግማን ታሪክ ነው፤ ይህም ኀጢአት ያመጣው ነበር፡፡

**ኦሪት ዘፍጥረት** 3 ፡ 16-17

ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፣ በጭንቅ ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል። አዳምንም አለው። የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና፥ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍም በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ

አዳምና ሔዋን በሰይጣን ተታለው በኃጢአት በወደቁ ሰዓት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሔዋን የመጣው የእርግማን ቃል በመራቢያ ስርአቷና በፈቃዷ ላይ

እንደ ነበር ከሕያው ቃሉ እናያለን፡፡ ይህንን ገሃዱ ዓለም ምስክር ይሆነናል፡፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ኀጢአት ጣልቃ በመግባቱ እርግማን መጥቷል፤ ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር የሔዋንን የወሊድና የወር አበባ ጊዜዋን ንጽሕና የሌለው ጊዜዋ እንደሆነ ደነገገ፤ ማንም ለምን እንዲህ አደረግህ ሊለው አይችልም፤ መለኪያው የራሱ ቅድስና ነውና፡፡ በኃጢአት ማለትም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ ምክንያት የመጣባት እርግማን ፍሬ በመሆኑ በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ ስትሆን፣ እራሷና ከእርሷ ጋር የሚነካካ ሁሉ ከንጽህና ይጎድላል፤ ማለትም የበደለኛነት ምልክት ነውና በአምላኩ ፊት የመቅረብ ብቃትን ያጣል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሴት ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖራት ሕብረት መታደስ በወሊድና በወር አበባዋ ፍጻሜ ላይ የመንጻት ስርዓት እንድትፈጽም ታዘዘች፡፡ የመንጻት ስርዓት በመፈጸም እንደገና ሕብረትን ከአምላክ ጋር መቀጠል እንደሚቻል ሕጉ ያመለክታል፤ ውኃ ከኃጢአት የመንጻት ምሳሌ ነው፡፡ ይህንን ስርአት እንዲህ በመደንገጉ ለምን? እንዴት? ብሎ ማንም ሊጠይቀው አይችልም፤ ቁርአን ላይ ስለተሰጡት መመሪያዎች ማንም ለምን ብለው ጠይቀውት እንደማያውቁት ሁሉ ማለቴ ነው፡፡

አሁን ግን ከ2000 ዓመታት በፊት ለአዳም በገነት ተገብቶለት የነበረው ተስፋ፣ "ከሴቲቱ የሚወለደው"[141] የተባለለት የሰይጣንን እራስ የሚቀጠቅጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፤ እርሱም ስለሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአታችንን ዋጋ ከፈለ፡፡ ከሞትም በሶስተኛውም ቀን ሞትን ድል ነስቶ በመነሳት ወደ ሰማይም በማረግ ያንን እርግማን ሽሮታል፡፡ አሁን ወደ እግዚአብሔር መድረሻው መንገድ፣ እውነትም ሕይወትም እርሱ በመሆኑ ያመኑበትና የኀጢአታቸው ማስተስረያ እንደሆነ የተቀበሉት፣ ኃጢአታቸው ሁሉ ተሽሮላቸው ከእርሱ ጋር ለዘለአለም በደስታ እንዲኖሩ በሩ ተከፍቶላቸዋል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ በሠራው ሥራ የሰይጣን የማታለልና በሰዎች ላይ በክፋት የሚሰለጥንበት ስርአቱ አክትሟል፡፡

**ወደ ዕብራውያን ሰዎች 2 ፡ 14-18**

> እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ÷ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር÷ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፤ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ÷ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ፣ የያዘው የመላእክትን አይደለም። ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ÷ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን÷ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ፣ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

[141] ኦሪት ዘፍጥረት 3 ፡ 15

አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ስልጣን ተቀብለዋል፤ ሰይጣንም በእነርሱ ላይ ስልጣን የለውም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ እንዳሉት እርሳቸው ውስጥና ሙስሊሙ አፍንጫ ውስጥ ሌሊቱን ሙሉ ያደረን ሰይጣን አፍንጫቸውን በውሃ አጥበው ማስወጣት እንደሚያስቡት አይደለም፡፡

**ሱና አን-ናሳኢ ቅጽ 1፣ 1 ፡ 90**

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 4፣ ቁ 3295**

ነቢዩ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፤ ከእናንተ ማንኛውም ሰው ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ውዱ ያድርግ፡፡ በአፍንጫው ውስጥ ውኃ በመጨመር ይጠበው ከዛም ያስወጣው፤ ይህንን ሦስት ጊዜ ያድርገው፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን በአፍንጫው የላይኛው ክፍል ሌሊቱን ሙሉ አድሮ ይሆናልና፡፡ አቡ ሁሬይራ የዘገቡት ሐዲስ ነው[142]

በሌላ ሃዲስ ደግሞ ስለራሳቸውና ስለ መላው ሙስሊም የሚከተለውን ብለዋል፤

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 7፣ ቁ 7108**

የአላህ መልዕክተኛ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፡- ከእናንተ መካከል ሰይጣን ያልተመደበበት የለም፡፡ ሱሃባዎቹም የአላህ መልእክተኛ ሆይ በእርሰዎም ላይ ሰይጣን ተመድቦበዎታልን? ብለው ጠየቁ፤ ሲመልሱ አዎን! ተመድቦብኛል፡፡ ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና ተቃወምኩት፤ ከሃይሉ እኔ ነጻ ነኝ፡፡ አሁን የሚያዘኝ ወደ መጥፎ ስራ ሳይሆን፣ ወደ መልካም ስራ ነው፡፡ አብዱላህ ኢብን መሱድ የዘገበው ሃዲስ ነው[143]

**ሐዲስ ሚሽካት አል- ሙሳቢሃ ምዕ 27 ክፍ 19 ሃቁ 131 ቅጽ 2**

ባሏ ሳይኖር ሴትን አትጎብኙ፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን ደም በደም ስር እንደሚዘዋወር እንዲሁ በውስጣችሁ ይሯሯጣልና አሉ፡፡ እኛም የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእርሰዎም ውስጥ እንደኛው ይሯሯጣልን? ስንል ጠየቅናቸው፡፡ እርሳቸውም አዎን፤ በእኔም ውስጥ ይሯሯጣል፡፡ ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና ተገዛልኝ አሉ፡፡[144]

ታዲያ በአላህ ላይ ባለው እምነት፣ ከሰይጣን እስራት መጠበቅ ያልቻለ ነቢይ፣ እንዴት የአላህ መልዕክተኛ ሊሆን ይችላል? በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ያመኑት

---

*[142] Sunan An-Nasai, vol 1 page 74; Sahih Al-Bukhari, vol 4 page 312*

*[143] Sahih Muslim vol 7 page 215*

*[144] Al-Hadis mishkat Ul-Masabi vol 2 page 694*

ግን ይህንን የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት፣ ለመከራና ለዘለአለም ሞት እንዲጣሉ፣ ከአምላካቸውም ጋር እንዳይስማሙ የሚያደርገውን ሰይጣንን በአመኑት በጌታቸው ስም ካለበት ያሳድዱታል፡፡

**የማርቆስ ወንጌል 16 ፡ 16-18**

*ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።*

**የሉቃስ ወንጌል 10 ፡ 17-20**

*ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት። እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።*

ውድ አንባቢ፤ ሙስሊም ነዎት? በቁራኛዎት በሰይጣን ከሚደርስበዎት ስቃይና ከዘለአለም ሞት መዳን ይፈልጋሉ? ለርስዎ የምስራች አለኝ፡፡ ከዚህ ሁሉ የማምለጫው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ በእርሱ በኩል የተሠራለዎትን የቤዛነት ሥራ አምነው ቢቀበሉና ኀጢአትዎትን ተናዘው ወደ እርሱ ቢመለሱ ለዘለአለም ነጻ ይወጣሉ፤ የዘለአለም ሕይወትንም ይቀበላሉ፡፡ በዚህ መንገድ ብቻ ከሰይጣን እስራትና ከዘለአለም ሞት ያመልጣሉ፤ በነቢዩ ሙሐመድ ምክር መትረፍ አይችሉም፡፡

## 2.5. ኦሪት ዘዳግም 25 ፡ 5-10

*ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፣ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፥ ከእርስዋም ጋር ይኑር። የምዋቹ ስም ከእስራኤል ዘንድ እንዳይጠፋ ከእርስዋ የሚወለደው በኵር ልጅ በሞተው በወንድሙ ስም ይጠራ። ያም ሰው የወንድሙን ሚስት ማግባት ባይወድድ፥ ዋርሳይቱ በበሩ አደባባይ ወደሚቀመጡ ሽማግሌዎች ሄዳ። ዋርሳዬ በእስራኤል ዘንድ ለወንድሙ ስም ማቆም እንቢ አለ፤ ከእኔ ጋር ሊኖርም አልወደደም ትበላቸው። የከተማውም ሽማግሌዎች ጠርተው ይጠይቁት፣ እርሱም በዚያ ቆሞ፣ አገባት ዘንድ*

*አልወድድም ቢል፥ ዋርሳይቱ በሽማግሌዎቹ ፊት ወደ እርሱ ቀርባ። የወንድሙን ቤት በማይሠራ ሰው ላይ እንዲህ ይደረግበታል ስትል፣ ጫማውን ከእግሩ ታውጣ፥ በፊቱም እንትፍ ትበልበት። በእስራኤልም ዘንድ ስሙ የጫማ ፈቱ ቤት ተብሎ ይጠራ።*

*ይህ ትእዛዝ ለአዕምሮ የሚከብደው አለ፡-*

- ❖ *ሁለቱ ባይፈላለጉስ?*
- ❖ *ከሁለቱ አንዱ የአካል ነውር ቢኖርባቸውስ?*
- ❖ *እርሱ ስልብ ቢሆንስ?*[145]

*ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩት አካላት አሁንም እያነሱት ያለው መሞገቻ ለራሳቸው መጽሐፍት የእውቀት ድሀ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በዚህ ጥያቄ ሦስት እንከኖች ይታዩባቸዋል በመጀመሪያ ቁርአንንና ሐዲሳቱን በማገናዘብ የተጠየቁት ጥያቄ አለመሆኑ፤ ሁለተኛ አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን ዘንግተዋል፤ ሦስተኛው ደግሞ ክፍሉን በትክክል አለማንበብና አለመገንዘብ ይታይባቸዋል፡፡ ይሁንና ምላሽ መስጠት የምጀምረው እነርሱ ካላዩት የነቢዩ ሐዲስ ነው፡-*

**ሱና አቡ ዳውድ ቅጽ 2፣ ቁ 2089**

*… ኢብን አባስ እንዲህ አለ፡- 'ባል በሞተ ጊዜ ከእርሷ ሞግዚቶች ይልቅ የሚች ዘመዶች በሚስቱ ላይ መብት አላቸው፡፡ ከእነርሱ መካከል አንዱ ሊያገባት ቢፈልግ ያግባት፤ ወይንም እነርሱ ማግባት ባይፈልጉና ለሌላ መዳር ቢፈልጉ ይችላሉ፡፡'*[146]

- ❖ *ይህንን ትእዛዝ መተላለፍ ይቻላል ወይንስ አይቻልም? ካልተቻለ ለምን?*
- ❖ *ነቢዩ እንዲህ አይነት ትእዛዝ ያስተላለፉት ለምንድን ነው? በባሏ ዘመዶች በጎ ፈቃድ ላይ መተዋ ለምን? እራሷ እንድትወስን ለምን አልተተወችም? ይህንንስ በማድረግና በመደንገግ ሌላውን የጋብቻ ሕግጋት መቃረን ለምን አስፈለጋቸው?*
- ❖ *ከእነርሱ መካከል ሆነ፣ እነርሱ ያመጡላትን ባል በአካሉ ላይ ጉዳት ኖሮበት ባትፈልገውስ?*
- ❖ *ይህ ትእዛዝ የተሰጠበት አላማ ምንድን ነው? ምን አልባት ሴቶች የበታችና የባሎቻቸው ሐብት ጠባቂዎች ስለሆኑ፣ ከሚች ባሏ ሐብት የምትወስዳትን ትንሽ ሽርፍራፊ ገንዘብ ለማስቀረት? ያስ ቢሆን ምን ያህል ይደርሳታል? ልጅ ከሌለው፣ እዳ ካለበት፣ እርሱ ተከፍሎ*

---

[145] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 36-38

[146] *Sunan Abu Dawud Vol 2, page 523*

ከሚተርፈው የሚደርሳትን አንድ አራተኛ፤ ልጅ ካለው ደግሞ አንድ ስምንተኛ የሆነች ብጣቂ ነገር?

**ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 34**

***ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፡፡ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች፣ አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እነዚያንም ማመጻቸውን የምትፈሩትን ገስጹዋቸው፡፡ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው፡፡ (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዟችሁም (ለመጨቆን) በእነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፤ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡***

الرِّجَالُ قَوَّامُونَ عَلَى النِّسَاءِ بِمَا فَضَّلَ اللَّهُ بَعْضَهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ وَبِمَا أَنفَقُوا مِنْ أَمْوَالِهِمْ ۚ فَالصَّالِحَاتُ قَانِتَاتٌ حَافِظَاتٌ لِّلْغَيْبِ بِمَا حَفِظَ اللَّهُ ۚ وَاللَّاتِي تَخَافُونَ نُشُوزَهُنَّ فَعِظُوهُنَّ وَاهْجُرُوهُنَّ فِي الْمَضَاجِعِ وَاضْرِبُوهُنَّ ۖ فَإِنْ أَطَعْنَكُمْ فَلَا تَبْغُوا عَلَيْهِنَّ سَبِيلًا ۗ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيًّا كَبِيرًا

- ***ነቢዩ እንዲህ ካሉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነውን? ፍትሐዊ ህሊና ያላቸው ሰዎች አይደሉም፤ ይህ የነቢዩ ንግግርና የቁርአኑ አንቀጽ በአዕምሯቸው ተቀባይነትን ካገኘ የመጽሐፍ ቅዱሱ ትእዛዝ መልእክት እንዴት ሊከብዳቸው ቻለ?***

*ነቢዩ እራሳቸው በሚስቶቻቸው ላይ ይህንኑ ፈጽመውት ያውቃሉና አንቀጹ የወረደው ከአላህ ነው ብሎ መቀበል አይቻልም* [147]*፡፡ አንድ የቁርአን አንቀጽ ወረደ እየተባለ የሚነገረው ሁኔታዎች ከተከሰቱ በኋላና ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከከሊፋ ኡመር ጋር መክረው የተናገሩት ላለመሆኑ ማረጋገጫው ማቅረብ አይችሉም፡፡ ምን አልባት አላህ ሴቶችን የሃይማኖትና የእውቀት ጎደሎዎች ስላደረጋቸው የራሳቸው የሆነ መብት የሌላቸው ስለሆኑ፣ ወንድ የሆነ ሁሉ ይወክላቸው ተብሎ ይሆን? መልሱን ለእነርሱ እተወዋለሁ፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የቤተሰብ ሕጉን ለምን እንደሰጠ አጥጋቢ ምክንያት ይሰጣል፡፡ አላማው ነቢዩ ሙሐመድ ስለ ቁርአን መሰጠት ከተናገሩት አላማ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሐም በገባው ቃል መሠረት በጸናችው እጁ ከፈርኦን አገዛዝ ነጻ በማውጣት እርስቱን ያወረሰውን ሕዝብ ልጄ ብሎ ጠርቶታል፤ ለሱም ያለውን ጥልቅ ፍቅር በዚህ የቤተሰብ ሕግ በኩል ገልጦታል፡፡*

[147] *Sahih al-Bukhari, vol 7, # 5191, page 85-90*

**ኦሪት ዘፀአት 4 ፡ 23**

<u>እስራኤል የበኵር ልጄ ነው፤</u> ይገዛልኝ ዘንድ <u>ልጄን ልቀቅ አልሁህ፣</u> አንተም ትለቅቀው ዘንድ እንቢ አልህ፣ እነሆ እኔ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ ትለዋለህ።

**ኦሪት ዘዳግም 7 ፡ 8**

ነገር ግን <u>እግዚአብሔር ስለ ወደዳችሁ</u>፣ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን መሐላ ስለ ጠበቀ፥ ስለዚህ እግዚአብሔር በጸኑ እጅ አወጣችሁ፥ ከባርነትም ቤት ከግብፅ ንጉሥ ከፈርዖን እጅ አዳናችሁ።

ምንም ቁርአን የአላህ ቃል እንደሆነ ባላምንም፣ ሁሉን የሚችል አምላክ ለዚህ ሕዝብ ምን እንዳደረገ ሲናገር፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 47**

የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ (አባቶቻችሁን በጊዜያቸው ከነበሩት ዓለማት ያበለጥኩዋቸው) መኾኔን አስታውሱ፡፡

يَا بَنِي إِسْرَائِيلَ اذْكُرُوا نِعْمَتِيَ الَّتِي أَنْعَمْتُ عَلَيْكُمْ وَأَنِّي فَضَّلْتُكُمْ عَلَى الْعَالَمِينَ

ለሙሴ በተሠጠው ሕግ የሚተዳደረው ይህ ሕዝብ፣ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል፤ ታዲያ ከዚህ ወገን የሆነ የማንኛውም ሰው ስም ከዚህ ምድር ያለ መታሰቢያ እንዲቀር አልተፈቀደም፡፡ በትውልዱ መካከል እንዳይረሳ፣ እየታሰበ እንዲኖር፣ ስሙም እንዲጠራ ይህንን የመሰለ ስርአት ተዘረጋለት፡፡

**ኦሪት ዘዳግም 25 ፡ 6**

<u>የምዋቹ ስም ከእስራኤል ዘንድ እንዳይጠፋ</u>፣ ከእርስዋ የሚወለደው በኵር ልጅ በሞተው በወንድሙ ስም ይጠራ።

ሆኖም አምላካችን ቅዱስ እግዚአብሔር ሕጉ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንጂ፣ በግዴታ የሚሠራ አይደለም፡፡ ምንም አይነት ምክንያት ያቅርቡ ካልፈለጉ ያለማግባት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ይህንንም እራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚቆጥሩት ወገኖች ለመሞገቻ በጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ስርዓት መሠረት የተዳኙ የሁለት ሰዎችን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ዘግቦልናል፡፡ የመጀመሪያው የወንድሙን ስም በወንድሞቹ መካከል ለማስጠራት ያልፈለገውን ሰው ታሪክና ሁለተኛው ለአምላኩ ሕግ በመታዘዝ የሟች ዘመዱን ስም ለማስጠራት ፈልጎ የወረሰን ሰው ታሪክ

ያስነብበናል፡፡ ውድ አንባቢ እባክዎትን መጽሐፍ ቅዱስዎትን ከፍተው የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያንብቡት፡-

**መጽሐፈ ሩት** 3 ፡ 1- 4 ፡ 16

የወንድሙን ስም ለማስጠራትና ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ሕግ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆነው አመጸኛ እንዲሁ ይሂድ አይልም፡፡ ለአምላኩ ባለመታዘዙና የወንድሙን ስም በወገኖቹ መካከል ለማስጠራት ፈቃደኝነቱን ባለማሳየቱ፣ ቤቱ የጫማ ፈቱ ቤት ተብሎ ሁሌ እንዲጠራ ያዛል፡፡ ምናልባት ይህንንም ለምን ይሉ ይሆን?

እንግዲህ በቅንነት ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያነብ ማንኛውም ሰው፣ ከክፍሉ የሚማረው ምን ያህል በአምላኩ በእግዚአብሔር እንደሚወደው፣ ልዩ ጥንቃቄ እንደሚደረግለት ቢሆን እንጂ፣ መጽሐፉን እንዲጠራጠረው አያደርገውም፡፡ እነርሱ ግን ምን አልባት ቁርአን አላህ ለሰው ልጆች ያለውን ጥልቅ ፍቅር ሳይሆን፣ ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ፣ አፍቃሪ ያልሆነ አድሎኛ አምላክ መሆኑን ስለነገራቸው ፍቅሩ ሊገባቸው አልቻለም፤ ፍቅረ እግዚአብሔር እንግዳ ሆኖባቸው ግራ ስለተጋቡ፣ ግራ የገባው ነገር ይናገራሉ፤ ግራ ለማጋባትም ጨክነው ይሠራሉ፡፡

ውድ አንባቢ፤ እርሰዎ ከሚያስቡት በላይ አላህ ለእርስዎ ጥልቅ ፍቅር እንዳለው ምን ያክል ያውቁ ይሆን? ከእርሱስ ጋር እንደ አባትና ልጅ በመተሳሰር በፊቱ ዋጋው የከበረ ሰው መሆንን ምን ያክል ይፈልጋሉ? ምላሽዎትን በጉጉት ይጠብቀዋል፡፡ ይፈልጋሉ? ይህንን ሕብረት ከፈለጉ መንገዱ ከሚያስቡት በላይ እጅግ ቀላል ነው፡፡

**የዮሐንስ ወንጌል** 14 ፡ 6

> ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

ከእርስዎ የሚጠበቀው የሰው ልጆች ወደ አብ ይደርሱና ለዘላለም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ፣ እራሱን ስለ ኃጢአተኞች በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአትዎን ዋጋ የከፈለውን ይህንን የሕይወት መንገድ አምኖ መቀበል ብቻ ነው፡፡ ስለ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ተከፍሏል፤ እርስዎ ኃጢአተኛ መሆንዎትን አምነው በመቀበል ይናዘዙና ወስነው ወደ ልቤ ግባ ብለው ይጥሩት፡፡ የዘለአለም ሕይወትን ይቀበላሉ፡፡ ይህ እድል ካመለጠዎት ግን ዘመኑን በኪሳራ የኖረ ምስኪን ሰው ይሆናሉ፡፡

## 2.6. 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2 ፡ 16

> ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ።

እራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ ያሚያዩት ወገኖች በዚህ ክፍል አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው አህያ በሰው ቋንቋ ተናገረች መባሉ ነው ብለዋል[148]፡፡

እንግዲህ በአላህ ተአምራቶች አምናለሁ የሚል ሰው፣ በእርሱ ሁሉን ቻይነት የተከናወነን ተአምር መጽሐፍ ቅዱስ ዘግቦ ሲመለከት "ይህን አዕምሮዬ ሊቀበለው አይችልም" ሲል ምን ማለት ሊሆን ይችላል? አላህ ከፈቀደና እንድትናገር ከሰጣት በሰው አይደለም በመልአክ ቋንቋ ብትናገር ያስገርማል? የተምር ዛፍ እንደ ግመል ስቅስቅ ብሎ አለቀስ መባሉን አምነው ተቀብለው እዚህ ላይ እንዴት ወገባቸውን ያዙ? ይህ ለሙስሊሙም ሆነ ወደ እስልምና እየጠራውህ ነው ለሚሉት ሕዝብ አለመታመናቸውንና ሥራቸው በማስተዋል ያልተቃኘ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለመሞገቻ መጥቀሳቸው ለተነሱበት አላማ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? ቁርአንና የነቢዩ ሐዲሳት ምን እንደተሞሉ አያውቁምን? ካወቁ የዋሁን ሙስሊም ወንድሞቻቸውን ማታለል ለምን አስፈለገ? ውድ አንባቢ ከዚህ በፊት የጠቀስኳቸውን መሞገቻዎቼን አሁንም ደግሜ ለማንሳት እገደዳለሁ፡-

- **ሳዲቅ ሙሐመድ "ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ)" በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ ገጽ 149-150 ላይ የቴምር ዛፍ ተንሰቅስቆ ማልቀስ**

"የአላህ መልዕክተኛ የጁምአ ሁጥባ የሚያደርጉት የቴምር ግንድን በመደገፍ ነበር፡፡ መንበር ከተሠራላቸው በኋላ ግን ያንን የቴምር ግንድ ትተው ወደ ተሠራላቸው መንበር ሲወጡ የቴምር ግንዱ እንደ ግመል መንሰቅሰቅ ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ወደ እርሱ በመምጣት እጃቸውን ሲያሳርፉበት ወዲያው ጸጥ አለ፡፡ ቡኻሪ፣ ናሳኢና ትርሚዝ የዘገቡት ሐዲስ ነው፡፡" ይላል፡፡

- ❖ የሚገርም ሐዲስ ነው፤ ለአላህ መልእክተኛ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ገብቶት በደስታ የቆየው የተምር ዛፍ፣ በእርሱ ላይ እየተሠራ ያለውን ሽፍጥ ሲረዳና አገልግሎት መስጠት ማቆሙን ሲያስብ፣ ክፍት ብሎት ከሰው ይልቅ የግመልን መርጦ ልክ እንደ ግመል ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡ ይህንን ዜና አምኖ የተቀበለ አዕምሮ መጽሐፍ ቅዱስ የነቢዩን ስህተት

[148] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 38

አህያ በአላህ ፈቃድ በሰው ቋንቋ ተናግራ እብደቱን ገሰጸች ሲል፣ ይህ የማይታመን ነገር ነው! እንዴት ሊል ቻለ?

- አንዴ ነብዩ በግመል በረት ስለመስገድ ተጠይቀው ሲመልሱ 'እነርሱ ከሰይጣን ናቸውና አትስገዱ'[149] ብለው ነበር፡፡ እንግዲህ እነዚህን ሁለት ሐዲሳት እንዴት ልናስታርቃቸውና የግንዱን ለቅሶ ከአምላክ ተአምራት ጋር ልናያይዘው እንችላለን? ምናልባት እንደ ግመል ያለቀሰው ግንዱ ሳይሆን፣ ከግመል ጋር አብሮ የሚኖረው ራሱ ሰይጣን ቢሆንስ? አይታይ፤ ሲያባብሉት ዝም ካለ ደግሞ ነገሩ ሌላ ነው፡፡ ነቢዩ እኔም ሰይጣን አለብኝ፣ እናንተም ሰይጣን አለባችሁ፣ ብለው ስለ ሰይጣን ቁራኛነት ወደተናገሩት ሊወስደን ነው፤ ይብቃ፡፡
- እንዲህ ከሆነ ሳዲቅና መሰሎቹ የቁርአን አስተማሪ ሊባሉ፣ የሚሰጡት ዳዕዋም ታማኝና ሰው ጆሮውን ሰጥቶ ሊሰማቸው የሚገባ እንዴት ሊሆን ይችላል?

## የገነት በርና የምድር ለቅሶ

**ሱረቱል አል-ዱሀን (የጭስ ምዕራፍ) 44 ፡ 29**

ሰማይና ምድርም በእነርሱ ላይ አላለቀሱም፡፡ የሚቆዩም አልነበሩም፡፡

فَمَا بَكَتْ عَلَيْهِمُ السَّمَاءُ وَالْأَرْضُ وَمَا كَانُوا مُنظَرِينَ

ይህንን አንቀጽ አስመልክቶ የታወቁት ሙፈሲሮች ኢማም ኢብን ካሲር ኢብን አባስን ምንጭ አድርገው የዚህን አንቀጽ ማብራሪያ ሲሰጡ እንዲህ ብለዋል፡-

"ሳኢድ ቢነ ጁባይር እንዲህ አለ፡- አንድ ሰው ወደ ኢብን አባስ መጣና እንዲህ አለው፡- 'አቡ አል-አባስ ሆይ አላህ 'ሰማይና ምድርም በእነርሱ ላይ አላለቀሱም፡፡ የሚቆዩም አልነበሩም፡፡' ብሏል፤ ገነትና መሬት ለማንኛውም ሰው ያለቅሳሉን?' እርሱም እንዲህ አለው፡- 'አዎን፤ መልካም ሥራዎ የሚያርግበት ስጦታውም ወደ እርሱ የሚወርድበት የገነት በር የሌለው ሰው የለም፡፡ ሙስሊም በሚሞትበት ጊዜ ይህ በር ይዘጋል፤ ያኔ ይናፍቀዋል ለእርሱም ያለቅስለታል፤ ደግሞም አላህ ለማውሳትና ለሰላት የሚጠቀምበት የሰላት ቦታውም ለእርሱ ታለቅስለታለች፡፡'"[150]

ውድ አንባቢ፤ አንድ ሙስሊም በመልካም ሥራው ጀነት ይገባል ወይስ አይገባ፣ ከነጭራሹስ ገነት ይገባልን? የሚሉትን ብዙ ጥያቄዎች ይቆዩ፤ ቁራጭ መሬትና የገነት በር ማልቀሳቸውና ያለቀሱበት ምክንያት ግራ ደግሞ የሚያጋባ ነው፡፡

---

149 *Sunan Abu Dawud vol 8, # 184, page 123*

150 *Tafsir Ibn Kathir, vol 8 page 684-685*

ይሁንና አዕምሮ ሊቀበለው የማይችል ባዮቹን ጥያቄ ልጠይቅ ሻትኩ፡-

- የገነት በርና መሬት የአንድን ግለሰብ መሞት ተረድተው፣ መሬት ከዚያ ቀን በኋላ ደግሞ ላይሰግድባት፣ እርሷም ሁለተኛ በዛ ሁኔታ ላታየው ከእርሷ እንደ አንዱ ቅንጣት ሊሆን መሆኑ ገብቷት፣ የገነት በርም የእርሱን ነገሮች ላታስወጣ ላታስገባ ጥርቅም በማለቷ፣ ሁለቱም ሀዘን ተሰምቷቸው ስቅስቅ ብለው ማልቀሳቸውን ቁርአን ስለተናገረ አዕምሯቸው ተቀብሎታል፡፡ ይህንን ማመን የቻለ አዕምሮ፣ በገንዘብ ተገዝቶ የእግዚአብሄርን ሕዝብ ለመርገም እየሄደ ያለን ሆዳም ነቢይ ከስህተቱ ለመመለስ አህያዋ በሰው ቋንቋ ብትናገር ለመቀበል እንዴት አሻፈረኝ አላቸው?
- እነዚህ አካላት የሚያለቅሱት ለመላው ሙስሊም ይመስላል፡፡ ሆኖም ቁርአኑንና ሐዲሳቱን ስንመረምር ከነቢዩ ሙሐመድ ጀምሮ ሁሉም ሙስሊም ጀነት የመግባት ተስፋ እንዳላቸው አያመለክቱም፡፡[151] ሁለቱም የመረጃ ምንጮች የማንኛውም ሙስሊም መልካም ሥራ ጀነት እንደ ማያስገባው ይታወቃል፡፡ ታዲያ ሁለቱ መልእክቶች እንዴት ሊታረቁ ይችላሉ? ሁሉም ሙስሊሞች የማይገቡ ከሆነ፣ ከማያምኑት ጋር አንድ ስለሚሆኑ ቁርአን እርስ በእርሱ ይቃረናል፤ ስለዚህ ቁርአን የአላህ ቃል ነው ማለት ይቻላል?

መጽሐፍ ቅዱስ አህያ በሰው ቋንቋ ተናገረች ብሎ መዘገቡን መሞገቻ ማድረግ ክርስቲያኑ ማሕበረሰብ የመጽሐፉን የእግዚአብሔር ቃልነት እንዲጠራጠር በር ይከፍትልናል ብለው አስበው ከሆነ በጣም ተሳስተዋል፡፡ ቁርአን ቢሆን በሰይፍ ከታትሮ አያችሁት ቢለን እንጂ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተትን ፈጽሞ፣ አምላኩን እንዳይበድል የተደረገለትን ጥበቃና ምህረት አያሳየንም ነበር፡፡ ስለዚህ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ ለአንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር ለእርሱ የሚያደርግለትን ጥበቃ የሚማርበት እንጂ ለጥርጣሬ በር ከፋች ሊሆንበት አይችልም፡፡ አምላኩ እንዴት እንደሚወደው፣ ከማያየው ጠላት ስጋት ሊገባው እንደማይገባ፣ በመታመን ተዘልሎ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ እረጋሚዎችና አንይህን ላፈር የሚሉ ጠላቶች ቢበዙበትም፣ በጠላቶቹ ስውር ሴራ እንደማይጠመድ አምኖ ተረጋግቶ እንዲቀመጥ እምነትን ይፈጥርለታል፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ጥርጣሬን አይዘራበትም፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር የኀጢአተኛውን ሰው ሞት የማይፈልግ፤ ግን ከጥፋታቸው እየመለሰ የሚታደግ አምላክ መሆኑን አውቆ፣ አብዝቶ ለአምላኩ እንዲገዛ በቃሉም እንዲታመን የሚያደርገው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፡፡

ውድ አንባቢ፤ እርስዎም ከጥፋትና ከኃጢአት መንገድ ተመልሰው እዚህ ኪዳን ውስጥ እንዲገቡ ይፈልጋል፡፡ እድሜን ሰጥቶ በሕይወት ያኖረበት ዋና ምክንያት

[151] ሱረቱል መርየም 19 ፡ 71፡- 'ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፡፡ (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው፡፡'

ከመንገድዎት ተመልሰው ንስሃ በመግባት ወደ ዘለአለም ደስታው እንዲገቡ እድል ለመስጠት ነው፡፡ አሁንም ይህንን በማድረግ ከእርሱ ጋር እንዲታረቁ ይጠብቅዎታል፡፡ ይህ ባይሆን የዘለአለም ጥፋት ያገኝዎታል፡፡ ይህንን እድል አሁን ይጠቀሙበት፡፡ አሁን በቀረችለዎ አጭር ጊዜ ወደ እርሱ ይመለሱ፤ በጽድቁ መንገድ ወደ እርሱ ይቸኩሉ፡፡ የደህንነተዎና የጽድቁ መንገድ፣ ስለ ኀጢአተኛው ሰው የኃጢአትን ዋጋ መስቀል ላይ በመሞትና በሦስተኛው ቀን ከሙታን በመነሳት የከፈለውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ብቻ ነው፡፡ እርሱ ያለው ሕይወት አለው፤ ወደዚህ ጌታ ይምጡ፤ በናፍቆትና በጉጉት ይጠብቅዎታል፡፡ የቅዱስ ቃሉ መተማመኛ እንዲህ በሚል ታትሟል፡-

**1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5 ፡ 12-13**

ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ፣ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።

## 2.7. መጽሐፈ መሳፍንት 9 ፡ 7-13

ይህንም ነገር ለኢዮአታም በነገሩት ጊዜ፥ ሄዶ በገሪዛን ተራራ ራስ ላይ ቆመ፥ ድምፁንም አንሥቶ ጮኸ፥ እንዲህም አላቸው፦ የሴኬም ሰዎች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንዲሰማችሁ ስሙኝ። አንድ ጊዜ ዛፎች በላያቸው ንጉሥ ሊያነግሡ ሔዱ ወይራውንም፣ በእኛ ላይ ንገሥ አሉት። ወይራው ግን፦ እግዚአብሔርና ሰዎች በእኔ የሚከበሩበትን ቅባቴን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው። ዛፎችም በለሱን፦ መጥተህ በላያችን ንገሥ አሉት። በለሱ ግን፦ ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው። ዛፎችም ወይኑን፦ መጥተህ በላያችን ንገሥ አሉት። ወይኑም፣ እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው።

የማይታመነውና አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው የዛፎች የንግሥና ውይይት ማድረጋቸውን ነው ይላሉ፡፡[152]

ቁርአን ልዩ የሆነ ቅኔያዊ ይዘት እንዳለው የሚያምን፣ ሀሁ በሎ ፊደል የቆጠረ ሰው እንዲህ አይነት ደካማ የሙግት ነጥብ መነሳቱ አስገርሞኛል፡፡ ይሁንና መልሴን አንድ ጥያቄ በመጠየቅ እጀምራለሁ፡፡ በቅድሚያ ቁርአን ውስጥ አንድ

152 ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 39

አንቀጽና የእርሱን ደጋፊ አንድ ሐዲስ ከሳሂህ አል-ቡኻሪ እስነብባለሁ፡፡ ከዛም አመለካከታቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ይንገሩን፡-

ሱረቱል ያሲን 36 ፡ 38

ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው፡፡

ይህ አንቀጽ የወረደው ነቢዩ አቡ ሐር ከተባለ ሰው ጋር በመስጊድ እያሉ እንደ ነበር የተለያዩ መዛግብት ያሳያሉ፡፡

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁ 4802

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 4፣ ቁ 3199

አንድ ቀን ፀሐይ በመጥለቂያዋ ሰዓት እኔና የአላህ መልእክተኛ መስጊድ ውስጥ ነበርን፡፡ ነቢዩም አቡ ሐር ፀሐይ ስትጠልቅ ወዴት እንደምትጠልቅ ታውቃልህን? አሉኝ፡፡ እኔም አላህና የአላህ መልእክተኛ ያውቃሉ ስል መለስኩ፡፡ እርሳቸውም በአላህ ዙፋን ስር ለመስገድ ትሄዳለች፤ ከዛም ይህ የአላህ ቃል ሱረቱል ያሲን 36 ፡ 38 ወረደ፡፡ አቡ ሐር የተናገረው ሐዲስ ነው[153]

የቁርአን መዝገበ ቃላት ሱጁድ/ስግደት/ ማለት፡- በትህትና ወደ መሬት መስገድ፣ የስግደት ሁኔታ በተለይ በጸሎት ጊዜ፤ ሙስሊሞች በሰባት አጥንቶች መሬትን ይነካሉ፤ በግንባራቸው፣ በእጃቸው፣ በጉልበታቸውና በእግር ጣቶች ይለዋል[154]፡፡ እንግዲህ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹን የምጠይቀው፡-

- ❖ ይህንን የነቢዩን ሐዲስ ትክክለኛ (ሳሂህ) የተሰኘ ሐዲስ ስለሆነና ነቢዩ የተናገሩት ስለሆነ ማመን ግድ ይሆናል፡፡ ካላመናችሁ የቁርአኑን አንቀጽም የአላህ ቃል አለመሆኑን መመስከር ይኖርባችኋል፡፡ የመደበኛውን ዓለማዊ ትምህርት እስከ ስንተኛ ክፍል እንደዘለቃችሁ ባላውቅም እንደተማራችሁ ግን አስባለሁ፡፡ ታዲያ ይህንን የሚያምኑትን ሐዲስ ከገሀዱ ዓለም እውነታ ጋር ማለትም በስነ ከዋክብት ጥናት መነጽር ሲታይ ምድር ትዞራለች ወይንስ ፀሐይ ትሄዳለች? መልሱ ድንገት ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ሲያጋጫቸው እንደሚያገኙት አያጠራጥርም፡፡
- ❖ ፀሐይ ሄዳ የምትሰግድበት የአላህ ዙፋን የት ነው ያለው? ከሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 255 ጋር እንዴት ይታረቃል? ትሰግዳለች ከተባለ ስትሰግድ

---

[153] *Sahih Al-Bukhari vol 6 page 280 and vol 4 page 269*

[154]

እንደ ሰው በሰባት አጥንቶቿ መሬትን እየነካች ነው? ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ አላህና ሳይንስን እንዴት ታስታርቋቸው ይሆን? ፀሐይ በሰይጣን ቀንድ መካከል ትወጣለች ትገባለች የሚለውን የነቢዩን ሐዲስም አልረሳሁትም[155]፡፡

- ❖ የዚህ ምስቅልቅሎሽ ተጠያቂ ማን ነው? ነቢዩ ወይንስ አላህ? ወይንስ የቁርአንና የሐዲስ ጸሐፊዎች?

ለምስቅልቅሎሹ ተጠያቂው አላህ ነው፣ እንደማይሉኝ አምናለሁ፡፡ ነው ካሉም ያ አላህ ማን እንደሆነ እንዲነግሩን ጥያቄ እናቀርባለን፡፡ ነገር ግን ከአብርሃም አምላክ እንደበት **ሱረቱል ያሲን 36 ፡ 38** ወጥቶ የተነገረ ነው ብሎ ማመን ፍጹም ስህተት ይሆናል፡፡ በዚህም ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሆኖም አንቀጹን በተመለከተ የተለያዩ ሙፈሲሮች የተለያየ ትርጉም ሰጥተውት ይታያል፡፡ ራሳቸው ግራ ተጋብተው የዋሁን ሙስሊም ማሕበረሰብ ግራ የሚያጋቡ ሙፈሲሮች የሰጡት ተፍሲር የማይያያዝ በመሆኑ የትኛውን መጨበጥ እንደሚገባ አይታወቅም፡፡ እነርሱን ለዚህ ያበቃቸው እራሱ ቁርአን የተጨበጠ እውነተኛ መረጃ የሌለው መሆኑ ነው፡፡

ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ አድርገው የሚቆጥሩት ወገኖች ከዚህ ሞልቶ ከተረፈው አመለካከት የትኛውን እንደሚከተሉ አላውቅም፡፡ ፊደል የቆጠሩ ስለሆኑ፣ "ፀሐይ ሰገደች" የሚለውን የነቢዩን አባባል እነርሱ ዉዱ አድርገው፣ መስገጃቸው ላይ ቆመው፣ ይህ ለሱናው ይህኛው ለፊርድ እያሉ ከእግራቸው እጥፍ ከወገባቸው ጎንበስ እያሉ እንደሚሰግዱት አይነት ታደርጋለች ብለው እንደማያስቡ እገምታለሁ፡፡ ነቢዩ ይህን ያሉት መሬት በእራሷ ዛቢያ ስትዞር የሚከሰተውን ሁኔታ ለመግለጽ የተጠቀሙበት ምሳሌያዊ አገላለጽ ይሆናል፡፡ ይህን የምለው ንግግራቸው የመሬት ዙረት ስርዓት ወጣ በማለቱ ትንሽ ቢታረቅልን በሚል እንጂ፣ ነቢዩ ሙሐመድና 'አላህ' ማለት የፈለጉት ይህን ሆኖ አይደለም፡፡ ወደተነሳሁበት ክፍል ስመለስ፡-

- ❖ እንዲህ ከሆነ ወንድሞቹ በሌላኛው ወንድሙና በቅጥር ወሮበሎች እጅ የታረዱበት ሰው ነፍሰ ገዳይ ወንድሙን ሊያነግሱት እንደሆነ ሰማ፡፡ ከዛም በአገሬው ቋንቋና የጥበብ ቃል፣ እርሱና ሕዝቡ በሚግባቡበት መንገድ ማስተላለፍ የፈለገውን መልእክቱን አስተላለፈ፡፡ የአንድ ስንኝን ሰምና ወርቅ እያወጣ የተማረ አዕምሮ፣ ይህንን የጥበብ ቃል በትክክል አንብቦ መረዳት እንዴት ተሳነው?
- ❖ እንቆቅልህ ምን አውቅልህ እየተጫወተ ያደገ፣ ፀሐይ ሰገደች ሲባል ያመነ አዕምሮ፣ ይህንን ተምሳሌታዊ አነጋገር ሲያነብ እንዴት መረዳት ተሳነው?

155 Sahih Al-Bukhari vol 4, # 3273, page 303

❖ ነቢዩ ፀሐይ በአላህ ትእዛዝ መጓዟን ሰገደች፣ የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ፣ ማመን የቻለ አዕምሮ፣ ክፉና መልካም ሰዎችን በዛፎች መስሎ እያወያየና እያስተላለፈ የነበረን ሰው ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ዘግቦ ሲመለከቱ፣ ይህ አእምሮ ሊቀበለው አይችልም እንዴት ሊሉ ቻሉ? ታሪኩን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዘገበው? ጽንፈኝነት ወይስ አላዋቂነት?

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዛፍ ነገሠ ወይንም ዛፍ አፍ አውጥቶ ተናገረ ለማለት ሳይሆን ተምሳሌታዊ አነጋገር እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ውድ አንባቢ፤ አንድ ነገር ብዬ ላጠቃለው፡፡ አሁንም እግዚአብሄር አምላክ ከኀጢአት ጋር በሚኖርዎት ሕብረት ዘላለማዊ ሕይወትዎ እንዲበላሽ አይፈልግም፡፡ ለሰው ልጆች ያለው ጥልቅ ፍቅር ግድ ብሎት አንድ ልጁን ስለኀጢአተኞች ዋጋ ሰጥቷል፡፡ ይህንን የፍቅር ስጦታ ቸል ባይሉና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተሠራለዎትን የቤዛነት ሥራ አምነው ቢቀበሉ፣ ወደ ዘላለም ደስታው፣ ያለምንም ጥርጥር ይገባሉ፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ዛሬን በሕይወት እንዲኖሩ የፈቀደው፣ ለመመለስ የሚሆን ጊዜ ሊሰጥዎት ፈልጎ ነው፡፡ በፊቱ መልካሙንና ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ያልሠራ ሰው ወደ መንግስቱ ሊገባ እንደማይችል እርስዎም ያውቃሉ፡፡ እርሱ ደስ የሚሰኝበት የመልካም ሥራ መጀመሪያ ደግሞ በልጁ ማመን ነው፡፡ እርሱን በማመን ዳግም ሊወለዱና ከሚያፈቅርዎት ጌታ ጋር ሕብረት ሊመሰርቱ ይገባዎታል፡፡ ያለ እርሱ ምንም ማድረግ አይችሉም፡፡ የእግዚአብሐየር የልቡ ደስታ ያለው እርሱ ላይ ነው፡፡

**የማርቆስ ወንጌል** 9 ፡ 7

*ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው፥ ከደመናውም የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።*

**የሉቃስ ወንጌል** 3 ፡ 22

*መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ።*

## 2.8. መኃልየ መኃልይ 7 ፡ 1-9

*አንቺ ሱላማጢስ ሆይ፥ ተመለሽ፥ ተመለሽ እናይሽ ዘንድ ተመለሽ፥ ተመለሽ። በሱላማጢስ ምን ታያላችሁ? እርስዋ እንደ መሃናይም ዘፈን ናት። አንቺ የመኰንን ልጅ ሆይ፥ እግሮችሽ በጫማ ውስጥ እንዴት ውቦች ናቸው! ዳሌዎችሽስ በአንጥረኛ እጅ እንደ ተሠሩ እንደ ዕንቍዎች ይመስላሉ። እንብርትሽ የወይን ጠጅ እንደማይጕድልበት እንደ ተነጠጠ ጽዋ ነው፣ ሆድሽ እንደ ስንዴ ክምር፥ በአበባም እንደ ታጠረ ነው።*

ሁለቱ ጡቶችሽ እንደ ሁለቱ መንታ እንደ ሚዳቋ ግልገሎች ናቸው። አንገትሽ እንደ ዝሆን ጥርስ ግንብ ነው፣ ዓይኖችሽ በሐሴቦን ውስጥ በባትረቢ በር አጠገብ እንደ ውኃ ኵሬዎች ናቸው፣ አፍንጫሽ ወደ ደማስቆ አፋዛዥ እንደሚመለከት እንደ ሊባኖስ ግንብ ነው።...

አዕምሮ ሊቀበለው የማይችለው የአምላክ ቃል ነው በተባለ መጽሐፍ ውስጥ የጾታ ፍቅር መካተቱ ነው፤ ይላሉ፡፡

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሙግት መነሻ ነጥብ የሚያደርግ ሙስሊም ስለራሱ መጽሐፍትና ስለሚጠባበቀው ተስፋ እውቀቱ እዚህ ግባ የማይባል መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የዘመናችን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮች ከዚህ መደብ ውስጥ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ የእውቀት ባለጸጋ እና አስተዋይ ተችዎች ቢሆኑ ኖሮ ቁርአንን ለማሞገስ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንቋሸሽ መኃልየ መኃልይን መጥቀስ አልነበረባቸውም፡፡ ሆኖም እውቀቱም፣ ብቃቱም ሆነ ሞራሉ እንደሌላቸው የእስካሁኑ ጉዟችን ያሳየን ይመስለኛል፤ ስለዚህ አድርገዋታል፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ የአላህ ቃል አይደለም ለማለት ድፍረት ያገኙት መኃልየ መኃልይ የጾታዊ ፍቅር መግለጫ ተራ ቅኔ መስሏቸው ይሆናል፡፡ የአላህ ቃል መለኪያው ይህ ከሆነ በሞራላዊ ይዘቱ የወረደ እና ራሳቸው የሚያፍሩበትን መልእክት፣ ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ውስጥ ሲመለከቱ፣ ለምን ቁርአን የአላህ ቃል አይደለም፣ ነቢዩም የአላህ መልእክተኛ አይደሉም ማለት ተሳናቸው?
- መኃልየ መኃልይን እንደ አላህ ቃል መቀበል ከከበዳቸው በሐዲሳቱ የሰፈሩትን የነቢዩን ሱናዎች አላህ የተቀበላቸው እንደ ሆኑ አድርገው አምነው ሊቀበሏቸው እንዴት ቻሉ? የቁርአኑንና የነቢዩን ሱናዎች እንዴት ቢመለከቷቸው መኃልየ መኃልይ ሊደንቃቸው ቻለ? ምናልባት ሥጋቸው የጣፋጭነቱ ተጋሪ ስለሆነ፣ የሚጠባበቁት ተስፋ ይሔው ስለሆነ ሚዛናዊነትን እንዳይኖራቸው አድርጓቸው ይሆን?

ውድ አንባቢ በምድርና በሰማይ ስለሚከናወኑና ተስፋ ስለሚያደርጉት አንድ በአንድ እንነጋገራለን፡፡ ከዚያም የትኛው መለኮታዊ እንደሆነ እናንተው ትመሰክራላችሁ፡፡ በምድር ምን እንዲደረግ ቁርአንና ነቢዩ እንደፈቀዱ ከሚናገረው ልጀምር፡-

**ሱረቱል አል-ኒሳእ 4 ፡ 24**

**ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው**፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡ ከዚሃችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ ጥብቆች ኾናችሁ **ዝሙተኞች ሳትኾኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ፡፡ ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን**

ስጧቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡

وَالْمُحْصَنَاتُ مِنَ النِّسَاءِ إِلَّا مَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ۖ كِتَابَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ ۚ وَأُحِلَّ لَكُم مَّا وَرَاءَ ذَٰلِكُمْ أَن تَبْتَغُوا بِأَمْوَالِكُم مُّحْصِنِينَ غَيْرَ مُسَافِحِينَ ۚ فَمَا اسْتَمْتَعْتُم بِهِ مِنْهُنَّ فَآتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ فَرِيضَةً ۚ وَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ فِيمَا تَرَاضَيْتُم بِهِ مِن بَعْدِ الْفَرِيضَةِ ۚ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمًا

ስለዚህ የቁርአን አንቀጽ ሙፈሲሮች ምን አሉ? የሚለውን ስንመለከት ኢብን ካሲር እንዲህ ነበር ያሉት፡- "ሙጃህዲን እንደገለጸው 'ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን ስጧቸው' የሚለው የወረደው ስለ ሙታ (መደሰቻ) ጋብቻ ነው፡፡ ሙታ (የመደሰቻ) ጋብቻ አስቀድሞ በስምምነት በተወሰነ ቀን የሚያበቃ ጋብቻ ነው[156]" ብለውለታል፡፡

ኢብን አባስ ይህንኑ አሳብ ሲብራሩ፡- "'በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ' ማለት እስከ አራት ሚስት ማለት ነው፤ ደግሞም በተጨማሪ ይህ ማለት ምርኮኛ ሴቶችን በገንዘባችሁ ልትገዙ ትችላላችሁ ማለት ነው፡፡ ደግሞም በስምምነት ለተወሰነ ጊዜ በገንዘባችሁ የመደሰቻ ሚስት (ዘዋጅ አል-ሙታ) ልታገቡ ትችላላችሁ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የመደሰቻ ጋብቻ ህጋዊነት በኋላ ተሽሯል..." ብለዋል፡፡[157]

አያቱላህ አጋ መሐዲ ፑያ እና ኤስ.ቪ. ሚር አህመድ አሊ በጥምረት ባዘጋጁት ማብራሪያ እንዲህ ብለዋል፡- "'فَمَا اسْتَمْتَعْتُم بِهِ (ፋማስታምታ-ቱም ቢሂ)' የተደነገገው ሙታ ተብሎ ለሚጠራው ለጊዜያዊ ጋብቻ ነው፡፡ ይህ በተለየ ሁኔታ ሕጋዊ የተደረገው በቁርአን እና በነቢዩ ሙሐመድ ነው፤ ስለዚህ ይህ ስጦታ ላይሻር ለሁልጊዜ ይኖራል፡፡"[158]

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 4፣ ቁ 3413**

ጃብር ቢን አብዱላህና ሰላማ ቢን አል-አክዋ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፤ የነቢዩ አፈ ቀላጤዎች ወደእኛ መጥተው የአላህ መልእክተኛ ከሴቶች ጋር የመደሰቻ ጋብቻ በማድረግ እራሳችሁን እንድታስደስቱ ፈቅደዋል አሉን፡፡[159]

---

[156] *Tafsir ibn kathir vol 2 page 423-424*

[157] *Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās page 86*

[158] *Tafsir Ayatullah Agha Mehdi Pooya and S.V Mir Ahmed Ali, sura 1-5 page 365*

[159] *Sahih muslim vol 4, page 21*

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 4፣ 3415**

> አቲ እንደዘገበው፤ ጃብር ቢን አብዱላህ ኡምራ ለማድረግ መጣ፡፡ እኛም ወደ መኖሪያው ሄድን፤ ሰዎችም ስለተለያዩ ነገሮች ይጠይቁት ነበር፡፡ ከዛም ስለጊዜያዊ ጋብቻ ጥያቄ አነሱ፤ እርሱም በዚህ ላይ ሲናገር አዎን በአላህ መልእክተኛ የሕይወት ዘመን፣ በአቡበከር ዘመን፣ በኡመርም ዘመን ሁሉ በዚሁ በመደሰቻ ጋብቻ እራሳችንን እናስደስት ነበር፡፡[160]

የዚህ ጋብቻ በስምምነት የሚወሰነው የጊዜ ገደብ ከስንት እስከ ስንት ሊሆን ይችላል? የሚለውን የነቢዩ ሐዲሳትና የእስልምና ምሁራኑ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡-

**ሳሂህ ሙስሊም 8 ፡ 3252**

> ሳብራ ጁሃኒ እንደዘገበው፤ የአላህ መልእክተኛ ጊዜያዊ ጋብቻን ፈቀዱልን፡፡ እኔና ሌላ አንድ ሰው ወጥተን ሄድን፡፡ እንደ ወጣት ሴት ግምል አንገቷ የረዘመ ባን-አሚራዊት ሴት አየን፤ ለመደሰቻ ጋብቻም እራሳችንን አቀረብንላት፡፡ እርሷም ምን ያህል ትከፍሉኛላችሁ? አለች፡፡ እኔም ካባዬን አልኳት፤ ጓደኛዬም እንዲሁ ካባዬን አለ፡፡ የጓደኛዬ ካባ ከእኔ ካባ የተሻለ ነበር፡፡ ነገር ግን ከእርሱ ይልቅ እኔ ወጣት ነበርኩ፡፡ ወደ ጓደኛዬ ካባ ባየች ጊዜ ወደደችው፤ ደግሞ ወደ እኔ በጨረፍታ ስትመለከት እኔን ወደደችኝ፡፡ እርሷም ደህና አንተና የአንተ ካባ ለእኔ በቂ ነው አለች፡፡ <u>ከእርሷ ጋር ለሦስት ምሽቶች ቆየሁ</u>፤ ከዛም የአላህ መልእክተኛ ከእናንተ መካከል በጊዜያዊ ጋብቻ ከሴቶች ጋር ያለ ሊለያይ ይገባዋል አሉ፡፡[161]

ሙታ ጋብቻን በተመለከተ ከሙስሊም ምእመናን የተጠየቀን ጥያቄ ምሁራኑ እንዴት ምላሽ እንደሰጡ ላስነብባችሁ፡-

> "አንደኛ ጥያቄ፤ አንድ ሰው የመደሰቻ ጋብቻን ለአንድ ሰዓት መዋዋል ይችላልን? መልስ፡- በመርህ ደረጃ አዎን እላለሁ፤ በተመሳሳይ መንገድ አንድ በቋሚ ጋብቻ ሚስት ያገባ ሰው በአንድ ሰዓት ውስጥ እንዲያውም ከዛ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሊፈታት ይችላል፡፡ በተግባር በዚህ መልኩ ቋሚ ጋብቻን የማፍረሱ አጋጣሚ የለውም፤ ስለዚህ በመደሰቻ ወይንም በጊዜያዊ ጋብቻም ውስጥ አይተገበርም፡፡[162]

---

[160] *Sahih Muslim vol 4, page 22*

[161] *Ibid page 23*

[162] *Ahlul Bayt Digital Islamic Library Project Team [3], A Shi'ite Encyclopedia, temporary-marriage-islam-part-8, Ahlul Bayt Digital Islamic Library Project [4],* www.al-islam.org

ስንት የመደሰቻ ሚስቶች ይኑሩት ተብለው ለተጠየቁት ምላሽ ሲሰጡ እንዲህ ነበር ያሉት፡-

> "ጥያቄ ሰባት፡- አንድ ወንድ አራት ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ሚስቶች ወይም ቋሚ ሚስቶች እያሉት ተጨማሪ የመደሰቻ ጋብቻ ሚስት መዋዋል ይችላልን? መልስ፡- አዎን፤ ይህን በተመለከተ በጊዜያዊ (በመደሰቻ) ጋብቻ የተገባች ሴት ጉዳይ፣ በእስልምና ከባሪያ ሴት ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁሉም ሙስሊሞች እንደሚስማሙት አንድ ሙስሊም በቁጥር ሳይገደብ የፈለገውን ያክል ባሪያ ልጃገረዶችን እንዲያገባ ይፈቀዳል፡፡ እስልምና በቋሚ ጋብቻ ገደብን እንደሚያስቀምጠው በዚህ ላይ ገደብን አላስቀመጠም፡፡"[163]

አንድ የታብሊግ ጀምአቲ ምሑር ሙታን (ጊዜያዊ ጋብቻን) የመተዳደሪያ ሥራ ስለ ማድረግ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ላስነብባችሁ፡-

> "ጊዜያዊ ጋብቻን መተዳደሪያ ስለማድረግ፡- ጥያቄ፡- አንድ ሴት በመደሰቻ ጋብቻ አንድን ወንድ ብታገባ፣ መኽሯን ብትወስድ ከዛም ኢዳዋን ብትፈጽም፣ እንደገና ለአጭር ጊዜ ሌላ ወንድ ብታገባ፣ እንዲህ እንዲህ እያደረገች በዓመት ከግማሽ ደርዘን ወንዶች ጋር ብታገባና መተዳደሪያዋ ብታደርግ ሃራም ነውን? የጊዜያዊ ጋብቻ መርህ የሚደነግገውን እንከፈጸመች ሃራም የሚያደርገው ምንድን ነው? ሃራም ካልሆነ ደግሞ እንደ ነጢአተኛ ልትወገዝ ይገባልን? መልስ፡- በሚገባ የሻሪአውን ህግጋቶች ከተከተለች በዚህ መንገድ መተዳደሪያዋ ብታደርግ ሃራም አይደለም፡፡ ልትኮነንም አይገባም፡፡ ይህ እርሷን በሚያገቡ ወንዶችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"[164]

ከዚህ የቁርአን አንቀጽ ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ መፈቀዶች ይታያሉ፡፡ አንደኛው በጅሃድ ውጊያ የተማረኩ ሴቶችን ማራኪው ጦር የፈለገውን ሁሉ እንዲፈጽምባቸው፤ ቢሻው የወሲብ ባሪያ ሊያደርጋቸው ቢሻው ሊሸጣቸው ተፈቅዶለታል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በመደሰቻ (ጊዜያዊ ጋብቻን) ሴቷ ሙስሊም ሴት አዳሪ ወንዱም ገንዘቡን አፍስሶ ወደነዚህ የመደሰቻ ጋብቻ ባል ፈላጊ ሙስሊም ሴቶች እንዲዲገባ ተፈቅዶለታል፡፡ ይህንን ሁለተኛውን ተግባር አንዳንድ ጸሐፍት "ሴት አዳሪነት በሌላ ስም ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ 'prostitution by other name Muta marriage'"፣ "ሕጋዊ ሴት አዳሪነት ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ 'legal prostitution Muta Marriage'" በማለት ሰይመውታል፡፡

---

[163] *A Shi'ite Encyclopedia, temporary-marriage-islam-part-8*

[164] *Ali Rashid, copyright TAbligh Sub-committee, 2002. http://daiichicorp.com*

ለዚህ ተግባራዊ ማሳያ የሚሆነን በኢራን በብዙ ጎብኝዎች የሚጎበኝ የስምንተኛው ኢማም የኢማም ራዛ መኖሪያ ቤት አስተዳደር የጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ ቢሮ ካወጣው ማስታወቂያ የተወሰነውን ላስነብባችሁ፡-

"እድሜያችሁ ከ12 እስከ 35 ዓመት የሆናችሁ ልጃገረድ እህቶቻችን ከእኛ ጋር እንድትተባበሩ ጥሪ እናደርጋልን፡፡ የምትመዘገቡ እያንዳንዳችሁ እህቶቻቶቻችን ከምስራቅ ቅዱስ ራዛቭ መኖሪያ ጋር የሁለት ዓመት ኮንትራት ታደርጋላችሁ፤ በተጨማሪ በየወሩ ለ25 ቀናት ለመንፈሳዊ ጉዞ የሚመጡትን ወንዶች በመደሰቻ (ጊዜያዊ) ጋብቻን ትፈጽማላችሁ፡፡ ...በየትኛው ቦታ የእያንዳንዱ የጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ ጊዜ ከ5 ሰዓት እስከ 10 ቀናት ይሆናል፡፡ ዋጋውም እንደሚከተለው ነው፡-

- የ5 ሰዓት ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ.... 50,000 ቶማነስ ($50 US)
- 1 ቀን ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ.... 75,000 ቶማነስ ($75 US)
- 2 ቀን ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ....... 100,000 ቶማንስ ($100 US)
- 3 ቀን ጊዜያዊ (የመደሰቻ) ጋብቻ...... 150,000 ቶማንስ ($150 US)
- ከ4–10 ቀናት መካከል የመደሰቻ (ጊዜያዊ) ጋብቻ... 300,000 ($300 US)

ልጃገረድ የሆኑ እህቶቻችን ለክብረ ንጽህናቸው ከገሰስ 100,000 ቶማንስ (የኢራን ገንዘብ) ወይንም $100 US ተጨማሪ ክፍያ ያገኛሉ."[165] ይላል፡፡

ሱኒዎቹ ምንም አንቀጽ ቁርአን ውስጥ ቢሰፍርም፣ ሙስሊሟን ሴት ሴት አዳሪ እንደትሆን የሚያደርግና ወንዱንም ከእነዚህ ሴት አዳሪ ሙስሊሞች ጋር እንዲማግጡ ፈቃድ የሚሰጥ በመሆኑ እና የመልካም ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር መገለጫ ባለመሆኑ በተግባር ባይሆንም በቃል ደረጃ ይቃወማሉ፡፡ ይህንን ሲሉ አንቀጹን የሚሽር ሌላ የቁርአን አንቀጽ በማሳየት ሳይሆን በሞኝ ያሸንፋል ሙግት ነው፤ ሻሪ አንቀጽ አልወረደለትም፡፡ ነቢዩም በግልጽ የከለከሉት ነገር የለም፡፡ ከልክለዋል የሚሉ ወገኖች አሉ ነገር ግን የመደሰቻ (ጊዜያዊ) ጋብቻን የሚፈጽሙት ሙስሊሞች የሚያቀርቡትን የሙግት ሐሳብ ሊረታ የሚችል ምላሽ እስካሁን ያቀረበ አካል የለም፡፡

ወሲብ በእስልምና እዚህ ምድር ላይ ብቻ የሚቀር እንዳይመስላችሁ፡፡ እያንዳንዱ ሙጃህዲን (የጂሃድ ወታደር) ከሚሞትለትና ከሚገድልለት ተስፋ መካከል አንዱ ወሲብ ነው፡፡ ጥቂት ስለ እስልምና ገነት እስኪ እናውራ፤ ቁርአን እና የነቢዩ ሐዲሳት እንዲህ እንደሚሉ፡-

**ሱረቱል አን-ናባ 78 ፡ 31-33**

**ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አልላቸው፡፡ አትክልቶችና ወይኖችም፡፡ እኩያዎች የኾኑ <u>ጡተ ጉቻማዎችም፡፡</u>**

[165] *sheikyermami.com/.../muta-temporary-marriage-or-legalized-prostitution, FEBRUARY 27, 2011*

إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا حَدَائِقَ وَأَعْنَابًا وَكَوَاعِبَ أَتْرَابًا

**ሱረቱል አል-ሙምታሃና 55 ፡ 70-72**

በውስጣቸው ጠባየ መልካሞች መልክ ውቦች (ሴቶች) አልሉ፡፡ ከጌታችሁም ጸጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ? **በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የኾኑ** ናቸው፡፡

فِيهِنَّ خَيْرَاتٌ حِسَانٌ فَبِأَيِّ آلَاءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ حُورٌ مَّقْصُورَاتٌ فِي الْخِيَامِ

**ሱረቱል አጥ-ጡር 52 ፡ 20**

በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው (በገነት ይኖራሉ)፡፡ **ዓይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶችም** እናጠናዳቸዋለን፡፡

مُتَّكِئِينَ عَلَىٰ سُرُرٍ مَّصْفُوفَةٍ ۖ وَزَوَّجْنَاهُم بِحُورٍ عِينٍ

ነቢዩ የእነዚህን ነጫጭ ሴቶች የውበት ጣራ እንዲህ ገልጸውታል፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪቅጽ 4፤ ቁ 3246**

…ከእነርሱ እያንዳንዱ ሁለት ሚስቶች የኖሩታል፤ እነርሱም እያንዳንዳቸው ንጹህና ሥጋቸው እንደ መስታውት የሚያሳይ ቆንጆዎች ናቸው፤ ስለዚያ የእግራቸው አጥንት መቅኔ በሥጋቸው ውስጥ አልፎ ይታያል፤ …[166]

**ጃሚ አት-ትርሚዚ ቅጽ 4፣ ቁ 2522**

"… ከእነርሱ መካከል እያንዳንዱ ወንድ ሁለት ሁለት ሚስቶች ይኖሩታል፤ እያንዳንዷ ሚስት 70 አምባሮችን አድርገዋል፤ የአጥንታቸው መቅኒም ከአምባሮቹ ጀርባ ይታያል፡፡"[167]

**ሙስናድ አህመድ ኢብን ሐምባሊ ሐዲስ ቁጥር 10511**

"የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡- 'በገነት ዝቅተኛ ደረጃ ያለው ሰው 72 ደናግላን ይኖሩታል፤ እያንዳንዷ ልጃገረድ በምድር መለኪያ አንድ ማይል ያክል የመቀመጫ ስፋት አላት፡፡'"

---

[166] *Sahih Al-Bukhari vol 4, page 292-293*

[167] *Jami at-Tirmidhi vol 4, page 513*

**ጃሚ አት-ትርሚዚ ቅጽ 4፣ ቁ 2562**

"የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡- 'ከገነት ሰዎች በደረጃ ዝቅተኛው 80,000 አገልጋዮች እና 72 ሚስቶች ይኖሩታል'፤ አቡ ሳኢድ አል-ኹድሪ የተናገረው ሐዲስ ነው"[168]

እነዚህን ሴቶች በተመለከተ አላህ እንዲህ አለ፡-

**ሱረቱል አል-ሩምታሃና 55 ፡ 56**

በውስጣቸው **ከበፊታቸው** (ከባሎቻቸው በፊት) ሰውም ጃንም ያልገሰሳቸው ዓይኖቻቸውን (በባሎቻቸው ላይ) አሳጣሪዎች (ሴቶች) አልሉ፡፡

فِيهِنَّ قَاصِرَاتُ الطَّرْفِ لَمْ يَطْمِثْهُنَّ إِنسٌ قَبْلَهُمْ وَلَا جَانٌّ ۝

"**ከበፊታቸው**" የሚለው ቃል በጀነት ካለው የወሲብ ማዕከል ጋር በንጽጽር ሲታይ ከዛ በኋላ የሚሆነውን በግልጽ አያመላክትም፡፡ ምክንያቱም በጀነት 'ጅን'ም ሰውም ስላልነበር ከዛ በፊት ላይደፈሩ ይችላሉ፤ ከዛ በኋላ በአንድ ወንድ መጽናታቸው አልተገለጸም፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁ 4879**

"የአላህ መልዕክተኛ ሲናገሩ፡- 'በገነት ከአንድ ወጥ ሉል የተሰራ አዳራሽ አለ፤ ስፋቱም 60 ማይል ነው፣ በእያንዳንዱ ጥግ ከጥግ ጥግ እርስ በእርሳቸው የማይተያዩ ሚስቶች አሉ፤ እናም አማኞች ይጎበኟቸዋል እንዲሁም በእነርሱ ወሲብ በመፈጸም ይደሰቱባቸዋል፡፡' አብዱላህ ቢን ቃኢስ ያስተላለፈው ሐዲስ ነው"[169]

ውድ አንባቢ ወደ ምስራቅ አገራት ብቅ ያሉ አልመሰለዎትም? እነሱም የወሲብ ንግድ አዳራሾችን የገነቡት ከዚህ ተስፋ የተነሳ እዚሁ እንጀምረው ብለው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ለማንኛውም በአዳራሹ ጥጋ ጥግ የተደረደሩት '**ሚስት**' ተብዬ ሴቶች '**ከበፊታቸው**' ከተባለላቸው ሴቶች ውጭ ለመሆናቸው አመላካች ነገር የለም፡፡ ከእነርሱ ውጭ ናቸው ከተባለ አላህ ሙስሊም ወንዶች ወጣ ሲሉ በዛም በወሲብ የሚደሰቱባቸው ሌሎች ሴቶችን አዘጋጅቷል ማለት ነው፡፡ የመደሰቻ ጋብቻው እዚህ ብቻ ሳይሆን ሰማይ ቤትም አዘጋጅቷላ?

---

[168] *Jami at-Tirmidhi vol 4, page 548*

[169] *Sahih al-Bukhari vol 6, page 335; Jami at-Tirmidhi vol 4, # 2528, page 518*

ውድ አንባቢ በምድር በመደሰቻ (በጊዜያዊ) ጋብቻ በሰማይ ደግሞ እንዲያ ሊያደርግ ምራቁን እየዋጠ የሚጠባበቅ አዕምሮ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመኃልየ መኃልይ ቅኔዎችን ሲመለከት 'ላምነው አልችልም' ካለ ሐሰተኛ ነው፡፡ ይህንን የመሰለ ጉድ በጓዳ ተሸክሞ እንደ ንጹህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የትችት በትር መሰንዘር እንዴት ይቻላል? ይህንን የሚያደርጉት ሽአዎች ናቸው እንዳትሉ ሁሉም ሐዲሶች የናንተው ናቸው፡-

ውድ አንባቢ፡-

- ❖ ውድ አንባቢ፤ ሴት ልጅዎት በመኽር ስም ገንዘብ እየተቀበለች ከተለያዩ ወንዶች ጋር ብትተኛ፣ እህትዎት ይህንን መተዳደሪያዋ ብታደርገው፣ ምናልባት ሴት ከሆኑ ደግሞ ባለቤትዎት ወጣ ባለ ቁጥር ሴት አዳሪ ሙስሊም ቤት ጎራ እያለ የመደሰቻ ጋብቻውን ቢያጧጡፍ ምን ይሰማዎታል?
- ❖ ደስታን እንደማይፈጥርልዎት እርግጠኛ ነኝ፤ ታዲያ በርስዎ ፊት እንዲህ አስቀያሚ የሆነን ነገር ሁሉን የሚችለው አምላክ የሚያዝ ይመስልዎታል? ቅድመ እስልምና ላይ በኖሩት የዚህ ባህል ባለቤቶች ላይ ለመፍረድስ ምን ያክል አቅም ወይም ፍትሃዊነት ሊኖረው ይችላል?
- ❖ ይህን የፈቀደና እንዲያ ያዘጋጀ አላህ የትኛው አላህ ነው? ይህን የመሰለ አሳፋሪ የዝሙት ፈቃድ የሚሰጠው ቁርአንስ የየትኛው አላህ ቃል ነው? እንደ እውነተኛው አምላክ ቃል አድርጎ መቀበል እንዲሁም የሕይወት መመሪያ አድርጎ መያዝ ይስፈልጋል ብለው ያምናሉ? ዛሬ ላይ ያለው ትውልድ እንደ ኀጢአት ተመልክቶ በተጸየፈውና አዕምሮው ሊቀበለው በከበደው ጸያፍ ድርጊት የሚያዙት ምን አይነት አምላክና ምን አይነት ነቢይ ቢሆኑ ነው?
- ❖ እንዲህ አይነት መልእክት ተሸክሞ የመጣ ነቢይ ከእውነተኛው አምላክ የተላከ መልእክተኛ ነው ብሎ መቀበል እንዴት ይቻላል? እነርሱን በመታዘዝስ ጀነትን የሚቀዳጁ ይመስለዎታል? ሕይወትዎ ቀልድ አይደለምና የት እንዳሉ ቆም ብለው አሁን ያስቡ፤ ራስዎንና ወዳጆችዎን ከዘላለም ጥፋት የሚታደጉበት ሰዓቱ አሁን ነው፡፡

እስልምና እንዲህ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት ምን አፍ ይኖራል? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የሚያምኑትን አመለካከታቸው ምን እንደሆነ ጠይቀዋል? ከጠየቁ አይሁዳዊው ምን አላቸው? ክርስቲያኑስ ምን ምላሽ ሰጣቸው? እንዲህ አይነት አካሄድ ተከትለው ቢሆን ኖሮ መደናገር ውስጥ ባልገቡ ነበር፡፡ ለነገሩ እንዲህ ዓይነት መንገድ ሊከተል የሚችለው እውነትን የሚፈልግ ሰው ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ለማንኛውም ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩ ሰዎች መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን እንደሚሉት ተራ የጾታ ፍቅር መግለጫ አለመሆኑን ሊያውቁ

ይገባል፡፡ መጽሐፉ ከሰለሞን 1005 መዝሙሮች መካከል የተመረጠ የመዝሙሮች መዝሙር ተብሎ ይታወቃል፡፡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት መጽሐፍ ለመሆኑ አይሁዳውያኑም ሆኑ ክርስቲያኖች መካከል ጥርጣሬ የለም፡፡ ምናልባት የአመለካከት ልዩነት ቢኖር በሥነ አፈታት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት መለያየት በቁርአን ማብራሪያ አዘጋጆችም መካከል የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ኪዳን በጋብቻ በመመሰል ማቅረብ የተለመደ ነው፡፡ በምድራቱ ጣኦት ሲመለክም ምንዝርና እንደፈጸመች ይቆጠር ነበር፡፡[170] እናም አይሁዳውያን እግዚአብሔር አምላክ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገውን ኪዳን ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ የገለጸበት ቅዱስ መዝሙር እንደሆነ ያምናሉ፤ ነውም፡፡ ስለዚህ ይህ ዝማሬ በየዓመቱ ከግብጽ የወጡበትን መታሰቢያ የፋሲካን በዓል ሲያከብሩ በምእራፍ ከፋፍለው ለአንድ ሳምንት ያህል ይዘምሩት እንደ ነበር ትውፊቶች ያስረዳሉ፡፡ እንዲያውም ዝማሬው ቅዱስ ዝማሬ በመሆኑ የዝማሬውን ክብርና ቅድስና እንዳያጎድፉና እንዳያዋርዱ ወጣቶች እድሜያቸው ዝማሬውን ለመረዳት እስከሚደርስ ድረስ እንዳያነቡት ይከለከል ነበር፡፡ ስለዚህ የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ የእስራኤል ሕዝብ እና የእግዚአብሔር የኪዳን ተምሳሌታዊ መግለጫ ዝማሬ እንጂ እንዳሉት የዝሙት መጽሐፍ አይደለም፡፡

> ትንቢተ ሆሴዕ ምእራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3፣ ትንቢተ ኤርምያስ ምእራፍ 3፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል ምእራፍ 16 እና 23፣ ትንቢተ ኢሳይያስ ምእራፍ 50፣ 54

ከዚያም የቀጠለው የክርስትናው ዘመን አሁንም ክርስቶስ ለቤተክርስያን እንዲሁም ክርስቶስ ለአንድ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ የሚገልጽ መጽሐፍ እንደሆነ ይታመናል ነውም፡፡ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት አሁንም በአህዳዊ ጋብቻ ተመስሎ ተገልጾ እንመለከታለን፡፡

> ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5 ፡ 21-30
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 11 ፡ 2፣ ራዕይ 19 ፡ 7-9፣ 21 ፡ 2፣ 9

የፍቅርና የኪዳን ምንነት ለእስልምና ሊገባው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ለአላህ ባሕሪው ለቁርአንም የተልእኮው ዓላማ አይደሉምና ለገባው አይችልም፡፡፡ ሴትንና ውሻን፣ ሴትንና አህያን አንድ አድርጎ የሚያይ እምነት እንዲህ አይነት ጥልቅ ነገር እንዴት ሊረዳ ይችላል?

---

[170] ራዕይ አሳታሚ፣ የብሉይ ኪዳን ማብራሪያ፣ ራዕይ አሳታሚ 2004፣ ገጽ 733.

## 2.9. 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4 ፡ 9-13

በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል፤ ቄርቂስም ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤ ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር አለ። ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛልና ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው። ቲኪቆስን ግን ወደ ኤፌሶን ላክሁት። ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ።

አእምሮ ሊቀበለው የማይችለው ጉዳይ በአላህ ቃል ውስጥ የሰው የግል መልእክት መኖሩ ነው ይላሉ፡፡[171]

አዕምሯቸው እንዴት ነው የሚያስበው ወገኖቼ? ሌላ ሰው ስላጣ ሙስሊሙ ልቡን ቢከፍትላቸው ሳያስተነትኑ እንደመጣላቸው ያገኙትን ለምን ይናገራሉ? ቁርአን ምንና የማን ቃላት እንደሞሉት አያውቁምን? ለመሆኑ የቁርአኑ አስተምህሮ በእርግጥ ተረድተውት ይሆን? ብዬ እንድጠይቅ እገደዳለሁ፡፡ እስልምናን የሕይወት መንገዳቸው ያደረጉት እውነትን መርምረው ስላረጋገጡ ስላልሆነ የት ያውቁትና፤ አይፈረድባቸውም፡፡ እስልምና ቁርአን የአላህ ቃል ነው፣ ነቢዩን ያስተማራቸው መልአኩ ገብርኤል ነው፣ ሲባል ስለሰሙና ጀሯቸው ስለጠገበ ቤተሰቦቻቸውንም በዚሁ ጎዳና ውስጥ ስለአገኟቸው የተጓዙበት መንገድ ነው፡፡

እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያነሱት የሙግት ነጥብ መለኮታዊ መጽሐፍን ለመገምገም የሚያስችል መለኪያ ነው ብለው ካመኑ እንግዲያው ቁርአን የአላህ ቃል አይደለም ማለት ነዋ? ይህንን ራሳቸው ስላረጋገጡልን እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡ እስኪ ቁርአን ውስጥ የተሰገሰጉትን የአላህ ያልሆኑ አሳቦችን እንመልከት፡-

ሱረቱል አል-ጂን (የጋኔን ምዕራፍ) 72 ፡ 1-4

(ሙሐመድ ሆይ!) <u>በል</u> «እነሆ ከጂን የኾኑ ጭፍሮች (ቁርኣንን) አዳመጡ፡፡‹እኛ አስደናቂ የኾነን ቁርኣን ሰማንም› አሉ፣ ማለት ወደእኔ ተወረደ፡፡ ‹ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን)፡፡ በእርሱም አመንን፡፡ በጌታችንም አንድንም አናጋራም፡፡› ‹እነሆም የጌታችን ክብር ላቀ፡፡ **ሚስትንም ልጅንም አልያዘም፡፡›** ‹እነሆም ቂላችን በአላህ ላይ ወሰን ያለፈን (ውሸት) ይናገር ነበር፡፡›

[171] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 41

قُلْ أُوحِيَ إِلَيَّ أَنَّهُ اسْتَمَعَ نَفَرٌ مِّنَ الْجِنِّ فَقَالُوا إِنَّا سَمِعْنَا قُرْآنًا عَجَبًا يَهْدِي إِلَى الرُّشْدِ فَآمَنَّا بِهِ ۖ وَلَن
نُّشْرِكَ بِرَبِّنَا أَحَدًا وَأَنَّهُ تَعَالَىٰ جَدُّ رَبِّنَا مَا اتَّخَذَ صَاحِبَةً وَلَا وَلَدًا وَأَنَّهُ كَانَ يَقُولُ سَفِيهُنَا عَلَى اللَّهِ شَطَطًا

ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ አድርገው የሚቆጥሩ ወገኖች ይህ የቁርአን ክፍል የሚናገረው ዜና ከየት ተገኘ? ብዬ ብጠይቃቸው ከአላህ ማለታቸው አይቀርም፡፡ ኢማም ቡኻሪ ግን ሳሂህ ባሉት ዘገባ ከየት እንደተገኘ ይነግሩናል፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 5፣ ቁጥር 3859**

ጅኖቹ በምሽት ቁርአን ሲቀራ ማድመጣቸውን ለነቢዩ ማን ነገራቸው? ስል ማስሩቅን ጠየቅኩት፤ እርሱም ጅኖቹ ቁርአኑን በምሽት ማድመጣቸውን፣ ለነቢዩ የነገራቸው **ዛፍ ነው** ሲል አባትህ አብዱላህ ነግሮኛል፤ አለኝ፡፡ አብዱር-ራህማን የተናገረው ሐዲስ ነው[172]

ስለዚህ በል እያለ የነገራቸው አላህ ሳይሆን '**ዛፍ**' ነው ማለት ነው፡፡ ዛፍ ሰምቶ ዛፍ አምኖ የሚከተል ሰው ምን ልትሉት እንደምትችሉ አላውቅም፤ በተጨማሪ እስከ ቁጥር 14 ድረስ ያለው የጅኖች ንግግር ነው፡-

ሱረቱል አል-ጅን (የጋኔን) 72 ፡ 8-14

‹እኛም ሰማይን (ለመድረስ) ፈለግን፡፡ **ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት**፡፡ ‹እኛም ከእርሷ (ወሬን) ለማደመጥ በመቀመጫዎች እንቀመጥ ነበርን፡፡ **አሁን ግን የሚያዳምጥ ሰው ለእርሱ ተጠባባቂ ችቦን ያገኛል፡፡** ‹እኛም በምድር ውስጥ ባሉት ሰዎች ክፉ ተሽቷል? ወይስ በእነርሱ ጌታቸው ደግን ነገር ሽቷል? ማለትን አናውቅም፡፡ **‹እኛም ከእኛ ውስጥ ደጎች አልሉ፡፡ ከኛም ከዚህ ሌላ የኾኑ አልሉ፡፡ የተለያዩ መንገዶች (ባለ ቤቶች) ነበርን፡፡** ‹እኛም አላህን በምድር ውስጥ ፈጽሞ የማናቅተው፤ ሸሽተንም ፈጽሞ የማናመልጠው መኾናችንን አረጋገጥን፡፡ ‹እኛም መሪውን በሰማን ጊዜ በርሱ አመንን፡፡ በጌታውም የሚያምን ሰው መግጎደልንም መጭጨመርንም አይፈራም፡፡ **«እኛም ከእኛ ውስጥ ሙስሊሞች አልሉ፡፡** ከእኛም ውስጥ በዳዮች አልሉ፡፡ የሰለሙም ሰዎች እነዚያ ቅንን መንገድ መረጡ፡፡»

ውድ አንባቢ ወደ ሌላው የሌላ አካል ንግግር ከማለፌ በፊት እዚህ ላይ ትንሽ ማለት የምፈልገው ነገር አለ፡፡ አንድ ፊደል የቆጠረ ሰው እነዚህን **በሱረቱል አል-ጅን** 72 ፡ 1-14 ድረስ ያለውን በማንበብ ብቻ ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ የቁርአን ክፍል፡-

[172] *Sahih al-Bukhari vol 5, #3859, page 117*

❖ የትርጉም ችግር ይታያል፤ جَدُّ (Jaddu) ለሚለው የአረብኛ ቃል መዝገበ ቃላት የሚሰጠው ትርጉም '**አያት**' የሚል ነው[173]፡፡ ሆኖም ትርጉሙ ሲሰራ ክብር ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ የትርጉሙ ምንጭ ደግሞ ቋንቋው ሳይሆን የሰዎች አሳብ ነው፡፡ እንግዲህ ጅኖቹ እንዳሉት አላህ ለጌታቸው አያት ከሆነ፣ ከማን ቢወልዳቸው ይሆን አያት የሆናቸው? ሚስቱስ ማን ትባላለች? አላህስ አያት የሆነለት የጅኖቹ ጌታ ማን ይባላል? ይህ አባባላቸው ደግሞ ከአራት ነጥብ በኋላ ካለው መልእክት ጋር ይጋጫል፡፡ አላህ የማይወልድ የማይወለድ ከሆነ፣ የጌታችን አያት ብለው እንዴት ሊጠሩት ቻሉ? አያት ከሆነስ 'ሚስትንም ልጅንም አልያዘም' እንዴት ይባላል? አላህ ሚስትም ሆነ ከሚስት የተወለደ ልጅ እንደሌለው እኛም ክርስቲያኖች እናምናለን፣ እንመሰክራለን፣ እያስተማርንም እንገኛለን የቁርአኑ ተናጋሪና ባለቤት አላህ ከሆነ ይህን ውል የሌለውን ነገር መናገሩ ለምንድን ነው? አላህ ለሰው ልጆችም ጠላት እንደሆኑ የተናገረላቸውን እነዚህን ዋሾዎች እንደገና ስለ እርሱና ስለ ቃሉ ምስክሮች ቢያደርጋቸው በሰው ዘንድ ምስክርነታቸው ተቀባይነት ያገኛል ብሎ እንዴት አሰበ? ነቢዩስ ይህን እንዴት ተቀበሉት? እርስዎስ የቁርአን አማኝ የሆኑት ይህንን እንዴት አምነው ተቀበሉት?

❖ ሌላው ችግር ሳይንሳዊ ስህተት መናገሩ ነው፤ '**ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት**' የሚለው ተወርዋሪ ኮከቦችን ለማመላከት ነው፡፡ ይህንን ከሱራ 15 ፡ 18፣ ሱራ 37 ፡ 8፣ ሱራ 41 ፡ 12 እንዲሁም ከሱራ 67 ፡ 5 ጋር ማመሳከር ትችላላችሁ፡፡ ከዋክብት የተፈጠሩት ወሬ ለመስረቅ ጀነት የሚሔድን ሰይጣን ለመምታት እንደሆነ ያበስራል፡፡ እንዴት ነው ሰይጣን በኮከብ የሚመታው? ተወርዋሪ ኮከብስ ኮከብ ነውን? ይህ ግልጥ ያለ ስህተት ነው፡፡ ቁርአን የአላህ ቃል ቢሆን ኖሮ ይህንን ግልጽ ስህተት አይናገርም ነበር፡፡

❖ ቁርአን እርስ በእርሱ የሚጋጭ መጽሐፍ መሆኑን ይገልጣል፡፡ እርስ በእርሱ የሚቃረን መልእክት ደግሞ ከአላህ ሊሆን አይችልም፡፡ የሰው መልእክት በአላህ ቃል ውስጥ ያሉት የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ የጅኖችን ውሸት ቁርአን ውስጥ እያዩትና ሁሌ እየቀሩት፣ የአላህ ቃል ብለውም እያስተማሩት፣ ለያንኑ ጅን ከሰው ውስጥ ለማስወጣት እየቀሩ እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን በዚህ ሁኔታ ሊተቹ አሰቡ?

ውድ አንባቢ፤ በዛፍ ምስክርነት ላይ ላይ ተመሥርቶ ክርስቲያን ጅን እና ሙስሊም ጅን አለ ብሎ ማመን ራስን ለሰይጣን እስረኝነት አሳልፎ መስጠት

---

[173] *Hans Wehr, Dictionary of modern written arabic, edited by JM.Cowan, spoken language services.Inc, Urbana USA 1994, page 135;* *Commentary on Suratul Jinn, written by a group of muslim scholars under supervision of Ayatullah al-Uzma al-Hajj as-Shaikh Nasir Makarimshirazi, translated by Saleem Bhimij, Canada 2003 page 26*

ነው፡፡ ሃይማኖተኛ መሆን ለሰይጣንና ለዘሮቹ ምንም ለውጥ እንደማያመጣላቸው ቁርአን እያቃረነም ቢሆን ይናገራል፡፡ ይህንን ሙስሊሞች ምናልባት እንደ ነቢዩ ቁራኛ ሰይጣናቸውን አግኝተው ማናገር ከቻሉ ቢጠይቁት ሁሉን ይነግራቸዋል፡፡ ለማንኛውም ያለኝን ትልቅ የምሥራች ላብስራችሁ፡- በማንኛውም መልኩ ሰይጣን ጥቃት ያደረሰባችሁ፣ በሌሊትና በቀን የሚያስቸግራችሁ፣ ቁራኛ ጅናችሁ የሚያስፈራራችሁ እና ከዚህም ማረፍ የምትፈልጉ ካላችሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ እውነተኛ መፍትሔ ነውና ወደ እርሱ ኑ እረፍት ይሰጣችኋል፡፡ እንዲህ እያለ ይጠራችኋል፡-

**የማቴዎስ ወንጌል** 11 ፡ 28-29

> እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ፣ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤

ከዚህ ቀጥለን ስለ ነቢይ ኸሊፋ ኡመር ኢብን አል ኸታብ ቃሎች እንነጋገር፡፡ የነቢያት መደምደሚያ ነቢዩ ሙሐመድ ሆነው እያለ እንዴት ነቢይ ብለህ ትጠራዋለህ? የምትሉ እንደማትጠፉ አውቃለሁ፡፡ ነቢይ ብዬ የጠራሁት እኔ ሳልሆን ራሳቸው ነቢዩ መሆናቸው ሊታወቅልኝ ይገባል፡፡ ይኸው ሐዲሱ፡-

> አት-ታባራኒ ሲናገር አቡ ሳኢድ አል-ኹድሪ እንዲህ አለ፡- ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- ከኡመር ጋር የሚጣላ ማንኛውም ሰው ከእኔ ጋር ይጣላል፤ ኡመርን የሚወድ ሁሉ እኔንም ይወዳል፡፡ አላህ በአረፋ ምሽት ላይ በአጠቃላይ በህዝቡ ይመሰገናል፤ በተለይ ደግሞ በኡመር የመሰገናል፡፡ **<u>አላህ ነቢይን ከተከታዮቹ መካከል መገለጥን የሚቀበል ሰው ሳይጨምር አይልከውም</u>**፤ እናም **<u>በእኔም ተከታዮች ዘንድ አንድ አለ እርሱም ኡመር ነው</u>**፡፡ እነርሱም እንዲህ አሉ፡- የአላህ መልእክተኛ እንዴት ነው ራዕይ የሚገለጥለት? **<u>ሲመልሱም መልአክቶች በእርሱ አንደበት ይናገሩበታል</u>**፡፡ ይህ የሐዲስ ሰንሰለት ሀሰን ወይንም ጥሩ የሚባል ነው፡፡[174]
>
> በአቡ አብዱላህ አሽ-ሻይባኒ ፋዳኢል አል-ኢማማይን በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ አይቻለሁ፡- **<u>ኡመር ከአላህ ጋር በሃያ አንድ ሁኔታዎች ተስማምቶ ነበር</u>**፤ ከነዛ እነዚህን ስድስቱን ጠቅሷል፡፡[175]

ነቢዩ ሙሐመድስ ነቢይ የተባሉት መልአኩ 'ገብርኤል' ቁርአኑን ይዞላቸው ስለማጣ አይደለምን? ለነቢዩ ኸሊፋ ኡመርም እንዲሁ አድርጓል፤ አሉን ነቢዩ

---

[174] *Jalal ad-Din as-Suyuti, The History of the Khalifahs, 3rd Revised edition, Translated by Abdassamad Clarke, Ta-Ha Publishers Ltd, London 1995, page 120*
[175] *Ibid page 124*

ሙሐመድ ራሳቸው፡፡ ታዲያ አላህ በነቢዩ ኸሊፋ ኡመር በኩል ካወረዳቸው የቁርአን አንቀጾች መካከል ሦስቱን አሁን እንመልከት፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁጥር 402 ገጽ 265**

"አላህ ከእኔ ጋር በሦስት ነገሮች ተስማማ፡-

ሀ) እንዲህ አልኩ፡- 'የአላህ መልእክተኛ ሆይ ለጥቂት ሶላቶቻችን የአብርሐምን መቋሚያ የሶላት ቦታችን ብናደርግ ብዬ ተመኘሁ' አልኳቸው፡፡ ወዲያው **ሱረቱል አል-በቀራ** 2 ፡ 125 'እናንተ ሰዎች ለአንዳንድ ሶላቶቻችሁ (ምሳሌ በካባው ሁለት ረክአት ጠዋፍ ለማድረግ) የአብርሐምን መቆሚያ የሶላት ቦታ አድርጋችሁ ውሰዱ' የሚለው ወረደ፡፡

ለ) ስለ ሴቶች መሸፈን የወረደውን በተመለከተ እንዲህ አልኩ፡- 'የአላህ መልእክተኛ ሆይ ከወንዶች ራሳቸውን እንዲሸፍኑ ሚስቶችዎትን ቢያዙ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም መጥፎና መልካም ከሆኑት ጋር ያወራሉና' አልኩ፤ በዚህ ጊዜ ሂጃብን የተመለከተው ራዕይ ወረደ፡፡

ሐ) አንድ ጊዜ ነቢዩን ለመቃወም የነቢዩ ሚስቶች በፊታቸው ሕብረትን ፈጠሩ፤ እኔም እንዲህ አልኳቸው፡- 'ምናልባት ነቢዩ ሁላችሁን ቢፈታችሁ ጌታው በእናንተ ምትክ ከእናንተ የተሻሉትን ሚስቶች ይሰጠዋል'፡፡ ወዲያውም እንዳልኩት ያለ የቁርአን አያት ወረደ፡፡

**ሱረቱል አል-ተህሪም (የማውገዝ ምዕራፍ)** 66 ፡ 5

(መላችሁንም) ቢፈታችሁ ከእናንተ የበለጡ ሚስቶችን ሙስሊሞች አማኞች ታዛገሮች ተጸጻቾች፣ (ለአላህ) ተገዢዎች፣ ጾመኞዎች ፈቶች፣ ደናግልም የኾኑትን ጌታው ሊለውጠው ይከጀላል፡፡"[176]

ከዚሁ ሰው ከከሊፋ ኡመር ጋር የተያያዘ ሌላ ሐዲስ ላስነብባችሁ፡-

ኢብን ማርዳውያህ ሲናገር ሙጃሁድ እንዲህ አለ፡- <u>**ኡመር አስተያየት ሲኖረው በዛ ላይ ቁርአን ይወርዳል (ያንን ለማረጋገጥ)**</u>፡፡ ኢብን አስካሪ ሲናገር አሊ እንዲህ አለ፡- <u>**የኡመር የተወሰኑ አስተያየቶች ቁርአን ውስጥ አሉ**</u>፡፡ [177]

[176] *Sahih al-Bukhari vol 1, page 265*
[177] *The History of the Khalifahs, page 123*

ይህ ማለት ቁርአን አላህና ኸሊፋ ኡመር ያዋጡት ነው ማለት ነው፡፡ ታዲያ ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽርሊቆች አድርገው የቆጠሩት ወገኖች ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን እያረጋገጡልን እንደሆነ አልታያቸውምን?

ሐዲሳቱ የተወሰኑ ጥያቄዎችን እንዳነሳ እየኮረኮሩኝ ነው፤ እስኪ ይህኛውን አንብቡና ከጥያቄዎቼ ጋር አነጻጽሩ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2032**
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2042-2043**

*ኡመር ነቢዩን ከእስልምና መምጣት በፊት በድንቁርናው ጊዜ በአል-ሃረም መስጅድ አላህን በማውሳት/ኢቲካፍ/ አንድ ምሽት ለመቆየት ተስየ ነበር፤ ሲል ጠየቀ፡፡ ነቢዩም የገባኸውን ስእለትህን ፈጽም አሉት፡፡ ኢብን ኡመር የተናገረው*[178]

- ❖ ነቢዩ ሙሐመድ ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ነቢይነታቸው 13ኛ ዓመት ድረስ ካዕባን ቂብላቸው አድርገው ሲሰግዱ ኖረዋል፡፡ የመናገሻ ከተማ አስፈልጓቸው ወደ መዲና ሲሄዱ ያለ አላህ ፈቃድ ቂብላቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ቀይረው ከ16-18 ወራት[179] ከተከታዮቻቸው ጋር ሲሰግዱ ቆይተዋል፡፡ ከዛ ነቢይ ኸሊፋ ኡመር ወደ መጀመሪያው ወደ አደግንበት ቂብላችን ብንመለስ ምን ይመስለዎታል ብሎ ነቢዩን ሲያማክር **ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 125** ወረደ ተባለ፡፡ በካዕባው ዙሪያ ያደርጉት የነበረው ኡምራ፣ ጠዋፍና ስግደት በአላህ ነበርን? ከሆነ ቅድመ እስልምና የነበሩት ለምን ወንጀለኛ ተባሉ?
- ❖ አላህ ነቢዩ መዲና ሲደርሱ ቂብላቸውን ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቀይሩ ምንም አላላቸውም፡፡ ታዲያ ኸሊፋው ለነቢዩ ማሳሰቢያውን ሲያቀርብ ወዲያው ይህንን አለ መባሉን ምን ያህል አምኖ መቀበል ይቻላል? አላህ የተናገረ ከሆነና መካ የሙስሊሞች የመጨረሻ ቂብላ ከሆነ ከመቀየሩ በፊት መጀመሪያ ቀድሞ የነበራቸውን ቂብላ እንዲጠብቁ ለምን አላሳሰበም? ይህም ይቅር፤ ከሊፋው ማሳሰቢያውን ከማቅረቡ በፊት ለነቢዩ ትዕዛዙን ማስተላለፍ ያልቻለው ለምን ነበር? አላህ ምን ዓይነት ጨዋታ እየተጫወተ ነው ያለው? የቁርአን ባለቤት ማን ነው? ኸሊፋ ኡመር እና ነቢዩ ሙሐመድ?
- ❖ ሂጃብን የሚመለከው የቁርአን አንቀጽ የወረደበትን ጊዜ በተመለከተ ሳሂህ የሆኑት ሐዲሳቱ የያዙት ዘገባ እርስ በእርሱ የሚጋጫል፡፡ በሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2637[180] ላይ እንደተገለጸው ሕጻኗ ሚስታቸው

---

[178] *Sahih al-Bukhari vol 3, page 145-146, 152*
[179] *Sahih al-Bukhari vol 6, #4486 page 31*
[180] *Sahih al-Bukhari vol 3, page 463*

አይሻ በትዳር ላይ በመማገጥ ወንጀል ተከሳ እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ኸሊፋው **'ከአላህ ጋር ተስማማሁ'** ባለበት ሐዲስ አንቀጹ የወረደው ነቢዩ ሙሐመድና ከሊፋ ኡመር ከተመካከሩ በኋላ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ሂጃብን የተመከተው አንቀጽ አላህ ያወረደው ወይስ ነቢዩን ከገጠማቸው ችግር የተነሳ ነቢዩ ሙሐመድ እና ከሊፋ ኡመር ተመካክረው ያወረዱት? ችግር የተፈጠረው ነቢዩ ቤት ስለሆነ አንቀጹ አላማ ያደረገውስ የነቢዩን ሚስቶች ብቻ ነበርን?

- ❖ ሃፍሳ በቤቷ በአልጋዋ ላይ ነቢዩን እና ማርያህ የተባለችውን የነቢዩን ባሪያ ወሲብ ሲያደርጉ ያዘቻቸው፤ ነቢዩም ደግመው እንደማያደርጉትና እርሷ እንደማትገባቸው ምለው ተገዝተው ቃል ገቡላት ለሌላ ሰውም እንዳትናገር አስጠነቀቋት፡፡ እርሷ ቃሏን ጥሳ ለአይሻ በመናገሯ **ሱረቱል አል-ተህሪም** 66 ፡ 5 ወረደ ተባለ[181]፡፡ እናም አንቀጹ የወረደው ኸሊፋ ኡመር ሴቶቹን በነቢዩ ቤት ከገሰጻቸው በኋላ ነበር፡፡ ለነገሩ ከሁኔታዎች በፊት ወርዶ የሚያውቅ የቁርአን አንቀጽ የለም፡፡ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ የወረደው የቁርአን አንቀጽ የአላህ ወይስ ነቢዩን ከመጣባቸው ውርደት ስላጣቸውና ከጎናቸው በመቆም ስላስደሰታቸው ያጸደቁት የኸሊፋ ኡመር ቃል?
- ❖ ለነቢዩ ሚስቶች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ከቀደሙት ነቢያት አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ ነው፤ ከዚህ የተነሳ ከሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 89-90 ጋር ይጋጫል ማለት ነው፡፡ ሁለቱም መልእክቶች ከአላህ የወረዱ ከሆኑ ራሱን በራሱ የሚቃረን አምላክ ነዋ?
- ❖ አላህ እንዲህ ባለ ሁኔታ እንዲህ አይነት አንቀጽ ባወርድ ሰዎች ቃሉን ከእኔ እንደሆነ አምነው ሊቀበሉት ይችላሉ ብሎ እንዴት አሰበ? ምክንያቱም ችግሩ ተፈጥሮ፣ የሰው ምክርና ማስፈራራት ፈሶ ካበቃ በኋላ ወረደ የተባለ አንቀጽ ነው፡፡
- ❖ ቁርአን የማን ቃል ነው? የአላህ ከሆነ የከሊፋ ኡመር ቃላት ስብስብ ምን ሊያደርግ ገባ?

አላህ ተውሂዱንም እየሻረ የሰይጣን፣ የሰው፣ የአላህ በተባሉና ማንነቱ ባልተለየ አካል ንግግሮችን ቁርአኑን አጨናንቆት ይገኛል፡፡ ነቢዩ ከመልአኩ ገብርኤል ተማሩት የተባለው ቁርአን በእንዲህ ሁኔታ መኖሩ እየታወቀ፣ የሐዋርያውን መልእክት በየትኛው መመዘኛቸው መዝነው የአላህ ቃል አይደለም ለማለት በቁ? የአላህ ቃል የሐዋርያውን አይነት መልእክት ማካተት የለበትም ብለው ካሉ፣ ቁርአን ከዚህ የላቀውን ይዟል፤ ስለዚህ እውነተኞች እንድንላቸው ቁርአን ውስጥ ካለው ምስቅልቅሉ ከወጣው ቃል ላይ በመጠቃቀስ ይህንንና ያንን አዕምሯችን ሊቀበለው አልቻለም ብለው ሲናገሩ እንስማቸው!!!

**ሱረቱል አል- አዕራፍ (የአዕራፍ ምዕራፍ) 7 ፡ 12-26**

---

[181] *Sahih al-Bukhari vol 6, #4915-4916, page 364-365*; *Asbāb al-Nuzūl PAGE 158*

**ሱረቱል አል-ሒጅር (የሒጅር ምዕራፍ) 15 ፡ 28-49**
**ሱረቱል ሳድ (የሷድ ወይም የዳውድ ምዕራፍ) 38 ፡ 71-85**

ውድ አንባቢ፤ ለአብነት ይህንን ያህል ካሳየኋችሁ ይበቃኛል፤ ልቀጥል ብል ለመለኮታዊ ቃልነቱ ምንም አይነት ማረጋገጫ ማቅረብ በማይችለው ቁርአን ውስጥ የሰው አዕምሮ ሊቀበላቸው የማይችላቸውን በርካታ አንቀጾችን ማሳየት በቻልኩ፡፡ እንግዲህ ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩ ወገኖች የአላህ ቃል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናውቃለን ከሚሉበት ድፍረት አንዴ ቆም በማለት መጽሐፍትን በቅን ልብ ቢመረምሩ መልካም ነው እላለሁ፡፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስመለስ፣ መለኮታዊ መጽሐፍ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

**2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ** 3 ፡ 16-17

የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ÷ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ፣ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

እናም ሐዋርያው ጳውሎስ ለወጣቱ መጋቢ ለጢሞቴዎስ የጻፈው መልእክትና የመዝጊያ ሰላምታ ተራ የሰው መልእክት ቢመስልም ተራ ግን አይደለም፤ የ2ኛ **ጢሞቴዎስ** 4 ፡ 9-13ን ዓላማ የሰነቀ ድንቅ መልእክት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለጢሞቴዎስም ሆነ በየዘመናቱ ለሚኖሩት ልጆቹ አስተማሪ የሆነ ልብንም የሚያቀና መልእክት ነው፡፡ ይህ ተራ የመሰላቸው የመልእክት ክፍል ለአንድ ክርስቲያን የሚያስተላልፈውን መልእክት ማወቅ ከፈለጉ፡-

- ለወንጌል በጠላትነት ከሚመላለሱ ሰዎች ጋር እንዴት መኖር እንደሚገባ **ከቁጥር** 14-16
- ይህን ዓለምና በውስጡ ያለውን ትርፍ ወዶ ከእግዚአብሔር መንገድ ወደኋላ መመለስ የሚያመጣውን የሕይወት ኪሳራ፤ በአንጻሩ በታማኝነት አገልግሎትን መወጣት የሚያስገኘውን ብድራት መዝኖ ስለመዳዝ ደግሞ **ቁጥር** 10፣ **1ኛ የዮሐንስ** 2 ፡ 15-16፣ **ያዕቆብ** 4 ፡ 4
- በታማኝነት እግዚአብሔርን ማገልገል በመጨረሻ የሚያስገኘውን ብድራትና ሽልማት፤ **ቁጥር** 18
- የወንጌሉን ሥራ ወንጌላውያኑ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር እንዴት በትጋት እየሠሩ እንዳሉ፣ ሌሎችም እንዴት ቀጣይነቱን ሊያስጠብቁ እንደሚገባ፣ በመካከላቸው የነበራቸው እጅ ለእጅ መያያዝ ለሥራው ያስገኘውን ጠቀሜታ፤ **ከቁጥር** 10-12
- በሰላሙ ጊዜ ከጎን አብሮ የነበረ ወገን፣ በመከራ ሰዓት ትቶ ሲሸሽ ሊሰጥ ስለሚገባ የፍቅርና የምሕረት ምላሽ፤ **ቁጥር** 16

- ሰው ቢጥል በችግር ጊዜ አብሮ ባይቆም፣ እግዚአብሔር አምላካችን ሁል ጊዜ ከአማኙ ጋር እንደሚሆን፣ በመከራም ሆነ በደስታ ጊዜ ብቻን እንደማይተው፣ አገልጋዩን ለጠላቶቹ መጫወቻ እንደ ማይጥለው እንዲያስተውል አማኙን ያስተምራል፤ ከቁጥር 17-18፣ የሉቃስ ወንጌል 21 ፡ 12-19፣ የማቴዎስ ወንጌል 28 ፡ 20

ይህን በሐዋርያው የመዝጊያ ሰላምታ ውስጥ ያለውን አስተምህሮ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ፣ ነቢዩ ሙሐመድ ስለመጨረሻው ፍርድ ባስተማሩ ጊዜ አንዳንዱን እንዳስተማሩ ሐዲሳቱና ቁርአን እራሱ ዘግበውት ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ሰው ከዓለም ትርፍን ፈልጎ መሄድ እንደሌለበትና ቢሔድ የሚቀበለውን ብድራት ሲያሳዩ፡-

**ሱና አን-ናሳኢ ቅጽ 1፣ ቁጥር 75**
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁጥር 1**

"የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- 'የሥራዎች ብድራት በአላማቸው ላይ ይወሰናል፡፡ እናም ማንኛውም ሰው ዋጋውን የሚያገኘው አቅዶ በአላማ በሚሠራው መሠረት ነው፡፡ ታዲያ ማንም ለዚህ ዓለም ትርፍ ወይም ሚስት ለማግባት የሚሰደድ የሱ ስደት ለተሰደደለት ነገር ይሆናል'፡፡ ኡመር የተናገረው ሐዲስ ነው"[182]

ይህን የነቢዩን ቃል አምኖ የተቀበለ አዕምሮ ያለው ሰው፣ የሐዋርያውን መልእክት መንቀፍ ቢጀምር ታማኝነቱ ይሞታል እንጂ፣ በእውነተኞች ዘንድ ሰሚ አያገኝም፡፡

# 3. ሙግት ሦስት

## መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በአሳብም ሆነ በመልእክት ያላቸው አለመስማማት

የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች እንደሆኑ እራሳቸውን የሚቆጥሩት የአገራችንና የውጮቹ ዳኢዎች መጽሐፍ ቅዱስ የአላህ ቃል አይደለም፣ ብሎ ለመሟገት አዕምሮ ሊቀበላቸው የማይችላቸውን አሳቦች መያዙና የተበረዘ መሆኑ በሚሉት

---

*[182] Ahmad bin 'Ali - An-Nasai, Sunan An-NasaI, Translated by Niisiruddin al-Khattiib, Dar-us-Salam, Riyadh-2007, vol 1 page 64-65; Sahih al-Bukhari vol 1, page 45*

መሞገቻዎች አልቆሙም፡፡ ከቁርአን ጋር በአሳብም ሆነ በመልእክት የሚጋጭ መሆኑም ሌላው ተጨማሪው መሞገቻችን ነው ይላሉ፡፡ ለዚህ ሙግት ከመጽሐፍ ቅዱስ ያወጧቸው ጥቅሶችም እኒቸው፡-

❖ "**ኦሪት ዘፍጥረት** 2 ፡ 1-2

**ኦሪት ዘፀአት** 31 ፡ 17

በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች አላህ ከሥራው አረፈ ይላል፤ ማረፍ የሰው ባህሪ እንጂ ለአምላክ የሚመጥን ቃል አይደለም፡፡

❖ **ኦሪት ዘፍጥረት** 37 ፡ 5-10

በዮሴፍ ህልም ምክንያት አባቱ ያዕቆብ የቅንአት ስሜት ተፈጠረበት፤ ነቢይ ሆኖ በልጁ እንደቀናበት መገለጹ

❖ **ኦሪት ዘፀአት** 33 ፡ 17-23

ሙሴ ሰው ሆኖ እያለ አላህን አየ መባሉ፣ የሚሉትን ይጠቃቅሳሉ፡፡"[183]

ውድ አንባቢ፤ ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ አድርገው የሚቆጥሩትን ወገኖች ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን እንደገና ማረጋገጫ ስለሰጡን ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ቁርአን እና መጽሐፍ ቅዱስ በአሳብና በመልእክት የሚለያዩ ከሆነ በርካታ የቁርአን አንቀጾች ከመለኮታዊ ቃልነታቸው ወጥተው ይወድቃሉ፤ አላህንም ሐሰተኛ ያደርጉታል፡፡ አላህ መቼም ቢሆን ሐሰት ከአንደበቱ አይወጣም፤ ነቢዩ ሙሐመድና ቁርአን ግን ከአላህ የተላኩ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ቁርአን ስለራሱ ተልእኮ በተመለከተ ሲናገር፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ (የላም ምዕራፍ)** 2 ፡ 41

ከናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ) **የሚያረጋግጥ** (مُصَدِّقًا) ሆኖ ባወረድኩትም (ቁርአን) እመኑ፡፡ በርሱም የመጀመሪያ ከሓዲ አትሁኑ፡፡ በአንቀጾቼም ጥቂትን ዋጋ አትለውጡ፡፡ እኔንም ብቻ ተጠንቀቁ፡፡

وَآمِنُوا بِمَا أَنزَلْتُ مُصَدِّقًا لِّمَا مَعَكُمْ وَلَا تَكُونُوا أَوَّلَ كَافِرٍ بِهِ ۖ وَلَا تَشْتَرُوا بِآيَاتِي ثَمَنًا قَلِيلًا وَإِيَّايَ فَاتَّقُونِ

ሱረቱል አሊ-ኢምራን (የኢምራን ቤተሶች ምዕራፍ) 3 ፡ 3-4

---

[183] ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ) ገጽ 41-48

ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት **<u>የሚያረጋግጥ</u>** (مُصَدِّقًا) ሲኾን መጽሐፉን (ቁርኣንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ፡፡ ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል፡፡ (ከቁርኣን) በፊት ለሰዎች መሪ አድርጎ (አወረዳቸው)፡፡ ፉርቃንንም አወረደ፡፡ እነዚያ በአላህ ተዓምራቶች የካዱ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አላቸው፡፡ አላህም አሸናፊ የመበቀል ባለቤት ነው፡፡

نَزَّلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَأَنزَلَ التَّوْرَاةَ وَالْإِنجِيلَ مِن قَبْلُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَأَنزَلَ الْفُرْقَانَ ۗ إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا بِآيَاتِ اللَّهِ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌ ۗ وَاللَّهُ عَزِيزٌ ذُو انتِقَامٍ

እንግዲህ ቁርአን ለቀደሙት መጽሐፍት እውነተኛነት ምስክር ተደርጎ ተልኳል እየተባለ በአሳብና በመልእክት የሚጋጭ ከሆነ ቁርአንና አላህ ዋሽተዋልና መለኮታዊ ቃል ሊሆን አይችልም፤ ስለ ሰጡን ስለዚህ ማረጋገጫ ደግሜ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ለቀደሙት መጽሐፍት ቁርአን ከተናገራቸው፡-

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 44**

**<u>እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፡፡</u>** እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በእነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡...

**ሱረቱል አል-ማኢዳ (የማእድ ምዕራፍ) 5 ፡ 46**

በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡ **<u>ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት</u>** በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡

ውድ አንባቢ፤ እኔ ቁርአን ከእውነተኛው አምላክ ዘንድ በመልአኩ ገብርኤል በኩል የተላከ መገለጥ መሆኑን ከማያምኑት ወገን ነኝ፡፡ ስለዚህ "መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን ጋር በአሳብና በመልእክት የማይስማማ መሆኑ" የሚለውን የሙግት ነጥባቸውን እጋራቸዋለሁ፡፡ እምነቴ መረጃን መሠረት ያደረገ እንጂ እንደ እነርሱ በጭፍን ጥላቻና እስልምናን በማጣጣል መንፈስ ተነድፎ አይደለም፡፡ ይህንን በእስካሁኑ የአብሮነት ጉዟችን ያሳየሁ ይመስለኛል፡፡ የሙስሊሞችን ሙስሊም የመሆን ምርጫቸውን እያዘነም ቢሆን አምላኬና መድሐኒቴ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያከብር ሁሉ እኔም እንደ እርሱ ሙስሊም የመሆን መብትና ፍላጎት እያዘንኩ አከብራለሁ፡፡ ለማንኛውም ከቁርአን ጋር በአሳብም በመልእክትም ልዩነት አላቸው የተባሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንመልከታቸው፡-

## 3.1. ኦሪት ዘፍጥረት 2 ፡ 1-2

*ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ።*

## ኦሪት ዘፀአት 31 ፡ 17

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፥ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ፥ በእኔና በእስራኤል ልጆች ዘንድ የዘላለም ምልክት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ አላህ **ከሥራው አረፈም ተነፈሰም** ይላል፤ ቁርአን ግን በሱረቱል አል-ቃፍ 50 ፡ 38 **አልደከመውም** ይላል፡፡ ሰርቶ መድከም የሰው ባህርይ እንጂ የአላህ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የአላህ ቃል ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይናገርም ነበር ይላሉ፡፡

**ሱረቱል አል-ቃፍ 50 ፡ 38**

*ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን፡፡ **ድካምም ምንም አልነካንም**፡፡*

وَلَقَدْ خَلَقْنَا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ وَمَا مَسَّنَا مِن لُّغُوبٍ

ቁርአን የአላህ ቃል እንዳልሆነ፣ መልአኩ ገብርኤል እርሱን ወደ ነቢዩ ሙሐመድ በማድረስ ተግባር ላይ አለመሳተፉን እንዳምን ያደረጉኝ የቁርአን አንቀጾች ብዙ ናቸው፡፡ **ሱረቱል አል-ቃፍ (የቃፍ ምዕራፍ) 50 ፡ 38** ከእነዛ መካከል አንዱ ነው፡፡ ቁርአን የአላህ ቃል ቢሆን ኑሮ ምንም አይነት እንከን ባልተገኘበት ነበር፡፡ ሆኖም አይደለምና ከዚህ የጠራ ሊሆን አልቻለም፡፡ አንዱ ማሳያ ይህ የቁርአን አንቀጽ ነው፡፡ እንከኖቹን ከማሳየቴ በፊት አንቀጹ ለምን እንደወረደ ከሚተርከው ዘገባ ልጀምር፡-

> ኢብን አባስ እንዲህ አለ፡- አይሁዳውያን ወደ ነቢዩ መጡና ስለ ሰማይና ምድር አፈጣጠር ጠየቁ፡፡ እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡- 'አላህ መሬትን እሁድና ሰኞ ፈጠረ፤ ተራሮችን እና በውስጡ የያዛቸውን ማክሰኞ ፈጠረ፤ ዛፎችን እና ውኃን ሮብ ላይ ፈጠረ፤ ሰማይን ሐሙስ ፈጠረ፤ አርብ ላይ ከዋክብትን፣ ፀሐይን እና ጨረቃን ፈጠረ፡፡' 'ሙሐመድ ሆይ እና ከዛ በኋላስ?' በማለት አይሁዶች ጠየቁ፤ እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡- 'ከዛ ራሱን በዙፋኑ ላይ አደላደለ፡፡' እነርሱም እንዲህ አሉ፡- 'በትክክል

ልትመልስ ይገባሃል፤ ከዛም አረፈ የሚለውን ጨምርበት፡፡' የአላህ መልእክተኛ ተናደዱ፤ ከዛም ይህ አንቀጽ ወረደ፡-…[184]

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በአሳብ እንደማይስማማ ያሳይልናል ተብሎ የተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ የወረደበት ምክንያት ደግሞ የመሠረታዊ አስተምህሮ መፋለስ ስለታየ የወረደ አለመሆኑን ያስተዋላችሁ ይመስለኛል፡፡ 'አረፈ' እና 'ተደላደለ' በሚሉት ቃላት ጨዋታ ምክንያት የወረደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቁርአን የአላህ ቃል ላለመሆኑ ግልጽ ማረጋገጫ ነው፡፡ ሁለት እንከኖቹን ላሳያችሁ፡-

- የአላህ ቃል ቢሆን ኖሮ ለጨዋታው ትክክለኛ ምላሽ በመስጠት ይቋጨው ነበር እንጂ 'ድካምም ምንም አልነካንም' በማለት የቃላት ጨዋታውን አይቀላቀልም ነበር፡፡ ሲሠራ ደክሞት አረፈ አልተባለምና፡፡ ከሥራው ደክሞት አረፈ የሚል ቃል በሙሴ በኩል እንዳላስተላለፈና እነርሱ ደክሞት ነው ያረፈው ሊሉ እንደማይችሉ ራሱ ያውቃል፡፡ ተናጋሪው እውነተኛው አምላክ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ ማረፍ የሚለውን ቃል ስንት ጊዜ እንደጠቀሰውና በዛም ምን ለማስተላለፍ እንደተጠቀመበት ያውቅ ነበር፡፡ እንዲሁም ስለ ሰንበት እረፍት የተጠቀሱት ክፍሎች በአማኙ ዘንድና በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምሕሮ በምን አግባብ ጥቅም ላይ እንደዋለ ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህ መልሱ ይህ ሊሆን አይችልም፡፡ ምናልባት 'አረፈ በል ሲሏቸው' ነቢዩን እኔ ድካም አልነካኝም በል ያላቸው አላህ የሚችለው አረብኛ ቋንቋ ብቻ ስለሆነ ይሆናል፡፡
- የእውነተኛው አምላክ ቃል ቢሆን ኖሮ እርስ በእርሱ የሚቃረን መልእክት አያስተላልፍም ነበር፡፡ ይህንን አንቀጽ ከማውረዱ በፊት ነቢዩ መካ ሳሉ ፍጥረትን በስምንት ቀናት ፈጥሮ እንደ ጨረሰ ተናግሮ ነበር፤ መዲና ሲሔዱ ረስቶት ሳይሆን አይቀርም በስድስት ቀናት እንደፈጠረ ተናገረ፡፡ ምናልባት ከ8 ወደ 6 የወረደው የመጽሐፉ ሰዎች አላህ ለመፍጠር የወሰደበት ስድስት ቀናት እንደሆነ ሲናገሩ ስለሰማ ማስተካከያ አድርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ማረጋገጥ የምትፈልጉ **ሱረቱል ፉሲላት** 41 ፡ 9-12 ያለውን ማንበብ ትችላላችሁ፡፡ በተጨማሪም አንቀጹ የወረደበትን ምክንያት የሚናገረውን ዘገባ መለስ ብላችሁ እዩ፤ ስድስቱ ቀናት የሚያልቁት ሰው ሳይፈጠር ነው፡፡ ቀሪዎቹ ቀናት በሰው መፈጠር ይሞላሉ ማለት ነው፡፡

በዚህ በሱረቱል አል-ቃፍ አንቀጽ አልደከመውም ለሚለው ቃል ኢማም ኢብን ካቲር ቃታዳህ የተባሉትን ሱሃባ ዋቢ አድርገው እንዲህ ብለዋል፡-

> "አይሁዶች የአላህ <u>እርግማን ይውረድባቸውና</u> አላህ ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀናት ፈጠረ፤ ከዛም በሰባተኛው ቀን <u>አረፈ</u> አሉ፡፡ ይህም

[184] *Asbāb al-Nuzūl page 143*

**ሰንበት ነው፤ ለዚህ ነው የተቀደሰ ቀን ብለው የጠሩት፡፡ ከዚያም ከሁሉም በላይ ከፍ ያለው አላህ ስለ ተሳሳተው አሳባቸው ስህተታቸውን ገላጭ ቃል አወረደላቸው አሉ፡፡"[185]**

ይገርማል! አላህ እውቀት አጠር፣ ነቢዩ እውቀት አጠር! ተከታዮቻቸው እውቀት አጠር፣ ሙፈሲሮቹም እውቀት አጠር፣ የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹም በጀሮ ጠገብ ከሚያቁት የሚናገሩ እውቀት አጠር ናቸው፡፡ ቁርአናቸውን ሲቃረኑ ሃይ የሚላቸው አንድም አስተዋይ በመካከላቸው የለምን? እስኪ የቃታዳህን ንግግሮች ነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳትና በቁርአኑ መነጽር እንገምግም፤ በዛውም የነቢዩንና የቁርአንን ስህተት እንዲሁም በዚህ ዘመን የተነሱትን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹን ስህተት አብራችሁ ለመገምገም ሞክሩ፡-

## ➢ የአላህ እርግማን ይውረድባቸውና

ነቢዩን አላህ አንዴ እንዲህ አላቸው ተባለ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2125**

…ነቢዩ ሆይ፤ እኛ አንተን ምስክር፣ አስጠንቃቂ፣ የማህይማኑ ጠባቂ አድርገን ላክንህ፡፡ አንተ የእኔ ባሪያና መልእክተኛ ነህ፤ ስምህንም ሙታወኪል ብዬ ሰይሜሃለሁ፡፡ አንተ መጥፎ ሥነ ምግባር ያለው ጨካኝ ወይም በገበያ የሚጮህ ለፍላፊ አይደለህም፡፡ ደግሞም ክፉን ሚያደርጉብህ ላይ ክፉን አታድርግ፤ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር በይቅርታ በርህራሄ ተስማማ፡፡[186]

በሌላ ሐዲስ ደግሞ ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 8፣ ቁጥር 5997**
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 9፣ ቁጥር 7376**

…ለሌላው ምህረትን የማይሰጥ እርሱም ምህረት አይቀበልም፡፡ አቡ ሁሬይራ እንደዘገቡት[187]

ከቁርአን ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ ሐዲሶች ናቸው፤ ለነቢዩ አላህ የነገራቸው መርሆዎች ከሆኑ የቃታዳህ እርግማን አግባብ አለመሆኑን ያሳዩናል፡፡ የእውቀትን ዲካ ጨብጦ ቢራገም ትክክል ባይሆንም ሊታለፍ ይችል ነበር፡፡ የእውቀት ድህነት በአጥንቱ እያስኬደው እንደ አዋቂ ሲራገም ግን ያሳፍራል፡፡ ለነገሩ ከነቢዩ የተማረውን የት ይጣለው፡፡ እርሳቸው አላህ ግንኙነቴ እንዲህ ይሁን ብሎ

---

*185 Tafsir Ibn Kathir vol 9, page 243-244*

*186 Sahih al-Bukhari vol 3, page 194-195*

*187 Ibid vol 8, page 30; vol 9, page 287*

ተናግሮኛል ካሉ በኋላ እረስተውት ሳይሆን አይቀርም (ብዙ ጊዜ ይዘነጉ ስለነበር ነው) ነብይነቴን አልተቀበሉትም ያሏቸውን የአረብ ጎሳዎች ለአንድ ወር ቁጭ ብለው ይራገሙ ነበር፡፡ ታዲያ ተማሪ መምህሩን ቢመስል አይፈረድበት፡፡ ማረጋገጥ ለምትሹ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 4፣ ቁጥር 3185 መመልከት ትችላላችሁ፡፡

- ❖ አላህ፣ ነቢዩ ሙሐመድና ተከታዮቻቸው በየሁኔታው አሳባቸው የሚገለባበጠው ለምን ይሆን? አላህ እንዲህ አለኝ ያሉ ሰው፣ ተመልሰው ተራጋሚና በቀለኛ ሆኑ፤ ታዲያ የታዘዘውን የማይኖር ነቢይ የዘለአለሙ አምላክ ልኮታል ማለት ይቻላል?
- ❖ ይህንን ከላይ ያነበባችሁትን ሐዲስ አላህ እንደተናገራቸው የሚታመን ከሆነ ተከታዮቻቸው ይህንን እንዲከተሉም ታዘዋል፡፡ ከበዳይ ጋር በይቅርታ ግንኙነትን መገንባት ይገባል እየተባለ ምንም ያልበደለን ሕዝብ ከመሬት ተነስቶ መራገም ምን የሚሉት ነው? ታዲያ ይህ ሰውና መሰሎቹ የሚሰጡት ምስክርነት እንዴት ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል?

## ➢ ለዚህ ነው የተቀደሰ ቀን ብለው የጠሩት

ሰንበትን የተቀደሰ ያለው እግዚአብሔር ራሱ ወይስ ሰው? እነዚህ ሰዎች ቁርአናቸውን አያውቁትምን? ሙፈሲሩ የአላህ ቃል ነው ከሚሉት ከቁርአን ሙሉ አስተምህሮ ጋር እየተጋጩ እንዳሉ አያስተውሉምን? ሰንበት ከቀኖች ሁሉ ተለይቶ የተቀደሰው በአምላክ እንጂ በሰው አይደለም፤ ቁርአናቸውም ይህንኑ ነው የሚደግመው፡፡ ቁርአን ቀኑን ቀዳሹ አላህ እንደሆነ ስላመነ ሰንበትን ያላከበሩትን ሰዎች አላህ እንደቀጣ ዘግቦልን ይገኛል፡፡ የታሪኩ የታማኝነት ነገር ሳይነሳ ማለቴ ነው፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 65**

እነዚያንም ከእናንተ ውስጥ በቅዳሜ ቀን (ዐሣን በማጥመድ) ወሰን ያለፉትንና ለነሱ «ወራዳዎች ስትኾኑ ዝንጀሮዎች ኹኑ» ያልናቸውን በእርግጥ ዐወቃችሁ፡፡

**ሱረቱል አል-አዕራፍ 7 ፡ 166**

ከእርሱም ከተከለከሉት ነገር በኮሩ ጊዜ ለእነሱ «ወራዶች ዝንጀሮች ኹኑ አልን፤» (ኾኑም)፡፡

- ሰንበትን ሰዎች ቅዱስ ብለው የጠሩትና ከቀኖች የለዩት ከሆነ አላህ እንደ ኃጢአተኛ ቆጥሮ የቅጣት ፍርድ እንዴት ሊያስተላልፍባቸው በቃ? ቁርአንስ ሌሎቹን ሊያስፈራራበት ታሪኩን ሊዘግብና 'ይህ የአላህ ቃል ነው' ሊለን እንዴት ቻለ? ቁርአን እየመሰከረለት እርሱን የተላለፉትንም

አላህ እየቀጣ እያለ ቃታዳህ "የጠሩት" በማለት "የሰው ፈቃድ ውጤት" ማስመሰሉ ምን ሊባል ይችላል?

- እነዚህን አንቀጾች **ከሱረቱል አል-ቃፍ 50 ፡ 38** ጋር ያላቸውን ተቃርኖ ማን ያስታርቅ? አላህ በአንድ ጉዳይ ላይ እንዲህ የሚቃረኑ ሁለት የተለያዩ ንግግሮችን የሚናገር አምላክ ይመስለዎታል?
- ቃታዳህስ እውነተኛ ሰው ተብሎ፣ ቃሉም "የአላህ ቃል" ነው ለተባለው ለቁርአን እንደ ምስክር ሊጠቀስ ይገባዋል? ቃታዳህን እና እርሱን መሰል ሰዎችን ምንጭ ተደርገው የተሰሩ የኢብን ካቲርና የሌሎቹ ሙፈሲሮች የማብራሪያ መጽሐፍት ታማኝ ናቸው ብሎ ለመቀበልስ ይቻላል?

## ➢ ሥህተታቸውን ገላጭ ቁርአን አወረደላቸው

- ቁርአን ስለራሱ ማንነት ምን ብሎ ነበር የተናገረው? ስህተታቸውን ገላጭ እንደሆነ ወይንስ ስለቀደሙት መጻሕፍት እውነተኛነት አረጋጋጭ? ቁርአን የገለጠው የአይሁዳውያኑ ስህተት ምንድን ነው?
- ከላይ ያነበባችኋቸው የቁርአኑ አንቀጾች የሚያሳዩት የቀደሙት መጽሐፍት ሥህተት ያለባቸው እንደ ነበሩ ወይስ ሰንበትን ማክበር አምላካዊ ትእዛዝ እንደሆነ?
- ሌላው ሰንበትን ስለተላለፉ አላህ እንደቀጣቸው በአንቀጾቹ የተነገረን ሕዝቦች የሙሴ ሕግ ከሚመለከታቸው ወገን ነበሩን? የሚለው ለጊዜው ይቆይና ከሙሴ ዘመን ጀምሮ አረፈ እያሉ ሰንበትን አርፈው ሲያከብሩ እንዴት አረፈ ትሉኛላችሁ ብሎ ከፍቶት አላህ ሕዝቡን ሲቀጣ አልታየም፤ ግን አንድ ቀን በሰንበት አሣ ያጠመዱትን እንደ ወንጀለኛ ቆጥሮ ቀጣ፤ ለምን?
- አይሁዳውያኑ በሰባተኛው ቀን አረፈ እያሉ ሲያርፉ፣ ምን ለማለት እንደፈለጉ ሳይረዳቸው ነበር እረጅሙን መንገድ አብሯቸው የተጓዘው? ታዲያ ነቢዩ ሙሐመድ ሰንበትን ማክበር የተላለፈበት የሕጉ ቃል አምላካዊ ትዕዛዝ ስለሆነ ትክክለኛነቱን ላረጋግጥ ነው የመጣሁት የሚሉት ለምን ይሆን? በሙሴ ሕግ በኩል ያስተላለፈውን የሰንበት ተላላፊን መቅጫ ሕግ እንዴት ረሳውና ሰዎችን ወደ ዝንጀሮነት መቀየር ጀመረ? እርሱም እንደ ነቢዩ ረሳ ይሆን?
- ውድ አንባቢ፤ በዚህ ምስቅልቅሎሽ ውስጥ የሁሉን ቻዩ አምላክ እጅ ያለበት ይመስለዎታል? መልስዎት አዎን ከሆነ፣ ምን አይነት አምላክ ነው እያመለኩ ያሉት? አላህ አዋቂና ፍትሃዊ አምላክ ነው፣ ብለው የውመል ቂያማ ላይ ከእርሱ ፍትሃዊ ፍርድ እንዲጠብቁ ያስችለዎታል?

ውድ አንባቢ፤ ሙስሊም ይሆኑ ይሆን? ከሆኑ አሁን ቆም ብለው የዘለአለም መኖሪያዎት የት ሊሆን እንዳለው ማሰብ የሚገባዎት አይመስልዎትም? እውነተኛ አምላክ እንዲህ ግራ አጋቢ አምላክ አይደለም፡፡ በእስካሁኑ ጉዟችን ቁርአንን ሆነ

መጽሐፍ ቅዱስን፣ እንዲሁም ሕይወትም፣ እውነትም፣ መንገድም የሆነውን ጌታ ኢየሱስንና ነቢዩ ሙሐመድን ለመለየት የሚያስችልዎትን ትንሽ ብርሃን ያገኙ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ከዘላለማዊ ጥፋት ለመትረፍ አሁኑኑ ቆም ብሎ ማሰብ መጀመር ይኖርበዎታል፡፡ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኖረው ዘላለማዊውን ደስታ ሊያገኙ አይችሉም፡፡ አላህ እርሰዎን እንደሌሎቹ በሞት ከመውሰድ የታገሰበትን ምክንያት ደጋግሜ መናገሬን አልዘነጋሁትም፤ ቢሆንም አሁንም ደግሜ እናገረዋለሁ፡፡ የታገሰው ንስሃ እንዲገቡና በክርስቶስ ያዘጋጀልዎትን የዘላለም ሕይወት ተቀብለው ከዘለአለም ሞት እንዲተርፉለት እድል ለመስጠት አስቦ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ከተረዱለት ለእርስዎ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ያሳያል፡፡ በአጭር ቃል ያፈቅረዎታል፤ ገነት ውስጥ ከቅዱሳኑ ጋር እርስዎንም ማየት ይናፍቃል፡፡

ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የቆጠሩት ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ '**አረፈ**' ሲል ቁርአን '**ድካምም ምንም አልነካንም**' ይላል እናም የአላህ ቃል አይደለም ላሉበት መሞገቻቸው ማብራሪያ ያቀርባሉ፡፡ '**አረፈ**' ወይም ሰርቶ ማረፍ የሰው ባህርይ መገለጫ እንጂ የአምላክ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሰው ባህርይ አላህን በመግለጡ መለኮታዊ ሊሆን አይችልም ይላሉ፡፡ ድምዳሜያቸው በዚህ ላይ የተመሠረተ ከሆነ አሁንም ቁርአን የአላህ ቃል አለመሆኑን ስላረጋገጡልን አሁንም ደግሜ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ምክንያቱም አላህም ቁርአን ውስጥ በሰው መገለጫ ባህሪያት እራሱን ገልጿልና፡፡

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 15**

**አላህ በነሱ <u>ይሳለቅባቸዋል</u>፤** በጥመታቸውም ውስጥ የሚዋልሉ ሲኾኑ ያዘገያቸዋል፡፡

اللَّهُ <u>يَسْتَهْزِئُ</u> بِهِمْ وَيَمُدُّهُمْ فِي طُغْيَانِهِمْ يَعْمَهُونَ

Sura 2: 14-15

…They say: Truly, we are with you, verlly, we were but mocking. Allah **<u>mocks</u>** at them …

**ተሳለቀ፡-** ማለት አፌዘ፣ አላገጠ፣ አሾፈ፣ ቀለደ፣ ዘበተ፣ አሽካበበ ማለት ነው[188]፡፡ ይህ ደግሞ የሰዎችን ባህርይ በመልካም ሁኔታ የሚገልጽ አይደለም፡፡ ቁርአንም ላይ የሰፈረው የሰዎቹን መልካምነት ለማሳየት ሳይሆን፣ ዘባች ማንነታቸውን ለማሳየት የሚባል ነው፡፡

---

[188] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ኢ.አ ዩኒቨርስቲ 1993 ገጽ 106

- *ታዲያ አላህ ይህንን የዘባችነት ባህርይ ከሰዎቹ ጋር ይጋራል ማለት ነውን? ሁሉን ማድረግ እየቻለ እንዲህ ፌዘኛ ይሆናል?*

**ሱረቱል አል-ኒሳእ 4 ፡ 142**

***መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፡፡ እርሱም <u>አታላያቸው</u> ነው፡፡ (ይቀጣቸዋል)፡፡ ወደ ሶላትም በቆሙ ጊዜ ታካቾች ስዎችን የሚያሳዩ ኾነው ይቆማሉ፡፡ አላህንም ጥቂትን እንጅ አያወሱም፡፡***

إِنَّ الْمُنَافِقِينَ يُخَادِعُونَ اللَّهَ وَهُوَ خَادِعُهُمْ وَإِذَا قَامُوا إِلَى الصَّلَاةِ قَامُوا كُسَالَىٰ يُرَاءُونَ النَّاسَ وَلَا يَذْكُرُونَ اللَّهَ إِلَّا قَلِيلًا

**Sura 4: 142**

Verily, the hypocrites seek to **<u>deceive</u>** Allah, but it is He who deceives them …

***አታለለ፡- ማለት ደለለ፣ ሸነገለ፣ ሸለፈ፣ ሸወደ፣ አሞኘ፣ አሽበለበለ፣ ሸፈጠ፣ በደረቅ ላጨ፣ አወናበደ፣ አጭበረበረ፣ ሸለተ፣ ሸበቀ ማለት ነው[189]፡፡***

- *ታዲያ ቁርአን ይህንን የሰዎችን መጥፎ ሥነ ምግባር አሁንም አላህ ከሰዎች ጋር ይጋራል እያለን ይሆን?*
- *እያለ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አረፈ ሲል ደከመው ለማለት ባይሆንም አረፈ ቢል ምን አስደናቂ ይሆናል? ይህንን ሁሉ የሚያደርግ አምላክ ይህንን ሁሉ ሲያከናውን እንዴት አይደክመው፤*
- *ቆይ ቆይ አላህ እነዚህ ሁሉ ካደረገ ለሰይጣን ምን ቀረለት?*

**ሱረቱል አል-ኢምራን 3 ፡ 54**

***(አይሁዶችም) አደሙ አላህም አድማቸውን መለሰባቸው፡፡ አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው፡፡***

وَمَكَرُوا وَمَكَرَ اللَّهُ ۖ وَاللَّهُ خَيْرُ <u>الْمَاكِرِينَ</u>

***አድመኛ፡- ማለት ለተንኮል ሥራ ሌሎቹን ሰዎች የሚያስተባብር፣ ሴረኛ ማለት ነው[190]፡፡ ቁርአንም አላህን ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው ብሎታል፡፡***

---

189 ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አ.አ 1994፣ ገጽ 358

190 የአማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 337

- እና አላህ ከሴረኞች በላይ በጣም ሴረኛ ነው ማለት ነው?

አንድ ሌላ ልጨምር? መልካም፣ የሰዎች የመገልገያ እቃ ለአላህ ጥቅም ላይ ሲውል፡-

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 255**

*አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ሕያው ራሱን ቻይ ነው፡፡ ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም፡፡ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡ ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፡፡ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)፡፡ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፡፡ ጥበቃቸውም አያቅተውም፡፡ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው፡፡*

ይህን የቁርአን አንቀጽ በመላው ሙስሊም ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሌ ወደ መኝታው ሲሄድ አልጋው ላይ በቀኝ ጎኑ ጋደም ብሎ ከሌሊት መጋኛ እንዲከላከልለት ይቀራዋል፡፡ በቤቱም ግድግዳው ላይ ጽፎ እንደ ጥቅስ ይሰቅለዋል፡፡ ለብዙዎች ይህ እየሆነ ያለው አላህ እንዲያ እንዲያደርጉ ስላዘዘ ይመስላቸዋል፣ ነገር ግን አልነበረም፡፡ የነገሩ ምንጭና አስተማሪ በረመዳን የሰዳቃ ምግብ ሊሰርቅ የመጣ ሰይጣን ነበር፡፡ የመጀመሪያው ተማሪ ደግሞ ምግቡን ሲሰርቅ የያዘው የነቢዩ ሙሐመድ የቅርብ ጓደኛ አቡ ሁሬይራ ነበር፡፡ ነቢዩም ትምህርቱን ከአቡ ሁሬይራ ከሰሙ በኋላ ትክክለኛነቱን አረጋገጡ፣ ሕዝቡም ከዛ ቀን ጀምሮ መኝታው ላይ ከሰይጣን ለመጠበቅ አንቀጹን ይቀራ ጀመር፣ የአላህ እጅ በዚህ የለበትም[191]፡፡ የሚገርመው ነቢዩ ሙሐመድን ጨምሮ ማታ ይህንን አንቀጽ የቀራው ሙስሊም ሁሉ ባደረሰው ጽሎት መታመን ተስኖት ከእንቅልፉ እንደነቃ ወዲያው ከአልጋው ወርዶ በአፍንጫው የላይኛው ክፍል ሌሊቱን ሙሉ ያደረን ሰይጣን ለማስወጣት አፍንጫውን በውኃ ሦስቴ ማጠቡ ነው፡-

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 4፣ ቁጥር 3295

*ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- ከእናንተ ማንኛውም ሰው ከእንቅልፉ ሲነሳ ውዱ ያደርግ፣ አፍንጫውን ውኃ ውስጡ በማስገባት ይጠበው፣ ከዛም ሦስቴ ይናፈጠው፣ ምክንያቱም ሰይጣን በአፍንጫው የላኛኛው ክፍል ሌሊቱን ሙሉ አድሮ ሊሆን ይችላል፡፡*[192]

---

[191] *Sahih al-Bukhari vol 3, #2311, page 287-289*

[192] *Sahih al-Bukhari vol 3, page 312*

- ውድ አንባቢ፤ ቆይ እርስዎ ከሰይጣን ለመጠበቅ ብለው አያት አል-ኩርሲ ይቀራሉ እንዴ? በማን መመሪያ ውስጥ ሆነው እየቀሩ እንዳሉ አሁን እያስተዋሉ ነው? እንግዲህ የሰይጣን ምክር እንጂ የአላህ ትእዛዝ አይደለም፤ ታዲያ ጥበቃው የሚፈጸም ይመስለዎታል? ምክሩንስ እንዴት አምነው ተቀበሉት? ወይንስ ከዚህ በፊት እንዲህ መሆኑን አያውቁም ነበር?
- ሰይጣን ለጠላቱ፣ ሊያጠመው ምሎ ለውጣለት ለሰው ልጅ አላማው የሚጨናገፍበትን መንገድ የሚናገር ይመስለዎታል? እንዴት ይህንን አምነው ተቀበሉ? ምንስ ቢል ሰይጣን ይታመናል? ከጀነት የወጣው ለሰው ልጆች ምክር ለመለገስ ሳይሆን ለማጥመምና በመንገዳቸው ላይ ለመቆም መሆኑን ቁርአን ተናግሮ እያለ አሁን ላይ ለብጣሽ ምግብ ተልዕኮውን የሚረሳ ጅል ይመስለዎታል?
- በጠዋት ከእንቅልፌዎት እንደተነሱ ውዱ በማድረግ አፍንጫዎትን ሦስቴ በውኃ እንዲያጥቡ ታዘዋል፤ ትእዛዙ ሰይጣን በአፍንጫዎት የላይኛው ክፍል ሌሊቱን ሙሉ አድሮ ከሆነ ለማስዎጣት ታስቦ ነው፡፡ ሲጀመር ባእድ አካል አፍንጫዎት ውስጥ ሲገባ እንዴት አላስነጥሰዎትም? ይህን ምክር ሲለግስስ ቀሪውን ሌሊቶች የት ለማደር አቅዶ ይሆን? እውን ሰይጣን ይህንን የመሰለ ምክር ይለግሳል ብላችሁ ታምናላችሁ? ጨዋታ አልመሰለዎትም? ቢመስልም ነቢዩ የተናገሩት ነው፡፡

ወደ ተነሳንበት ልምለስ፤ የአማርኛው መንበር ማለት ዙፋን፣ አልጋ፣ ወንበር ማለት ነው፡፡ የአረብኛው ኩርሲ የተቀመጠ ሰው የእግር ማሳረፊያ (footstool) ወንበር ማለት ነው፡፡

- ታዲያ አላህ እንደ ሰው ልጆች ከባለ አራት እግር ወንበር ወይንም ኩርሲ ላይ የሚቀመጥ አምላክ ነው? እንዲያ ቢሆን ነው እንዴ ነቢዩ ሙሴን የአላህን ዙፋን እግር ይዞ እንዳዩት የተናገሩት[193]?

ኩርሲ የተባለውን የአላህን ወንበር በተመለከተ ሁለቱ ሳሂህ የሆኑት ሐዲሶች ምንም አላሉም፤ ምሑራኑ ግን የራሳቸው የሆነ አመለካከት አላቸው፡፡ ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚቆጥሩት ወገኖች ኩርሲ የሚለውን '**አጽናፈ ዓለም**' ብለው ከሚተረጉሙት ወገን ይሆናሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡ ወንበር ለእኛ አራት ወይንም ሦስት እግር ያለው መቀመጫ ነው፤ የእንግሊዝኛው ፍች ደግሞ ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው እግሩን ለማሳረፍ የሚጠቀምበት አነስ ያለ ዱካ ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል ለአላህ አጽናፈ ዓለም ተብሎ ከተተረጎመ በመጽሐፍ ቅዱስ '**አረፈ**' ለአላህ ደከመው ማለት ባይሆንም ከሰው ባህርይ ጋር ባልተያያዘ መልኩ የሚተረጎም ሊሆን እንደሚችል እንዴት ማሰብ ተሳናቸው? በዚህ ሁሉ የጥላቻ ዘመቻ እያደረጉ መሆናቸውን ቁልጭ አድርገው አሳይተዋል፡፡ ሆኖም

---

[193] *Sahih al-Bukhari vol 4, #3398, page 378*

'አረፈ' ደከመው ለማለት እንዳልሆነ፣ የሚያመላክቱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ኦሪት ዘፍጥረት 2 ፡ 1-2 ያለውን ክፍል ለማየት መጽሐፍ ቅዱስን ባነበቡበት ጊዜ እንዳዩ አውቃለሁ፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ድካምን የማያውቅና ብርታቱም ከመታወቅ ያለፈ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

ትንቢተ ኢሳይያስ 40 ፡ 28-31

አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፣ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጕበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፣ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።

መጽሐፈ ኢዮብ 11 ፡ 7-9

የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፥ ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል።

መዝሙረ ዳዊት 121 ፡ 3-4

እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፣ የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።

እግዚአብሔር ከሰው ቋንቋ ውጭ፣ ከሰው ፍጥረታዊ ባህርይ ውጭ ለመሆኑ በጥቂቱ ይህንን ያክል ካልኩ፣ አረፈ ተብለው የተተረጎሙት ሁለት ቃላት ናቸው፤ שבת (shâbath) እና נוּח (nûach)፡፡ ቃላቶቹ ተለዋዋጭ ሆነው ለተለያዩ አግባቦች ጥቅም ላይ እንደዋሉ እንመለከታለን፡-

- እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን መጨረሱን መፈጸሙን ለመግለጽ

    **ኦሪት ዘፍጥረት 2 ፡ 2-3**
    **ኦሪት ዘጸአት 20 ፡ 8-11**

- ይንቀሳቀስ የነበረ ነገር እንቅስቃሴ ሲያቆም

**መጽሐፈ ኢያሱ 3 ፡ 13**
**ኦሪት ዘፍጥረት 8 ፡ 4**
**መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 21 ፡ 10**

- ❖ በመንፈሳዊ ነገር ስለመሸፈን

**መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 2 ፡ 15**

- ❖ ሰንበትን ለማክበር ከማንኛውም ሥራ ስለማረፍ (ሥራን ማቆም)

ኦሪት ዘፀአት 23 ፡ 12
ኦሪት ዘሌዋውያን 25 ፡ 2-4+
ኦሪት ዘሌዋውያን 23 ፡ 3፣ 24፣ 39

ምን አልባት እግዚአብሔር ካልደከመው ሰንበትን እንዲያከብሩ ለማዘዝ **'እረፈ'** ብሎ መናገር ያስፈለገበት ምክንያት ምን ይሆን? ይባል ይሆናል፡፡ የተወሰኑ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡-

- ትዕዛዝ ተቀባዩ ሰው ስለሆነ፣ እንዲገባው በራሱ አግባብ፣ ሊረዳው በሚችል አገላለጽ ሊነገረው ስለሚገባ
- እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የሚያስብ አምላክ ነው፤ ስለዚህ ሕዝቡ ስድስት ቀናትን በሥራ የደከመ አካሉን ማሳረፍ ስለሚኖርበት እንዲያፍ **'እረፈ'** ብሎ መንገር አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ
- ሰው በሰንበት የማረፉ አላማ በቀኑ ላይ ሆኖ የሚወደውን አምላኩን እግዚአብሔርን ማሰብና ማምለክ እንዲችል ጊዜ ለመስጠት ታስቦ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን በማጠናከር ሲናገር ሰንበት የተፈጠረው ለሰው ጥቅም እንጂ ለአምላክ ተብሎ አይደለም፤ የሰው መፈጠር ለሰንበት ሳይሆን፣ ሰንበት ለሰው ተፈጥሯል ነበር ያለው፡፡

**የማቴዎስ ወንጌል 12 ፡ 1-14**
**የሉቃስ ወንጌል 6 ፡ 1-6**
**የማርቆስ ወንጌል 2 ፡ 27-28**

ደግሞ። <u>**ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም**</u>፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው አላቸው።

እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነጻ ወጥቶ ወደ ከንዓን በመጓዝ የተስፋውን ምድር በመውረስ ያገኘውን ደስታና ባለ ርስት መሆናቸውን እግዚአብሔር ወደ እረፍቴ

መግባት ብሎ ጠርቶታል፡፡ አብዛኞቹ ካለማመናቸው ጠንቅ የተነሳ ይህንን የእግዚአብሔርን እረፍት ሳያዩት በምድረ በዳ ወድቀው ቀርተዋል፡፡

**መዝሙረ ዳዊት** 95 ፡ 10-11

ያችን ትውልድ አርባ ዓመት ተቈጥቻት ነበር። ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል፥ እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልሁ። ወደ ዕረፍቴም እንዳይገቡ በቍጣዬ ማልሁ።

**ወደ ዕብራውያን** 3 ፡ 10-11

ስለዚህ ያን ትውልድ ተቆጥቼ። ዘወትር በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ፤ እንዲሁ። ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቍጣዬ ማልሁ።

**ኦሪት ዘኍልቁ** 32 ፡ 10-12

በዚያም ቀን የእግዚአብሔር ቍጣ ነደደ፥ እርሱም፦ በእውነት እግዚአብሔርን ፈጽመው ከተከተሉ ከእነዚህ ከቄኔዛዊው ከዮፎኔ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር፥ ከግብፅ የወጡት ከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያሉት ሰዎች እኔን ፈጽመው አልተከተሉምና ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እሰጥ ዘንድ የማልሁበትን ምድር አያዩም ብሎ ማለ።

ይህም እረፍት ቅዱሳን ለዘለአለም በገነት ከእግዚአብሔር ጋር በደስታ ለሚኖሩት ኑሮ ምሳሌ በመሆን በዛ የሚኖሩትን ኑሮ በምድር ላይ የመለማመድ የሕይወት መንገድ ሆኖም ኖሯል፡፡ ውድ አንባቢ፤ ለዚህ የዘላለም እረፍት፣ ለዘላለም ደስታ ተጋብዘዋል፤ እድሉም አለዎት፡፡ ወደዚህ እረፍት የሚወስደው መንገድም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከፍቷል፡፡ ኀጢአተኛ እንደሆነ ያወቀ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ የኀጢአቱን ዋጋ እንደከፈለለት ያመነና የተቀበለ፣ ከእርሱም ጋር በመታዘዝ ለመኖር የወሰነ ሰው፣ ወደዚህ የዘላለም ደስታ ይገባል፡፡ ለዚህ ጥሪ ምላሽ መስጠት የእርስዎ ድርሻ ነው፡፡ እሺ ብለው ቢታዘዙ ወደ እረፍቱ ይገባሉ፡፡

**የዮሐንስ ራዕይ** 21 ፡ 1-4

አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፣

ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።

## 3.2. ኦሪት ዘፍጥረት 37 ፡ 5-10

ዮሴፍም ሕልምን አለመ፥ ለወንድሞቹም ነገራቸው እነርሱም እንደ ገና በብዙ ጠሉት። እርሱም አላቸው። እኔ ያለምሁትን ሕልም ስሙ እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበርና፥ እነሆም፥ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች የእናንተም ነዶች በዙሪያ ከብበው እነሆ ለእኔ ነዶ ሰገዱ። ወንድሞቹም በእኛ ላይ ልትነግሥብን ይሆን? ወይስ ልትገዛ ይሆን? አሉት። እንደ ገናም ስለ ሕልሙና ስለ ነገሩ ይልቁን ጠሉት። ደግሞም ሌላ ሕልምን አለመ፥ ለወንድሞቹም ነገራቸው፥እንዲህም አለ፦ እነሆ ደግሞ ሌላ ሕልምን አለምሁ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ። ለአባቱና ለወንድሞቹም ነገራቸው አባቱም **ገሠጸው**፥ እንዲህም አለው፦ ይህ ያለምኸው ሕልም ምንድር ነው? በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?

የሃይማኖት ንጽጽር ሊቆች ነን ባዮቹ ዮሴፍ ሕልሙን በተናገረ ጊዜ አባቱ ተመቅኝቷል ወይንስ ተደስቷል? የሚል ጥያቄ በመጠየቅ መጽሐፍ ቅዱስ ነቢዩ ያዕቆብን እንደ ምቀኛ አይቆታል፤ እርሱ ግን ነቢይ ስለሆነ እንዲህ አያደርግም፡፡ ይህ አሳብ በቁርአን በሱረቱል ዩሱፍ (የዮሴፍ ምዕራፍ) 12 ፡ 1-5 ከተገለጸው ጋር ስለማይስማማ የአላህ ቃል ነው ብሎ መቀበል አይቻልም ይላሉ፡፡

ውድ አንባቢ፤ የተጠቀሰውን የቁርአን ክፍል ላስነብበዎት፤ ከዛም ከመጽሐፍ ቅዱሱ ክፍል ጋር ያነጻጸረው እነዚህ ወገኖች የሰጡትን የመደምደሚያ አሳብ ይገምግሙ፡፡

### ሱረቱል ዩሱፍ (የዮሴፍ ምዕራፍ) 12 ፡ 2-5

እኛ (ፍቹን) ታውቁ ዘንድ ዐረብኛ ቁርኣን ሲሆን፣ በእርግጥ አወረድነው፡፡ እኛ ይህንን ቁርኣን ወደ አንተ በማውረዳችን በጣም መልካም ዜናዎችን በአንተ ላይ እንተርክልሃለን፡፡ እነሆ ከእርሱ በፊት (ካለፉት ሕዝቦች ታሪክ) በእርግጥ ከዘንጊዎቹ ነበርክ፡፡ ዩሱፍ ለአባቱ፡- «አባቴ ሆይ! እኔ ዐስራ አንድ ከዋክብትን ፀሐይንና ጨረቃንም (በሕልሜ) አየሁ፡፡ ለእኔ ሰጋጆች ሆነው አየኋቸው» ባለ ጊዜ

(አስታውስ)፡፡(አባቱም) አለ **«ልጄ ሆይ! ሕልምህን ለወንድሞችህ አታውራ፡፡ ላንተ ተንኮልን ይሰሩብሃልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና፡፡»**

- ምን ላይ ደረሱ? እውን መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ያዕቆብ ልጁን ተመቅኝቷል ሊያሰኝ የሚችል አንዳች ፍንጭ አገኙ ይሆን?
- ይህ የቁርአን ክፍል ከሌሎች የቁርአን ክፍሎች ጋር እንደሚጋጭና መሠረታዊ ችግር እንዳለበት ማስተዋል ቻላችሁ ይሆን?

ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ ከመቁጠርና ወንዝን ወደ ተራራ ለማፍሰስ ከመሞከር ይልቅ በበርካታ ችግሮች ለተጣበበው ቁርአን ደጋፊ አድርገው ማቅረብ ችለው ቢሆን አስተዋዮች ባሰኛቸው ነበር፡፡ ደግሞም ታማኞችና እውነተኞች ቢሆኑ ኖሮ ትችታቸውን የአንቀጹን መጨረሻ አስራ አንደኛውን ቁጥር በማካተት ማቅረብ በቻሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የአንቀጹ መቋጫ ያነሱትን ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ስለሚቋጭባቸው ያንን ማድረግ አልፈለጉም፡፡ አደረጉት አላደረጉት ጥያቄያቸው ያኔውኑ እንደተመለሰላቸው እርግጠኛ ነኝ፡፡ ቁጥር አስራ አንድ እንዲህ ይላል፡-

"ወንድሞቹም ቀኑበት **አባቱ ግን ነገሩን ይጠብቀው ነበር።"**

ምንአልባት ይህን ሁሉ እንዲሉ ያስቻላቸው ቁጥር 10 ላይ '**ገሰጸው**'፣ የሚለው ቃል ይሆን? እስልምና የነቢያትን ባህርይ በተመለከተ ከሚያራምደው አመለካከት ጋር ተጋጭቶባቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ገድለ ነቢያት የተሰኘው መጽሐፍ በ14ኛው ገጹ ላይ ስለ ነቢያት ባህርይ በእስልምና ያለውን አስተሳሰብ እንዲህ አስፍሮት ይገኛል፡-

> "በእስልምና አመለካከት ነቢያት ብጹአን (መእሱም) ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አነስተኛ ስህተት ሊፈታተናቸው ይችላሉ፡፡ **ሆኖም ከልባዊ እምነት (አቂዳ) እና ከሞራል ሕግጋት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሊኖራቸው የማይችል ስህተቶች** ናቸው፡፡ እንደ መጥፎ ተግባር የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡"

ጎላ ብሎ በተሰመረበት አሳብ የነቢዩ ሙሐመድን ሕይወት ብንፈትሽ ማንነታቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳየን ነበር፡፡ አሁን ጊዜው አይደለምና እዘለዋለሁ፡፡ እናም እስልምና የነቢያትን ስብዕና ከሚያይበት እይታ ተነስቶ መጽሐፍ ቅዱስን መተቸት የሚያስችል መርህ ፈጽሞ የለም፤ ለዚህ በርካታ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከነዛ አንዱ ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ይህንን አመለካከታቸውን በሚቃረኑ መልእክቶች የተጣበቡ መሆናቸው ነው፡፡

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2459**

ማንም የሚከተሉት አራት ባሕርያት ያሉት ሰው መናፍቅ ነው፡፡ ደግሞም ማንም ከአራቱ ባህርይዎች አንዱ ያለው እስካላቆመ አንድ የመናፍቅ ባህርይ ያለው ይባላል፡-

- ምንጊዜም ሲያወራ ይዋሻል
- ምንጊዜም ቃል ከገባ በኋላ ያፈርሳል
- ምንጊዜም የገባውን ቃል ኪዳን ይክዳል
- ምንጊዜም ሲጋጭ ምላሹ አስተዋይነት በጎደለው በጭካኔ በስድብና በዘለፋ ተሞልቶ ነው፡፡ አብዱላህ ቢን አምር የተናገረው[194]

ውድ አንባቢ፣ ስለ ነቢያት የተባለው ኢስላማዊ አመለካከት ከነቢዩ ሙሐመድ ሐዲስ ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? ወይስ ሐዲሱ ነቢያትን አይመለከትም? ከሆነ ከአላህ ፍትሕ ጋር እንዴት ሊስማማ ይችላል? ምሳሌዎችን እያነሳን እስኪ እንገምግም፡-

❖ በቁርአንና በሐዲሱ ተጠቅሶ እንደሚገኘው አብርሐም ነቢይ ሆኖ እያለ በተለያዩ ጊዜያት ሦስት ጊዜ ዋሽቷል፣ ታዲያ ምን ብለን እንጥራው? አንድ የመናፍቃን ባህርይ ያለበት የአላህ ነቢይ እንበለውን? ነቢያት ፍጹም ናቸው ከተባለ ይህ እንከን እንዴት ሊገኝበት ቻለ?

ሱረቱል አል-አንቢያ 21 ፡ 51-63
ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 7፣ ቁጥር 5084

የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ አብርሐም ሶስት ጊዜ ከመዋሸቱ ውጭ ሌላ ውሸት አልተናገረም፡፡ አቡ ሁሬይራ የተናገሩት[195]

❖ ስንት ዓመታት ንስሃ እንደገቡ ባይታወቅም ነቢዩ ሙሐመድ በቀን ሰባ ጊዜ ያህል ንስሃ ይገቡ እንደነበር በሐዲሳቸው ተዘግቧል፡፡ ታዲያ ምን እንበላቸው? ስለነቢያት ከተባለው አመለካከት ጋር እንዴት ይታረቅ?

**ሱረቱል አል-ሙእሚን (የምእምናን ምዕራፍ) 40 ፡ 55**

(ሙሐመድ ሆይ!) ታገስም የአላህ ተስፋ እውነት ነውና፡፡ ለስህተትህም ምሕረትን ለምን፡፡ ከቀትር በኋላም በማለዳም ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው፡፡

**ሱረቱል አል-ኒሳዕ 4 ፡ 79**

---

[194] *Sahih al-Bukhari vol 3, 369*
[195] *Sahih al-Bukhari vol 7, page 29*

ከደግ ነገር የሚያገኝህ ከአላህ (ችሮታ) ነው፡፡ ከመከራም የሚደርስብህ ከራስህ (ጥፋት የተነሳ) ነው፡፡ ለሰዎችም ሁሉ መልክተኛ ኾነህ ላክንህ፡፡ መስካሪም በአላህ በቃ፡፡

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 8፣ ቁጥር 6307**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፤ በአላህ! እኔ አላህን በቀን ከሰባ ጊዜ በላይ ይቅርታን በመለመንና በንስሃ ወደ እርሱ ለመመለስ እጠይቀዋለሁ፡፡ አቡ ሁረይራ የተናገሩት[196]

- እንግዲህ እንደሚባለው ነቢዩ ሙሐመድ የደረሰባቸው መከራ ቁጥሩ ብዙ ነው፡፡ ሁሉም መከራ የደረሰባቸው ከጥፋታቸው የተነሳ ከሆነ ስለነቢያት ባህርይ ከተባለው ጋር እንዴት አብሮ ሊሄድ ይችላል? ለሚፈጽሙት ሰህተት በየቀኑ ይህንን ያክል ጊዜ ንስሃ ይገባሉ፤ በመጀመሪያው ልመና ብቻ ምህረትን የማይሰጣቸው ምን አይነት አምላክ ቢሆን ነው? እርሳቸውስ ከኀጢአት ያልተለየ ኑሮ የሚኖሩት ለምንድን ነው?
- ይህንን ያክል ጊዜ ደጋግመው መለመናቸው ምህረት እንደሚደረግላቸው ማመን ስለተሳናቸው ይሆን? ለዚህ ይሆናል ከሞት በኋላ አላህ በርሳቸው ላይ ምን እንደሚያደርግ ማወቅ የተሳናቸው፡፡

የሃይማኖቱ ምሑራን በአስተምህሯቸው ዙሪያ ከሚነሱ ጥያቄዎች ለማምለጥ ሲሉ፣ ነቢያት የሚሠሯቸው ኃጢአቶች ቢኖሩም እንደ ኃጢያት ሊቆጠሩ አይገባም፤ ምክንያቱም "ለአላህ ጥቅም" ብለው የሚያደርጉት ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ እንደ ምሳሌ የሚያነሱት አብርሐምን ነው፡-

> "በዚህ ላይ ኢብን ጅሪር ከአቡ ሁሬይራ የሰማውን ሐዲስ ሲናግር፡- የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- 'ኢብራሒም ከሦስት ሁኔታዎች በስተቀር አልዋሸም፡፡ ሁለቱ ስለ አላህ ሲል ነው፡- አንደኛው 'በእውነት አሞኛል' ባለ ጊዜ፤ ሁለተኛው ደግሞ 'አይደለም ይህ ታላቃቸው ሠራው' ባለ ጊዜ ሦስተኛውም ስለ ሚስቱ ስለ ሣራ 'እርሷ እህቴ ናት' ባለ ጊዜ ነበር፡፡' ይህ ሐዲስ ሳሂህ በሆኑትና በሱናዎቹ በተለያዩ ሰንሰለቶች ተነግሮ ተመዝግቧል፡፡ ነገር ግን ሰዎችን የሚኮነኑበት ዓይነት እውነተኛ ውሸት አይደለም፡፡ አንድም ሰው ይህንን የተሻለ ቃል እጥረት የተነሳ ውሸት ብሎ እንዳይጠራው አላህ ከልክሏል፤ ምክንያቱም ይህ ተገቢ የሆነ ሃይማኖታዊ አላማ የተነገረ ጥልቅ ንግግር ነው፡፡"[197]

ከዚህ አባባላቸውም የተወሰኑ ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልገኛል፡-

---

[196] *Sahih al-Bukhari vol 8, page 180*

[197] *Tafsir Ibn Kathir vol 8 page 267*

- ውሸት ውሸት ነው፤ ምን ዓይነት አምላክ ቢሆን ነው ሰዎች ሲዋሹለት ለእኔ ብለው ስለሆነ ችግር የለውም የሚለው? የራሱ ስልጣን፣ ችሎታው ባለመብትነቱ የት ሄደና በሰው ውሸት ይረዳ ጀመር? ማንን ፈርቶ ይሆን ይህ ያስፈለገው? ከ99 ስሞቹ የቱንስ ይወክላል? እንዲህ የሚያደርግ ከሆነ ሐሰት ተናጋሪዎችን ለምን ይነቅፋል? ለምንስ እንደ ኃጢአተኛ ይኮንናል? በቀድሩ ሐሰት እንዲናገሩ የተወሰነባቸው ሰዎች ለምን እንደ መናፍቅ ይቆጠራሉ?
- አላህ በምድር ላይ በሰዎች ውሸት ፈቃዱን ያስፈጽማል የሚል እምነት የለኝም፤ እንደ ሱረቱል አል-ነጂም 53 ፡ 18-19 እና ሱረቱል አል-ሐጅ 22 ፡ 52 ነቢዩ ሙሐመድ መካ ሳሉ ከፍርሃት የተነሳ ጣኦታት ከአላህ እንደሚያማልዱ ተናግረው[198] ከጣኦት አምላኪዎቹ ጋር አብረው ሰግደው ነበር፡፡ ይህን በመሰለ ሁኔታ ተውሂዱን የጣሱትና በጣኦት ምልጃ ምስክርነት ስግደታቸውን ያሳረጉት ለአላህ ጥቅም ብለው ነበር ማለት ነው?
- እንደ ነቢዩ ሙሐመድ አባባል ውሸት መናገር መናፍቃንን በባህርይ መምሰል ከሆነ ነቢያት ይህንን የመናፍቃኑን ባህርይ ሲጋሩ ሰዎች ነቢይነታቸውን አምነው ሊቀበሉ እንዴት ይችላሉ? ሰዎች እንዲገዙለት በነቢያቱ ውሸት መጠቀምን እንዴት ፈለገው? አላህ ይህንን በማድረግ ሌሎቹን ከራሱ አንደበት የወጡትን ሕጎች የሚቃረን አምላክ ይመስለዎታል? ይህስ የአላህን ፍትሐዊነት ያሳያል ብለው ያስባሉ?
- አላህ እንዲህ ዓይነቱን የነቢያቱን ክፉ አመል ሳይቀጣ አሜን ብሎ ከተቀበለው፣ ሌሎቹን ኃጢአተኞች ለመቅጣት የሚያስችል ፍትሃዊነት ለሰዎች ሁሉ ማሳየት ይችላል ብለው ያምናሉ? መልስዎ አይችልም ከሆነ፣ የእነዚህ ወገኖች ስለ ነቢያት የያዙት አመለካከትም ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ በያዛቸው የነቢያት ታሪክ ላይ ያነሱት ጥያቄ እንዴት ትክክል ሊሆን ይችላል?

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዴ ነቢዩ ሙሐመድ ለአስር ሰላት ቆመው ሰላውን ሲመሩ ከታወቀውና በፊት ሕዝቡን ካስተማሩት ውጭ አሰገዱ፤ ሕዝቡም ጥያቄ አነሳ፡፡ በዛን ጊዜ ነቢያት እንከን የለሽ፣ ምንም ቢያደርጉ አላህ የማይነቅፋቸው ልዩ ፍጥረቶች አለመሆናቸውን የሚያሳይና የእነዚህን ወገኖች አመለካከት ውድቅ የሚያደርግ ንግግር ተናግረዋል፡፡

**ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 2፣ ቁጥር 1274**

---

[198] *Al-Imam Jalal-ud-din Al-Mahaly and Al-Imam Jalal-ud-din As-suyuti, tafsir Al-Jalalayn, translated by Muhammad Anis Gad Khalil, Dar Al-Manarah, Egypt 2010 vol 2, page 974-975*

……. ነገር ግን እኔ ሰው ነኝ፤ እናንተ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ፡፡ ስለዚህ በረሳሁ ጊዜ እናንተ አስታውሱኝ፡፡[199]

እንግዲህ ነቢዩ ስለ ራሳቸው ይህንን እያሉ፣ ነቢያትን እንደ ልዩ ፍጥረት መመልከትና እምነትን በዚያ ላይ መመስረት ስህተት አይመስልዎትም? በተጨማሪም በሌላ ሐዲስ ነቢዩ ሙሐመድ አንድን ኃጢአት የሠራ ሰው በሠራበት በዛ ሰዓት ከእስልምና ተመልሷል በማለት የተናገሩትን መዘንጋት አይገባም፡፡

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2475**[200]

እንግዲህ እንደዚህ የአል-ቡኻሪ ዘገባ ነቢዩ ሙሐመድ ከፈጸሟቸው ኃጢአቶች የተነሳ ብዙ ጊዜ ከእስልምና አፈግፍገው ነበር፤ ማለት ነው፡፡ ይገርማል!!

ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚቆጥሩት ወገኖች ከኦሪት ዘፍጥረት 37 ፡ 5-10 ውስጥ ከሰፈረው የያዕቆብ ንግግር የትኛው ይሆን ምቀኝነት የመሰላቸው? አልገባኝም፡፡ ሆኖም የሚሉትን ባህርይ መለየት የሚችሉ ከሆነ አንድም መለኮታዊ ትዕዛዝ ሳይወርድላቸው ከራሳቸው ጥቅምና ክብር በመነሳት ሥርአት ከሚደነግጉት ከነቢዩ ሙሐመድ ሕይወት ውስጥ ያገኙታል፡፡ ለዚህ አንድ ምሳሌ ማንሳት እችላለሁ፡፡ አንዴ ነቢዩ የወርቅ ቀለበት አድርገው ለሕዝቡ ታዩ፤ ሱናቸውን ስለመከተል ፋይዳ ተናግረውና የቁርአንም አንቀጽ ወርዶ ስለነበር ሕዝቡ እንደ እርሳቸው የወርቅ ቀለበት አሠርተው አደረጉ፡፡ ሕዝቡ እንደርሳቸው የወርቅ ቀለበት እንዳደረጉ ሲመለከቱ፡ ወረደልኝ ያሉትን የቁርአን አንቀጽና ያስተማሩትን እረስተው አሳማኝ ያልሆነና የአላህን ፍትሐዊ አምላክነት የሚያደበዝዝ ምክንያት በመስጠት እንዳይደረግ ከለከሉ፡፡[201] እንግዲህ ስለምቀኝነት ማውራት ካስፈለገ ይህ ባሕሪ በጉልህ የሚታየው እንዲህ አይነት የክልከላ ትዕዛዝ ከሚሰጥ ነቢይ ሕይወት ውስጥ ነው፡፡ ለክልከላቸው የሰጡት ምክንያት ምን እንደሆን ታውቁ ይሆን? በዚህ ዓለም ወርቅ የሚያደርግ ሰው በሚመጣው ዓለም ወርቅ አያደርግም የሚል ነው፡፡ ጨምረውም ወርቅ፣ ብር፣ ነሃስና ሐር በዚህ ዓለም ላሉ ከሃዲዎች እንጂ ለሙስሊም አይደለም በማለት ተናግረዋል፡፡ አይ ማስተዋል ማጣት፡-

- ታዲያ ሴቶቻቸው ወርቅንና ሌላውንም እንዲያደርጉ መፍቀዱ እነርሱ ሙስሊሞች ስላልሆኑ ይሆን? ወይንስ አብዛኞቹ ሴቶቻቸው ገሃነም እሳት ገቢዎች ስለሆኑ?[202]

---

[199] *Sahih Muslim vol 2, page 65*

[200] *Sahih al-Bukhari vol 3, page 380*

[201] *Sahih Al-Bukhari vol 7, #5866 and 5876, page 409-410 and 414*

[202] *Sahih al-Bukhari vol 7, #5197, page 92*

- ለወንድ ሙስሊሞች በጀነት የተዘጋጁት ሴቶች አዲስ ፍጡራን እንጂ፣ በዚህ ምድር ላይ የኖሩት እንዳልሆኑ ምን ያህል ያውቃሉ? ውድ አንባቢ፤ ሴት ከሆኑ እርስዎ፣ እናትዎት፣ እህትዎት፣ ሴት ልጅዎት፣ የት እንደሚሆኑ እያስተዋሉ ይሆን? አላህስ ምን ያክል ኢፍትሐዊ አምላክ እንደተደረገስ እያዩ ነው?
- ወርቅ፣ ብርና ነሃስ እንዲሁም ሐር በዚህ ዓለም ለማያምኑት ከሆነ እርሳቸውና ሙስሊም ወንዶች ሁሉ የብር ቀለበት ማድረጋቸውስ ለምን ይሆን?[203]

የእስልምና ነቢይ የተለየ ፍጥረት እንደሆነ ቢያስተምርም ከላይ ሐዲሳቱና በቁርአን የታየው ግን ልዩ ፍጥረቶች አለመሆናቸው ነው፡፡ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 3፣ ቁጥር 2458[204] "እኔ ሰው ብቻ ነኝ፤ የምፈርደው ስትከራከሩ በምሰማውና እንደ ምስክራችሁ ቃል ነው፡፡" ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ የመጡላቸውን ጉዳዮች እንደ ሰው ፍትሕ መስጠታቸውና "እኔ ሰው ብቻ ነኝ" ማለታቸው ተቀባይነት አግኝቷል፤ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ያዕቆብ ነገሮቹን ሰው ነውና እንደ ሰው ማሰቡንና ማገናዘቡን በማሳየቱ ትክክለኛ አይደለህም ሊባል ይገባ ነበር? የመሞገቻው ነጥብም የእግዚአብሔር ቃልነቱን ጥርጣሬ ውስጥ ሊያስገባው ብቃት የለውም፤ ይልቁንም ታሪኩ የመጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃልነት ያጎላል፤ እንዲሁም ደግሞ ክርስቲያን ለአምላኩ ፍጹም ፍቅር እንዲኖረው፣ ልቡን ቢያመቻችለት እንጅ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠርበት አያደርግም፡፡

የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ አንድን ነቢይ ነቢይ የሚያሰኘው፣ ከአላህ መልእክትን ተቀብሎ ወደ ሰዎች የማድረስ ተልዕኮው እንጂ፣ ከሰዎች የተለየ ፍጡር ስለሆነ አይደለም፤ ይለናል፡፡ እስልምና ልዩ ፍጥረታት እንደሆኑ የሚያስበው ነቢዩ ሙሐመድ ልዩ እንደሆኑ እንዲታሰብላቸው ፈልገው ስለተናገሩ ብቻ ነው፡፡ ይህ በሌላ ክፍል የምናየው ይሆናል፡፡ ነቢይ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሰው የማያስብ፣ እንደ ሰው የማይሰማው፣ እንደ ሰው የማይሳሳት ፍጡር አይደለም፡፡ በዮሴፍና በአባቱ በያዕቆብ ታሪክም የታየው ይኸው ነው፡፡ "ያዕቆብ ነቢይ ነበር" ከተባለ የልጁን ፍጻሜ ካቀደው ከእግዚአብሔር ካልሰማ በስተቀር ሊያውቅ የሚችልበት ምንም መንገድ ሊኖረው አይችልም፡፡ ወደፊት የዮሴፍ ፍጻሜ ምን እንደሚመስል እግዚአብሔር የተናገረው ለያዕቆብ ሳይሆን፣ ለራሱ ለዮሴፍ ነበር፡፡ ያዕቆብ ሲሰማ የሕልሙ ፍች ቢገባውም ከዘለአለም አምላክ ዘንድ የመጣ ለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ ስላልነበረው እንደ ቅዠት ቢመለከተው ሰው ነውና አልተሳሳተም፡፡ እንዲህ እንዲያስብ የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች ዙሪያውን ከበውት እንደነበር ማስተዋል አይሳንም፡-

---

[203] *Sahih al-Bukhari vol7, #5891, page 395*
[204] *Sahih al-Bukhari vol 3, page 368*

- በጊዜው እርሱና ቤተሰቡ የነበሩበት የአኗኗር ሁኔታ፤- ያዕቆብና ልጆቹ ምንም እግዚአብሔር እየኖሩበት ያለውን ምድር እንደሚያወርሳቸው ቃል ቢገባላቸውም፣ በሕጋዊነት የራሳቸው የሚሆንበት ጊዜ ገና ነበር፡፡ ስለዚህ በሰው አገር፣ በሌላ ሕዝብ ላይ ምጻተኛ ሆኖ ንግሥና ማሰብ ያውም ገና ወጣት ልጅ የማይታሰብ መሆኑ፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት 15 ፡ 12-16
- ያለው የቤተሰብ ቁጥር ማነስ፡- እንደ መንግሥት ተቋቁሞ ንግሥናው ቢታወጅ ራሱን ለመከላከል የሚችልበት የሕዝብ ብዛት ላይ ያልደረሰና ያልተደራጀ መሆኑ፡፡ ደግሞስ በማን ምድር ላይ? የማይቻል ከመሆኑ የተነሳ እንዲህ ቢያስብ አልተሳሳተም፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ ወደ ግብጽ ሲሄድ እንኳን ቁጥራቸው ገና ሰባ ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን እንዲህ መዘገቡ የእውነተኛነቱ መግለጫ ነው፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት 30 ፡ 30
- ከወጣበት ማሕበረሰብ ባሕል አንጻር ሲመለከተው፡- ባህሉ ቅድሚያ ኃላፊነትን የሚሰጠው ለመጨረሻ ሁለተኛ ልጅ ሳይሆን፣ ለበኩር ልጅ ነው፡፡ ስለሆነ ትንሹ ዮሴፍ ዙፋን ላይ ተቀምጦ የማስተዳደሩን ኃላፊነት የሚያገኝበት ምንም አይነት መንገድ አልነበረም፡፡ ራሱ ያዕቆብ በረከትን ከአባቱ ለመቀበል በፈለገ ጊዜ የጀመረው ብኩርናን ከወንድሙ ላይ በምስር ወጥ በመግዛት ነበር፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት 25፡ 29-34
- ራሱ ያለበትን ሁኔታ ሲመለከት፡- አባቱ ያዕቆብ የደረሰበትን የእድሜ ከፍታ ሲመለከት ዮሴፍ አድጎ ለንግሥና የሚያስፈልገውን እውቀትና ብስለት እስኪያገኝ፣ እንደተስፋው ቃል ርስት ወርሰው እስኪደላደሉና ዮሴፍ እስከሚነግሥ ለንጉሡም እስከሚሰግድ በሕይወት መቆየቱን ሳይጠራጠር አልቀረም፡፡

ከእነዚህ ጥቂት ምክንያቶች ተነስቶ ያዕቆብ ዮሴፍን ቢገስጸው ትክክለኛነቱን እንጂ ምቀኝነት የተባለውን አያመላክትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በመሰለ ሁኔታ ታሪኩን ማቅረቡ ለመጠርጠር አያበቃውም፡፡ ሆኖም ያዕቆብ መንፈሳዊ ሰው በመሆኑ ሕልሙን ሰምቶ እንደ ወንድሞቹ አልቀለደበትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በቁጥር 11 ላይ <u>"በልቡ ይጠብቀው ነበር"</u> ይለናል፡፡ ምቀኝነት የሚባል ነገር የለም፡፡

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር በየዘመናቱ ለሥራው የተጠቀመባቸው ሰዎች ከእኛ ያልተለዩ ነበሩ፡፡ በመሆናቸውም በዚህ ፍፁማን ያልሆነው እኛ ክርስቲያኖች ፍጹም ካልሆነው ሕይወታቸው ተምረን እርሱን እንድናመልክ፣ የሰጠንንም ተስፋ በጽናት በመጠበቅ በታማኝነት ለማገልገል ልባችንን እንድናዘጋጅ ያስተምረናል፤ ተስፋ አለን ብለን እንድናስብ ያደርገናል፤ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ፍፁም ማረጋገጫ ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን ጋር በአሳብም ሆነ በመልእክት አለመስማማቱ በማለት ያነሱት መሞገቻ ከዚህ በፊት እንዳልኩት እኔም እጋራቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም የሁለቱም ተጠሪ፣ የሁለቱም ባለቤቶች የተለያዩ ሁለት አካላት ናቸውና፡፡

## 3.3. ኦሪት ዘፀአት 33 ፡ 17-23

> እግዚአብሔርም ሙሴን፦ በፊቴ ሞገስ ስላገኘህ በስምህም ስላወቅሁህ ይህን ያልኸውን ነገር አደርጋለሁ አለው። እርሱም፦ እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለ። እግዚአብሔርም፦ እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፣ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም፦ <u>ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ</u>። እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፥ <u>በዓለቱም ላይ ትቆማለህ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዓለት አኖርሃለሁ፥ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ፣ ፊቴ ግን አይታይም።</u>

የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ ራሳቸውን የሚቆጥሩት ወገኖች ይህ የመጽሐፍ ክፍል **በሱረቱል አል-አዕራፍ 7 ፡ 143** ካለው የቁርአን አሳብ ጋር ስለማይስማማ የአላህ ቃል ነው ብሎ መቀበል አይቻልም፡፡ ደግሞስ ሙሴ የአላህን ጀርባ አይቷል ወይስ አላየም? ብለው ከጥያቄ ጋር አሳባቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

አለማወቅ ኃጢአት አይደለም፤ በትክክል እንኳን ሳያነቡ እንደ አዋቂ ብዙ ማውራት መልካም አይደለም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱ ክፍል የሚናገረው ስለምንድን ነው? የሚለውን እናቆየውና 'ሙሴ አላህን አይቷል' እንኳን ቢል እንደ ስህተት ማየት ይሻላል ወይስ እንደማረጋገጫ? ማስተዋላቸውን ምን ወሰደው ይሆን? ለማንኛውም አላህን ማንም አያየውም ከሆነ ሙግታቸው ቁርአን እርስ በእርሱ እንደሚጋጭ እየነገሩን ስለሆነ እናመሰግናለን፡፡ ለማንኛውም አላህ መታየት ይችላል ወደ ሚለው የቁርአን ቃልና የነቢዩ ሐዲሳት ልውሰዳችሁ፡-

> ሱረቱል አል-ነጅም 53 ፡ 11
>
> (ነቢዩም በዓይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም፡፡
>
> مَا كَذَبَ الْفُؤَادُ مَا رَأَىٰ

ይህንን የቁርአን አንቀጽ ያብራሩ ምሁራን እንዲህ ብለዋል፡-

ኢብን አባስ፡- "(ልቡ) ማለት የሙሐመድ (ያየውን አልዋሸም) ማለት ጌታውን በልቡ ባየው ጊዜ፤ በተጨማሪም ጌታውን በዓይኖቹ ባየው ጊዜ ምለት ነው፡፡"[205]

[205] Tafsir Ibn Abbas page 621

ኢብን ካሲርም፡- "ሙስሊም ከኢብን አባስ ስለ ሱረቱል አል-ነጅም 53 ፡ 11-13 ያስተላለፈውን ሐዲስ መዝግቧል፡- 'ሙሐመድ አላህን በልቡ ሁለት ጊዜ አይቶታል፡፡'[206] ሲማክም ከኢክሪማህ፣ ከኢብን አባስ የተላለፈውን ተመሳሳይ ሐዲስ አስተላልፏል፡፡ አቡ ሳሊህ፣ አስ-ሱዲና ሌሎች ብዙዎች በተመሳሳይ 'ነቢዩ ሙሐመድ አላህን በልቡ ሁለት ጊዜ አይቶታል' ብለው ተናግረዋል፡፡"[207]

ውድ አንባቢ፡- ነቢዩ ሙሐመድን የመሰለ ሰው አላህን በልቡ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም ካየ፤ በዓይኖቹም ማየት ከቻለ ሙሴን የመሰለ የተመሰከረለት ጻድቅ ሰው ዓየ ቢባል ምንድን ነው ስህተቱ? ወይስ ቁርአንና ሐዲሳቱ እንዲህ መዘገባቸውን ራሳቸውን ያገዘፉት ተሟጋቾች አላነበቧቸውም? ምናልባት አንዳንዶች እንደሚሉት ያዩት ገብርኤልን ነው ይሉ ይሆናል፤ ገብርኤልን አይደለም ነቢዩ ሙሐመድ አብረዋቸው የነበሩ ተከታዮቻቸው፣ ሚስታቸው ኡሙ ሰላማ ሳይቀሩ አይተውታል፡፡ ስለዚህ ገብረኤልን ማየት ብርቅ አይደለም፡፡ አላህን በምን ሁኔታ እንዳዩት ራሳቸው የተናገሩትን ኢብን ካሲር ይዘውታል፡- "ሙስሊም አቡ ዛር እንዲህ ማለቱን ዘግቧል፡- "የአላህን መልዕክተኛ እንዲህ ስል ጠየኳቸው፡- 'አላህን አይተውታለን?' እርሳቸውም፡- 'ብርሃን ነው እንዴት ላየው እችላለሁ?'"[208] በሌላ ዘገባ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- 'ብርሃን ብቻ አይቻለሁ፡፡'"[209]

ራሳቸውም ነቢዩ የአላህ ብረሃን ሆነው ከፍጥረታት በፊት ከአላህ ጋር አብረው እንደ ነበሩና አላህን ያዩት ያኔ እንደሆነ የሚናገሩ ወገኖችም አሉ፡፡[210] ከነቢዩ ሙሐመድ 99 ወይም 201 ስሞች መካከል አንዱ አል-ኑር የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ ማስተዋል እንደማይከብዳችሁ በማሰብ አሁን አልፈውና ዝርዝሩን "እስልምና መቸ ተጀመረ?" በሚለው ሥራዬ እመለስበታለሁ፡፡ አሁን ወደ አንድ የነቢዩ ሙሐመድ የጉብኝት ሥፍራ ልውሰዳችሁ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁጥር 349 ገጽ 237**

የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ፤ በመካ ሳለሁ የቤቴ ጣራ ተከፈተና ገብርኤል ወረደ፤ ደረቴንም ከፍቶ በዘምዘም ውሃ አጠበው፡፡ ከዚያም ጥበብንና እምነትን የተሞላ ወርቃማ ሰሃን አምጥቶ የያዘውን ነገር

---

206 *Sahih Muslim vol 1, #437-438 page 281*

207 *Tafsir Ibn Kathir vol 9, page 312-313*

208 *Sahih Muslim vol 1, #443-444, page 285*

209 *Tafsir Ibn Kathir vlo9, page 113*

210 *Sahl b. ʿAbd Allāh al-Tustarī, Tafsīr al-Tustarī, translated by Annabel Keeler and Ali Keeler, Royal Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought Amman, Jordan 2011, page 212; Allamah Muhammad Baqir Al-Majlisi, Hayat Al-Qulub, Translator Sayyid Athar Husayn S. H. Rizvi, Ansariyan Publications – Qum, India 2010, vlo 2, page 4-6*

በደረቴ አፍስሶ ዘጋው፡፡ ከዚያም በኋላ እጄን ይዞኝ ቅርብ ወደሆነው ገነት አረገን፡፡ እዚያ እንደደረስኩም ገብርኤል በር ጠባቂውን በሩን ክፈት አለው፤ ዘበኛውም ማን ነው? አለ፤ ግብርኤልም እኔ ነኝ አለ፡፡ ዘበኛው ካንተ ጋር ሌላ ሰው አለን? ሲል ጠየቀ፤ ገብርኤልም አዎን ሙሐመድ ከእኔ ጋር ነው አለው፡፡ ዘበኛውም ተጠርቷልን? ሲል ጠየቀ፤ ገብርኤልም አዎን አለው፡፡ በሩም ተከፈተና ቅርብ ወደሆነው ገነት ገባን፡፡ በዛም የተቀመጠ አንድ ሰው ሌሎች ሰዎችም በግራውና በቀኙ አብረው የተቀምጠው አየሁ፡፡ **ወደ ቀኝ ዞሮ ሲመለከት ሳቅ አለ፤ ከዛም ወደ ግራው በዞረ ጊዜ አለቀሰ**፡፡ እንዲህም ሲል ተናገረ፤ የተባረክ የአላህ ነቢይና ልጄ እንኳን ደህና መጣህ፡፡ ገብርኤልንም ማን ነው? ብዬ ጠየኩት፤ አዳም ነው፡፡ በቀኙና በግራው ያሉት ደግሞ የልጆቹ ነፍሶች ናቸው፡፡ <u>በቀኙ ያሉት የገነት ሰዎች ሲሆኑ በግራው ያሉት ደግሞ የገሃነም ሰዎች ናቸው፡፡</u> ወደ ቀኝ በዞረ ጊዜ ስቋል ወደ ግራው በዞረ ጊዜ ደግሞ አልቅሷል አለኝ፡፡ ከዛም ወደ ሁለተኛው ገነት እስከምንደርስ ድረስ ወደ ላይ አረግን፡፡ እንደደረስን በር ዘበኛውን በሩን ክፈት አለው፡፡ ዘበኛውም እንደ መጀመሪያው ገነት ዘበኛ ተናገረ፤ በሩንም ከፈተው፡፡... ከዛም በአብርሐም በኩል አለፍኩ፤ እርሱም እንኳን ደህና መጣህ የተባረክህ የአላህ ነቢይና ልጄ አለኝ፡፡ ነቢዩም ጨምረው ሲናገሩ፤ ገብርኤል እንደገና የብዕሮችን መነካካት ድምጽ ወደምሰማበት ቦታ አብረን ወደ ላይ አረግን፡፡ ኢብን ሃዘምና አናስ ኢብን ማሊክ እንደ ተናገሩት ነቢዩ ሲናገሩ ከዛም <u>አላህ በእኔ ተከታዮች ላይ ሃምሳ ሰላቶችን አዝዟል አሉ</u>፤ ይህንን ትዕዛዝ ተቀብዬ ስመለስ <u>በሙሴ በኩል አለፍኩ</u>፤ እርሱም ጠየቀኝ፤ በተከታዮችህ ላይ አላህ በምን አዘዘ? አለኝ፡፡ እኔም ሃምሳ ሰላቶችን እንድንሰግድ አዟል ስል መለስኩለት፡፡ ሙሴም ወደ ጌታህ ተመለስና <u>ለተከታዮችህ እንዲቀንስላቸው ጠይቅ ሊስማሙበት አይችሉም አለኝ</u>፡፡ እኔም ወደ አላህ ተመለስኩና እንዲቀንስ ጠየኩት፤ እርሱም <u>በግማሽ ቀነሰ</u>፡፡ እንደገና በሙሴ በኩል አለፍኩና ስለሁኔታው ገለጽኩለት፤ እርሱም <u>ወደ ጌታህ ተመለስና ተከታዮችህ ሊስማሙበት እንደማይችሉ ግለጽ አለኝ</u>፡፡ እኔም ወደ አላህ ተመለስኩና ተጨማሪ ቅነሳ ጠየኩ፤ እርሱም <u>ቀነሰ</u>፡፡ በሙሴ በኩል እንደገና አለፍኩ፤ ስለሁኔታው ገለጽኩለት፡፡ እርሱም <u>ወደ ጌታህ ተመለስና ተከታዮችህ ሊስማሙበት እንደማይችሉ ግለጽ አለኝ፡፡</u> እኔም ወደ አላህ ተመለስኩ፤ <u>ተጨማሪ ቅነሳ ጠየኩ በግማሽ ተቀነሰ</u>፡፡ እንደገናም በሙሴ በኩል አለፍኩ፤ እርሱም እንዲህ አለኝ፤ <u>ወደ ጌታህ ተመለስ ተከታዮችህ ሊስማሙበት አይችሉም</u>፡፡ ስለዚህ ወደ አለህ ተመለስኩ፤ <u>እርሱም አምስት ወቅት ሰላቶት ይሁን፤ እነርሱ ሁሉም ከሃምሳዎቹ ጋር ዋጋቸው እኩል ነው፤ ቃሌ አይለወጥም አለኝ፡፡</u> ወደ ሙሴም ተመለስኩ አንድ ጊዜ ደግመህ ተመለስ አለኝ እኔም አሁን ጌታዬን ደግሜ ለመጠየቅ ሃፍረት ተሰምቶኛል ስል መለስኩለት አሉ፡፡ አቡ ዳር የተናገሩት

ውድ አንባቢ፤ ነቢዩ በሚያስገርም ሁኔታ ገነትን አስጎብኝተውናል፡፡ ለመሆኑ እንዴት አገኙት? የታሪክ ምሁራን ይህ የሚራጅ ታሪክ ከዞሮአስተሮች የተቀዳ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይሁንና እርስዎ ይህንን የነቢዩን የጉዞ ትረካ እውነት ነው ብለው ያምናሉ? እውነት ነው ብለው እንዲቀበሉትስ የሚያደርግ አንዳች ነገር አለውን? የአላህን መንግስታዊ አስተዳደር እንዴት አገኙት? ስለ መላእክት፣ ስለ አላህ፣ ስለ ቅዱሳኑና ስለ ገነት ትረካው እንደጠበቁት ነበር?

ውድ አንባቢ፤ ለእኔ አላህን ከመሳደብ ለይቸ አላየውም፡፡ የአንድ ባለጸጋ ግቢ እንኳን እንዲህ አይሆንም፡፡ የአምላካችንን ገነት የትኛውም የሰው ልጆች ቋንቋ ብቃት ኖሮት ሊተርከው ብቃት የለውም፡፡ ከነቢዩ ሙሐመድ 600 ዓመታት ቀደም ብሎ ወደዛው ተጉዞ የነበረ ትሁት ሰው እንዲህ ነበር የገለጸው፡-

**2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች** 12 ፡ 2-4

> ከአስራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛ ሰማይ ድረስ የተነጠቀ በክርስቶስ አንድ ሰው አውቃለሁ፤ የተነጠቀው በሥጋ ይሁን ከሥጋ ውጭ አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፡፡ ይህ ሰው በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ እኔ አላውቅምም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፡፡ እርሱ ወደ ገነት እንደተነጠቀ በዚያም **በሰው እንደበት ሊገለጥ የማይችል ሰውም እንዲናገረው ያልተፈቀደለት ነገር ሰማ፡፡**

እንግዲህ ነቢዩ ደርሰው የመጡት ሐዋርያው ጳውሎስ ሔዶበት ከነበረው ቦታ አልነበረም ማለት ነው፡፡ ቢሆን ኖሮ ይህ ሰው ቃል ያጣለትን ጉዳይ እንዲህ አውርደው ሊነግሩን ባልተገባ ነበር፡፡ ራሳቸውን እንደ ሐይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚቆጥሩትን ወገኖች ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን ልጠይቃቸው ወደድኩ፡፡ በሚራጁ ሐዲስ ውስጥ የተሰመረባቸውና ጎላ ብለው የተጻፉትን ቃላት ተጠቅሞ ሁኔታውን የመገምገሙን ሥራ ደግሞ ለአንባቢ እተወዋለሁ፡-

- ነቢዩ ሙሐመድ አንዴ ሲወጡ ሌላ ጊዜ ሲወርዱ የነበረው አላህ ምን አይነት ክፍል ውስጥ የሚኖር ቢሆን ነው? ሙሴስ የት ነበር? በትንሳኤ ስለሚሆነው ነቢዩ ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፡-

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4813፣ ገጽ 288

ሁለተኛው መለከት በተነፋ ጊዜ ለመነሳት አንገቴን መጀመሪያ ቀና የማደርገው እኔ ነኝ፤ **ሙሴም የአላህን ዙፋን እንቅ አድርጎ ይዞ አየዋለሁ**፡፡ ሆኖም ከመለከቱ መነፋት በኋላ ይሁን ነሁልጊዜ እንደዚያ ይኑር አላውቅም፡፡

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6፣ ቁጥር 4638፣ ገጽ 128

…ሙሴ የአላህን ዙፋን አንድ እግር ይዞ አየዋልሁ፡፡…

- ነቢዩ ከሞት በኋላ ገነት ስለመግባታቸው እርግጠኛ ሳይሆኑ[211]፣ በትንሳኤ ስለሚሆነው መናገራቸው አስገራሚ ነው፡፡ ይሁንም በትንሣኤ ሙሴን እንዲያ የሚያዩት ከሆነ፣ ሙሴ ከያዘው ጋር የአላህ ዙፋን ስንት እግሮች አሉት? የአላህ ዙፋን እግር በሙሴ እጆች ለመያዝ የሚቻል ከሆነ ዙፋኑ ላይ የሚኖረውን አላህ ማንን ያህላል? እርሱን ማየት አይቻልም ማለት ይቻላልን? የአላህና የነቢዩ ግንኙነትስ እንዴት ነው የነበረው? ነቢዩ የዙፋኑን እግር የያዘውን ሰው ማየት ከቻሉ አላህንም ያዩት ነበርን? እንዳዩት መናገራቸውን ቀደም ብዬ ማስነበቤን ትዘነጉም
- ለአላህ የሚገባው የሰላት ብዛት የሚወሰነው በሙሴና በነቢዩ ሙሐመድ እንዲሁም በሙስሊሞች በጎ ፈቃድ፣ ወይንስ አምልኮው በሚገባው በአላህ? ድርድሩንስ ምን አመጣው? የሕዝቡን ልክ የሚያስፈልገውንም ሆነ ደስ የሚያሰኘውን ራሱ አላህ አያውቅም? ስለ ሕዝቡ በማሰብ ሙሴ ከአላህ ተሽሎ ይሆን?
- በነቢዩ ላይ የተካሄደው ቀዶ ጥገና ከሳይንስ ጋር ያለው ግጭትስ እንዴት ይታያል? የሰው የአስተዋይነቱና የጠቢብነቱ ቦታ አዕምሮው ወይስ በደረቱ መካከል ያለችው ጭብጥ የሥጋ ልብ? ይህንን የሠራው ገብርኤል ከሆነ ለጥበብ የሚሆነውን ስፍራ ማወቅ እንዴት ተሳነው? ደግሞስ የሰውየውን ደረት ከፍቶ በዘምዘም ውሃ ማጠቡ ምን የሚሉት ነው? ከነቢይ ማንነትስ ጋር ምን አገናኘው?
- የአዳምን ልጆች ስንመለከት ሁለቱም ዓይነት ገነት ውስጥ ይገኛሉ፤ ሕጋዊ እና ሕገ ወጥ የገሃነም ልጆች የሆኑ፡፡
  - እንግዲህ አላህና የቀድር አስተምህሮው እንዴት ይታረቁ? የእሳት ፍርደኞች ሆነው እያለ፣ አድራሻ ቀይረው ገነት ውስጥ እየኖሩ ከሆነ እነርሱን የገሃነም ልጆች ብሎ መጥራት ይቻላል? ወይስ በኋላ የአባታቸውን ናፍቆት ሲጨርሱ ይባረራሉ? ቁጥራቸውስ ስንት ነው? ነቢዩ ሙሐመድን ልጅ ብሎ ከጠራቸው አዳም አባት የሆነላቸው ልጆቹ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚወለዱት ሁሉ ናቸው ማለት ነው፡፡ ታዲያ እስካሁን ከሞቱት መካከል ወደ ሲኦል የሔደ የለም ማለት ነዋ?
  - እነዚህ ወገኖች ገነት ውስጥ የተገኙት፣ የመቃብሩን ቅጣት ማን እየተቀጣላቸው ነው? ሙንኪርና ናኪር የተባሉት መላእክት የመቃብር ድብደባ የጀመሩት ከዚህ ከነቢዩ የሚራጅ ጉዞ በኋላ ነበርን? እነዚህ መላእክት በድን የሆነ የማይሰማ፣ የማይናገር፣ ከቀናት በኋላ አፈር የሚሆን በድን ነው እንዴ የሚገርፉት?

---

211 *Sahih Al-Bukhari vol 2, #1243 page 199*

❖ እንግዲህ ጥልቅ የሕይወት ጥራት ችግር ያለባቸው ነቢዩ ሙሐመድ አላህን አየሁት ካሉ መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ይታያል ብሎ ባይልም ባያስተምርም ሙሴን የመሰለ ጻድቅ ሰው "አላህን አየ" ማለቱ እንዴት አልዋጥ አላቸው? ከዙፋን ስር መዋልና ማደሩን እየነገሩን ሙግቱን ማንሳት ነበረባቸው?

ውድ አንባቢ፣ አይስማሙም የተባሉትን የመጽሐፍ ቅዱስና የቁርአን አንቀጾች እስኪ በንጽጽር ይገምግሟቸው፡፡ ሁለቱንም ክፍሎች እነሆ፡-

ሱረቱል አል-አዕራፍ 7 ፡ 143

ሙሳም ለቀጠሯችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፡- «ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና» አለ፡፡ (አላህም)፡- «በፍጹም አታየኝም ግን ወደ ተራራው ተመልከት፡፡ በስፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ» አለው፡፡ ጌታው ለተራራው በተገለጸ ጊዜ እንኩትኩት አደረገው፡፡ ሙሳም ራሱን ስቶ ወደቀ፡፡ በአንሰራራም ጊዜ «ጥራት ይገባህ፡፡ ወዳንተ ተመለስኩ፡፡ እኔም (በወቅቱ) የምእምናን መጀመሪያ ነኝ» አለ፡፡

ኦሪት ዘፀአት 33 ፡ 17-23

እግዚአብሔርም ሙሴን፦ በፊቴ ሞገስ ስላገኘህ በስምህም ስላወቅሁህ ይህን ያልኸውን ነገር አደርጋለሁ አለው። እርሱም፦ እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለ። እግዚአብሔርም፦ እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ፤ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፥ በዓለቱም ላይ ትቆማለህ፤ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዓለት አኖርሃለሁ፥ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ ፊቴ ግን አይታይም።

እንግዲህ የአላህን ትክክለኛ ማንነት ያንጸባረቀ፣ ሰዎች አምላካቸውን እየወደዱት ተስፋም እያደረጉት እንዲገዙለት የሚጋብዝ፣ የሙሴን ጥያቄና የአላህን ምላሽ ተቀባይነት ባለው መልኩ የዘገበ የትኛው መጽሐፍ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ወይንስ ቁርአን? ቁርአን ሙሴ የአላህን "ነፍስ" የማየት ጥያቄ አቀረበ ይለናል፣ ነፍስ ማለት ደግሞ ልትያዝ፣ ልትጨበጥ፣ ልትዳሰስና ልትታይ የማትችል ማንኛውም ፍጡር ሲጸነስ ጀምሮ አብራ ያለች በሞት ብቻ የምትለይ ሕይወት ማለት

ነው[212]፡፡ ታዲያ ሙሴን የመሰለ የተማረ ሰው ይህንን ጥያቄ የሚያቀርብ ይመስለዎታል? የአላህ ምላሽም፡-

- ተራራ መሰባበር
- ተራራውን ስገለጥለት መቆም ችለህ ካየኸው፣ እኔን ማየት ትችላለህ፤ አላዛ አትችልም አለው፡፡
- ሙሴም አልቻለም፤ ተመለስኩ አለ፡፡ የምእምናንም መጀመሪያ ነኝ አለ፡፡

እስኪ ጥያቄዎችን ልጠይቅ፡-

- ❖ ባሕር ሲከፈል ያየ፣ ቁጥቋጦ እሳት እየነደደባት ሳትቃጠል ስትቀርና ድምጽም ከመካከል ወጥቶ ሲያናግረው ያዬ የሰማ፣ አምላክ ብዙ ተአምራትን በእጁ የሠራበት ሰው፣ እንዲህ አይነት ጥያቄ ይጠይቃል ብለው ያስባሉ? አላህስ ኑሮን እየገፋ ያለው እንደ ሰው ባለች ነፍስ ነውን?
- ❖ ሙሴ ወደ አንተ ተመለስኩ ማለቱ ምኑ ከኀጢአት ተቆጥሮበት ነው?
- ❖ ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ "ሙሴ የምእመናን መጀመሪያ ነኝ" አለ ብሎናል፤ እውን ሙሴ የምእመናን መጀመሪያ ነበርን? ስለ ሕዝቡ ከግብጽ መውጣትና የተስፋ ምድር ቃል የተገባላቸው የእስራኤል ቀደምት አባቶች አብርሐም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ የአስራ ሁለቱ ነገድ አባቶች የት ሄደው ሙሴ የመጀመሪያ ሰው ሆነ? ይህ የቁርአን አንቀጽ ከሌሎች የቁርአን አንቀጾች ጋር የሚኖረውን ግጭት እንዴት ሊያስታርቅ እንዲህ ተናገረ?
- ❖ የሲና ተራራስ እውነት ብናኝ አመድ ሆኗል? አላህና ሙሴ የተገናኙበት የሲና ተራራ አሁን የለም? ሰዎች በአምላካቸው ተስፋ እንዲኖራቸው፣ ስለ አሁን የሚያስተምራቸው ምንድን ነው? ውድ አንባቢ፤ ከዚህ አላህን ተስፋ እንዲያደርጉ የሚማሩት ነገር ይኖር ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሙሴ **"ክብርህን አሳየኝ"** ብሎ እንደጠየቀ ይነግረናል፡፡ ክብር ማለት ደግሞ መግነን፣ መክበር፣ የበላይ ሆኖ መታየት፣ ክብርና ማእረግ፣ የሐብት ብልጽግና ማለት ነው[213]፡፡ ይህ ደግሞ መገለጫው ብዙ ስለሆነ ጥያቄው ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በምላሹ የሚታይና የማይታይ የክብር መገለጫዎች እንዳሉት፤ የማይታየውን ለማየት ቢሞክር የሚፈጠረውን ችግርም ነገረው፡፡ መታየት የሌለበት የክብሩ መገለጫ ደግሞ ፊቱ ነበር፡፡ ሌሎቹን የክብሩን መገለጫዎች እንደተናገረው አደርጋለሁ እንዳለው

---

[212] ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ 293
[213] ዝኒ ከማሁ ገጽ 478

ሊያሳየው ሲመጣ የማይታየውን አይቶ እንዳይሞት መሸሸጊያ እንደ ሚያዘጋጅለት እንዲህ ሲል ነገረው፡-

> "እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ የእግዚአብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ፥ የምምረውንም እምራለሁ አለ። ደግሞም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። እግዚአብሔርም አለ፦ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፥ በዓለቱም ላይ ትቆማለህ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዓለት አኖርሃለሁ፥ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ ፊቴ ግን አይታይም።"

ይህንን የተናገረውን ሲያደርግለት ደግሞ በቀጣዩ ምዕራፍ ውስጥ ማለትም በኦሪት ዘፀአት 34 ፡ 5-7 ባለው ክፍል ላይ እንመለከታለን፤ እንዲህ ይላል፤

> ኦሪት ዘፀአት 34 ፡ 5-7
>
> እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ወረደ፥ በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ፥ የእግዚአብሔርንም ስም አወጀ። እግዚአብሔርም በፊቱ አልፎ እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት፥ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፥ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፥ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ፥ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው ሲል አወጀ።

ሙሴ የታወጀውን የእግዚአብሔርን የስሙን ክብርና ባህርይ እንደ ሰማ፣ አዋጁ ሰዎች ከአምላካቸው ምህረትን፣ ፍቅርን፣ ርህራሄውን ተስፋ እንዲያደርጉ የሚያደርግ ስለነበር ከመታዘዝ ይልቅ አመጸኝነት ለሚቀናው ለእስራኤል ሕዝብ ምህረትን መለመን ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም ልመናውን ተቀብሎ ምን ሊያደርጉ እንደሚገባቸው መመሪያን ሲሰጠው እናያለን፡፡

> ኦሪት ዘፀአት 34 ፡ 8-17
>
> ሙሴም ፈጥኖ ወደ መሬት ተጐነበሰና ሰገደ። አቤቱ በፊትህስ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ፥ ይህ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነውና ጌታዬ በመካከላችን ይሂድ፣ ጠማማነታችንንና ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ ለርስትህም ተቀበለን አለ። (ከቁጥር 8-9)

እዚህ ላይ ሁሌ ዳኢዎቹ እንደሚሉት ምን አልባት ልጆችን በአባቶች ኀጢአት እየቀጣ እንዴት ስለ ምህረትና ፍቅር ይናገራል፤ ይሉ ይሆን? ይህ እነ ማንንና ምን አይነት ሰዎችን በተመለከተ እየተናገረ እንደሆነ ኦሪት ዘፀአት 20 ፡ 1-6 ያለውን በማንበብ ምላሽ ማግኘት ይቻላል፡፡ እኔው ላስነብባችሁ መሰለኝ፡-

ኦሪት ዘፀአት 20 ፡ 1-6

> እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ። ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።

አምላክ ማን እንደሆነ እያወቁ እርሱን ችላ ብለው ወደ ጣኦት አምልኮ ለሚገቡት የተባለ መሆኑን አስተዋሉ ይሆን? እንዲህ የሚያደርጉትን እኔን የጠላ ይላቸዋል፤ የእነርሱ ኀጢአት ለልጆቻቸው ይተርፋል፡፡ የእስራኤል ልጆች በዚህ አይነት ኀጢአት በድለውና ቅጣት ደርሶባቸው እንደሚያውቅ ቀደም ብለን ተመልክተናል፤ በተጨማሪም የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብና ማረጋገጥ ይችላሉ፡-

ትንቢተ ዳንኤል 9 ፡ 1-19 1 መጽሐፈ ነገስት 16 ፡ 29-34
1 መጽሐፈ ነገስት 21 ፡ 20-26 1 መጽሐፈ ነገስት 15 ፡ 29-30
1 መጽሐፈ ነገስት 16 ፡ 1-4

ይህማ በቁርአንም ተገልጿል ይሉ ይሆናል፤ ከቁርአን ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዛም አንዱ ቁርአን ውስጥ የሰፈረው አላህ ራሱ ሰዎች ባልነበሩበት ዘመን ጣኦትን እንዲያመልኩ ወስኖባቸው ያንኑ የወሰነባቸውን ባከናወኑ እንደ ወንጀለኛ ቆጥሮ እንዳስጨፈጨፋቸው ነው ፡፡ በዚህም የቁርአኑ አላህ ፍትህዊ አምላክ አለመሆኑን ወይንም እውነተኛ አምላክ አለመሆኑን አስመስክሯል፡፡ እርስዎስ ቢሆኑ፤ ሁሌ መልካም ሆነ ክፉ ሲያጋጥመዎት "አላህ ቀድሮብኝ ነው" አይደል የሚሉት? ከዚህ የተነሳ ስለ ዘላለም ሕይወትዎትም በሚሠሯቸው መልካም ሥራዎች ተማምነው ገነት እገባለሁ ብለው መናገር አይችሉም! አዎን ምናልባት ለገሃነመ እሳት ፈጥሮኝ ቢሆንስ ብለው ስለሚያስቡ አይችሉም፡፡ እስኪ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የቁርአን አንቀጾችና የሐዲሶቹን ክፍሎች ያንብቡና የመጽሐፍ ቅዱስን አላህና የቁርአኑን አላህ ያነጻጽሩ፤ የትኛው እውነተኛ አምላክ እንደሆነ የራስዎን ምስክርነት ይስጡ፡፡

ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 253 ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 39
ሱረቱል ሁድ 11 ፡ 118-120 ሱረቱል ሁድ 11 ፡ 32-34
ሱረቱል አል-ኒሳእ 4 ፡ 88 ሱረቱል መርየም 19 ፡ 83

ሱረቱል አል-ኢስራእ 17 ፡ 45-47
ሱረቱል አል-አንአም 6 ፡ 107-108

አላህም በሻ ኖሮ ባላጋሩ ነበር፡፡ በእነሱም ላይ ጠባቂ አላደረግንህም፡፡ አንተም በእነሱ ላይ ኃላፊ አይደለህም፡፡ እነዚያንም ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸውን (ጣዖታትን) አትስደቡ፡፡ ድንበርን በማለፍ ያለዕውቀት አላህን ይሰድባሉና፡፡ እንደዚሁ ለሕዝቦች ሁሉ ሥራቸውን ደግ አስመሰልንላቸው፡፡ ከዚያም መመለሻቸው ወደ ጌታቸው ነው፡፡ ይሠሩት የነበሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡

ሱረቱል ዩኑስ 10 ፡ 99-100

ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን? ለማንኛዋም ነፍስ በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ ልታምን (ችሎታ) የላትም፡፡ (አላህ ለከፊሎቹ እምነትን ይሻል)፡፡ በእነዚያም በማያውቁት ላይ ርክሰትን ያደርጋል፡፡

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 4 ቁጥር 3332
ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 6 ቁጥር 4947
ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 8 ቁጥር 6463

- ነቢዩ ሙሐመድ ጀነት ስለመግባታቸው እርግጠኛ አይደሉም፤ ታዲያ ለእርስዎ ሊኖር የሚችለው ተስፋ ምንድን ነው?

ውድ አንባቢ፤ የመጽሐፍ ቅዱሱ አላህ የሰዎችን ልብ አጥምሞ ፈጥሮ ገሃነም የሚከትና በሰዎች ስቃይ ሁሉን ቻይነቴን ተመልከቱልኝ የሚል ኢ-ፍትሃዊ አምላክ አይደለም፡፡ የፈጠረው ሰው እንጂ ሮቦት አይደለም፡፡ ከመፈጠራቸው በፊት፣ ከመወለዳቸው በፊት ወስኖባቸው፣ የተወሰነባቸውን ሥራ ባከናወኑ ሽልማቱ ቢቀር እንደ ወንጀለኛ መቆጠር ነበረባቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ግን እግዚአብሔርን እንዲህ ይለዋል፡-

መዝሙረ ዳዊት 89(90) ፡ 3

ሰውን ወደ ጎሳር አትመልስም፤ የሰው ልጆች ሆይ፥ ተመለሱ ትላለህ፤

ውድ አንባቢ፤ እስኪ አንዴ ወደተጠቀሱት የኦሪት ዘፀአት ክፍሎች ይመለሱና እንደገና ይመልከቷቸው፡፡ ምን ያህል ከዘላለም ሞት የመዳን ተስፋ እንዳለዎትና በአምላክዎ የተወደዱ ተፈቃሪ ሰው እንደሆኑ አስተዋሉ? ውድ አንባቢ፤ ብዙ ኀጢአትዎን ይቅር ሊል፤ ሊምርዎትና ሊራራልዎት ሁሌ ዝግጁ የሆነ አምላክ ነው፡፡ ለእርስዎም ሆነ ለትውልድዎ ሁሉ ፍቅሩን፣ ምህረቱን፣ ርህራሄውን አብዝቶ

ማሳየት ይፈልጋል፡፡ ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን ፍቅር ያሳየው በልጁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ የኀጢአታችን ማስተሰረያና ቤዛችን ነው፡፡ በእርሱ የሚያምን ለዘለአለም አይጠፋም፡-

የዮሐንስ ወንጌል 3 ፡ 16-17

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።

1 ወደ ጢሞቴዎስ 2 ፡ 3-4

ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።

ስለዚህ ጊዜው እያለዎት ጨለማ ወደ ሕይወትዎ ሳይመጣ እግዚአብሔር ለደህንነትዎ ሲል ለሠራው ልዩ ፍቅር ሥራ ምላሽ ሊሰጡ ይገባዎታል፡፡

ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ የሚቆጥሩ ወገኖች "ሙሴ የአላህን ጀርባ አይቷል ወይንስ አላየም?" የሚለውን ጥያቄያቸውን አሁን ልመልስ፡፡ ምናልባት ለሙግት ያነሳሳቸው "ጀርባ" የሚለው ቃል ይሆን? እነዚህ ወገኖች ይህንን ሙግት ከማንሳት ይልቅ በአላህ አካል (Person) ዙሪያ በራሳቸው ምሁራን መካከል እስከ ዛሬ መፍትሔ ያላገኘውን አመለካከት ቢመረምሩ ምላሽ ያገኙ ነበር፡፡ ግማሹ አላህ እንደ ሰው እጅ፣ እግር፣ አይን ያለው አምላክ ነው ብሎ ሐዲሱን ምስክር ይጠራል፤ ግማሹ ደግሞ አይ እርሱ መንፈስ ነው፣ እጅ እግር የለውም ይላል፡፡ በዚህ ልዩነት የሚኖር አካል ይህንን ደብቆ ሌላውን ልክ አይደለህም ሊል አይችልም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የእስልምና ምሑራን እንደሚሉት አምላክ እንደ ሰው እጅ፣ እግር፣ ፊት፣ ጀርባ አለው፤ ጆሮ አይን አለው ብሎ አያምንም፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ነው[214] ይላል፡፡ እንዲህ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት እነዚያ በርካታ የሰዋዊነት መገለጫዎች ለአላህ አገልግሎት ላይ ውለው የሚታዩት ለምን ይሆን? ይባል ይሆናል፡፡ አዎን እንደተባለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በሰዋዊ መገለጫዎች ተነግሮለት ይገኛል፡፡ ሆኖም የተነገሩት እርሱ እንደዚያ ነው በሚል ሳይሆን መልእክት ሰጭው ራሱን ለሰዎች ለማስረዳት በትክክል ሊገልጸው የሚችል የሰው ቋንቋ ስለሌለ የግድ መናገር ያለበት በዚሁ መንገድ ስለነበር ነው፡፡ እግዚአብሔር ከቋንቋ ያልፋል፤ እርሱን ለመግለጽ

[214] የዮሐንስ ወንጌል 4 ፡ 24

የሚችል የሰው ቋንቋ የለም፡፡ ስለዚህ መልእክት ተቀባዩ ሰው ስለሆነ መልእክቱ የተላከላቸውም ሰዎች ስለሆኑ፣ እነርሱም የሚግባቡት እንደ ሰውነታቸው ባላቸው ቋንቋ ነው፤ ስለዚህ በዚህ መልኩ ሊተላለፍ ግድ ነው፡፡ ውዱ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንፈስ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

የዮሐንስ ወንጌል 4 ፡ 24

*እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡*

የሉቃስ ወንጌል 24 ፡ 36-39

*ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ፣ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። እርሱም፦ ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ እዩ አላቸው።*

ስለዚህ ሙሴ የጠየቀው መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርን ስለማየት ሳይሆን ክብሩን ማየት ነበር፡፡ የክብሩ መገለጫዎች በርካታ እንደሆነ ደግሞ ከዚህ በፊት ተነጋግረናል፡፡ ያንንም የሚታይና የማይታይ ብሎ ከፋፍሏቸዋል፡፡ የማይታየው የክብሩ ክፍል ፊቱ ነው፤ ሰው እርሱን አይቶ በሕይወት መኖር ስለማይችል አላየውም፡፡ ሌላው የክብሩ መገለጫ ደግሞ ስሙና ባህርይው ነው፤ እርሱንም እያወጀ በፊቱ በማለፍ እግዚአብሔር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲያውቅና ዛሬም እኛ እንድናውቀው አድርጓል፡፡ ቀጣዩ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ስለሚታየው የክብሩ ክፍል ማስረዳት ነበርና ጀርባዬን ታያለህ አለው፡፡ ይህንን ደግሞ በሁለት መልክ መልሶለት እራሱን አሳይቶታል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?

- እግዚአብሔር ስሙን እያወጀ ካለፈ በኋላ በእግዚአብሔር መገኘት የሚሆነውን ሁኔታ "ጀርባዬ" ብሎታል፤ ያም እንዱ ክብሩ የሚታይበት መገለጫው ነበር፡፡ ሙሴ ለእስራኤል ምህረት የለመነውና አስርቱን ትዕዛዛት የያዙትን ሁለቱን ጽላቶች እንደገና ተቀብሎ የሔደው በዚሁ ክብርና ከሰማው ማንነቱ ተነስቶ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ተነጋገረ፣ የፊቱ ቆዳ ስለተቀየረ፣ ሰዎች እርሱን ለማየት እስኪቸገሩ ድረስ ማንጸባረቅ የጀመረው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ (ኦሪት ዘፀአት 34 ፡ 29-35)
- ሌላው የክብሩ መገለጫ ለሰዎች ሁሉ መዳን መድኃኒት የሆነውን መልካምነቱ፣ ፍቅሩ፣ ርህራሄው፣ ማዳኑ፣ ይቅርታው፣ ምህረቱ የተገለጸበትን ልጁን፣ የክብሩን ነጸብራቅ ጌታ ኢየሱስን ታያለህ ማለቱ ነበር፡፡ እርሱ ለሰዎች ክብሬን፣ መውደዴን፣ ምህረቴን የማሳይበት የክብሬ መገለጫ ነው፣ አለው፡፡ ሙሴም ከዛ በኋላ ከወንድሞቻችሁ

መካከል እንደእኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል ብሎ ትንቢት ተናግሮለት አለፈ፡፡ (ኦሪት ዘዳግም 18 ፡ 17-18)

በመጨረሻውም ጊዜው በደረሰ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ተወልዶ አገልግሎት ጀምሮ እያለ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ተናገረው የተስፋውን ፍጻሜና የእግዚአብሔርን ሌላውን የክብሩን መገለጥ ይመለከት ዘንድ ከኤልያስ ጋር አብረው ከሰማይ በመምጣት የእግዚአብሔርን የክብር ነጸብራቅ ሌላውን ክብር አየው፡፡

የማቴዎስ ወንጌል 17 ፡ 1-4

ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ።

ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

የዮሐንስ ወንጌል 1 ፡ 18

መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።

ወደ ዕብራውያን ሰዎች 1 ፡ 1-3

ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፤

አሁን መልሱ አዎን ሙሴ የእግዚአብሔርን ጀርባ አይቷል!

# 4. ሙግት አራት

## መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ስህተቶችን መያዙ

ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ በሚቆጥሩት ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ብሎ ለመሞገት የሚያነሱት ሌላው አሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተቶችን በውስጡ መያዙ ነው የሚል ነው፡፡ ለዚህ መሞገቻቸው ከጠቀሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል ሁለቱ፡-

❖ የማቴዎስ ወንጌል 2 ፡ 19-23

በዚህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ ተብሎ በነቢያት ቃል በየትኛውም ነቢይ ሳይጠራ የተባለው የትንቢት ቃል ይፈጸም ዘንድ ማለቱ ስህተት ነው ይላሉ፡፡

❖ የማቴዎስ ወንጌል 27 ፡ 9-10

ይሁዳ ኢየሱስን ስለሸጠበት ሰላሳ ብር የትንቢቱ ቃል ዘካርያስ ላይ ተነግሮ እያለ ማቴዎስ ኤርምያስ ላይ ማለቱ ሌላው ስህተት ነው ይላሉ፡፡

የእነዚህ ወገኖች "መጽሐፍ ቅዱስን ስህተትን ይዟል" ለሚለው ሙግታቸው የጠቀሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስንመለከት ምላሽ የሚያገኝ ይሆናል፡፡ ሆኖም ቁርአን ውስጥ ስላሉት ቁጥር ስፍር ስለሌላቸው ስህተቶች ምንይሉ ይሆን? የቁርአንን ስህተቶች በአይነት በአይነት በጥቂቱም ቢሆን በመጀመሪያው ገጾች ላይ አሳይቻለሁ፡፡ አሁንም ሌላ ተጨማሪ ስህተቶችን ማሳየት ቢቻልም ከብዛታቸው የተነሳ ጀምሬ ማቆሙን ስለማልፈልግ ራሳቸውን ችለው የሚተነተኑበትና መጽሐፍ ቅዱስ ስህተትን ይዟል ባዮቹ ምላሽ ካገኙ መልስ እንዲሰጡባቸው የሚሆንበት ቀን ስለተቀጠረ አሁን እዘላቸዋለሁ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን አሳቦች በተመለከተ ለተነሱት ደግሞ ጌታ በረዳኝ መጠን ምላሹ ይኸውና፡-

### 4.1. የማቴዎስ ወንጌል 2 ፡ 19-23

ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ። የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ። በአባቱም በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ፥ ወደዚያ መሄድን ፈራ፤ በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ፤ በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ።

ከስህተቶቹ አንዱ ይህ ነው፤ እስኪ በየትኛው ነቢይ ነው ኢየሱስ ናዝራዊ ይባላል ተብሎ የተነገረው? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ፡፡

ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ እንደሆኑ አድርገው የሚቆጥሩት ወገኖች፡-

- ስለ ቁርአን እንዲሁም ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ሱናዎችና ሐዲሳት ስነ አፈታት ያላቸው እውቀት ምን ያህል ይሆን? እውቀቱ ካላቸው እንዴት ነበር የሚፈቷቸው?

መቼም አንድ ምላሽ እንደምትሰጡን አምናለሁ፡፡ ምናልባት አንዱ መንገድ ነቢዩ ሙሐመድ በነበሩበት ዘመን የቁርአኑ አንቀጽ በሚወርድበት ጊዜ ከነበረው ሁኔታ በመነሳት ነው ማለታችሁ አይቀርም፤ የምታውቁ ከሆነ፡፡ እያንዳንዱ የቁርአን አንቀጽ የወረደው ከድርጊት በኋላ ነበር፤ ስለዚህ የወረደው በጊዜው ድርጊቱን ይፈጽም ለነበረው ማሕበረሰብ ነበር፡፡ ያም ማለት ቁርአን በተደጋጋሚ "አስፈራሪ" ሆኖ መላኩን እንደተናገረው፣ የወረደው እንዲፈሩና እንዲጠነቀቁ ከነቢዩ አፍ ቃል በሚሰማው ሕዝብ የቃላት አጠቃቀም፣ አካባቢያዊ ዘይቤ፣ በሕዝቡ በራሱ ባህል፣ የተለያየ እውቀትና የግንዛቤ ደረጃ መሠረት ነው፡፡

**ሱረቱል ዩሱፍ 12 ፡ 2**

እኛ (ፍቹን) ታውቁ ዘንድ ዐረብኛ ቁርኣን ሲሆን በእርግጥ አወረድነው፡፡

በተጨማሪም አላህ በሌላ ሐዲስ ሰዎች ቁርአንን እንዲረዱትና የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላቸው በማሰብ በሰባት አይነት የዓረብኛ ዝዬዎች (dialects) እንዲነበብ ትዕዛዝ መሰጠቱን ነቢዩ ሙሐመድ መናገራቸው ተዘግቧል፡፡ (ሳሂህ ሙስሊም ቅጽ 2፣ ቁጥር 1906 ገጽ 339) ስለዚህ የዛሬዎቹ ሙስሊም ወገኖች እነዚህን ጉዳዮች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቁርአንን እንዴት ሊተረጉሙ እንደሚገባቸው ያሳያል፡፡ ቁርአን በሰባት የዓረብኛ ዝዬዎች እንዲነበብ የሚፈቅደው የአላህ ትዕዛዝ በከሊፋ ኡስማን ቢጣስም፣ የቁርአንና የሐዲሳቱ አተረጓጎም ሳይንስ የሚያዘውና የመስኩም ምሁራን የሚጠቀሙበት፣ ለተማሪዎቻቸውም የሚያስተምሩት የአተረጓጎም መንገድ ይህ ነው፡፡ አለበለዚያ የአላህን ፈቃድ ማወቅና ለእርሱ በመገዛት መኖር አይቻልም፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተትን መያዙ በማለት ለመሞገት የተነሱት ወገኖች ይህንን የሚያውቁ ይሆን? ከሆነ ቁርአን የራሱ የአተረጓጎም መንገድ እንዳለው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስም የራሱ የአተረጓጎም መንገድ እንዳለው ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ እርሱን ለመሞገት ሲፈልጉ የራሱን የአተረጓጎም መንገድ መከተል ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ ሆኖም አላማቸው እውነትን መፈለግና ማረጋገጥ ስላልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስን የአተረጓጎም መንገድ መጠቀም አልፈለጉም፡፡ ይህም ይቅርና ቢያንስ የራሳቸውን መጽሐፍት የአተረጓጎም ሳይንስ በመጠቀም የጠቀሱትን

ክፍል መመልከት አልቻሉም፡፡ ይህንን ማድረግ ችለው ቢሆን ኖሮ በእኛ ዘንድ እንደጭፍን ተሟጋች ባልታዩ፤ እነርሱም እንዲህ አይነት ጥያቄ ባላነሱ ነበር፡፡

እንግዲህ በእነዚህ ወገኖች ስህተት ነው ስለተባለው የማቴዎስ ወንጌል ክፍል ቀጥተኛ ምላሽ ልስጥ፡፡ በመጀመሪያ የአነባባቸውን ክህሎት ማዳበር ይኖርባቸዋል፤ ሐዋርያው ማቴዎስ "በነቢያት" አለ እንጂ ስለ አንድ ነቢይ አልተናገረም፡፡ ስለዚህ "በየትኛው ነቢይ?" የሚለው ጥያቄያቸው የሚመጥን ወይንም ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ አይደለም፡፡ ይሁን ከተባለና አንድ ነቢይ መጠቀስ ካለበት ጎላ ብሎ በሚደመጥ መልኩ "ናዝራዊ ይባላል" ተብሎ ትንቢቱ የተነገረው በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ነበር፡፡ ግን ደግሞ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ነቢያት ትንቢት መናገራቸውን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በነገራችን ላይ ራሳቸውን የሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ አድርገው የሚቆጥሩት ወገኖች ስለ አይሁዳውያኑ ባህል፣ ቋንቋና የሥነ ጽሁፍ ባህላቸው እንዲሁም መልክአ ምድራዊ ሁኔታ ምን ያህል እውቀት አላቸው? ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ሁኔታቸው ምን ይመስል እንደነበርስ እውቀቱ አላቸው? ስመለከታቸው የሃይማኖት ጽንፈኝነት የሚያናግራቸው እንጂ ስለዚህ ምንም አይነት እውቀት ያላቸው አይመስሉም፡፡

ናዝራዊ የሚለው ቃል በሙሴ መጽሐፍትና በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰፍሮ የሚገኝ ቢሆንም፣ ይህ በሐዋርያው የተገለጸው የኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊነት ከእነዚህ የተለየ መልእክት ያለው ነበር፡፡ የተስፋው ቃል ተጠባባቂ የሆኑት አይሁዳውያኑ እንዲያስተውሉት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊነት እንደ ትንቢቱ ቃል ከከተማዋ ጋር ተያይዞ ሲተረክላቸው እንመለከታለን፡፡ ይህች ከተማ ከእስራኤል ሶስት አውራጃዎች አንዱ በሆነው በገሊላ አውራጃ ከሚገኙ ከተሞች መካከል አንዷ ናት፡፡ በዚህች ከተማም የሚኖር ሰው ሁሉ ናዝራዊ ተብሎ ይጠራል፡፡ ወንጌላዊው ይህንን መጠሪያ ለታላቁ ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠቀምበት ምክንያት ያደረገው ከተማ ነዋሪነት አቀፍ ብቻ ሳይሆን፣ ለዚህች ከተማ ነዋሪዎች ሌሎች ወገኖች ያላቸውን አመለካከት ብዙ ቁጥሮች ያሉትን የትንቢት መልእክት በእነዚህ አራት ቃላት መልእክቱን ለማስተላለፍ ስለፈለገ ነው[215]፡፡ ይህንን መጠሪያ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተጠቀመበት ማቴዎስ ብቻ ሳይሆን ፈሪሳውያኑና ሕዝቡም ተጠቅመውበታል፡፡

ሁለቱም ወገኖች ማለትም የኢየሱስ ተከታዮችና ፈሪሳውያኑ ይህንን ስም ተጠቅመው ሲጠሩት በትርጉም ደረጃና በሚጠሩበት ልባዊ ዝንባሌ ይለያዩ ነበር፡፡ ይህ ቁርአን ውስጥ ወደ ተጠቀሰ በሁለት ወገኖች አንደበት ሲነገር ሁለት ትርጉም ያለውን አንድ ቃል እንድናስታውስ ያደርጋል፡፡

**ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 104**

---

215 የአትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 6ኛ እትም፣ በባናዊ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1992 ዓም፣ ገጽ 140-141

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! (ለነቢዩ) ራዒና አትበሉ፡፡ ተመለከትን በሉም፡፡ ስሙም፤ ለከሓዲዎችም አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَقُولُوا رَاعِنَا وَقُولُوا انظُرْنَا وَاسْمَعُوا ۗ وَلِلْكَافِرِينَ عَذَابٌ أَلِيمٌ

ራኢና የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡ በአረብኛው አድምጠን እናድምጥህ ማለት ሲሆን በእብራይስጥ ደግሞ ጂል ማለት ነው[216]፡፡ እንግዲህ አንድ ሰው ይህን ቃል ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ እንደተጣራ ትርጉሙን ሊያውቀው የሚችለው ተናጋሪው ብቻ ነው፡፡

ልክ እንደዚሁ ናዝራዊ የሚለው መጠሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን በተቀበሉትና ባልተቀበሉት ወገኖች ጥቅም ላይ ሲውል የሚሰጠው የተለያየ ትርጉም ነው፡፡ በጠላትነት ለሚመለከቱት ናዝራዊነት የደካማነት፣ ያልተሳካለት፣ ተቀባይነት የሌለው፣ የማይረባ ለማለት ነው[217]፡፡ ለዚህ ነው ናትናኤል እንድርያስ ሲጠራው ከናዝሬት መልካም ነገር? ያለው፡፡

የዮሐንስ ወንጌል 1 ፡ 46-47

ፊልጶስ ናትናኤልን አገኘ። ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው። ናትናኤልም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው። ፊልጶስ። መጥተህ እይ አለው።

የዮሐንስ ወንጌል 7 ፡ 52

እነርሱም መለሱና። አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ መርምርና እይ አሉት

ለተቀበሉት ደግሞ ናዝራዊነት በትንቢቱ ቃል ነቢዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው ነው፡፡ እርሱም እንዲህ በማለት አስተላልፏል፡-

ትንቢተ ኢሳይያስ 53 ፡ 1-12

የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠአል? በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አደገ። መልክና ውበት የለውም፥ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም

---

*216 Muhammad Mahar Ali, A word for Word Meaning of the Quran, Jamiyat Ihyaa Minhajj al sunna 2003, vol 1, page 39*

*217 John Gill`s, Exposition of the entire bible, e-sword free Bible software,commentary on john 1 : 46*

የሚያውቅ ነው፣ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፣ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፣ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፣ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፣ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ተጨነቀ፣ ተሣቀየም፣ አፉንም አልከፈተም፣ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፣ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር። እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፣ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፣ ደስም ይለዋል፣ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፣ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።

ውድ አንባቢ፤ ምንም ናዝራዊ ተብሎ ከከተማው ጋር በተያያዘ መልኩ በትእቢተኞችና በትምክህተኞች አንደበት መጠራት አሳፋሪና ውርደት ቢመስልም፣ ጌታ ኢየሱስ ካለፈበት መንገድና ከመጣበት አላማ አንጻር ሲታይ ግን፣ ለተቀበልነው የክብራችን መንገድ ስለሆነ አናፍርበትም፡፡ ሐዋርያው ማቴዎስም ክብር እንጂ ውርደት እንዳልሆነ ስለገባው ከወገኖቹ ጋር በሚግባባበት መንገድ ሰፊ የሆነውን የነቢዩን የትንቢት ቃል በአጭር መንገድ ከሙሉ ደስታ ጋር መተረክ የፈለገው፡፡

ብርቱና ሁሉን ቻይ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ በሥጋ ተገልጦ መከራ ቢቀበል፣ ሁሉ የእርሱ ሆኖ ሳለ እራሱን ባዶ አድርጎ በሰዎች መካከል ድሃ ሆኖ መመላለሱ፣ መከራን ሁሉ መታገሱና ካለፈባቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሳ በእግዚአብሔር እንደተቀሰፈ መቆጠሩ፣ የተናቀም ሆኖ መውጣቱና መግባቱ፣ ሰዎች እንዳሉት ሆኖ ሳይሆን፣ ለሰው ልጆች ካለው የጠለቀ ፍቅር የተነሳ፣ ከአምላካቸው ጋር ያስታርቅ ዘንድ የሁላችንንም ኃጢአት መሸከሙ ያመጣበት ነበር፡፡ ይህ የገባው ወንጌላዊ በደስታ ናዝራዊው ኢየሱስ ቢል አልተሳሳተም፤ ይህ ትልቅ ክብር ነው፡፡

ትንቢተ ኢሳይያስ 9 ፡ 6

ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።

ውድ አንባቢ፤ ይህ በዘለአለሙ ጌታ ሕይወት ላይ ያለፈበት የመከራ ጎርፍ ስለ እርስዎ መሆኑ ገብቶዎት ይሆን? እውነት ነው ተንቋል፣ ተተፍቶበታል፣ ተዘብቶበታል፣ የከበረ ደሙን በመስቀል ላይ አፍስሷል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የሰዎችን ሁሉ ኀጢአት በፍቅር አስገዳጅነት ተሸክሞ ሞቷል፡፡ ይህም ለእርስዎም ነው፤ የኃጢአትዎን ዋጋ በመስቀል ላይ በመሞት ከፍሎታል፡፡ አሁን ይህንን በማመንና በመቀበል ከፈጣሪዎ ጋር ታርቀው ወዳዘጋጀልዎት የዘለአለም ደስታ እንዲገቡ ተጋብዘዋል፡፡

የማቴዎስ ወንጌል 25 ፡ 34

ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።

እናንተ ራሳችሁን እንደ ሃይማኖት ሊቅ የምትቆጥሩ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ምንም እንደማታውቁት አሁን አልተገነዘባችሁም ይሆን? ያወቃችሁ መስሏችሁ ስህተትን ከመፈጸምና ተደናግሮ ከማደናገር፣ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለማወቅና የከበረውን ከተዋረደው ለመለየት ጊዜ ውሰዱ ስል ወንድማዊ ምክሬን እለግሳለሁ፡፡

## 4.2. የማቴዎስ ወንጌል 27 ፡ 9-10

በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው። ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት። የሚለው ተፈጸመ።

ስህተቱ የትንቢቱ ቃል በዘካርያስ 11 ፡ 12 ላይ የተጠቀሰ ሆኖ እያለ ማቴዎስ በኤርምያስ እንደተባለ ማለቱ ነው ይላሉ፡፡

እንደተለመደው አሁንም ለዚህ የሚሆነውን ምላሽ የምጀምረው ራሳቸውን እንደ ሃይማኖት ንጽጽር ሊቅ የሚቆጥሩትን ወገኖች ጥቂት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይሆናል፡፡ ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነቢዩ ሙሐመድና የእምነት መጽሐፎቻቸው ትርጉሙን ባልተስተካከለ መልኩ እንዳሰፈሩት ግልጽ ነው፡፡ ደግሞም ከእስልምና የእምነት መሠረቶች መካከል አንዱ በሆነው በመጽሐፍት ማመን በሚለው አንቀጽ እናምናለን እንደምትሉ የታወቀ ቢሆንም፡-

- እነዚያን እናምንባቸዋለን የምትሏቸውን መጽሐፍት የተቀበሉት የመጽሐፉ ሰዎች እንዴት ከፋፍለው ይጠቀሙባቸው እንደነበር ታውቃላችሁ? እንዴት እያሉ ይጠሯቸው እንደ ነበርስ እውቀቱ አላችሁ?
- የአይሁዳውያኑ ጸሐፍት የአጻጻፍ ባሕል ምን እንደሚመስልስ እውቀቱ አላችሁ?

ስለነዚህ ጉዳዮች ምንም አይነት እውቀት ሳይኖራችሁ በጭፍን የምትሚገቱ ሰዎች መሆናችሁ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ሐዋርያው ማቴዎስ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሲጽፍ የተጻፈላቸው ወገኖች ይረዱት ዘንድ ከአይሁዳውያኑ የአጻጻፍ ባሕል፣ የመጽሐፍት አከፋፈልና አጠራር ስርአት ሳይወጣ ሁሉን በግልጽ አስፍሮት ይገኛል፡፡ ይህ መልእክት ለአይሁዳውያኑ በሁለት መንገድ ሊገባቸው ይችል ነበር፡፡ የመጀመሪያው እነዚህ የመጽሐፉ ሰዎች የቀደሙትን መጽሐፍት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለው ለእያንዳንዱ ስያሜ ሰጥተው ይጠቀሙባቸው ስለነበር መልእክቱ ግልጽ ስለሚሆንላቸው፡፡ አከፋፈሉ የሚከተለውን ይመስላል፡-

1. የሕግ መጽሐፍት ፡- የሙሴ የሕግ መጽሐፍት የመጀመሪያዎቹ ናቸው

2. የመዝሙር መጽሐፍት፡- ከመዝሙረ ዳዊት ይጀምር ስለነበር ስየሜውን ከዚህ አግኝቷል

3. የኤርምያስ መጽሐፍት፡- የነቢያት መጽሐፍት በወል የሚጠሩበት ነበር፡፡

ይህንን አከፋፈል ውድ ጌታችንና መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይጠቀምበትና ጠቅሶ ይናገር እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነሳ የሚለው ዜና በተሰማ ጊዜ ግራ ተጋብተው ለነበሩት ሰዎች እውነታውን አምነው በመቀበል ደስ እንዲላቸው ስለ ትንሳኤው በመጽሐፍት ቀድሞ የተገለጸ መሆኑን ሲናገር እንዲህ ነበር ያላቸው፡-

ሉቃስ ወንጌል 24 ፡ 44

እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።

ስለዚህ የአይሁዳውያኑ መጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት መጽሐፍት አደራደር ከኤርምያስ በመጀመር ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ ብሎ ቀሪዎቹን አስራ ሁለቱን የነቢያት መጽሐፍት ይደረድራል፡፡ የኤርምያስ መጽሐፍ ለነቢያት መጽሐፍ

የወል ስም መጠሪያ በመሆን ያገለግል ነበር[218]፡፡ ሐዋርያው ማቴዎስ ሲጽፍ አላማ ያደረገው የትንቢቱ ጸሐፊ እገሌ የተባለው ነቢይ ነው የሚለው ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ በሠላሳ ብር የመሸጡ ነገር እንደ ትንቢቱ ቃል ነው ለማለት መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሐዋርያው ማቴዎስ ይህንን መሠረት አድርጎ በነቢዩ ዘካርያስ የትንቢት ቃል የተዘገበውን መልእክት በኤርምያስ ብሎ ማስተላለፍ ችሏል፡፡ በትንቢት ቃሉ ላይ ምንም አይነት የይዘት ለውጥ አላሳየም፤ ሁለቱም ዘገባዎች ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ አሁንም ለመጽሐፍ ቅዱስ የዘለአለሙ አምላክ ቃል ለመሆኑ ጉልህ ምስክር ቢሆንለት እንጂ የአምላክ ቃል መሆኑን ሰዎች እንዲጠራጠሩት የሚያደርግ አይደለም፡፡

# አባሪ

አባሪ 1

From the Pre-Islam poetry, Hanifian, Sabians Rites

Quotations from the Pre-Islam poetry: Islam had quoted poetry from Emrie' Al-Q'ies who lived 30 years before Mohammed:

In one of the poems of Emrie' Al-Q'ies he said:
The Hour has drawn near, and the moon has been cleft asunder
For a spinner that captured my heart I found myself unable to describe it
With a sleepy charming look and wonderful eyes
The feast passed by me in his adornment he took a sword and killed me
With the swards of a destructive look turned me into a dry stubble of fold-builder
If he left me for an hour the hour will be a bitter decade
The beauty was written on his face with the perfume of Misk
The moons kept going in the darkness I saw the night with its moon
By "Ad-Duha" and by the night when it is still in its ways

"Ad-Duha" means the forenoon after sun-rise. Those expressions are present literally in the following verses:
The Moon chapter (Surat Al-Qamar) 1:" the Hour has drawn near, and the moon has been cleft asunder
The Moon chapter (Surat Al-Qamar) 29:"he took a sword and killed her"
The Moon chapter (Surat Al-Qamar) 31:" they became like the dry stubble of a fold-builder.
The Forenoon chapter (Surat Ad-Duha) 1, 2:" By "Ad-Doha" And by the night, when it is still"

Another poem for Emrie' Al-Q'ies is:

---

[218] *Albert Barnes, Notes on the Bible, e-sword free bible software, commentary on Mat 27 : 9*

He came and the lovers behind him as if they swiftly swarm from every mound
It came in the day of feast in its adornment for like this let the workers work
Those expressions are present literally in the following verses:
The Prophets chapter (Surat Al-Anbiya') 96:"Until, when ya'jûj and Ma'jûj (Gog and Magog), and they swiftly swarm from every mound. "
The rangers' chapter (Surat As-Saffaat) 61:" For like this let the workers work"

**አባሪ 2**

*Omi'ah Ibn Abe-Alsalat who had a great influence on Muhammad, as he liked his poems very much*

*-In Sahih Muslim, the poetry book, there are three converses: number 6022, 6023, and 6024 about a man was sitting with the prophet and he asked him do you have any of thepoems of Omi'ah Ibn Abe-Alsalat?, the man replied : yes , then recite to me some of them, the prophet said:, the man recited for him one line , he said to him tell me more , theman recited for him another line , he kept saying to him more, till he finished a hundred lines of the poem "so the prophet liked it so much*
*-In the quran there are quotations from these poems as in:*

*Omi'ah Ibn Abe-Alsalat said in his poem*
*The God of All that exist and every land*
*He built of them seven strong skies*
*He formed it and decorated it with a lightAnd of meteors*
*the lord of the firm mountains*
*without any pillars that you see*
*of the shining sun and the moon*
*that are glowing in it*
*Those expressions are present literally in:*

*Luqman chapter (Surat Luqman) 10:" He has created the heavens without any pillars that you see and has set on the earth firm mountains, lest it should shake with you.*
*-In the book of "the poets of Nazarenes, page 227:*
*Omi'ah Ibn Abe-Alsalat also said in his poem:*
*To you the thanks and grace and kingdom, our lord*
*Nothing greater than you in glory*
*You ruled over the throne of heaven dominating over all*

*For his glory faces bow down and prostrate*
*He has a veil of light and the light is around him*
*Glowing rivers of light are surrounding him*
*And the angels with their feet under his throne*
*If without God ' palms they would be tired*

*Those expressions are present in the following verses:*

*Consultation chapter (Surat Ash-Shura) 51:" It is not given to any human being that Allah should speak to him unless by Inspiration, or from behind a veil,"*
*The Gathering chapter (Surat Al-Hashr) 24:"He is Allah, the Creator the dominator over His creatures … All that is in the heavens and the earths glorify Him"*
*The Cattle chapter (Surat Al-An'am) 103:" No vision can grasp Him*
*The Forgiver chapter (Surat Ghafir) 7:"Those angels who bear the Throne"*

# ማጣቀሻዎች


- የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ 1962 እትም
- ትምህርተ ክርስቶስ በቄስ ኮሊን ማንሰል
- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግስት፣ ህዳር 27/ 1987
- ዶ/ር ዩሱፍ አል ቀረደዊ፣ ኢስላምን ለመረዳት ትርጉም በሐሰን ታጁ፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ 2004
- ሳዲቅ መሃመድ አህመድ (አቡ ሃይደር)፣ ላለመደናገር ማመሳከር (ተሻሽሎ የቀረበ)፣ 2003.
- ኢቅራ ቁርአን ሶፍት ዌር፣ ነጃሺ መልቲሚዲያ ፕሮዳክሽን የተዘጋጀ
- *Ibn Ishaq, The life of Muhammad, translated by A.Guillaume, Ameena Saiyid oxford university press, Karachi 1955.*
- *Abdullāh Ibn 'Abbās, Tanwīr al-Miqbās min Tafsīr Ibn 'Abbās, translated by Mokrane Guezzou, Royal Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought, Amman 2008*
- *Jalal al-din al-Mahalli and Jalal al-din al-Suyuti, Tafsir Al-Jalalayn, translated by Feras Hamza, Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought Amman, Jordan 2007*
- *Imâm Abul Hussain Muslim bin al-Hajjaj, Sahih Muslim, translated by Nasiruddin al-Khattab, Dar-us-Salam, Riyadh-2007*
- *Al-Bukhari Muhammed Ibn Ismaiel, Sahih Al-Bukhari, translated by Muhammad Muhsin Khan, Dar us Salam, Riyadh 1997*
- *Ahmad von Denffer, Ulum al Qur'an, 1981 pdf*
- *Arthur Jeffery, Materials For The History Of The Text Of The Qur'an,The Old codices, Cairo, 1936*
- *Sheykh Muhammad Bin Yaqoub Al-Kulayni, Kitab Al Kafi, Islamic seminary INCNY, New York, 1999*
- *Sayyid Saeed Akhtar Rizvi, WAHHABIS' FITNAH EXPOSED, Bilal Muslim Mission of Tanzania, Tanzania 1997*
- *Imam Abu Al-Fida Ismail Ibn Kathir, Tafsir Ibn Kathir, maktaba Dar-us-salam, Lebabon 2003, vol 1*
- *Theodor Nöldeke, The History of the Qurʾān, edited and translated by Wolfgang H. Behn, IDC Publishers and Martinus Nijhoff Publishers*
- *Muhammad Mustafa Al-Azami, The history of the quranic text From Revelation to Compilation, Uk Islamic academy, England 2003*
- *Abu Dawud Sulaiman bin Ash'ath, Sunan Abu Dawud, Maktaba Dar-us-Salam, Riyadh-2008, vol 1*
- *Muhammad lbn Eisa At-Tirmidhi, Sunan At-Tirmidhi, Maktaba Dar-us-Salam, Riyadh2007, vol 5*
- *Muhammad Mustafa al-Azami, The History of Quranic text From Revelation to Compilation, uk islamic academy leicester· England 2003*
- *Gabriel Sawma, The Qur'an: Misinterpreted, Mistranslated, and Misread. The Aramaic Language of the Qur'an*
- *Imaam Abi 'Eesaa Muhammad bin 'Eesaa bin Sorah At-Tirmiai, Shamaail-Tirmizi, Translated by Muhammad bin 'Abdurrahmaan Ebrahim*

- *Father Zakaria Boutros, Sources of Islam, The pre-islam poetry, hanifian, sabians Rites, (Epidose 55, TV program)*
- *Arthur Jeffery, The Foreign Vocabulary Of The Qur'an, Oriental Institute Baroda 1938.*
- *Muhammad Mohar Ali, Sirat Al-Nabi and the Orietalists, King Fahd complex for the printing of the holy Quran 1997, vol 1*
- *lmam Al-Qurtubi, Tafseer Al-Qurtubi, translated by Aisha Bewley, Dar Al Taqwa Ltd, London 2003*
- *Ali ibn Ahmad al-Wahidi, Asbab al-Nzul,translated by Mokrane Guezzou, Royal Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought, Amman, Jordan 2008*
- *Ibn kathir, Al-sira Al-Nabawiyya, the life of Muhammad, Translated by Professor Trevor Le Gassick, Garner Publishing Limired, London 2006, vol 1*
- *Al-Haj Maulana Fazlul Karim, Mishkat Ul Masabih, Darul-Ishat, Pakistan Karachi 1994, vol 1*
- *Jalal Al-Din Al-Mahaly & Jalal Al-Din As-Suyuti, Tafsir Al-Jalalayn, translated by Muhammad Anis Gad Khalil, Dar Al-Manarah, Egypt 2010*
- *Ibn Kathir, Tafsir Ibn Kathir Juz' 3 (Part 3), by Muhammad Saed Abdul-Rahman, MSA Publication Limited, 2009*
- *Ayatullah Agha Mehdi Pooya and S.V. Mir Ahmed Ali, Tafsir Sura 1-5,translated by Mirza M. Pooya, ISLAMICMOBILITY.COM, 2013*
- *Imam Ibn kathir, tafsir Ibn kathir(Abridged), translated by Safi ur-Rahman Al Mubarak Puri, Dar us salam, Riyadh 2003, vol 3*
- *Sayyid Qutb, In the Shade of Quran, vol; Seyyed Hossein Nasr, The study Quran : a new translation and commentary, HarperCollins Publishers, UK 2015*
- *Ruqaiyyah Waris Maqsood, Abasic Dictionary of Islam, goodword books, India 2007*
- *Ibn Kathir, Stories of the Quran, translated by Ali As-Sayed Al-Halawani, Dar Al-Manarah, Egypt 2001*
- *Louis Ginzberg, The Legends Of The Jews, The Jewish Publication Society of America 1928, vol 6*
- *Rev. W. St. Clair Tisdall, The Original Sources Of The Qur'an, Society For Promoting Christian Knowledge, London 1905*
- *Ahmad bin 'Ali - An-Nasai, Sunan An-Nasai, translated by Niisiruddin al-Khattiib, Dar-us-Salam, Riyadh-2007 vol 1*
- *Abu 'Abd Allah Muhammad Ibn Sa'd, KITAB AL-TABAQAT AL-KABIR, http://www.soebratie.nl/religie/hadith/IbnSad.html, Volume 1*
- *Ahlul Bayt Digital Islamic Library Project Team [3], A Shi'ite Encyclopedia, temporary-marriage-islam-part-8, Ahlul Bayt Digital Islamic Library Project [4], www.al-islam.org*
- *Ali Rashid, copyright TAbligh Sub-committee, 2002. http://daiichicorp.com*
- *sheikyermami.com/.../muta-temporary-marriage-or-legalized-prostitution, FEBRUARY 27, 2011*
- *ራዕይ አሳታሚ፣ የብሉይ ኪዳን ማብራሪያ፣ ራዕይ አሳታሚ 2004*
- *Hans Wehr, Dictionary of modern written arabic, edited by JM.Cowan, spoken language services.Inc, Urbana USA 1994*

- *Commentary on suratul jinn, written by a group of muslim scholars under supervision of Ayatullah al-Uzma al-Hajj as-shaikh nasir Makarimshirazi, translated by Saleem Bhimij, Canada 2003*
- *Jalal ad-Din as-Suyuti, The History of the Khalifahs, 3rd Revised edition, Translated by Abdassamad Clarke, Ta-Ha Publishers Ltd, London 1995*
- *Ahmad bin 'Ali - An-Nasai, Sunan An-NasaI, Translated by Niisiruddin al-Khattiib, Dar-us-Salam, Riyadh-2007, vol 1*
- የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አ.አ ዩኒቨርስቲ *1993*
- *sunan Ibnu Majah, by Imam Muhammad Bin Yazeed Ibn Majah Al-Qazwinf, Maktaba Dar-usSalam, 2007*
- ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አ.አ *1994*
- *Al-Imam Jalal-ud-din Al-Mahaly and Al-Imam Jalal-ud-din As-suyuti, tafsir Al-Jalalayn, translated by Muhammad Anis Gad Khalil, Dar Al-Manarah, Egypt 2010 vol 2*
- *Sahl b. ʿAbd Allāh al-Tustarī, Tafsīr al-Tustarī, translated by Annabel Keeler and Ali Keeler, Royal Aal al-Bayt Institute for Islamic Thought Amman, Jordan 2011*
- *Allamah Muhammad Baqir Al-Majlisi, Hayat Al-Qulub, Translator Sayyid Athar Husayn S. H. Rizvi, Ansariyan Publications – Qum, India 2010*
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት *6*ኛ እትም፣ በባናዊ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ *1992*
- *Muhammad Mahar Ali, A word for Word Meaning of the Quran, Jamiyat Ihyaa Minhajj al sunna 2003, vol 1*

*https://www.al-islam.org/restatement...and-***muslims***.../***uthman***-third-***khalifa***-***muslims**
**http:www.answering-islam.org/authors/gilchrist/quran/chapter5.html**
**http://www.islamic-awareness.org/Quran/Text/Qiraat/hafs.html**
*www.free-minds.org/sites/default/files/WhichQuran.pdf*
*www.alfatihonline.com/en/articles/***ahruf***.htm*
*https://my.vanderbilt.edu/.../Chapter-Nineteen.-Muhammad-and-the-Beginnings-of-Islam*
*http://www.shiapen.com/comprehensive/tahreef/sunni-reports-deletions-quran.html*
*http://www.universalunity.org/6.html*


**ለአስተያየትም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ የሚተለውን አድራሻ ይጠቀሙ፡-**


amangeremew@yahoo.com